# የሐዋርያት ሥራ

## መግቢያ

ይህን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የጻፈው ሉቃስ፣ከአራቱ ወንጌሎች አንዱ የሆነውን የሉቃስንም ወንጌል፣የጻፈው ሰው ነው። ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን በ63 ዓ.ም. አካባቢ ላይ እንደጻፈው ይገመታል። ክርስቶስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ አገልጋዮቹ ወንጌልን በማሠራጨት ሥራቸው ላይ ካከናወኗቸው ታላላቅ ተግባሮች መካከል ጥቂቶቹን፣ጸሐፊው በሐዋርያት ሥራ መጽሐፉ ውስጥ መዝግቧቸው እናገኛለን። ጌታ ኢየሱስ በምድረ እሥራኤል እየተዘዋወረ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል ሰብኳል፤ድንቅ ድንቅ የሆኑ ታላላቅ ሥራዎችንም ፈጽሟል። እነዚህ በምድረ እሥራኤል ተመላልሶ ራሱ በቃሉ ያስተማራቸውና በተግባር ያከናወናቸው ነገሮች በደቀመዛሙርቱም አገልግሎት በየሥፍራው በድጋሚ እንዲፈጸሙ አድርጓል። ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያሠፈረው ይህ የወንጌል ሥርጭት ታሪክ፣የተከናወነው በሠላሳ ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው።

---

## ምዕራፍ 1

1-2 ወዳጄ ቴዎፍሎስ ሆይ፣
ኢየሱስ ለመረጣቸው ደቀመዛሙርቱ
በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት አስፈላጊ መመ
ሪያ ሰጥቷቸው ወደ ሰማይ እስካረገበት ጊዜ
ድረስ፣ሊያደርግና ሊያስተምር ስለጀመረው
ነገር ከዚህ በፊት በጻፍኩልህ መጽሐፌ ገል
ጬልሃለሁ። 3 ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ
በኋላ፣በምድር ላይ በቆየባቸው አርባ ቀናት
ውስጥ ለደቀመዛሙርቱ በየጊዜው በግልፅ
ታይቷቸዋል። በእርግጥ እርሱ ራሱ ከሞት
የተነሣ መሆኑን እንዲያምኑም፣በልዩ ልዩ
ምልክቶች ራሱን ገልጦላቸው ስለ እግዚአ
ብሔር መንግሥት አስተምሯቸዋል።
4 አብሮአቸው ማዕድ ላይ ተቀምጦ ሳለ፣
ደቀመዛሙርቱን፣ «ከዚህ በፊት አባቴ ይል
ክላችኋል ብዬ የነገርኳችሁን፣መንፈስ ቅዱ
ስን እስክትቀበሉ ድረስ ከኢየሩሳሌም ሳት
ወጡ በዚያው ቆዩ።
5 «ዮሐንስ በውኃ እንዳጠመቀ ታውቃላ
ችሁ። እናንተ ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ በመ
ንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ» አላቸው።
6 አንድ ቀን ደቀመዛሙርቱ ፣ «ጌታ
ሆይ ፣ እሥራኤል ከሮማውያን ቅኝ አገዛዝ
ነፃ ሆና፣ራሷን በራሷ እንድታስተዳድር የም
ታደርገው መቼ ነው? አሁን በቅርቡ ነፃነ
ቷን እንድታገኝ ታደርጋለህ?» ሲሉ ጠየ
ቁት።
7 ኢየሱስም መልሶ ፣ «አብ በሥልጣኑ
የወሰነውን ቀን ወይንም ጊዜ እንድታውቁ
ለእናንተ አልተፈቀደላችሁም። 8 ነገር ግን
መንፈስ ቅዱስን ስትቀበሉ ከላይ ኃይል ይሰ
ጣችኋል። በዚያን ጊዜም በኢየሩሳሌም፣በይ
ሁዳ አውራጃዎችና በሰማርያ ፣ ከዚያም
አልፎ እስከ ምድር ዳርቻ ባሉ አገሮች
ሁሉ፣ስለ እኔ ትመሰክራላችሁ» አላቸው።
9 ይህንንም ነግሮአቸው ትክ ብለው እያ
ዩት ወደ ሰማይ ወጣ። ደመና ስለ ጋረደው
ከዓይናቸው ተሰወረ። 10 ደቀመዛሙርቱም
ወደ ላይ አንጋጠው በመገረም ሲመለከቱ፣
ነጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች ድንገት
በአጠገባቸው ቆሙ። 11 እነዚያም ሰዎች
ለደቀመዛሙርቱ ፣ «እዚህ ቆማችሁ ወደ
ሰማይ አንጋጣችሁ የምትመለከቱት ለምን
ድን ነው? ኢየሱስ እንደሆነ ወደ ሰማይ
እንደ ወጣ በዚያው የሚቀር አይደለም።
አሁን ወደ ሰማይ ሲወጣ እንዳያችሁት እን
ደዚሁ ደግሞ ተመልሶ ይመጣል፤ አይቀ
ርም» አሏቸው።
12 ይህ ድርጊት የተፈጸመው ፣ ከኢየሩሳ
ሌም ከተማ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ወጣ
ብሎ በሚገኘው በደብረ ዘይት ተራራ ላይ
ነበር። ሐዋርያትም ከዚያ ወደ ኢየሩሳሌም
ተመለሱ። 13-14 ወዲያውኑ እንደተመለሱ
ፎቁ ላይ ወደሚገኘው ማረፊያ ክፍላቸው
ገቡ። በዚያ የነበሩትም ጴጥሮስ፣ዮሐንስ፣
ያዕቆብ፣እንድርያስ፣ፊልጶስ፣ቶማስ፣በርተሎ
ሜዎስ፣ማቴዎስ፣የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፣
ቀናተኛው ስምዖን ፣ የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ
ነበሩ። ከእነርሱም ጋር የኢየሱስ እናት ማር
ያም ፣ የኢየሱስ ወንድሞችና ሌሎችም

ሴቶች ፣ በአንድነት ያለማቋረጥ በጸሎት
ይተጉ ነበር። 15 አንድ ቀን ጴጥሮስ፣ቁጥራ
ቸው አንድ መቶ ሃያ ያህል በሚሆኑ በነ
ዚህ ደቀመዛሙርት መካከል ቆሞ፣የሚከተ
ለውን ንግግር አደረገ።
16 «ወንድሞቼ ሆይ፣ኢየሱስን ለመያደል
ታጥቀው ለተነሡት ሰዎች መሪ ሆኖ ያስያ
ዘው ይሁዳ፣አስቀድሞ ትንቢት የተነገረበት
መሆኑን እንድታውቁ እወዳለሁ። ትንቢቱን
የተናገረው ዳዊት ነው። መቼም ፣ መንፈስ
ቅዱስ ያናገረው ይህ ትንቢት መፈጸም ስለነ
በረበት ፣ ትንቢቱ ደርሷል። 17 ጌታን ያስያ
ዘው ይሁዳ፣እንደ እኛ ሐዋርያ ሆኖ የተመ
ረጠ የሥራ ባልደረባችን ነበር። 18 ይህ ሰው
ኢየሱስን ለማስያዝ ተዋውሎ በተቀበለው
ገንዘብ መሬት ገዛ። ግን በገዛው መሬት ላይ
ጠቀምበት በግምባሩ ተደፍቶ፣ሰውነቱ ለሁ
ለት ተሰንጥቆ ፣ አንጀቱም ተዘርግፎ ክፉ
አሟሟት ሞተ። 19 በዚህም አስቃቂ ሁኔታ
መሞቱን፣የኢየሩሳሌም ከተማ ኗሪ ሁሉ የሰ
ማው ነገር ነው። ስለዚህም ይሁዳ የገዛው
ያ መሬት ፣ 'የደም መሬት' ተብሎ ተሠ
የመ። 20 ከፍ ብሎ ዳዊት ስለዚህ ጉዳይ
ተናገረ ያልኩት ትንቢት ፣ 'ቤቱ ማንም
የማይኖርበት ኦና ይሁን፤ሹመቱም ለሌላ
ሰው ይሰጥበት' ይላል።
21-22 «ስለዚህ በእርሱ እግር ተተክቶ ፣
ስለ ኢየሱስ ትንሣኤ የሚመሰክር ሰው
መምረጥ ያስፈልገናል። ይህም የሚመረ
ጠው ሰው ፣ ኢየሱስ በዮሐንስ እጅ ከተጠ
መቀ አንሥቶ ወደ ሰማይ እስከ ወጣበት
ቀን ድረስ ፣ በመካከላችን በኖረበት ዘመን
ሁሉ አብረውን ከነበሩት ከእነዚህ ወንድሞ
ቻችን ውስጥ መሆን አለበት» ብሎ ንግግ
ሩን አቆመ።
23 ከጴጥሮስ ንግግርም በኋላ የሁለት
ሰዎች ስም ቀረበ። እነርሱም ፣ አንዱ በርስ
ያን ወይም ኢዮስጦስ በመባል የሚታወቀው
ዮሴፍ ሲሆን፣ሌላው ደግሞ ማትያስ የሚባ
ለው ነበር። 24-25 ከዚያም ፣ «የሰውን ልብ
መርምረህ የምታውቅ ጌታ ሆይ ፣ ይሁዳ
የግል ፍላጐቱን በመከተል ጥሎት በሄደው
በዚህ የሐዋርያነት ቦታ ፣ ከእነዚህ ሁለት
ሰዎች አንዱን ለመተካት ስላሰብን ፣ አንተ
ለዚች የሐዋርያነት ቦታ የመረጥኸው የት
ኛው መሆኑን እንድትገልጥልን እንለምንሃ
ለን» ሲሉ ጸለዩ።
26 ከዚህ በኋላ ዕጣ ተጥሎ፣ዕጣው ለማት
ያስ ወጣ። እርሱም ከአሥራ አንዱ ሐዋር
ያት ጋር ተቆጠረ።

## ምዕራፍ 2

1-2 የጰንጤቆስጤ በዓል በሚከበርበት
ቀን ሁሉም በአንድነት ሳሉ ፣ በድንገት
እንደ ብርቱ አውሎ ነፋስ የሚመስል
ድምፅ፣ከሰማይ መጣ። ድምፁም ፣ ደቀመዛ
ሙርቱ በአንድነት ተሰብስበው የነበሩበትን
ቤት ባንድ ጊዜ ሞላው። 3 የምላስ ቅርጽ
ያላቸው የእሳት ነበልባል የሚመስሉ ነገሮ
ችም ታዩአቸው። በእያንዳንዳቸውም ራስ
ላይ አረፉባቸው። 4 ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ
ተሞሉ። መንፈስ ቅዱስ መናገር እንዳስታላ
ቸውም ፣ ከዚህ በፊት በማያውቋቸው ልዩ
ልዩ ቋንቋዎች መናገር ጀመሩ።
5 በዚያን ጊዜ ከመላው ዓለም መጥተው
ኢየሩሳሌም ውስጥ የሚኖሩ እግዚአብሔርን
የሚያመልኩ አይሁዶች ነበሩ። 6 እነርሱም
ይህንን ድምፅ በሰሙ ጊዜ ፣ ምን እንደሆነ
ለማወቅ ደቀመዛሙርቱ ወደ ነበሩበት
ሥፍራ እየተሯሯጡ መጡ። የመጡትም
ሰዎች የገዛ አገሮቻቸውን ቋንቋ ደቀመዛሙ
ርቱ ሲናገሩ በመስማታቸው እጅግ አድርጎ
ደነቃቸው።
7 እርስ በርሳቸውም እንዲህ ተባባሉ።
«ይህ ነገር ምንድነው? እንዴትስ ሊሆን
ቻለ? እነዚህ ሰዎች የገሊላ ባላገሮች
ናቸው። ሌላ አገር እንኳን ረግጠው አያ
ውቁ? 8 ታዲያ በየትውልድ አገሮቻችን
ቋንቋ እንዲህ አቀላጥፈው ሲናገሩ የምንሰማ
ቸው እንዴት ነው? 9 አሁን እዚህ ያለነው
ከጳርቴ ፣ ከሜድ፣ከኢላሜጤ፣ከመስጴጦሚያ
ከይሁዳ ፣ ከቀጳዶቂያ ፣ ከጳንጦስ ከእስያ ፣
10 ከፍርግያ፣ከጵንፍልያ፣ከግብፅ፣ከቀሬናና
በአካባቢዋ ካሉት ከሊቢያ አውራጃዎች እን
ዲሁም ከሮም የመጣን ፣ አይሁዶችና ወደ
አይሁድ ሃይማኖት የገባን የአሕዛብ ወገኖች
ነን። 11 ደግሞም የቀርጤስ ሰዎችና አረብ
ችም በመካከላችን ይገኛሉ። ታዲያ እን
ዴት ነው እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን
ታላቅ ሥራ በየቋንቋዎቻችን ሲናገሩ የምን
ሰማቸው?»
12 ሁሉም ተገርመው እርስ በእርሳቸው፣
«ይህ ነገር ምን ይሆን?» ሲሉ ተነጋገሩ
በት። 13 አንዳንዶቹ ግን ፣ «እንዲህ የሚዘላ
ብዱት ፣ ሳይነጋ የወይን ጠጅ ጠጥተው ሰክ
ረው ይሆናል እንጂ ፣ በጤናቸውስ አይደ
ለም!» ብለው አፌዙባቸው።
14 በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ፣ ከአሥራ አንዱ
ጋር በሕዝቡ ፊት ቆሞ ድምፁን ከፍ በማ
ድረግ እንዲህ አለ። «እናንተ ከውጭ አገር

የመጣችሁ እንግዶችና የኢየሩሳሌም ከተማ
ነዋሪዎች! ስለምትገረሙበት ስለዚህ ነገር
ማብራሪያ መስጠቱ ተገቢ ሆኖ ስላገኘሁት
ልብ ብላችሁ አድምጡኝ። 15 እናንተ እንደ
ምትሉት እነዚህ ሰዎች ፈጽሞ አልሰከ
ሩም። ገና ከጠዋቱ በሦስት ሰዓት ላይ ሰክረ
ዋል ማለት ፈጽሞ የማይሆን ነው። 16 ነገር
ግን ይህ የምታዩት ነገር የሆነው፥ ነቢዩ
ኢዮኤል አስቀድሞ የተናገረው ትንቢት
መፈጸም ስላለበት ነው። እርሱም እንዲህ
ብሎ ነበር፥ 17 'እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል። በመጨረሻው ዘመን መንፈሴን
በሰው ልጆች ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ። ወንዶ
ችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ።
ወጣቶቻችሁ ራእይ ያያሉ። ሽማግሌዎቻች
ሁም ሕልም ያልማሉ። 18 በወንዶችና በሴ
ቶች አገልጋዮቼም ላይ ሁሉ መንፈሴን አፈ
ስሳለሁ። እነርሱም ትንቢት ይናገራሉ።
19 በላይ በሰማይና በታችም በምድር ድንቅ
ድንቅ ነገሮችን ለትንግርት አሳያለሁ።
ደም፥እሳትና የጪስ ጭጋግ ይታያል። 20 ያ
ታላቅና ክቡር የሆነው የእግዚአብሔር ቀን
ከመድረሱ አስቀድሞ ፀሐይ ይጨልማል፤
ጨረቃም እንደ ደም ትቀላለች። 21 ነገር
ግን የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ ምሕረትን
የሚለምን ሁሉ ይድናል።'

22 «እናንተ የእሥራኤል ሰዎች የምናገረ
ውን ነገር ልብ ብላችሁ አድምጡ! የናዝ
ሬቱ ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣበት ምክ
ንያት፥ ለእናንተ ግልጽ እንዲሆን ያስፈል
ጋል። እግዚአብሔር በእርሱ አማካይነት
በመካከላችሁ ለትንግርት የሚታዩ ድንቅ
ሥራዎችንና ተአምራትን በማድረግ፥ልጁን
በይፋ አክብሮታል። 23 ነገር ግን እግዚአብ
ሔር በቀደመው እውቀቱና ባዘጋጀው
ዕቅዱ መሠረት፥ይህ ኢየሱስ በእናንተ እጅ
አልፎ ተሰጠ። እናንተም በአመፀኞች
ሰዎች እጅ በመስቀል ተሰቅሎ እንዲሞት
አደረጋችሁት። 24 እግዚአብሔር ግን የሞ
ትን ኃይል አስወግዶ አስነሣው። ምክንያ
ቱም ሞት ኢየሱስን ይዞ ሊያስቀረው አይች
ልምና ነው።

25 «ዳዊት ስለዚህ ጉዳይ አስቀድሞ ምን
ትንቢት እንደተናገረ ታውቃላችሁ? 'እግዚ
አብሔር ሁልጊዜ ከእኔ ጋር እንደሆነ አው
ቃለሁ፤ ይረዳኛል፤ እንዳልሰናከልም ኃይሉ
ደግፎ ይይዘኛል። 26 ስለዚህ ልቤ ምን
ጊዜም በደስታ እንደተሞላ ነው። አንደበ
ቴም የእግዚአብሔርን ክብር ከመናገር አይ
ቆጠብም። ብሞትም እንኳ ምንም ዓይነት
ጉዳት እንደማይደርስብኝ ስለማውቅ ሰው
ነቴ በተስፋ ያርፋል። 27 ነፍሴን በሲኦል
ውስጥ አትተዋትም። ቅዱስህንም በመቃ
ብር ውስጥ እንዲበሰብስ አታደርገውም።
28 የሕይወትን መንገድ አሳየኸኝ፤ፊትህንም
በማየት ደስታን ጠግቤ እንድኖር ታደርጋ
ለህ።'

29 «ወንድሞች ሆይ፥እስቲ ይህንን ቃል
በሚገባ አስተውሉት። አባታችን ዳዊት ይህ
ንን የተናገረው ስለ ራሱ አይደለም። ስለ
ራሱ ተናግሮታል እንዳትሉም፥ ዳዊት ሞቶ
ከተቀበረ ዘመናት አልፈዋል። መቃብሩም
ሩቅ አይደለም፤ እዚሁ አጠገባችን ነው፤
ማየት ይቻላል። 30 ነገር ግን ዳዊት ነቢይ
ስለነበር መንፈስ ቅዱስ በገለጠለት መሠረት
ይህንን ትንቢት አስቀድሞ ተናገረ። እግዚአ
ብሔር አስቀድሞ ለዳዊት፥ 'በዙፋንህ ላይ
የሚቀመጥ ንጉሥ ከዘርህ አስነሣለሁ' ሲል
ቃል እንደገባለት ተጽፏል። 31 ዳዊት ይህ
ሁሉ በክርስቶስ ላይ እንደሚደርስበትና
ከሙታን እንደሚነሣም፥አስቀድሞ ተገልጦ
ለት ትንቢት ተናገረ እንጂ፥ስለ ራሱ የተናገ
ረው ነገር አይደለም። ነፍሱ በሲኦል እንደ
ማትቀር፥ሥጋውም በመቃብር ፈርሶና በስ
ብሶ እንደማይቀር ስለ ክርስቶስ አስቀድሞ
ተናገረ። 32 በተነገረውም ትንቢት መሠረት
እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሞት እንደ አስነ
ሣው ጥርጥር የለውም። እኛ ሁላችንም
ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን።

33 «እርሱም አሁን በእግዚአብሔር ቀኝ
ባለው የክብር ዙፋን ላይ ተቀምጦአል።
ከአባቱም ተቀብሎ፥አስቀድሞ ተስፋ የገባ
ልንን መንፈስ ቅዱስን ይኸው አሁን እንደ
ምታዩትና እንደምትሰሙት አፍስሶልናል።
34-35 ወደ ሰማይ የወጣው ዳዊት ነው እንዳ
ይባልም፥ ዳዊት አይደለም። አለመሆኑንም
ለማረጋገጥ ዳዊት ራሱ፥ 'ጌታ ጌታዬን፥ጠላ
ቶችህን ከእግርህ በታች እስካደርግልህ
ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው' ብሎ ተናግ
ሯል።

36 «ስለዚህ፥ እያንዳንዱ እሥራኤላዊ
ይህን አባባል በጥሞና ሊያስተውለው ይገ
ባል። እናንተ የሰቀላችሁትን ይህንኑ ኢየሱ
ስን እግዚአብሔር፥ጌታና መሲሕ አድርጎ
አከበረው።»

37 ሰዎቹም ጴጥሮስ በተናገረው በዚህ
ነገር ልባቸው በጣም ስለተነካ፥ወደ ጴጥሮ
ስና ወደ ሌሎቹ ሐዋርያት ቀረብ ብለው፥
«ወንድሞቻችን ታዲያ አሁን ምን እናድ
ርግ?» ብለው በአንክሮ ጠየቋቸው።

38 ጴጥሮስም መልሶ ፥ «ከጠየቃችሁንማ
በሉ እንግዲህ የኃጢአት ይቅርታን ለማግ
ኘት ንስሐ ግቡ፤እያንዳንዳችሁም በኢየሱስ
ክርስቶስ ስም ተጠመቁ። የመንፈስ ቅዱስን
ስጦታም ትቀበላላችሁ። 39 እግዚአብሔር
የሰጠው ይህ ተስፋ ለእናንተና ለልጆቻችሁ
ነው። ደግሞም በቅርብም በሩቅም ላሉት
እርሱ ለሚጠራቸው ሁሉ ጭምር ነው።»
40 ጴጥሮስ ስለዚሁ ጉዳይ በሰፊው ተን
ትኖ በማስረዳት፥ራሳቸውን ከዚያ ክፉ ትው
ልድ አካሄድ ፡እንዲጠብቁ ፥ አበክሮ መከራ
ቸው። 41 ከእነርሱም ብዙዎቹ ጴጥሮስ የተ
ናገረውን ቃል በማመን ተጠመቁ። በዚያ
ቀን ያመኑትና የተጠመቁት ሰዎች ቁጥር
ወደ ሦስት ሺህ ይጠጋል። 42 እነርሱም
ሐዋርያት የሚያስተምሩትን ትምህርት
በመከታተል፥በወንድማማች ሕብረት፥ተግቶ
በመጸለይና የጌታን ማዕድ አብሮ በመስተፍ
ይበረቱ ነበር። 43 ሐዋርያት ለትንግርት
የሚታዩ ብዙ ታላላቅ ድንቅ ሥራዎችና
ተአምራት ያደርጉ ስለነበር፥ያየ የሰማ ሁሉ
ፍርሃትም አድናቆትም አደረበት። 44 ምዕ
መናን ሁሉ አብረው በአንድነት ይኖሩ ስለ
ነበር፥ያላቸው ነገር ሁሉ የጋራ እንጂ የግል
ሀብት የሚባል ነገር አልነበረም። 45 መሬት
ወይም ሌላ ንብረት ያላቸው ሰዎች ያንን
እየሸጡ ገንዘቡን ስለሚያመጡ፥ለያንዳንዱ
የሚያስፈልገው ያህል ይሰጠው ነበር።
46 በየዕለቱም በቤተ መቅደስ እየተሰበሰቡ
ጌታን ያመልኩ ነበር። በየቤታቸውም እየተ
ገናኙ በፍቅርና በደስታ ፥ ትሕትና በሞላበ
ትም መተሳሰብ አንድ ላይ ሆነው የጌታን
ማዕድ ይካፈሉ ፥ 47 እግዚአብሔርንም ያመ
ሰግኑ ነበር። ደቀመዛሙርቱ፥በትልቁም በት
ንሹም ዘንድ ተወዳጅነት ነበራቸው። ለሌ
ሎቹ መልካም ምሳሌ ነበሩ። እግዚአብሔ
ርም ብዙ ሰዎችን ስለሚያድን የምዕመናኑ
ቁጥር በየዕለቱ ይጨምርና ያድግ ነበር።

## ምዕራፍ 3

1-2 አንድ ቀን ዘጠኝ ሰዓት ላይ ጴጥሮ
ስና ዮሐንስ ለጸሎት ወደ ቤተ መቅደስ
ሄዱ። እዚያ እንደ ደረሱም ‘ውብ’ እየተ
ባለ በሚጠራው የመቅደስ በር አንድ ሰው
ተቀምጦ ሲለምን አገኙ። ይህ ሰው ከተወ
ለደ ጀምሮ ሽባ ስለነበር በእግሩ ቆሞ ለመ
ሄድ ስለማይችል ፥ ሰዎች በየዕለቱ ተሸከ
መው እያመጡ በዚያ ቦታ ያስቀምጡት
ነበር። ተቀምጦም ወደ ቤተ መቅደስ ከሚ
ገቡት ሰዎች ምጽዋት ይለምን ነበር። 3 ሽባ
ውም ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ ቤተ መቅደስ
በሚገቡበት ጊዜ እንዲመጸውቱት አስተዛ
ዝኖ ለመናቸው።
4 እነርሱም ትኩር ብለው ካዩት በኋላ፥
ጴጥሮስ ፥ «እስቲ ቀና ብለህ ተመልከተን»
አለው።
5 ሽባውም ምጽዋት የሚሰጡት መስ
ሎት በመጓጓት ፥ ቀና ብሎ ተመለከታ
ቸው።
6 ጴጥሮስም ፥ «የምሰጥህ ብርና ወርቅ
የለኝም። ግን አንድ የምሰጥህ ነገር አለኝ»
በማለት ድምፁን ከፍ አድርጎ፥ «በናዝሬቱ
በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ቆመህ
ሂድ» አለው። 7-10 ቀኝ እጁንም ይዞ ሲያስ
ነሣው ፥ እግሮቹና ቁርጭምጭሚቱ በርትተ
ውለት ወዲያውኑ ብድግ ብሎ ቆሞ እንደ
ልቡ መራመድ ቻለ። ከዚያም በቤተ መቅ
ደስ የነበረው ሁሉ ሲያየው እየፈነደቀና
እግዚአብሔርን እያመሰገነ፥ከጴጥሮስና ከዮ
ሐንስ ጋር ወደ ቤተ መቅደስ ገባ። ቀድሞ
የሚያውቁትም ሰዎች ‘ውብ’ እየተባለ
በሚጠራው መቅደስ በር ተቀምጦ በየዕለቱ
ምጽዋት የሚለምነው ሽባ መሆኑን ሲረዱ
እጅግ ተደነቁ።
11 የተፈወሰውም ሰው ፥ ‘የሰሎሞን
መመላለሻ’ እየተባለ በሚጠራው ቦታ ከጴ
ጥሮስና ከዮሐንስ ጋር ቆሞ ሳለ ፥ ከሽባነቱ
ተፈውሶ ሲራመድ አይተው የተደነቁት
ሰዎች ሁሉ ተንጋግተው እነርሱ ወደ ነበሩ
በት ቦታ መጡ።
12 ጴጥሮስም እዚያ የነበሩት ሰዎች ወደ
እነርሱ መሰብሰባቸውን ባየ ጊዜ እንዲህ
አላቸው ፤ «እናንተ የእሥራኤል ሰዎች ፥
በዚህ አሁን በተፈጸመው ነገር እጅግ ስትደ
ነቁ እናያችኋለን። ይህንንም ሰው እኛ በኃ
ይላችን ወይም በጽድቃችን እንደፈወስነው
አድርጋችሁ እንደተመለከታችሁትም ተረድ
ተናል። ነገሩ ግን እንደዚህ አይደለም።
13 የአብርሃም ፥ የይስሐቅ ፥ የያዕቆብና የሌሎ
ችም አባቶቻችን አምላክ የልጁ የኢየሱስ
ክርስቶስ ክብር እንዲገለጥ ስለፈለገ ፥ ይህን
አደረገ እንጂ በእኛ ኃይል ወይም ሥልጣን
የፈወስነው አይምሰላችሁ። እናንተ ግን እር
ሱን ወንጀለኛ ነው ብላችሁ እንዲገደል
በጲላጦስ ፊት አቀረባችሁት። ጲላጦስ ሊለ
ቀው እንኳ ቢፈልግ፥ሊለቀቅ አይገባውም!
መሰቀል አለበት! ብላችሁ ተንጫጫችሁ
በት። 14 ምንም በደል፥ምንም ጥፋት የሌለ
በትን ቅዱሱንና ጻድቁን ኢየሱስን ‘ይሰቀል’

ስትሉ፣በነፍስ ገዳይነቱ ድፍን አገር ያወቀ
ውን ወንበዴ በርባንን ግን 'ይፈታልን' ብላ
ችሁ ጲላጦስን ለመናችሁት። 15 እንዲህ
አድርጋችሁም የሕይወት ምንጭ የሆነውን
ጌታ ገደላችሁት። እግዚአብሔር ግን ከሞት
አስነሣው። ለመነሣቱም እኛ የዓይን ምስክ
ሮች ነን።

16 «ሽባ ሆኖ ሲለምን የምታውቁት ይህ
ሰው የተፈወሰውም፣ በዚሁ በኢየሱስ ስም
እንጂ በሌላ አይደለም። በኢየሱስ ስም
ማመኑም እንደምታዩት ይኸው ይህን
ፈውስ ሊያስገኝለት በቅቷል።

17 «ወንድሞቼ ሆይ፣ኢየሱስ እንዲሰቀል
ያደረጋችሁት እናንተም እንደ መሪዎቻችሁ
ባለማወቅ መሆኑን አውቃለሁ። 18 እሱማ
መከራ መቀበል እንዳለበት አስቀድሞ በነቢ
ያት ትንቢት ተነግሮ የለ? ስለዚህ ያ ትን
ቢት ግድ መፈጸም ስለነበረበት ይኸው
መከራ ለመቀበል በቃ። 19 ለወደፊቱ ግን
ኃጢአታችሁ እንዲሠረይላችሁ አሁኑኑ
ንስሐ ገብታችሁ ወደ እግዚአብሔር ተመ
ለሱ። 20 ይህን ብታደርጉ ከእግዚአብሔር
ዘንድ ደስታንና የመንፈስ ዕረፍትን ታገኛላ
ችሁ። አስቀድሞ ቃል የገባላችሁን መሲ
ሑን ኢየሱስ ክርስቶስንም ይልክላችኋል።
21-22 እግዚአብሔር አስቀድሞ በነቢያት
አድሮ እንደ ተናገረ፣ፍጥረት ሁሉ እስኪታ
ደስ ድረስ ግን ክርስቶስ በሰማይ ይቆያል።
ሕግን ከእግዚአብሔር የተቀበለ ሙሴ አስቀ
ድሞ፣ 'እግዚአብሔር እኔን እንዳስነሣኝ
ከእናንተ መካከል ነቢይ ያስነሣላችኋል፤
እርሱ የሚነግራችሁን ሁሉ ልብ በላችሁ
ስሙ። 23 እርሱን የማይሰማ ቢኖር ከሕዝቡ
መካከል ጨርሶ ይጥፋ!' ብሎ ተናግሯል።
እንግዲህ ሙሴ ትንቢት የተናገረለት
መሲሕ ይህ ኢየሱስ በመሆኑ ልትቀበሉት
ይገባል።

24 «በእርግጥም ከሳሙኤል ጀምሮ ትን
ቢት የተናገሩት ሌሎች ነቢያት ሁሉ
ስለዚህ ዘመን ተንብየዋል። 25 እናንተ
ይህን ትንቢት የተናገሩ የእነዚያ ነቢያ
ትና የቀድሞ አባቶቻችሁ ወራሾች
ናችሁ። ይህ በመሆኑም እግዚአብሔር
ለአብርሃም፣ 'በዘርህ የዓለም ሕዝቦች
ሁሉ ይባረካሉ' ሲል የሰጠው ተስፋ የእ
ናንተም ጭምር ነው። 26 እርሱም ልጁን
ኢየሱስ ክርስቶስን አስቀድሞ ወደ እና
ንተ የላከው፣እያንዳንዳችሁ ስለ ኃጢአታ
ችሁ ተጸጽታችሁ ንስሐ በመግባት በረከ
ቱን እንድትቀበሉ ነው።»

## ምዕራፍ 4

1 ጴጥሮስና ዮሐንስ ሕዝቡን በሚያናግሩ
በት ጊዜ፣ካህናት በቤተ መቅደሱ አዛዥና
በሰዱቃውያን ታጅበው መጡ። 2 ጴጥሮስና
ዮሐንስ በኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘውን የሙ
ታን ትንሣኤ ለሕዝቡ ማስተማራቸው
በጣም አስቆጣቸው። ጊዜው ስለመሸ፣
3 ጴጥሮስንና ዮሐንስን አስይዘው ሲነጋ ለፍ
ርድ እንዲቀርቡ እሥር ቤት ላኩዋቸው።
4 በዚያ ዕለት የጴጥሮስንና የዮሐንስን ትምህ
ርት ከሰሙት ሰዎች መካከል ብዙዎቹ በማ
መናቸው የወንዶች ቁጥር ብቻ ወደ አም
ስት ሺህ ከፍ አለ።

5 በማግስቱም የአይሁድ መሪዎች የአገር
ሽማግሌዎችና የአይሁድ ሃይማኖት መምህ
ራን፣በሙሉ በኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ። 6 ከተ
ሰበሰቡትም መካከል ሊቀ ካህናቱ ሐና፣እን
ዲሁም ቀያፋ፣ዮሐንስ፣እስክንድሮስና የሊቀ
ካህናቱ ዘመዶች ይገኙባቸው ነበር። 7 ሁለ
ቱን ሐዋርያትም በአደባባይ አቁመው፣
«ለመሆኑ ይህን ያደረጋችሁት በምን ኃይል
ወይንስ በማን ስም ነው?» ብለው ጠየቋ
ቸው።

8 በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ
ተሞልቶ እንዲህ ሲል መለሰላቸው። «የተከ
በራችሁ የሕዝብ መሪዎችና የአገር ሽማግሌ
ዎች። 9 ሽባ የነበረው ሰው በምን ኃይል
እንደተፈወሰ እንድናስረዳችሁ የምትፈልጉ
መሆኑን አውቀናል። 10 መልሱ ባጭሩ፣ይህ
ሰው የተፈወሰውና ፍጹም ጤነኛ ሆኖ በፊ
ታችሁ ሊቆም የቻለው እናንተ በሰቀላች
ሁት ግን እግዚአብሔር ከሞት በአስነሣው
በናዝሬቱ በኢየሱስ ስምና ሥልጣን ነው።
11 ኢየሱስ፣ 'እናንተ ግንበኞች የናቃችሁት
ድንጋይ የማዕዘናት ማዕዘን ሆነ' 12 ኢየሱስ
ክርስቶስን በማመን ካልሆነ በቀር፣በሌላ
በማንም ደኅንነት ሊገኝ አይችልም። እግዚ
አብሔር ለእኛ ለሰዎች እንድንድንበት ያዘ
ጋጀልን ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ከሰማይ
በታች ሌላ ስም የለምና።»

13 እነርሱም ጴጥሮስና ዮሐንስ ያለፍር
ሃት እንደመለሱላቸው ባዩ ጊዜ ተደነቁ።
ያልተማሩ ማይሞች ቢሆኑም እንኳ፣እንዲህ
ያለ መልስ ለመስጠት የቻሉት የኢየሱስ
ተከታዮች በመሆናቸው መሆኑን ተረዱ።
14 የተፈወሰውም ሰው እዚያው እፊታቸው
ቆሞ ስለ ነበር፣ሁኔታውን ለማስተባበል አል
ደፈሩም። 15 ጴጥሮስንና ዮሐንስን ከጉባ
ዔው አዳራሽ እንዲወጡ ካደረጉ በኋላ፣

እንዲህ ሲሉ ተማከሩ።
16 «እነዚህን ሰዎች ምን እናድርግ? በእ
ጃቸው የተደረገውን አስደናቂ ተአምር
መላው የኢየሩሳሌም ከተማ ነዋሪ ያየውና
የሰማው ስለሆነ፥ ‘ሐሰት ነው፥ አልተደረ
ገም’ ብለን እናስተባብል ብንል ማንም አይ
ቀበለንም። 17 ግን ወሬው እንዳይዛመትና
ትምህርታቸው ተስፋፍቶ ተቀባይነት እንዳ
ያገኝ፥ ካሁኑ አንድ ነገር መደረግ አለበት።
ስለዚህ ካሁን ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ለማንም
እንዳያስተምሩ ፥ አስጠንቅቀን እንልቀቃ
ቸው።» 18 ወዲያውም ጴጥሮስንና ዮሐንስን
ጠርተው ወደ ጉባዔው አዳራሽ አስገቧ
ቸው። ከዚያም፥ለወደፊቱ ስለ ኢየሱስ ለማ
ንም እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ አዘዙአ
ቸው።
19 ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን፥ «ለእግዚአብ
ሔር ከመታዘዝ፥ለእናንተ መታዘዝ የሚገባ
ከሆነ፥ እስቲ ራሳችሁ ፍረዱ። 20 እኛ ግን
ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ወደ ኋላ
አንልም» ብለው ቁርጥ ያለ መልስ ሰጡአ
ቸው።
21-22 ጉባዔውም ጴጥሮስንና ዮሐንስን
ለመቅጣት በቂ ምክንያት ባለማግኘቱ ማስ
ጠንቀቂያ ብቻ ሰጥቶ ለቀቃቸው። የለቀቃ
ቸው ግን፥ አርባ ዓመት ሙሉ ሽባ ሆኖ
የኖረ ሰው ሲፈወስ በገዛ ዓይኑ ያየውና እግ
ዚአብሔርን ያመሰግን የነበረው ያ ሁሉ
ሕዝብ፥ ጉባዔው በጴጥሮስና በዮሐንስ ላይ
ሊወስነው ስላሰበው ፍርድ ድጋፍ እንደማ
ይሰጠው ስለተረዳ ነበር።
23 ጴጥሮስና ዮሐንስ ከተለቀቁ በኋላ፥
በቀጥታ ሌሎቹ ደቀመዛሙርት ወዳሉበት
ሄደው፥ሊቀ ካህናቱና የአገር ሽማግሌዎች
ያሉአቸውን ሁሉ ነገሩአቸው።
24 እነርሱም ይህን ከሰሙ በኋላ በአንድ
ነት ሆነው እንዲህ ሲሉ ጸለዩ፤ «ሰማይን፥
ምድርን፥ባሕርንና በውስጣቸውም የሚኖሩ
ትን ሁሉ የፈጠርክ ጌታ ሆይ፥ 25-26 አንተ
በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በአባታችን በዳ
ዊት አንደበት ‘አሕዛብ ለምን አጉረመ
ረሙ? ሕዝቦቹስ ለምን በከንቱ ዶለቱ፤የም
ድር ነገሥታትስ እግዚአብሔርንና የተቀባ
ውን መሲሕ ለመቃወም ስለምን ተባበሩ?’
ብለህ ተናግረሃል።
27 «እነሆ ይህ ቃል በዚች ከተማ ውስጥ
በዛሬይቱ ዕለት በትክክል ተፈጽሟል። ሄሮ
ድስና ጴንጤናዊው ጲላጦስ ከአሕዛብና
ከሕዝበ እሥራኤል ጋር ተባብረው፥መሲሕ
አድርገህ የላክኸውን ኢየሱስን ለመቃወም
አብረዋል። 28 ያደረጉትም ሁሉ አንተ በኃ
ይልህና በፈቃድህ አስቀድመህ የወሰንከውን
ነው። 29 አሁንም ጌታ ሆይ፥እንዴት እንደዛ
ቱብን ተመልከት፤ ለእኛም ለአገልጋዮችህ
ቃልህን ያለ ፍርሃት ለመናገር እንድንችል
ድፍረትን ስጠን። 30 የፈውስ ኃይልህንም
ላክ። እንደዚሁም በቅዱስ ልጅህ በኢየሱስ
ክርስቶስ ስም ተአምራትና ድንቅ ሥራዎች
ይፈጸሙ።»
31 ይህንን ብለው ከጸለዩ በኋላ ተሰብስ
በው የነበሩበት ሥፍራ ተናወጠ። ሁሉም
በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ። የእግዚአብሔር
ንም ቃል ያለ ፍርሃት በድፍረት መናገር
ጀመሩ።
32 ምዕመናኑም ፍጹም የሆነ መግባባ
ትና መተሳሰብ ነበራቸው። ያላቸውን ነገር
ሁሉ በጋራ ይጠቀሙበት ነበር እንጂ
ማንም ሰው፥ ‘ይህ የእኔ ነው’ የሚለው
የግል ሀብት አልነበረውም። 33 ሐዋርያትም
ስለ ጌታ ኢየሱስ ትንሣኤ በታላቅ ኃይል
ይመሰክሩ ስለነበር፥በሁሉም ላይ የእግዚአ
ብሔር ጸጋ በሙላት አድሮባቸው ነበር።
34-35 በመካከላቸውም አንድ እንኳ ችግረኛ
አልነበረም። ምክንያቱም ቤት ወይም
ርስት ያላቸው ሁሉ ሸጠው እያመጡ ገንዘ
ቡን ለሐዋርያት ይሰጡ ነበር። ሐዋርያትም
ገንዘቡን ለያንዳንዱ እንደሚያስፈልገው
ያህል ያድሉ ነበር።
36 ከቆጵሮስ የመጣ ዮሴፍ የሚባል
ከሌዊ ወገን የሆነ ሰው ነበር። ሐዋርያት
ግን ስሙን ለውጠው በርናባስ ብለው ይጠ
ሩት ነበር። ትርጓሜውም ‘የመጽናናት
ልጅ’ ማለት ነው። 37 በርናባስ ርስታቸውን
ሸጠው ገንዘቡ ለችግረኞች እንዲሰጥ ለሐዋ
ርያት ካስረከቡት ሰዎች መካከል አንዱ
ነበር።

## ምዕራፍ 5

1 ሐናንያ የሚባል አንድ ሰው ሰጲራ
ከተባለች ሚስቱ ጋር ሆኖ መሬቱን ሸጠ።
2 ከሸጠም በኋላ ከሚስቱ ጋር ተማክሮ ከገን
ዘቡ ቀንሶ አስቀረና «መሬታችንን በዚህ
ዋጋ ሸጬለሁና ተቀበሉኝ» ሲል አምጥቶ
ለሐዋርያት አስረከበ።
3 ጴጥሮስም፥ «ሐናንያ ሆይ፥የሰይጣን
ማደሪያ እንደሆነ ሰው፥ ‘የሸጥኩት በዚህ
ዋጋ ነው’ ብለህ ለምን ትዋሻለህ? ይህን
የመሰለ ውሸት በመናገርህም ለማታለል
የሞከርከው፥እኛን ሳይሆን መንፈስ ቅዱስን
ነው። 4 ርስቱም ከመሸጡ በፊት የግል ንብ

ረትህ ስለነበር ፥ እንድትሸጠው ያስገደደህ
አልነበረም። ከሸጥከው በኋላም በገንዘብህ
ላይ ለማዘዝ መብት ስለነበረህ፥የፈለግኸውን
መወሰን ትችል ነበር። በመዋሸትህም ያታለ
ልከው ሰውን ሳይሆን እግዚአብሔርን ነው»
አለው።
5 ሐናንያም ይህንን ቃል ሲሰማ መሬት
ላይ ወድቆ ወዲያውኑ ሞተ። ይህንንም
ያዩና የሰሙ ሁሉ በጣም ፈሩ። 6 እዚያ የነ
በሩ ወጣት ወንዶችም ሬሳውን ገንዘው
አውጥተው ቀበሩት።
7 ይህ ከሆነ ከሦስት ሰዓት በኋላ፥በባሏ
ላይ የደረሰውን ነገር ያላወቀችው ሚስቱ
መጣች። 8 ጴጥሮስም፥ «እስቲ ንገሪኝ፥ለመ
ሆኑ ርስታችሁን የሸጣችሁት በምን ያህል
ዋጋ ነው? በዚሁ ብቻ ነው?» ሲል የገንዘ
ቡን ልክ ነግሮ ጠየቃት።
እርሷም መልሳ፥ «አዎን፥በዚሁ ዋጋ
ነው» አለችው።
9 ጴጥሮስም፥ «ይህማ የጌታን መንፈስ
ትፈታተኑት ዘንድ አንቺም ባልሽም ተስማ
ምታችሁበታል ማለት ነው! ባልሽን የቀበ
ሩት ሰዎች ይኸው ከደጅ ቆመውልሻል፤
አንቺንም ደግሞ ወስደው ይቀብሩሻል»
አላት።
10 ወዲያውም ከእግሩ ሥር ወድቃ
ሞተች። ወጣቶቹ ወንዶችም ገብተው ሬሳ
ዋን አንሥተው ከባሏ መቃብር አጠገብ ቀበ
ሯት። 11 በመላዋ ቤተ ክርስቲያንና ወሬ
ውን በሰሙ ሰዎች ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት
ወደቀ።
12 አማኞች ሁሉ 'የሰሎሞን መመላለሻ'
እየተባለ በሚጠራው ሥፍራ በየጊዜው ይሰ
በሰቡ ነበር። ሐዋርያትም ለትንግርት የሚ
ታዩ ልዩ ልዩ ድንቅ ሥራዎችና ተአምራት
በሕዝቡ መካከል ያደርጉ ነበር። 13 ምንም
እንኳ ከሚፈጽሙት ድንቅ ሥራዎች የተ
ነሣ ሰዎች ሐዋርያትን ቢያከብሩአቸውም፥
ከፍርሃታቸው የተነሣ ከእነርሱ ጋር አንድ
ሆኖ መቆጠርን አልደፈሩም። 14 ይሁን
እንጂ፥ብዙ ወንዶችና ሴቶች በጌታ በኢየ
ሱስ በማመናቸው የምዕመናን ቁጥር በየቀኑ
እየጨመረ ይሄድ ነበር። 15 ሰዎችም፥
«ጴጥሮስ ሲያልፍ ጥላው ቢያርፍባቸው
እንኳን ይድናሉ» በማለት በሽተኞችን በአ
ልጋ ተሸክመው፥በሰሌን ጠቅለው እያመጡ
ከመንገድ ዳር አስተኝተው፥በዚያ በኩል
ማለፉን ይጠባበቁ ነበር። 16 ከዚህም የተነሣ
በኢየሩሳሌም አካባቢ ከሚገኙ ከተሞች
ይህን የሰሙ ብዙ ሰዎች በሽተኞችንና አጋ
ንንት የሚጥላቸውን ሕመምተኞች እየያዙ
ይመጡ ነበር። የመጡትም ሁሉ ይፈወሱ
ነበር።
17 በዚህ ጊዜ ሊቀ ካህናቱና ተባባሪ
ዎቹ፥እንዲሁም ከሰዱቃውያን ወገን የሆኑ
ሰዎች፥በቅንዓት ተቃጥለው በሐዋርያት ላይ
ተነሡባቸው። 18 ይዘውም ከእሥር ቤት
አስገቡአቸው።
19 ነገር ግን ሲመሽ የእግዚአብሔር
መልአክ መጥቶ የእሥር ቤቱን በር ከፍቶ፥
20 «ከዚህ ውጡ፥ሄዳችሁም በቤተ መቅደሱ
አደባባይ ላይ ቆማችሁ ስለ ሕይወት ቃል
አስተምሩ» ብሎ ተለያቸው።
21 ሐዋርያትም ንጋት ላይ ወደ ቤተ
መቅደስ ሄደው መልአኩ እንደነገራቸው
የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ጀመሩ።
ሊቀ ካህናቱና ተባባሪዎች ከረፈደ በኋላ
መጥተው፥የአይሁድ ሸንጎ እንዲሰበሰብ አደ
ረጉ። ሐዋርያትንም ከእሥር ቤት አምጥ
ተው እንዲያቀርቡአቸው መልእክተኞች
ላኩ። 22 ነገር ግን የተላኩት መልእክተኞች
ሐዋርያትን በእሥር ቤት ውስጥ ሊያገኙአ
ቸው አልቻሉም። ስለዚህም ወደ ሸንጎው
ተመልሰው መጥተው፥ 23 «እሥር ቤቱ ስን
ደርስ በሩ በጥብቅ ተቆልፎ፥ዘበኞቹም ነቅ
ተው ሲጠብቁ አግኝተናቸዋል። በሩን ከፍ
ተን ወደ ውስጥ ስንገባ ግን እሥረኞቹ
የሉም» አሏቸው።
24 የቤተ መቅደሱ አዛዥና የካህናት አለ
ቆች ይህንን ሲሰሙ፥ «ምን ዓይነት ጉድ
ነው! የዚህ ነገር መጨረሻውስ ምን
ይሆን?» በማለት እርስ በርሳቸው ተያዩ።
25 ወዲያው ግን አንድ ሰው መጥቶ፥ «እነ
ዚያ እሥር ቤት የጨመራችኋቸው ሰዎች
ጠፍተዋል ስትሉ፥እነርሱ እንደሆን ይኸው
በቤተ መቅደስ አደባባይ ወጥተው ሕዝቡን
ያስተምራሉ» ብሎ ነገራቸው።
26-27 የመቅደሱ አዛዥ ይህን እንደሰማ
ወዲያውኑ ጭፍሮቹን አስከትሎ እነርሱ
ወደሚያስተምሩበት ቦታ ሄደ። ከዚያም
እንደደረሱ፥ትምህርቱን ያዳምጥ የነበረው
ሕዝብ በድንጋይ ይወግረናል ብለው ስለ
ፈሩ፥ሐዋርያትን በኃይልና በብትር ሳይሆን
ቀስ ብለው በዘዴና በማግባባት ብቻ ይዘዋ
ቸው መጥተው፥በጉባዔው ፊት አቀረቧ
ቸው።
28 ሊቀ ካህናቱም ሐዋርያትን፥ «'ኢየ
ሱስ' ስለምትሉት ስለዚህ ሰው እንዳታስተ
ምሩ ከዚህ በፊት ማስጠንቀቂያ ሰጥተናችሁ
አልነበረም? ይኸው አሁን የተሰጣችሁን

ማስጠንቀቂያ ጥሳችሁ የኢየሩሳሌምን
ከተማ በትምህርታችሁ ታምላላችሁ። ያን
ንም ሰው እኛ እንደ ገደልነው አድርጋችሁ
በሕዝቡ ፊት ታሳጡናላችሁ» አላቸው።
29 ጴጥሮስና ሌሎቹ ሐዋርያትም የሚከ
ተለውን መልስ ሰጡ፤ «ለሰዎች ከመታዘዝ
ይልቅ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይገባናል።
30 እናንተ ሰቅላችሁ የገደላችሁትን ኢየሱ
ስን፥ የአባቶቻችን አምላክ ከሞት አስነሥቶ
ታል። 31 የእሥራኤል ሕዝብም ንስሐ ገብ
ተው ስለ ኃጢአታቸው ይቅርታ እንዲያ
ገኙ፥ ኢየሱስን መሪና አዳኝ አድርጎ በኃይ
ልና በክብር ከቀኙ አስቀምጦታል። 32 ለዚ
ህም ነገር እኛ ምስክሮች ነን። እኛም ብቻ
አይደለንም። እግዚአብሔርን ለሚታዘዙ
የተሰጠው መንፈስ ቅዱስም፥ ለዚህ ነገር
ምስክር ነው።»
33 የሸንጎው አባላትም በሐዋርያት አነጋ
ገር በጣም ተቆጡ። የሞት ፍርድ ሊፈርዱ
ባቸውም ፈለጉ። 34 በዚህም ጊዜ ገማልያል
የተባለው የታወቀ ፈሪሳዊና የሕግ መምህር
ተነሥቶ፥ ሐዋርያትን ገለል እንዲያደርጉአ
ቸው ጠየቀ።
35 ከዚያም የሚከተለውን የምክር አሳብ
ለሸንጎው አቀረበ።
«የእሥራኤል ሰዎች ሆይ፥ በእነዚህ
ሰዎች ላይ ስለምታደርጉት ነገር አስቀድማ
ችሁ ልታስቡበት ይገባል። 36 ከዚህ በፊት
ቴዎዳስ የሚባል ሰው፥ አምፆ ተነሥቶ
አራት መቶ ያህል ተከታዮችም አግኝቶ
ነበር። ያው እንደምታውቁት መጨረሻው
አላማረም ተገደለ፤ተከታዮቹም ተበታትነው
የውኃ ሽታ ሆነው ቀርተዋል።
37 «ከእርሱ በኋላ ደግሞ፥የሕዝብ ቆጠራ
በተደረገበት ዘመን፥ገሊላዊው ይሁዳ ተነ
ሥቶ እሱም እንደዚሁ ብዙ ተከታዮች አግ
ኝቶ ነበር። የእርሱም መጨረሻ አላማረም፤
ተገደለ። ተከታዮቹም በያለበት ተበተኑ።
38 የእኔን ምክር መስማት ከፈለጋችሁ፥እነዚ
ህን ሰዎች ልቀቁአቸው። የሚያስተምሩትና
የሚያደርጉት ነገር ከሰው አሳብ የመነጨ
ከሆነ፥እናንተ ባትሉም በገዛ እጁ ይጠፋል።
39 ነገሩ ከእግዚአብሔር ከሆነ ግን፥በምንም
መንገድ ቢሆን ልታጠፏቸው አትችሉም።
ይልቁንም በዚህ በምታደርጉት ነገር ከእግ
ዚአብሔር ጋር እንዳትጣሉ መጠንቀቅ ይገ
ባችኋል።»
40 ገማልያል ባቀረበው በዚህ አሳብ
ሁሉም ተስማሙ። ስለዚህ ሐዋርያትን ወደ
እነርሱ ጠርተው ከገረፏቸው በኋላ፥ለወደ
ፊቱ በኢየሱስ ስም እንዳያስተምሩ በድጋሚ
አስጠንቅቀው ለቀቋቸው። 41 ሐዋርያትም
በኢየሱስ ምክንያት መከራ ለመቀበል በመ
ብቃታቸው ደስ እያላቸው ከአዳራሹ ወጥ
ተው ሄዱ። 42 በየቀኑም በቤተ መቅደስና
በየቤቱም፥ ለብዙ ጊዜ ይጠበቅ የነበረው
እውነተኛ መሲሕ ኢየሱስ መሆኑን ከማስተ
ማርና ከመስበክ ወደ ኋላ አላሉም።

## ምዕራፍ 6

1 የምዕመናን ቁጥር እየበዛ ሲሄድ፥የግ
ሪክ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑት አይሁድ ማጉረ
ምረም ጀመሩ። ያጉረመረሙበትም ምክን
ያት፥ «በየዕለቱ ምግብ በሚታደልበት ጊዜ
ባሎቻቸው ለሞቱባቸው ግሪክ ተናጋሪ አይ
ሁድ ሴቶች የሚሰጠው ምግብ፥ባሎቻቸው
ለሞቱባቸው ዕብራይስጥ ተናጋሪ የአይሁድ
ሴቶች ከሚሰጠው ያነሰ ነው» በማለት
ነበር። 2 ከዚህም የተነሣ አሥራ ሁለቱ ሐዋ
ርያት ምዕመናኑን ሁሉ ለስብሰባ ጠሩ።
ሐዋርያትም፥ «አሁን ይህን የምትሉት
የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማሩን ትተን፥
ምግብ እንድናድል ነው? 3 የሚሻለውስ
እናንተ በመልካም ጠባያቸው የታወቁ፥በመ
ንፈስ ቅዱስ ኃይልና በጥበብ የተሞሉ ሰባት
ሰዎች ከመካከላችሁ ብትመርጡ ነው። እና
ንተ የመረጣችኋቸውንም ሰዎች፥ ይህንኑ
ተግባር እንዲያከናውኑ እኛ ኃላፊነቱን እን
ሰጣቸዋለን። 4 እኛም የመጸለይ፥የመስበኩ
ንና የማስተማሩን ሥራ ለመሥራት በቂ
ጊዜ ይኖረናል» አሏቸው።
5 ሐዋርያት ያቀረቡት አሳብ ተቀባይነት
ስላገኘ፥የሚከተሉት ሰዎች ለዚሁ ተግባር
ተመረጡ። እነርሱም በእምነትና በመንፈስ
ቅዱስ የተሞላውን እስጢፋኖስን፥ፊልጶስን፥
ጵሮኮሮስን፥ኒቃሮናን፥ጢሞናን፥ጳርሜናን፥
እንዲሁም ወደ አይሁድ ሃይማኖት ገብቶ
የነበረውን የአንጾኪያውን ተወላጅ ኒቆላዎ
ስን መረጡ። 6 የተመረጡትም ሰባቱ ሰዎች
ከሐዋርያት ፊት ቀረቡ። ሐዋርያትም እጃ
ቸውን ጭነው በመጸለይ ሾሙአቸው።
7 የእግዚአብሔር ቃል በኃይልና በሙ
ላት በመሰበኩም፥በኢየሩሳሌም የምዕመናኑ
ቁጥር እጅግ እየበዛ ይሄድ ጀመር። ከአይ
ሁድ ካህናትም ብዙዎቹ በጌታ በኢየሱስ
ክርስቶስ አመኑ። 8 ጸጋንና ኃይል የተሞ
ላው እስጢፋኖስም እጅግ አስደናቂ የሆኑ
ተአምራትን በሕዝቡ ፊት ያደርግ ነበር።
9 'ነፃ የወጡ ሰዎች ምኵራብ' እየተባለ

የሚጠራው የአይሁድ ጸሎት ቤት አባሎች
የሆኑ፥ከቀሬናና ከእስክንድርያ፥ከኪልቅያና
ከእስያ ከመጡ አይሁድ መሰሎቻቸው ጋር
አብረው እስጢፋኖስን ክርክር ገጠሙት።
10 ነገር ግን ፥ ከመንፈስ ቅዱስ በተሰጠው
ኃይልና ጥበብ የተሞላውን እስጢፋኖስን፥
ሊቋቋሙት አልቻሉም።
11 ስለዚህ፥ «ይህ ሰው ሙሴንና እግዚአ
ብሔርን ሲሳደብ ሰምተነዋል» የሚሉ የሐ
ሰት ምስክሮች አዘጋጅተው ከሰሱት።
12 ይህ እንደ ተሰማም የሕዝቡ ቁጣ
በረታ። በዚህ ጊዜ የአገር ሽማግሌዎችና
የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን እስጢፋኖስ
እንዲያዝ አድርገው ወደ ፍርድ ሸንጎ አቀረ
ቡት። 13 የተቀጠሩትም የሐሰት ምስክሮች
ቀርበው፥ «ይህ ሰው ቤተ መቅደሳችንንና
የሙሴን ሕግ ሲነቅፍ ሰምተናል።
14 «እንደዚሁም ፥ 'የናዝሬቱ ኢየሱስ
ይህን ቤተ መቅደስ ያፈርሰዋል። የሙሴንም
ሕግ ይሽረዋል' ብሎ ሲናገር በጆሮአችን
ሰምተናል» ሲሉ መሰከሩበት። 15 በዚያ የነ
በሩትም የአይሁድ ሸንጎ አባላት ሁሉ የእስ
ጢፋኖስ ፊት እንደ መልአክ ፊት ሲያበራ
ታያቸው።

## ምዕራፍ 7

1 ሊቀ ካህናቱ እስጢፋኖስን፥ «ይህን
የቀረበብህን ክስ ታምናለህ? አታምንም?»
ብሎ ጠየቀው።
2 እስጢፋኖስም የሚከተለውን መልስ
ሰጠ። «አባቶቼና ወንድሞቼ አድምጡኝ።
አባታችን አብርሃም ወደ ካራን ምድር ከመ
ሄዱ በፊት በመስጴጦምያ አገር ሲኖር ሳለ፥
የክብር ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር ተገ
ለጠለት። 3 'ከአገርህ ወጥተህ፥ከዘመዶችህም
ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ አገር ሂድ' ሲል
አዘዘው። 4 አብርሃምም የከለዳውያንን አገር
ትቶ ወደ ካራን ሄደ። አብርሃም፥ አባቱ
ከሞተ በኋላ ግን ካራንን ትቶ ዛሬ እኛ ወደ
ምንኖርባት ወደዚች አገር መጣ። 5 በዚያን
ጊዜ እግዚአብሔር ለአብርሃም አንዲት ስን
ዝር መሬት እንኳ ርስት አድርጎ አልሰጠ
ውም ነበር። ግን የኋላ ኋላ ይህችን ምድር
ለእርሱና ከርሱም በኋላ ለዘሩ ርስት አድርጎ
እንደሚሰጠው ቃል ገባለት። አብርሃም
ይህን የተስፋ ቃል ሲቀበል ልጅ አልነበረ
ውም። 6 ከዚህም በቀር ዘሮቹ በባዕድ አገር
በስደት ለአራት መቶ ዓመታት በባርነት
እንደሚገዙ አስቀድሞ ነግሮት ነበር። 7 በተ
ጨማሪም፥ ባሪያ አድርገውና አስጨንቀው
የሚገዟቸውንም ሕዝብ እንደሚቀጣቸውና
ከዚያ በኋላም ነፃ አድርጎ ወደዚች ምድር
እንደሚመልሳቸው፥ወደዚች ምድር የተመ
ለሱትም የአብርሃም ዘሮች እግዚአብሔርን
እንደሚያመልኩ ነግሮት ነበር።
8 «እንደዚሁም እግዚአብሔር ለአብር
ሃም የመገረዝን ሥርዓት ደነገገለት። ይህ
የግዝረት ሥርዓት የተሰጠውም፥ በእርሱና
በአብርሃም መካከል ላለው ቃል ኪዳን
መጠበቅ፥ ማረጋገጫ ምልክት እንዲሆን
ነው። አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፥በስምንተ
ኛውም ቀን ገረዘው፤ከዚያም ይስሐቅ ያዕቆ
ብን ወለደ፥ያዕቆብም የአሥራ ሁለቱን ነገደ
እሥራኤል አባቶች ወለደ። 9 አባቶችም በዮ
ሴፍ ስለቀኑበት ለምድያም ነጋዴዎች ሸጡ
ትና በባርነት ወደ ግብፅ ተወሰደ። እግዚአ
ብሔር ግን ዮሴፍን አልተለየውም ነበር።
10 ስለዚህም ከችግሩና ከመከራው ሁሉ አወ
ጣው። ማስተዋልና ጥበብንም ሰጠው። በግ
ብፅ ንጉሥ በፈርዖንም ፊት ተወዳጅነትን
እንዲያገኝ አደረገው። የግብፅ ንጉሥም ከእ
ርሱ በታች ሙሉ ሥልጣን ሰጥቶ፥በመላ
አገሩ ላይ ኃላፊ አድርጎ ሾመው።
11 «በዚያን ዘመንም በግብፅና በከነዓን
ከፍተኛ እልቂት ያስከተለ ረሃብ ገባ። የሚ
በላ ነገር በመታጣቱም አባቶቻችን ከፉኛ
ተራቡ። 12 ያዕቆብም በምድረ ግብፅ እህል
መኖሩን ስለሰማ፥ሄደው እንዲሸምቱ አባቶ
ችን ለመጀመሪያ ጊዜ ላካቸው። እነርሱም
ያገኙትን ይዘው ተመለሱ። 13 አባቶችም
ለሁለተኛ ጊዜ እህል ፍለጋ ወደ ምድረ
ግብፅ ወረዱ። በዚህም ጊዜ ዮሴፍ ማንነቱን
እንዲያውቁ ራሱን ለወንድሞቹ ገለጠላ
ቸው። ፈርዖንም የዮሴፍን ዘመዶች አወቀ።
14 ከዚያም አባቱንና ወንድሞቹን፥የወንድሞ
ቹንም ቤተ ሰቦች ወደ ምድረ ግብፅ እንዲ
መጡ አደረገ። በዚያን ጊዜ ወደ ምድረ
ግብፅ የወረዱት የያዕቆብ ልጆችና የልጅ
ልጆቹ ቁጥር በጠቅላላው ሰባ አምስት
ነበር። 15 ያዕቆብም ወደ ምድረ ግብፅ
መጥቶ ሲኖር፥ ሞት አይቀርምና እርሱም
አባቶችም እዚያው ሞቱ። 16 በኋላ ግን አስ
ከሬናቸው ወደ ሴኬም መጥቶ፥አብርሃም
ከኤሞር ልጆች በገዛው የመቃብር ቦታ
ለመጨረሻ ጊዜ ዐረፈ።
17-18 «እግዚአብሔር ለአብርሃም በመ
ሐላ የሰጠው ተስፋ የሚፈጸምበት ጊዜ እን
ደተቃረበ፥በምድረ ግብፅ የነበረው የእሥራ
ኤል ሕዝብ ቁጥር እየበዛ ሄደ። በዚያን
ዘመን ስለ ዮሴፍ ምንም ነገር የማያውቅ

ሌላ ንጉሥ በግብፅ አገር ነገሠ። 19 ንጉ
ሡም ወገኖቻችንን ክፉኛ ተተናኰላቸው።
የሚወለዱትም ሕፃናት በሕይወት መኖር
እንዳይችሉ ፥ ከወላጆቻቸው ተለይተው እን
ዲጣሉ አዘዘ።
20 «ሙሴም በዚያኑ ዘመን ተወለደ።
በእግዚአብሔር ዘንድም የተወደደ ሕፃን
ሆነ። ወላጆቹም ሊጥሉት ስላልፈለጉ ለሦ
ስት ወራት በቤታቸው ደብቀው አስቀመ
ጡት። 21 ነገሩ የማያዋጣ መሆኑን ሲረ
ዱም ፥ ከቤት አውጥተው ከወንዝ ዳር በቅር
ጫት አስቀመጡት። የፈርዖንም ልጅ ከተጣ
ለበት አንሥታ ወስዳ እንደ ልጅዋ አድርጋ
አሳደገችው። 22 ሙሴም የግብፆችን ጥበብ
ሁሉ እየተማረ አደገ። በንግግር አዋቂነቱም
ሆነ በማናቸውም የሥራ ችሎታው የተመሰ
ገነ ሆነ።
23 «ሙሴ አርባ ዓመት ሲሞላው የወገኖ
ቹን የእሥራኤላውያንን ሁኔታ ለማየት
ፈለገ። 24 መንገድ ላይ አንድ ግብፃዊ አን
ዱን እሥራኤላዊ ሲያንገላታው አየ። ለእሥ
ራኤላዊ ወገኑ ረድቶ ግብፃዊውን መትቶ
ገደለው። 25 ሙሴ ፥ እግዚአብሔር በእርሱ
አማካይነት ነፃ እንደሚያወጣቸው ፥ ወገኖቹ
የተረዱ መስሎት ነበር። እነርሱ ግን ይህን
አልተረዱም ነበር።
26 «በማግስቱ ከወገኖቹ ሁለቱ ሲጣሉ
አግኝቶ ሊገላግላቸው በመፈለግ በለሰለሰ
አንደበት ፥ ‘ጎበዝ ፥ እናንተ ደግሞ ወንድማ
ማች ሆናችሁ ሳለ ፥ እንደባዳ ምን ያጣላች
ኋል?’ አላቸው።
27 «ነገር ግን ያ የገዛ ወገኑን ይደበድብ
የነበረው ሰው ፥ ሙሴን ገፈተረና ፥ ‘ምን አገ
ባህ? በእኛስ ላይ ገዢና ዳኛ አድርጎ ማን
ሾመህ? 28 ያን ግብፃዊ ትናንት እንደገደል
ከው እኔንም ልትገድለኝ ትፈልጋለህ?’
አለው። 29 ከዚህ በኋላ ሙሴ ፥ ‘ሰው መጣ
ደሌ ለካ ታውቆብኛል’ ብሎ ከግብፅ አገር
ሸሽቶ በምድያም ምድር በስደተኝነት ተቀ
መጠ። በዚያም ሁለት ወንዶች ልጆች
ወለደ።
30 «ከአርባ ዓመት በኋላ በሲና ተራራ
አጠገብ ባለው በረሃ በሚነድ ቁጥቋጦ
ውስጥ የእግዚአብሔር መልአክ ለሙሴ ተገ
ለጠለት። 31 እሱም ይህን ባየ ጊዜ በጣም
ደነቀው። ምን እንደሆነ ለማየት ንጉቶ ሲቀ
ርብ ፥ ጌታ 32 ‘እኔ የአባቶችህ የአብርሃም ፥
የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ነኝ’ ሲለው
ሰማ። ሙሴም በጣም ስለፈራ ቀና ብሎ
ለማየት አልቻለም።
33 «ቀጥሎም ፥ ‘ይህ የቆምክበት ምድር
የተቀደሰ ስለሆነ ጫማህን ከእግርህ አው
ልቅ። 34 በግብፅ ያለውን የሕዝቤን መከራ
አየሁ፤ የጭንቀት ጩኸታቸውንም ሰማሁ፤
ስለዚህም ላድናቸው ወረድሁ። አሁንም
አንተን ወደ ግብፅ እልክሃለሁና ተዘጋጅ’
አለው። 35 የእሥራኤል ሕዝብ ከዚህ
በፊት ፥ ‘በእኛ ላይ ገዢና ዳኛ አድርጎ የሾ
መህ ማን ነው?’ በማለት ያንጓጠጡትን
ያንኑ ሙሴን ፥ በቁጥቋጦ ውስጥ በታየው
መልአክ አማካይነት መሪና ታዳጊ አድርጎ
እግዚአብሔር ወደ እነርሱ ላከው። 36 የእ
ሥራኤልን ሕዝብ ከምድረ ግብፅ ያወጣ ፥
እንዲሁም በግብፅ ፥ በቀይ ባሕርና አርባ ዓመ
ትም በበረሃ ድንቅና ተአምራትን እያደረገ
የመራቸው ይኸው ሙሴ ነበር።
37 «እሥራኤላውያንን ፥ ‘እግዚአብሔር
ከወንድሞቻችሁ መካከል እንደ እኔ ያለ
ነቢይ ያስነሣላችኋልና እርሱን ስሙት’ ያላ
ቸውም ይኸው ሙሴ ነበር። 38 በበረሃ በሕ
ዝቡ ጉባዔ መካከል ከአባቶች ጋር የነበረ ፥
በሲና ተራራም ላይ ከእግዚአብሔር መል
አክ ጋር የተነጋገረና የሕይወትን ቃል ተቀ
ብሎ ለእኛ ያስተላለፈ ሙሴ ነበር።
39 «አባቶቻችን ግን ሙሴን ተቃወሙት
እንጂ አልታዘዙትም። በልባቸውም ወደ
ምድረ ግብፅ ተመለሱ። 40 አሮንንም ፥ ‘ከግ
ብፅ ምድር ያወጣን ሙሴ የት እንደ ደረሰ
አናውቅምና ፥ መርተው ወደ ምድረ ግብፅ
የሚመልሱን አማልክት ሥራልን’ ብለው
አስጨነቁት። 41 ከዚያም በጥጃ መልክ
ጣዖት ሠርተው መሥዋዕት አቀረቡለት።
በእጃቸውም ሥራ ደስ አላቸው። 42 ስለዚ
ህም እግዚአብሔር ተለያቸው። ፀሐይን ፥
ጨረቃንና ከዋክብትንም እንዲያመልኩ
ተዋቸው። ይህም በነቢያት መጽሐፍ ከተጻ
ፈው ጋር ይስማማል። በነቢያትም ‘እሥራ
ኤል ሆይ ፥ አርባ ዓመት ሙሉ በበረሃ የሠዋ
ኸው መሥዋዕት ለእኔ ነውን? 43 የጣዖታች
ሁን የሞሎክን ድንኳንና ፥ የሬምፋምን
ኮከብ ምስል አልነበረም የተሸከማችሁት?
በእጃችሁ ሠርታችሁ ትሰግዱላቸው የነበሩ
አማልክቶቻችሁ እነዚህ አልነበሩም? ስለ
ዚህ እኔም ከባቢሎን ወደ ራቀ ቦታ እንድት
ሰደዱ አደርጋችኋለሁ’ ተብሎ ተጽፏል።
44 «አባቶቻችን በረሃ ለበረሃ በሚንከራተ
ቱበት ጊዜ ፥ ‘የምስክር ድንኳን’ አብሯቸው
ነበር። ይህም ድንኳን የተሠራው እግዚአብ
ሔር ለሙሴ በነገረውና ባሳየው ቅርፅ መሠ
ረት ነበር። 45 ኢያሱ አባቶቻችንን እየመራ

አሕዛብን አሸንፎ ወደዚች ምድር ሲገባ፣
ይህ የምስክር ድንኳን አብሯቸው ነበረ።
እስከ ንጉሥ ዳዊት ዘመን ድረስም አልተለ
ያቸውም።

46 «እግዚአብሔር እጅግ አድርጎ በባረ
ከው ጊዜ፣ዳዊት ለያዕቆብ አምላክ ለእግዚአ
ብሔር ማደሪያ የሚሆን የቤተ መቅደስ
ሕንፃ ለመሥራት አሰበ። 47 ነገር ግን ቤተ
መቅደሱን የሠራው ዳዊት ሳይሆን ልጁ
ሰሎሞን ነበር። 48-49 ይሁን እንጂ ኃያሉ
እግዚአብሔር ሰው በሠራው ቤተ መቅደስ
ውስጥ አይኖርም። ነቢዩም፣ 'ሰማይ ዙፋኔ
ነው፤ምድርም የእግሬ ማረፊያ ናት። ታዲያ
ምን ቤት ያስፈልገኛና ነው የምትሠሩልኝ?
የማርፍበትስ ቦታ የቱ ነው? 50 እነዚህን
ሁሉ የፈጠርኳቸው እኔ አይደለሁምን?'
ብሏል።

51 «እናንተ ትከሻችሁ ያበጠ እምቢተ
ኞች፤መንፈስ ቅዱስን የምትቃወሙት እስከ
መቼ ድረስ ነው? እንደ አባቶቻችሁ እናን
ተም ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን እንደዚህ
እንደተቃወማችሁ ልትኖሩ ነው? 52 ከነቢ
ያት መካከል አባቶቻችሁ ያላሳደዱት ማን
አለ? አባቶቻችሁ ስለ ጻድቁ ስለ ክርስቶስ
መምጣት አስቀድመው ትንቢት የተናገሩ
ትን ነቢያት እንኳን ገድለዋቸዋል። እናን
ተም ጻድቁን ጌታ አሳልፋችሁ ሰጣችሁት፤
ገደላችሁትም። ታዲያ በአባቶቻችሁና በእና
ንተ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
53 በመላእክት አማካይነት ሕግን ተቀብላ
ችሁ ነበር። ነገር ግን፣ 'እምቢ አሻፈረን
ለዚህ ሕግ አንታዘዝም' አላችሁ» ብሎ ንግ
ግሩን አቆመ።

54 እነርሱም እስጢፋኖስ በተናገራቸው
በነዚህ ቃላት አምርረው ተቆጡ። ከቁጣቸ
ውም የተነሣ በንዴት ከንፈራቸውን ይነክሱ
ጀመር። 55 እስጢፋኖስ ግን በመንፈስ
ቅዱስ ኃይል ተሞልቶ ወደ ሰማይ ቀና
ብሎ ሲመለከት፣ የእግዚአብሔርን ክብር
አየ። ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ
ተመለከተ። 56 ስለዚህ፣ «እነሆ፣ሰማይ ተከ
ፍቶ፣ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ
አየዋለሁ» አላቸው።

57 እነርሱ ግን ይህን ሲሰሙ፣ ሊታገሡ
ባለመቻላቸው እየተሯሯጡ ሄደው ያዙት።
58 ከዚያም እያንገላቱ ከከተማው ውጭ አወ
ጡት። ገዳዮቹም መደረቢያቸውን አውል
ቀው፣ሳውል የሚባል ጐበዝ እንዲጠብቅላ
ቸው አድርገው፣ እስጢፋኖስን በድንጋይ
ይወግሩት ጀመር።

59 እስጢፋኖስ ግን በድንጋይ ሲወግ
ሩት፣ «ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ነፍሴን ተቀበ
ላት» ብሎ ጸለየ። 60 ከዚያም በጉልበቱ
ተንበርክኮ፣ «አቤቱ ጌታ ሆይ፣ እነዚህ
ሰዎች የሚያደርጉትን አያውቁምና ይህን
በደላቸውን አትቁጠርባቸው» በማለት ለሚ
ወግሩት ሰዎች ከልቡ ከጸለየላቸው በኋላ
ሞተ።

## ምዕራፍ 8

1 እስጢፋኖስ እንዲገደል በምክሩ ከተስ
ማሙት ሰዎች አንዱ ሳውል ነበር። እስጢ
ፋኖስ በተገደለበት በዚያኑ ዕለት፣ ኢየሩሳ
ሌም በምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ላይ
ታላቅ ስደት ተነሣ። በዚህም ምክንያት
ከሐዋርያት በቀር ሌሎች ደቀመዛሙርት
ሁሉ ወደ ይሁዳና ወደ ሰማርያ አገሮች እየ
ሸሹ ሄዱ። 2 እስጢፋኖስንም አንዳንድ
ደጋግ ሰዎች፣ተላቅሰው በታላቅ ኃዘን ቀበ
ሩት። 3 ሳውል ግን የክርስቲያኖችን ደብዛ
ለማጥፋት ቆርጦ የተነሣ በመሆኑ፣ በየቦ
ታው ይሯሯጥ ጀመር። ወንድ ሴት ሳይል
ያገኛቸውን ክርስቲያኖች ሁሉ ከየቤቱ
ጎትቶ እያወጣ፣ እሥር ቤት ያጉራቸው
ነበር።

4 የተበተኑትም ደቀመዛሙርት በየደረሱ
በት ቦታ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ያስተ
ምሩ ነበር። 5 ከነዚህም አንዱ ፊልጶስ
ነበር። እሱም ወደ አንድ የሰማርያ ከተማ
ሄዶ ስለ ክርስቶስ አስተማረ። 6 ሰዎችም
ፊልጶስ የሚያደርጋቸውን ታላላቅ ተአም
ራት በማየት ትምህርቱን በጥሞና ያደምጡ
ነበር። 7-8 ርኩሳን መናፍስት በኃይል እየ
ጮኹ ከብዙ ሰዎች በመውጣታቸው፣ሽባዎ
ችና አንካሶች በመፈወሳቸው፣ በከተማይቱ
ታላቅ ደስታ ሆነ።

9-11 በዚያች ከተማ የሚኖር ሲሞን የሚ
ባል አንድ አስማተኛ ሰው ነበር። እርሱም
ከብዙ ጊዜ ጀምሮ በአስማት ሥራው ሕዝ
ቡን አፍዝዞ እያስደነቀ፣ ታላቅ ሰው መሆ
ኑን አሳምኖ ድፍን ሰማርያን ሲያታልል
የኖረ ሰው ነበር። ከዚህም የተነሣ ትልቁም
ትንሹም ፈርቶና አክብሮ የሚናገረውንም
ሁሉ 'አሜን' ብሎ ይቀበለው ነበር።
12 ይሁን እንጂ ፊልጶስ ስለ እግዚአብሔር
መንግሥትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተ
ምር በሰሙ ጊዜ፣ ብዙ ወንዶችና ሴቶች
አምነው ተጠመቁ። 13 አስማተኛው ሲሞን
እንኳን ሳይቀር በጌታ ኢየሱስ አምኖ በመ
ጠመቅ፣ፊልጶስን በሄደበት ሁሉ ይከተለው

ነበር። ፊልጶስ በሚያደርጋቸውም ተአም
ራት ይደነቅ ነበር።
14 በኢየሩሳሌም የነበሩ ሐዋርያት፥የሰማ
ርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል መቀበላቸ
ውን ሲሰሙ፥ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ላኩላ
ቸው። 15 ጴጥሮስና ዮሐንስ ሰማርያ እንደ
ደረሱ፥ያመኑት ሰዎች መንፈስ ቅዱስን እን
ዲቀበሉ ጸለዩላቸው። 16 ምክንያቱም የሰማ
ርያ ሰዎች በጌታ ኢየሱስ አምነው ይጠ
መቁ እንጂ፥መንፈስ ቅዱስን ገና አልተቀበ
ሉም ነበር። 17 ስለዚህ ጴጥሮስና ዮሐንስ
በሰዎቹ ላይ እጆቻቸውን ጭነው በጸለዩላ
ቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ።
18-19 ሲሞን፥ሐዋርያት እጆቻቸውን በሰ
ዎቹ ላይ ሲጭኑባቸው መንፈስ ቅዱስን እን
ደተቀበሉ ባየ ጊዜ፥ለሐዋርያት ገንዘብ አም
ጥቶ በመስጠት፥ «እኔም እጄን የምጭንባ
ቸው ሰዎች ሁሉ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀ
በሉ ለማድረግ የሚያስችል ሥልጣን
ስጡኝ» ብሎ ጠየቃቸው።
20 ጴጥሮስም መልሶ፥ «የእግዚአብሔርን
ስጦታ በገንዘብ ለመግዛት አስበሃልና ገንዘብ
ህም አንተም አብራችሁ ጥፉ። 21 እግዚአብ
ሔርን በቅን ልቦና ስላልቀረብከው፥ ይህን
ስጦታ ከቶ መቀበል አትችልም። 22-23 በል
ብህ ስላሰብከው ስለዚህ ክፉ ነገር ንስሐ
ግባ። እግዚአብሔር ይቅርታ ሊያደርግልህ
ስለሚችልም ለምነው፤ምክንያቱም በመራራ
ቅናት ተሞልተሀና በኃጢአት ገመድ ተተ
ብትበህ አይሃለሁ» አለው።
24 ሲሞንም፥ «እነዚህ የተናገርካቸው
አስፈሪ ነገሮች እንዳይደርሱብኝ ጸልይልኝ»
ብሎ ለመነው።
25 ጴጥሮስና ዮሐንስ በዚያች ከተማ ስለ
ጌታ ከመሰከሩና ካስተማሩ በኋላ፥እግረ መን
ገዳቸውን በሌሎች ብዙ የሰማርያ መንደ
ሮች ውስጥ የምሥራቹን ቃል እያስተማሩ
ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።
26-27 የእግዚአብሔር መልአክ ፊልጶስን፥
«ተነሥና ከኢየሩሳሌም በጋዛ በኩል አቋ
ርጦ ወደ በረሃ በሚያወርደው መንገድ
ሂድ» አለው። እንደ ተነገረው ሲሄድ፥በሠረ
ገላ የሚጓዝ አንድ ሰው አገኘ። ይህ ሰው
የኢትዮጵያን ንግሥት የህንደኬን ንብረት
የሚያስተዳድር፥ከፍተኛ ባለሥልጣን ነበር።
እርሱም ለስግደት ከሄደበት ከኢየሩሳሌም
ወዳገሩ በመመለስ ላይ ነበር። ሰውየውም
ስልብ ነበረ። 28 በሠረገላውም ሆኖ የነቢዩ
የኢሳይያስን መጽሐፍ ድምፁን ከፍ አድ
ርጎ እያነበበ ይጓዝ ነበር።
29 መንፈስ ቅዱስም ፊልጶስን፥ «ወደ
ሠረገላው ቀርበህ ይህን ሰው አነጋግረው»
አለው።
30 ፊልጶስም ወደ ሠረገላው ቀርቦ ኢት
ዮጵያዊው ባለሥልጣን የሚያነበውን ከሰማ
በኋላ፥ «ለመሆኑ ይህ የምታነበው ይገባ
ሃል?» በማለት ጠየቀው።
31 ሰውየውም፥ «የሚያስረዳኝ ሰው ሳይ
ኖር እንዴት አድርጎ ሊገባኝ ይችላል?»
ብሎ መለሰለት። ወዲያውም ፊልጶስን ሠረገ
ላው ላይ እንዲወጣ ጋበዘው።
32 ኢትዮጵያዊው ባለሥልጣን ከቅዱሳት
መጻሕፍት የሚያነበው ክፍል፥ «ወደሚታ
ረድበት ቦታ እንደሚነዳ በግ ዝም ብሎ
ሄደ፤ ጠጉሩን ሲሸልቱት ዝም እንደሚል
ጠቦት ተቃውሞ አላሰማም፤ አንዲት ቃል
እንኳን አልተነፈሰም፤ 33 በውርደቱም ትክ
ክለኛ ፍርድ ተነፈገ፤ ስለ ትውልዱስ ማን
ሊያወራለት ይችላል? ሕይወቱም ከምድር
ላይ ባጭር ተቀጭታለችና» የሚል ነበር።
34 ጃንደረባው ባለሥልጣንም በመገረም፥
«ለመሆኑ ኢሳይያስ ይህን የሚናገረው ስለ
ራሱ ነው ወይስ ስለ ሌላ?» ሲል ፊልጶስን
ጠየቀው።
35 ከዚያም ፊልጶስ ኢትዮጵያዊው ባለሥ
ልጣን ያነበው ከነበረው መጽሐፍና ከሌሎ
ቹም መጻሕፍት ስለ ኢየሱስ የተጻፈውን
ሁሉ ተንትኖ አስረዳው።
36 አብረው ሲጓዙ ውኃ ካለበት ቦታ
ደረሱ። ኢትዮጵያዊው ባለሥልጣንም ፊልጶ
ስን፥ «ውኃ ይኸው! ታዲያ እንዳልጠመቅ
ምን የሚከለክለኝ ነገር አለ?» ብሎ ጠየ
ቀው።
37 ፊልጶስም፥ «በፍጹም ልብህ ካመንክ
እንዳትጠመቅ የሚከለክልህ ምንም ነገር
የለም» ሲል መለሰለት።
ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም፥ «ኢየሱስ
ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ
አምናለሁ» አለ።
38 ባለሥልጣኑም ሠረገላው እንዲቆም
አዘዘ። ሁለቱም ተያይዘው ወደ ውኃው
ውስጥ ገቡ። ፊልጶስም አጠመቀው።
39 ከውኃው እንደ ወጡም የእግዚአብሔር
መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው። ኢትዮጵያዊው
ባለሥልጣንም ከዚያ በኋላ ፊልጶስን አላየ
ውም። ሆኖም ደስ እያለው ጉዞውን
ቀጠለ። 40 ፊልጶስ ግን በኋላ በአዛጦን ታየ።
ቂሣርያ እስኪደርስ ድረስም በየከተማዎቹ
ሁሉ፥ የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማረ
አለፈ።

## ምዕራፍ 9

1 ሳውልም የጌታን ደቀመዛሙርት ከም
ድር ገጽ ለማጥፋት ዝቶ ተነሣ። ወደ ሊቀ
ካህናቱም ሄዶ፥ 2 በደማስቆ የሚገኙትን
ክርስቲያኖች ወንዱንም ሴቱንም እያሠረ
ወደ ኢየሩሳሌም ለማምጣት እንዲችል
በዚያ የሚገኙት የአይሁድ ጸሎት ቤቶች
እንዲተባበሩት የሚያሳስብ የአደራ ደብዳቤ
እንዲጻፍለት ጠየቀ።
3 ደማስቆ ለመድረስ ጥቂት ሲቀረው፥
በድንገት የሚያንጸባርቅ ብርሃን ከሰማይ
በራበት። 4 ወዲያውም ደንግጦ በምድር ላይ
ወደቀ። በወደቀበትም ቦታ ሆኖ፥ «ሳውል
ሳውል ለምንድነው የምታሳድደኝ?» የሚል
ድምፅ ሰማ።
5 ሳውልም፥ «ጌታ ሆይ፥ አንተ ማን
ነህ?» ብሎ በፍርሃት መልሶ ጠየቀ።
«የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ። 6 በል
ተነሥና ወደ ከተማ ግባ። እዚያም ከደረስክ
በኋላ ምን ማድረግ እንደሚገባህ ይነገር
ሃል» አለው።
7 ከሳውል ጋር የነበሩት ሰዎች ግን
ድምፅ እየሰሙ ተናጋሪውን መለየት ባለመ
ቻላቸው የሚያደርጉት ጠፍቷቸው በቆሙ
በት ፈዘው ቀሩ። 8-9 ሳውልም ከወደቀበት
ተነሣ። ይሁን እንጂ ዓይኖቹ ሊያዩለት አል
ቻሉም። ስለዚህ አብረውት የነበሩት ሰዎች
እየመሩ ወስደው ደማስቆ አደረሱት። እዚ
ያም ዓይኑ ሳያይ፥እህል ውኃም ሳይቀምስ፥
ሦስት ቀን ውሎ አደረ።
10 በደማስቆም ሐናንያ የሚባል አንድ
ደቀመዝሙር ነበር። ጌታም በራእይ፥ «ሐና
ንያ!» ሲል ጠራው።
እርሱም፥ «አቤት ጌታ ሆይ፥ምን ልታ
ዘዝ?» አለው።
11 ጌታም፥ «ተነሥተህ 'ቀጥተኛው መን
ገድ' እየተባለ በሚጠራው ጐዳና ላይ ወዳ
ለው ወደ ይሁዳ ቤት ሂድ። እዚያ እንደ
ደረስክ ሳውል የሚባል የጠርሴስ ሰው ሲጸ
ልይ ታገኘዋለህ። 12 እኔም፥ሐናንያ የሚባል
ሰው ገብቶ እጁን ጭኖ ሲጸልይለት ዓይኖቹ
እንደሚያዩለት በራእይ አሳይቼዋለሁ»
አለው።
13 ሐናንያም፥ «ጌታ ሆይ፥ይህ ሰው ኢየ
ሩሳሌም በሚኖሩ ደቀመዛሙርት ላይ ብዙ
መከራ እንዳደረሰባቸው ሰምቻለሁ። 14 ወደ
ዚህ የመጣውም እዚህ የሚገኙትን ደቀመዛ
ሙርት ለማሠር ከሊቀ ካህናቱ ሥልጣን
ተቀብሎ ነው» ሲል መለሰ።
15 ጌታም ሐናንያን፥ «ተነሥተህ ሂድ!
ከዛሬ ጀምሮ፥ይህ ሰው፥በአሕዛብና በነገሥ
ታት፥በእሥራኤልም ሕዝብ ፊት ስለ እኔ
እንዲመሰክር መርጬዋለሁ። 16 ስለ እኔም
ብዙ መከራ እንደሚቀበል እገልጥለታለሁ»
አለው።
17 ሐናንያም እንደ ታዘዘው አደረገ።
እቤት ሲገባም፥ሳውልን አገኘ። እጁንም
በላዩ ላይ ጭኖ፥ «ወንድሜ ሳውል ሆይ፥
ወደዚህ ስትመጣ በመንገድ ላይ የተገለጠ
ልህ ጌታ ኢየሱስ፥በመንፈስ ቅዱስ እንድት
ሞላና ዓይንህም እንዲበራልህ ወዳንተ
ልኮኝ መጥቻለሁ» አለው።
18 ወዲያውም ከዓይኑ ቅርፊት የሚመ
ስል ነገር ስለ ወደቀለት እንደገና ማየት
ቻለ። ወዲያውም ተጠመቀ። 19-20 ምግብም
ቀርቦለት ተመግቦ ሰውነቱ ብርታት አገኘ።
በደማስቆ ከተማ ከሚኖሩ ደቀመዛሙርት
ጋር ጥቂት ቀናት ከሰነበተ በኋላ፥በየምኩራ
ቦቹ እየተገኘ ኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት
የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ገልጦ መሰ
ከረ።
21 የሰሙትም ሁሉ በመገረም፥ «ይህ
ሰው ከዚህ በፊት በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን
ደቀመዛሙርት እየተከታተለ መድረሻ
ያሳጣ የነበረው ሳውል አይደለምን? ወደ
ዚህ የመጣውስ በዚህ ከተማ የሚኖሩትን
ደቀመዛሙርት እያሠረ ወደ ሊቀ ካህናቱ
ለማቅረብ አልነበረም?» ተባባሉ።
22 የሳውልም ስብከት እያየለ ሄደ። በደ
ማስቆ የሚኖሩ አይሁድም፥ኢየሱስ መሲሕ
መሆኑን ከመጻሕፍት እየጠቀሰ ሳውል የሚ
ያቀርባቸውን ማስረጃዎች መቋቋም አልቻ
ሉም።
23 በዚህ ዓይነት ብዙ ቀኖች ካለፉ
በኋላ፥አይሁድ ሳውልን ለመግደል ወሰኑ።
24 ሊገድሉት ማሰባቸውንም ሳውል አወቀ።
እነርሱ ግን እንዳያመልጣቸው የከተማይ
ቱን በር ይዘው ቀንም ማታም ይጠብቁ
ነበር። 25 አንድ ቀን ሌሊት ከምዕመናን
ጥቂቶቹ ሳውልን ከከተማው ግንብ በቅር
ጫት ወደታች አውርደው እንዲያመልጥ
አደረጉት።
26 ሳውልም ከዚያ ወደ ኢየሩሳሌም
ሄደ። ኢየሩሳሌም እንደ ደረሰም እዚያ
ካሉት ምዕመናን ጋር ለመሥራት ቢሞክ
ርም፥ መለወጡ እውነት ስላልመሰላቸው
ፈርተው ሊያቀርቡት አልፈለጉም።
27 በኋላ ግን በርናባስ ሳውልን ወደ ሐዋር
ያት አቅርቦ፥በደማስቆ መንገድ ላይ ጌታ

ተገልጦ ያነጋገረው መሆኑንና ፥ ስለ ኢየሱስ
ክርስቶስ መሲሕነት ያለ አንዳች ፍርሃት
በደማስቆ መመስከሩን አረጋግጦ ነገራቸው።
28 ከዚህ በኋላ ሳውል ከደቀመዛሙርቱ ጋር
ሆኖ በኢየሩሳሌም ከተማ እየተዘዋወረ
በጌታ በኢየሱስ ስም በድፍረት ይመሰክር
ጀመር። 29-30 ከእርሱ ጋር ይከራከሩ የነበሩ
ውጭ አገር ተወልደው ያደጉ የግሪክ ቋንቋ
ተናጋሪ አይሁድ ግን ፥ ሳውል ስለ ክርስቶስ
መሲሕነት አጥብቆ ስለተከራከራቸው
ውስጥ ውስጡን ሊገድሉት ተመካከሩ።
ደቀመዛሙርቱም ይህን እንዳወቁ ወደ ቂሣ
ርያ አሸሹት። ከዚያም ወደ ጠርሴስ እንዲ
ሄድ አደረጉ።

31 በይሁዳ ፥ በገሊላና በሰማርያ የሚገኙ
አብያተ ክርስቲያናትም ሰላም አግኝተው ፥
እግዚአብሔርን በመፍራት ከመንፈስ ቅዱስ
በሚገኘው መጽናናት ተሞልተው እያደጉ
ሄዱ።

32 ይህ በእንዲህ እንዳለ ፥ ጴጥሮስ ከቦታ
ወደ ቦታ እየተዘዋወረ ሲያስተምር ፥ ልዳ
በምትባል ሥፍራ ወደሚኖሩት ምዕመናን
ደረሰ። 33 እዚያም ስምንት ዓመት ሙሉ
ሽባ ሆኖ አልጋ ላይ የዋለ ፥ ኤንያ የሚባል
ሰው አገኘ።

34 ጴጥሮስም ፥ «ኤንያ ሆይ ፥ ኢየሱስ ክር
ስቶስ ፈውሶሃልና ተነሥተህ አልጋህን አን
ጥፍ!» አለው። ኤንያ ወዲያውኑ ተነሣ፤ከበ
ሽታውም ተፈወሰ። 35 የልዳና የሰሮና ነዋሪ
ዎችም የኤንያን መፈወስ በማየታቸው
በጌታ ኢየሱስ አመኑ።

36 በኢዮጴም ጣቢታ የሚሏት አንዲት
አማኝ ነበረች። በግሪክ ቋንቋ ጣቢታ ማለት
ሚዳቋ ማለት ነው። እርሷም አዘውትራ በጎ
ሥራ የምትሠራና በተለይም ድሆችን የምት
ረዳ ደግ ሴት ነበረች። 37 በዚያን ሰሞን
ጣቢታ ታማ ሞተች። ወዳጆችዋም ሬሳዋን
አጥበው ገንዘው ፥ ፎቅ ላይ ባለው ክፍል
ውስጥ አሳረፉት። 38 ጴጥሮስ ለኢዮጴ
ቅርብ በሆነችው በልዳ ስለነበር ፥ አማኞች
ይህን ሲሰሙ ፥ በቶሎ እንዲመጣ ሁለት
ሰዎች ላኩበት። 39 መልእክቱ እንደ ደረሰ
ውም ጴጥሮስ ከመልእክተኞቹ ጋር መጣ።
ሰዎቹም የጣቢታ ሬሳ ወዳለበት ፎቅ ይዘ
ውት ወጡ። ሬሳው ወዳረፈበት ክፍል
ሲገባ ፥ ጣቢታ በሕይወተ ሥጋ በነበረች ጊዜ
ትረዳቸው የነበሩ መበለቶች ፈትላ ያለበሰቻ
ቸውን ልብሶች ይዘው ሬሳዋን ከበው ይላ
ቀሱ ነበር። 40 ጴጥሮስ ግን ሁሉም ወደ
ውጭ እንዲወጡ ካደረገ በኋላ ተንበርክኮ
ጸለየ። ወደ ሬሳውም ዘወር ብሎ ፥ «ጣቢታ
ተነሺ» አለ። እርስዋም ዓይኖቿን ከፍታ ፥
ጴጥሮስን ቀና ብላ አየችውና ተነሥታ ተቀ
መጠች። 41 ጴጥሮስም እጇን ዘርግቶ ከአስነ
ሣት በኋላ ፥ የሚላቀሱትን ሴቶችና ምዕመ
ናን ወደ ክፍሉ እንዲገቡ አመለከታቸው።
በሕይወት ያለችውንም ጣቢታ ፊታቸው
አቆማት።

42 ጣቢታ ከሞት የመነሣቷ ዜና ባንድ
ጊዜ መላው ኢዮጴን አዳረሰው። ከሰሙትም
ውስጥ ብዙ ሰዎች በጌታ አመኑ። 43 ጴጥሮ
ስም በኢዮጴ ስምዖን ከሚባል አንድ ቁር
በት ፋቂ ቤት ብዙ ቀኖች ተቀመጠ።

## ምዕራፍ 10

1 በቂሣርያ የሚኖር ቆርኔሌዎስ የሚባል
አንድ የጦር መኰንን ነበር። እርሱም በኢ
ጣሊያ ጦር ኃይል ውስጥ የአንድ ክፍል
የመቶ አለቃ ነበር። 2 ቆርኔሌዎስም ከነቤተ
ሰቡ እግዚአብሔርን የሚፈራና ችግረኞችን
የሚረዳ ቸር ፥ ዘወትርም ወደ እግዚአብሔር
የሚጸልይ ሰው ነበር። 3 አንድ ቀን ፥ ከቀኑ
ዘጠኝ ሰዓት ላይ ፥ የእግዚአብሔር መልአክ
እርሱ ወዳለበት ሥፍራ ሲመጣ በራእይ
ታየው። መልአኩም ፥ «ቆርኔሌዎስ» ብሎ
ጠራው።

4 እርሱም ትክ ብሎ መልአኩን ተመለከ
ተና ደንግጦ ፥ «ጌታ ሆይ ፥ ምን ልታዘዝ?»
አለው።

መልአኩም ቆርኔሌዎስን ፥ «እግዚአብ
ሔር ጸሎትህንና ለችግረኞች የምታደርገ
ውን ቸርነት አይቶ ደስ ብሎታል።
5-6 ባሕሩ አጠገብ ከሚኖረው ቁርበት
ፋቂው ስምዖን ቤት ፥ በእንግድነት ያረፈ
ጴጥሮስ የተባለ ሰው አለና ፥ ወደ ኢዮጴ
ሰዎች ልከህ አስጠራው» አለው።

7-8 መልአኩ ይህን ነግሮት እንደሄደ ፥
ቆርኔሌዎስ ከአገልጋዮቹ ሁለቱን ፥ ከወታደሮ
ቹም እንደ እርሱው እግዚአብሔርን የሚ
ፈራ አንዱን ፥ ጠርቶ ያየውን ነገር ሁሉ ከነገ
ራቸው በኋላ ወደ ኢዮጴ ላካቸው።

9-10 በማግስቱ መልእክተኞቹ ወደ ከተ
ማው ለመድረስ ትንሽ ሲቀራቸው ፥ ስድስት
ሰዓት ገደማ ጴጥሮስ ሊጸልይ ከቤቱ ሰገነት
ላይ ወጣ። ለጊዜው ቢርበውም ምሳ ገና
ስላልደረሰ ሰገነቱ ላይ ሆኖ ሲጠባበቅ ፥ እንደ
ማሸለብ አደረገውና ራእይ አየ። 11 በራእ
ዩም ፥ ሰማይ ተከፍቶ በአራት ማዕዘን የተያዘ
ትልቅ የተወጠረ ሸራ የሚመስል ነገር
ከላይ ወደ ታች ወደምድር ሲወርድ አየ።

12 በሸራውም ላይ (በአይሁድ ሃይማኖት
ሕግ እንዳይበሉ የተከለከሉ) አራት እግር
ያላቸው ልዩ ልዩ እንስሳት፥ የሰማይ ወፎ
ችና በደረታቸው የሚሳቡ ፍጥረቶች ሁሉ
ይታዩ ነበር።
13 ጴጥሮስ፥ «ተነሣና እነዚህን አርደህ
ብላ» የሚል ድምፅ ሰማ።
14 እርሱም፥ «ጌታ ሆይ፥እነዚህ ነገሮች
እንዳይበሉ የተከለከሉ ስለሆኑ እስካሁን
በልቻቸው አላውቅም፤ አሁንም አልበላቸ
ውም» ብሎ መለሰ።
15 ከዚያም፥ «እግዚአብሔር ንጹሕ ያደ
ረገውን አንተ፥ 'ርኩስ ነው' ብለህ አትከራ
ከር» የሚል ድምፅ እንደገና ሰማ።
16 ይህም ነገር ሦስት ጊዜ ደጋግሞ ከሆነ
በኋላ፥ ሸራው ተመልሶ ወደ ሰማይ ተወ
ሰደ። 17 ጴጥሮስም፥ «ይህ ያየሁት ራእይ
ምን ይሆን?» እያለ በአሳቡ ሲያወጣ ሲያወ
ርድ ቆርኔሌዎስ የላካቸው መልእክተኞች፥
«የስምዖን ቤት የቱ ነው?» እያሉ በፍለጋ
መጡ። እንደ ደረሱም ከበራፍ ሆነው
18 ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ፥ «ቤቶች!
እዚህ ቤት ጴጥሮስ የሚባል ሰው ይኖር
ይሆን?» ሲሉ ጠየቁ።
19 ጴጥሮስም ስላየው ራእይ በልቡ ሲያሰ
ላስል ሳለ መንፈስ ቅዱስ፥ «ጴጥሮስ፥ሦስት
ሰዎች አንተን ፍለጋ መጥተዋል። 20 የላክኋ
ቸውም እኔ ስለሆንኩ ሳትጠራጠር አብረሃ
ቸው ሂድ» አለው።
21 ጴጥሮስም ከነበረበት ሰገነት ወርዶ፥
«ጴጥሮስ ማለት እኔ ነኝ። ምነው፥ ደህና
ፈለጋችሁኝ?» ብሎ ጠየቃቸው።
22 እነርሱም ሮማዊው መቶ አለቃ ቆርኔ
ሌዎስ፥እግዚአብሔርን የሚፈራ፥ደግ፥በአይ
ሁድ ዘንድ የተወደደና የተከበረ ሰው መሆ
ኑን በዝርዝር ነገሩት። የእግዚአብሔር መል
አክ ለቆርኔሌዎስ በራእይ ተገልጦ፥ ወደ
ጴጥሮስ መልእክተኞች ልኮ እንዲያስጠራ
ውና እግዚአብሔር የሚፈልግበትንም ነገር
ከእርሱ እንዲሰማ፥ትእዛዝ የተቀበለ መሆኑን
አስረዱት።
23 ጴጥሮስም ተልከው የመጡትን ሰዎች
ወደ ቤት አስገብቶ አስተናገዳቸው። በሚቀ
ጥለው ቀን ኢዮጴ ከነበሩት ደቀመዛሙርት
ጥቂት ሰዎች ይዞ ከመልእክተኞቹ ጋር
ወደ ቂሣርያ ሄደ።
24 በማግስቱም ቂሣርያ ገባ። ቆርኔሌዎ
ስም ዘመዶቹንና ወዳጆቹን ሰብስቦ መምጣ
ታቸውን በጉጉት ይጠባበቅ ነበር። 25 ወደ
ቤት እንደገቡም ቆርኔሌዎስ ወደ ጴጥሮስ
ቀርቦ በጉልበቱ ተንበርክኮ ሰገደለት።
26 ጴጥሮስ ግን፥ «እኔ እንደ አንተው
ፍጡር ነኝ እንጂ፥ የሚሰገድልኝ አይደለ
ሁም» ብሎ ከተንበረከከበት አስነሣው።
27 ከዚያም ጴጥሮስና ቆርኔሌዎስ ተያይ
ዘው እየተጨዋወቱ ሰዎቹ ወደ ተሰበሰቡ
በት ክፍል ገቡ።
28 ወዲያውም ጴጥሮስ እንዲህ አላቸው፥
«አንድ አይሁዳዊ ከአንድ አሕዛብ ቤት
መግባትና መቀላቀል እንደማይፈቀድለት
ታውቃላችሁ። ነገር ግን ማንንም ሰው በን
ቀት እንዳልመለከት እግዚአብሔር በራእይ
ገልጦልኛል። 29 እንግዲህ እግዚአብሔር
ወደዚህ ሲልከኝ፥ምንም ቅር ሳይለኝ ወዲያ
ውኑ ተነሥቼ የመጣሁት ስለዚህ ነው።
እስቲ ለምን እንደፈለጋችሁኝ አሁን ንገ
ሩኝ» አላቸው።
30-31 ቆርኔሌዎስም መልሶ፥ «ከአራት
ቀን በፊት ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት ላይ እጸልይ
ነበር። በጸሎት ላይ እንዳለሁም የሚያንጸባ
ርቅ ልብስ የለበሰ አንድ ሰው መጥቶ በፊቴ
ቆሞ፥ 'ቆርኔሌዎስ ሆይ፥እግዚአብሔር ጸሎ
ትህንና ለችግረኞች የምታደርገውን ቸርነት
ተመልክቶ ደስ ብሎታል። 32 አሁንም ወደ
ኢዮጴ ሰዎች ልከህ በባሕር አጠገብ ከቆዳ
ፋቂው ስምዖን ቤት፥ በእንግድነት ያረፈ
ጴጥሮስ የሚባል ሰው አለና አስጠራው'
አለኝ። 33 እኔም ወዲያውኑ ወደ አንተ
መልእክተኛ ላክሁ። አንተም መልእክቱ
እንደ ደረሰህ ወዲያውኑ መምጣትህ በእው
ነቱ ደስ የሚያሰኝ ነው። እንግዲህ ለእኛ
እንድትነግረን እግዚአብሔር ያዘዘህን ሁሉ፥
ለመስማት ተዘጋጅተናልና ንገረን» አለው።
34 ጴጥሮስም የሚከተለውን ቃል ተና
ገረ። «እግዚአብሔር ሰውን ከሰው እንደማ
ያበላልጥና እንደማያዳላ፥አሁን ገና ተረድቼ
አለሁ። 35 እርሱን የሚፈራና እውነትን
የሚከተል ከሆነ፥የማንኛውም ነገድ አባል፥
የየትኛውም አገር ሰው፥ በእግዚአብሔር
ዘንድ የተወደደና ተቀባይነት ያለው መሆኑ
ንም ለመገንዘብ ችያለሁ። 36-37 እግዚአብ
ሔር የሰላምን የምሥራች ቃል ለእሥራኤል
ሕዝብ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እንደ
ላከ ሳትሰሙ እንዳልቀራችሁ እርግጠኛ
ነኝ። ይህ ኢየሱስ ክርስቶስም የፍጥረት
ሁሉ ጌታ ነው። ዮሐንስ በገሊላ ማጥመቅና
ማስተማር ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ፥ በይ
ሁዳ ምድር የሆነውን ሁሉ ታውቃላችሁ።
38 እንደዚሁም፥ እግዚአብሔር የናዝሬቱን
ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ የቀባውና ኃይልም

የሰጠው መሆኑ ከእናንተ የተሰወረ አይደ
ለም። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበር፥
አጋንንት የያዛቸውን እየፈወሰ፥ በደረሰበት
ሁሉ መልካም ሥራ እየሠራ ይዘዋወር
ነበር።
39 «ኢየሱስ በመላዋ እሥራኤልና በኢየ
ሩሳሌም ከተማ ላደረጋቸው ነገሮች ሁሉ
እኛ ሐዋርያት የዓይን ምስክሮች ነን።
40-41 እርሱንም በመስቀል ላይ ሰቅለው ገደ
ሉት። እግዚአብሔርም በሦስተኛው ቀን
ከሞት አስነሣው። ክርስቶስም ከሞት ከተ
ነሣ በኋላ፥ እግዚአብሔር አስቀድሞ ምስክ
ሮቹ እንድንሆን ለመረጠን ለእኛ ብቻ ታየ።
በእነዚህም ለእኛ በታየባቸው ቀናት ከእ
ርሱ ጋር አብረን በልተን፥ አብረን ጠጥተ
ናል። 42 ከዚያም እከሌ ከእከሌ ብለን ሳን
ለይ ለሁሉም ቃሉን እንድናስተምር፥ በሕያ
ዋንና በሙታን ላይ የሚፈርደው እርሱ
መሆኑንም እንድንመሰክር ልኮናል።
43 በስሙ የሚያምኑ ሁሉ የኃጢአትን ይቅ
ርታ እንደሚያገኙ፥ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ
ነቢያት ሁሉ አስቀድመው ተናግረዋል።»
44 ጴጥሮስ ይህንን ሲናገር ሳለ፥ ንግግሩን
ይሰሙ በነበሩት ላይ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ
ወረደባቸው። 45 ከጴጥሮስ ጋር አብረው
የመጡት አይሁድ ክርስቲያኖች፥ አሕዛብ
እንኳ በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞሉ ሲያዩ
ተገረሙ። 46-47 እነዚያ አይሁድ ያልነበሩ
አሕዛብ ሰዎች፥ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበላ
ቸው የሚያጠራጥር ነገር አልነበረም። ምክ
ንያቱም በአዲስ ቋንቋ ሲናገሩና እግዚአብ
ሔርን ሲያመሰግኑ ይሰሙአቸው ነበርና።
ጴጥሮስም፥ «እነዚህ ሰዎች እንደ እኛ
መንፈስ ቅዱስን ስለተቀበሉ በውኃ እንዳይ
ጠመቁ የሚከለክላቸው ምን ነገር አለ?»
ሲል አብረውት የመጡትን ደቀመዛሙርት
ጠየቀ። 48 ከዚያም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም
እንዲጠመቁ ነገራቸው። ከዚህም በኋላ
ጥቂት ቀናት አብሮአቸው እንዲሰነብት
ጴጥሮስን ለመኑት።

## ምዕራፍ 11

1 ሐዋርያትና በይሁዳ ምድር የሚኖሩ
ደቀመዛሙርት፥ አሕዛብ ደግሞ የእግዚአብ
ሔርን ቃል መቀበላቸውን ሰሙ። 2 ስለዚህ
ጴጥሮስ ወደ ኢየሩሳሌም በመጣ ጊዜ ከአይ
ሁድ ሃይማኖት ወደ ክርስትና እምነት የተ
መለሱ ወገኖች፥ 3 «ሥርዓት አፍርሰህ ካል
ተገረዙት ከአሕዛብ ቤት ገብተሃል፤ አብረሃ
ቸውም በልተሃል» ብለው ነቀፉት።
4 ጴጥሮስ ግን የሆነውን ነገር ሁሉ
አንድ በአንድ እንዲህ ሲል አስረዳቸው።
5 «አንድ ቀን በኢዮጴ ከተማ ሳለሁ፥ በምጸ
ልይበት ሰዓት በራእይ አንድ ትልቅ የተወ
ጠረ ሸራ በአራት ማዕዘን ተይዞ ከሰማይ እኔ
ወደ ነበርኩበት ሥፍራ ሲወርድ አየሁ።
6 በሸራው ላይ ልዩ ልዩ አራት እግር ያላ
ቸው እንስሳት፥ ወፎችና በደረታቸው የሚ
ሳቡ ፍጥረቶች ነበሩበት። 7 ቀጥሎም፥ 'ጴጥ
ሮስ! ተነሣና አርደህ ብላ' የሚል ድምፅ
ሰማሁ።
8 «እኔም፥ 'ጌታ ሆይ፥ እነዚህ ነገሮች
እንዳይበሉ የተከለከሉ ስለሆኑ፥ እስካሁን
በልቼ አላውቅምና አሁንም አልበላም'
አልኩ።
9 «እንደገናም 'እግዚአብሔር ንጹሕ
ያደረገውን አንተ 'ርኩስ ነው' ብለህ አትከ
ራከር' የሚል ድምፅ ከሰማይ ሰማሁ።
10 «ይህን ነገር ሦስት ጊዜ ደጋግሞ
ከሆነ በኋላ፥ የተወጠረው ሸራ ተመልሶ ወደ
ሰማይ ሲወሰድ አየሁ። 11-12 ወዲያውም
ከቂሣርያ ተልከው የመጡ ሦስት ሰዎች እኔ
ወዳለሁበት ቤት ደረሱ። መንፈስ ቅዱስም፥
ሳላመነታ አብሬአቸው እንድሄድ አዘዘኝ።
እዚህ አሁን አብረውኝ ካሉት ስድስት ወን
ድሞችም ጋር ሆነን ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት
ሄድን። እዚያም እንደ ደረስን፥ 13 ቆርኔሌ
ዎስ በራእይ መልአክ እንዳየና መልአኩም፥
'ወደ ኢዮጴ መልእክተኞች ልከህ ስምዖን
ጴጥሮስ የተባለውን ሰው አስጠራ። 14 እር
ሱም አንተና ቤተሰብህ የምትድኑበትን
መንገድ ይነግርሃል' እንዳለው ገለጸልን።
15 «እኔም እዚያ ደርሼ ማስተማር ስጀ
ምር፥ መንፈስ ቅዱስ መጀመሪያ በእኛ ላይ
እንደወረደ በእነርሱም ላይ ወረደ። 16 በዚህ
ጊዜ፥ 'ዮሐንስ በውኃ አጠመቀ፤ እናንተ ግን
በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ' ሲል ጌታ
የተናገረው ቃል ትዝ አለኝ። 17 እኛ በጌታ
በኢየሱስ ክርስቶስ ባመንን ጊዜ የተሰጠንን
የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እግዚአብሔር ለእነ
ርሱም እንደ ሰጣቸው በተረዳሁ ጊዜ፥ ለእግ
ዚአብሔር ሥራ እንቅፋት መሆን አልፈለግ
ሁም።»
18 ጴጥሮስን ይከራከሩት የነበሩትም
ሰዎች ይህንን ከሰሙ በኋላ፥ «ነገሩ እንዲህ
ከሆነማ፥ እግዚአብሔር አሕዛብ ንስሐ እንዲ
ገቡና የዘላለም ሕይወት እንዲያገኙ ጠርቷ
ቸዋል ማለት ነው» በማለት ተቃውሞአቸ
ውን ትተው እግዚአብሔርን አመሰገኑ።
19 ከእስጢፋኖስ ሞት በኋላ በተነሣው

ስደት ምክንያት በየቦታው የተበተኑት ደቀ
መዛሙርት እስከ ፊንቄ፥ቆጵሮስና አንጾኪያ
ድረስ ሄደው የእግዚአብሔርን ቃል ለአይ
ሁድ ብቻ አስተማሩ። 20 ከቆጵሮስና ከቀ
ሬና ወደ አንጾኪያ የመጡ አንዳንድ ክርስ
ቲያኖች ግን፥ በዚያ ለሚኖሩ ግሪኮችም
ጭምር የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ወን
ጌል አስተማሩ። 21 ጌታም ከእነርሱ ጋር
ስለነበረና ይህን አገልግሎታቸውንም ስለባረ
ከው፥ ብዙ አሕዛብ በጌታ በኢየሱስ ክርስ
ቶስ ለማመን በቁ።

22 በኢየሩሳሌም የሚገኙ ክርስቲያኖችም
ይህን ሲሰሙ፥ በርናባስን ወደ አንጾኪያ
ላኩት። 23 በርናባስም አንጾኪያ እንደ
ደረሰ፥ እግዚአብሔር ለምዕመናን አትረፍ
ርፎ የሰጠውን ጸጋ ለማየት በመብቃቱ
እጅግ ደስ አለው። በሙሉ ልብ ጸንተውና
እስከ ወዲያኛው ለጌታ ታማኞች ሆነው
እንዲኖሩም መከራቸው። 24 በርናባስ መን
ፈስ ቅዱስ ያደረበትና በእምነቱ የጸና ደግ
ሰው ነበር። በርሱም ምክንያት ብዙ ሰዎች
በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ።

25 በዚያን ጊዜ በርናባስ ሳውልን ለመፈ
ለግ ወደ ጠርሴስ ሄደ። 26 ባገኘውም ጊዜ
ወደ አንጾኪያ አመጣው። ሁለቱም ቁጥራ
ቸው እየጨመረ የሚሄደውን ምዕመናን በአ
ንጾኪያ ቤተክርስቲያን በየዕለቱ እያስተማሩ
አንድ ዓመት ሙሉ ቆዩ። ደቀመዛሙርት
በመጀመሪያ ‘ክርስቲያን’ ተብለው የተጠሩ
ትም በአንጾኪያ ነበር።

27 በዚያን ጊዜ ትንቢት የመናገር ስጦታ
የተሰጣቸው ጥቂት ሰዎች ከኢየሩሳሌም
ወደ አንጾኪያ ሄዱ። 28 ከእነርሱም አንዱ
አጋቦስ ይባላል። ይህ ሰው በዓለም ላይ
ታላቅ ረሃብ እንደሚደርስ በመንፈስ ቅዱስ
ተገልጾለት፥ ምዕመናን በተሰበሰቡበት ትን
ቢት ተናገረ። በትንቢቱ መሠረትም ረሃቡ
ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠበት ዘመን ሆነ።
29 ስለዚህም በአንጾኪያ የሚኖሩ ክርስቲያ
ኖች፥የእርዳታ ገንዘብ አዋጥተው በይሁዳ
ለሚኖሩ ምዕመናን ለመላክ ወሰኑ። 30 የተ
ዋጣውንም ገንዘብ በበርናባስና በሳውል
እጅ፥ኢየሩሳሌም ለሚገኙ የቤተ ክርስቲያን
መሪዎች ላኩ።

## ምዕራፍ 12

1 በዚያን ዘመን ንጉሥ ሄሮድስ ምዕመ
ናን ያሳድድ ነበር። አንዳንዶችንም እየለየ
ያሳሥር ጀመር። 2 ከዚህም የተነሣ የዮሐን
ስን ወንድም ያዕቆብን በሰይፍ አስገደለው።
3 ይህም አድራጎቱ አይሁድን ደስ እንዳሰኛ
ቸው ሲረዳ፥ጴጥሮስን አስይዞ አሳሠረው።
ያሳሠረውም እርሾ ያልገባበት ቂጣ በሚበላ
በት በፋሲካ በዓል ሰሞን ነበር። 4 ሄሮድ
ስም ከበዓሉ ውጭ ጴጥሮስን ለአይሁድ አሳ
ልፎ ሊሰጠው ስላሰበ፥እስከዚያው ድረስ ን
በአሥራ ስድስት ወታደሮች በጥብቅ እንዲ
ጠበቅ አደረገ። 5 ይሁን እንጂ ጴጥሮስ ከታ
ሠረበት ቀን ጀምሮ፥ክርስቲያኖች በአንድ
ነት ሆነው ሌትም ቀንም ክፉ ነገር እንዳይ
ደርስበት፥አጥብቀው ይጸልዩለት ነበር።

6 ጴጥሮስም እንደ ነገ ፍርድ ፊት
ሊቆም፥ሌሊቱን በሁለት ሰንሰለት ታሥሮ፥
በሁለት ወታደሮች መካከል ተኝቶ ይጠበቅ
ነበር። ሌሎች ወታደሮች ደግሞ በእሥር
ቤቱ መግቢያ በር ላይ ዘብ ቆመው ነበር።
7 የጌታ መልአክ ድንገት በእሥር ቤቱ
ውስጥ እንደ ቆመ፥እሥር ቤቱን ብርሃን
አጥለቀለቀው። መልአኩም ጴጥሮስን ጎኑን፥
ነካ ነካ አድርጎ ቀሰቀሰውና፥ «ቶሎ ብለህ
ተነሣ!» አለው። ወዲያው እንደተነሣም፥
ታሥሮ የነበረባቸው ሰንሰለቶች ከእጁ
ውልቅ ውልቅ ብለው ወደቁ። 8 ቀጥሎም
መልአኩ ጴጥሮስን፥ «ልብስህን ልበስ፤ቀበቶ
ህን ታጠቅ፤ጫማህንም አድርግ» አለው።
ጴጥሮስም መልአኩ እንዳለው አደረገ። ከዚ
ያም፥ «መደረቢያህን ከላይ ጣል አድርግና
ተከተለኝ» አለው።

9 ጴጥሮስም ከታሠረበት ክፍል መልአ
ኩን ተከትሎ ወጣ። ይህ ሁሉ ሲሆን፥ጴጥ
ሮስ ሕልም የሚያይ እንጂ በውኑ አልመሰለ
ውም ነበር። 10 አንደኛውንና ሁለተኛውን
የዘብ መቆሚያ በር አልፈው፥ከእሥር ቤቱ
ከሚያስወጣው ዋና የብረት መዝጊያ ሲደ
ርሱ፥ መዝጊያው ማንም ሳይከፍተው በገዛ
ራሱ ወለል ብሎ ተከፈተላቸው። ወጥተ
ውም አብረው ጥቂት እንደ ሄዱ፥መልአኩ
ከጴጥሮስ ተለየ።

11 ነገሩ ካለፈ በኋላ ጴጥሮስ የሆነውን
ሁሉ መለስ ብሎ ሲያስተውለው፥ «ከሄሮ
ድስ እጅና አይሁዶችም ሊያደርሱብኝ ካሰ
ቡት ክፉ ነገር፥እግዚአብሔር መልአኩን
ልኮ እንዳዳነኝ አሁን ገና ገባኝ» አለ።
12 ከዚያም የሆነውን በአሳቡ ካወጣ ካወረደ
በኋላ፥ብዙ ክርስቲያኖች ተሰብስበው ወደ
ሚጸልዩበት ወደ ማርያም ቤት ሄደ። ይህ
ችም ማርያም፥ማርቆስ የተባለው የዮሐንስ
እናት ናት።

13 ጴጥሮስ ከማርያም ቤት እንደ ደረሰ
የአጥሩን በር አንኳኳ። ሮዴ የተባለች

የቤት ሠራተኛም በር መንኳኳቱን ስለሰ
ማች ወደበሩ ተጠግታ ፣ «ማን ልበል?»
አለች። 14 በውጭ ሆኖ በር የሚያንኳኳው
ጴጥሮስ መሆኑን በድምፁ እንዳወቀች፣ከደ
ስታዋ ብዛት የተነሣ በሩን ሳትከፍትለት
ጥላው ሮጣ ተመለሰችና፣ «ጴጥሮስ መጥቶ
ደጅ ቆሞላችኋል!» ብላ ቤት ውስጥ ለተሰ
በሰቡት ተናገረች። 15 እነርሱም የተናገረች
ውን ለማመን ስላልቻሉ ፣ «አብደሻል
እንዴ! አሁን ጴጥሮስ ከየት መጣ ልትዪ
ነው!» አሏት። እርሷ ግን ፣ «እውነቴን
ነው፤ጴጥሮስ በእርግጥ እበር ላይ ቆሞአል»
ብላ አረጋገጠችላቸው። እነርሱም፣ «እንግ
ዲያውስ የእርሱ መልአክ ይሆናል» አሏት።

16 ጴጥሮስም መላልሶ በሩን አንኳኳ።
ተሯሩጠው በሩን ሲከፍቱ እርሱ ራሱ ሆኖ
ስላገኙት በጣም ገረማቸው። 17 ጴጥሮስም
ዝም እንዲሉ በእጁ ምልክት ካሳያቸው
በኋላ፣ወደ ቤት ገብቶ ጌታ ከእሥር ቤት
እንዴት አድርጎ እንዳወጣው አጫወታ
ቸው። ከዚያም፣ «ይህንን ነገር ለያዕቆብና
ለቀሩት ወንድሞች ሁሉ ንገሩአቸው» ብሎ
ወጥቶ ወደ ሌላ ሰዋራ ቦታ ሄደ።

18 ሲነጋም፣ «ጴጥሮስ የት ጠፋ?» በማ
ለት ወታደሮቹ እንዴ ወደ ላይ፣እንዴ ወደ
ታች ይሯሯጡ ጀመር። 19 ሄሮድስም ጴጥሮ
ስን በጥብቅ አስፈልጎ ካጣው በኋላ፣እንዲጠ
ብቁት ታዝዘው የነበሩትን ወታደሮች መር
ምሮ በሞት እንዲቀጡ አደረገ። ብዙም ሳይ
ቆይ ሄሮድስ የይሁዳን ምድር ለቆ በቂሣርያ
መኖር ጀመረ።

20 በዚያን ጊዜ ሄሮድስ፣የጢሮስንና የሲ
ዶናን አገር ሰዎች ተጣልቶአቸው ነበር።
እነዚህ ሰዎች እህል የሚያስመጡት ሄሮ
ድስ ከሚገዛው አገር ስለነበር ፣ በመጣላታ
ቸው ምክንያት የሚያስመጡትን እህል እን
ዳያግድባቸው ፈሩ። ስለዚህም ተሰብስበው
ወደ ቂሣርያ መጥተው የንጉሡን ባለሟል
ብላስጦስን ፣ ከንጉሡ ጋር እንዲያስታርቃ
ቸው ተማጸኑት። 21 ከንጉሡ ፊት ቀርበው
ይቅርታ እንዲጠይቁ ተፈቀደላቸውና ቀጠሮ
ተያዘላቸው። በቀጠሮውም ዕለት ሕዝቡ
ሁሉ ተሰብስበው ሳሉ፣ሄሮድስ የክብር ልብ
ሱን ለብሶ በዙፋኑ ላይ እንደ ተቀመጠ ንግ
ግር አደረገ። 22 ንግግሩን ሲጨርስም በዚያ
ተሰብስበው የነበሩት ሰዎች ሁሉ፣ «ይህስ
'የአምላክ' ድምፅ ነው እንጂ የሰው ድምፅ
አይደለም» እያሉ በጩኸት ድምፅ አስተ
ጋቡ።

23 ሄሮድስም ለእግዚአብሔር የሚገባ
ውን ክብር ለራሱ ስላደረገ፣የእግዚአብሔር
መልአክ ቀሰፈው። ወዲያውም ትል በሰው
ነቱ ላይ ፈልቶበት ሞተ።

24 የእግዚአብሔር ቃል ግን በየሥፍራው
ሁሉ እየተሠራጨና እየተስፋፋ በመሄዱ
ብዙ ሰዎች በጌታ አመኑ።

25 በርናባስና ሳውልም፣ወደ ኢየሩሳሌም
የተላኩበትን መልእክት ከደረሱ በኋላ፣ማር
ቆስ የተባለውን ዮሐንስን ይዘው ወደ አንጾ
ኪያ ተመለሱ።

## ምዕራፍ 13

1 በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ነቢያትና
መምህራን ነበሩ። እነዚህም በርናባስ ፣
'ጥቁር' የሚባለው ስምዖን፣የቀሬናው ሉክ
ዮስ ፣ የሄሮድስ አብሮ አደግ ጓደኛ ምና
ሔና ፣ ሳውል ነበሩ። 2 አንድ ቀን በጾምና
በጸሎት ተጠምደው ሳሉ መንፈስ ቅዱስ፣
«በርናባስንና ሳውልን ለመረጥኳቸው ሐዋር
ያዊ ሥራ ለዩልኝ» አላቸው። 3 እነርሱም
ከጾሙና ከጸለዩ በኋላ፣በበርናባስና በሳውል
ላይ እጃቸውን ጭነው ፣ ወደ ተጠሩበት
ሥራ እንዲሄዱ አሰናበቷቸው።

4 በርናባስና ሳውልም በመንፈስ ቅዱስ
ተመርተው ወደ ሴሌውቅያ ሄዱ። ከዚያም
በመርከብ ሆነው ወደ ቆጵሮስ አመሩ።
5 ስልማና ከተባለው ቦታም ሲደርሱ ፣ ወደ
አይሁድ ምኲራብ ገብተው ማስተማር
ጀመሩ። ማርቆስ የተባለው ዮሐንስም ይረዳ
ቸው ነበር።

6-7 የቆጵሮስን ደሴት መንደሮች በሙሉ
ዞረው ጳፉ ከተባለው ቦታ ሲደርሱ ፣ በርያ
ሱስ የተባለ አንድ አስማተኛ አይሁዳዊ
አገኙ። በርያሱስ፣ 'ነቢይ ነኝ' እያለ በአካባ
ቢው የሐሰት ወሬ ያስወራ ነበር። በርያ
ሱስ፣ሰርግዮስ ጳውሎስ ለተባለው የደሴቲቱ
አስተዳዳሪ የቅርብ ወዳጅ ነበር። ሰርግዮስ
አስተዋይና ቅን ሰው ነበር። አንድ ቀን ሰር
ግዮስ ጳውሎስ፣የእግዚአብሔርን ቃል ለመ
ስማት ፈልጎ በርናባስንና ሳውልን አስጠራ
ቸው። 8 ነገር ግን በግሪክ ቋንቋ «ኤልማስ»
ተብሎ የሚጠራው ይህ አስማተኛ፣ሰርግዮስ
ጳውሎስ በጌታ እንዲያምን ስላልፈለገ፣የበር
ናባስንና የሳውልን ትምህርት እንዳይቀበል
ለማድረግ ይጥር ነበር።

9 በዚህም ጊዜ ጳውሎስ የተባለው
ሳውል ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልቶ
ይህን አስማተኛ ሰው ትክ ብሎ ተመለከተ
ውና፣ 10 «አንተ ክፉ ተንኰለኛ የሰይጣን
ልጅ! አንተ የጽድቅ ጠላት! ቀጥተኛውን

የእግዚአብሔርን መንገድ ለምን ታጣምማ
ለህ? ይህን አድራጎትህንስ ለምን አትተ
ውም? 11 አሁንም የእግዚአብሔር እጅ አር
ፎብሃል ፤ ዕውር ትሆናለህ ፤ ለጥቂት ጊዜም
የፀሐይን ብርሃን አታይም!» አለው።
ይህን እንዳለውም የኤልማስ ዓይኖች
ታወሩ። ከዚያም በዳበሳ ፣ የሚመራው ሰው
ይፈልግ ጀመር። 12 የደሴቲቱ አስተዳዳሪም
ይህን ባየ ጊዜ በጌታ አመነ፤በእግዚአብሔር
ቃል ኀይልም ተደነቀ።
13 ከዚህ በኋላ ጳውሎስና ጓደኞቹ ከጳፉ
በመርከብ ተሳፍረው ፣ በጵንፍልያ ወደምትገ
ኘው ወደ ጴርጌን ሄዱ። ጴርጌን ሲደርሱም
ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ ፣ ሳያሰናብቱት
ከእነርሱ ተለይቶ ወደ ኢየሩሳሌም ተመ
ለሰ። 14 በርናባስና ጳውሎስ ግን በጲስድያ
ወደምትገኘው ወደ አንጾኪያ ሄዱ። በሰንበ
ትም ቀን ወደ ምኵራብ ገብተው ተቀ
መጡ። 15 የሙሴና የነቢያት መጻሕፍት
እንደተለመደው ከተነበቡ በኋላ፣የምኵራቡ
ኃላፊዎች ጳውሎስና በርናባስን፣ «ለሕዝቡ
መናገር የምትፈልጉት ምክር ካለ ልታሰሙ
ትችላላችሁ» አሏቸው።
16 በዚህ ጊዜ ጳውሎስ ከተቀመጠበት
ተነሥቶ እንዲህ ሲል ተናገረ። «እናንተ የእ
ሥራኤል ሰዎች ፣ እንዲሁም እዚህ ያላችሁ
እግዚአብሔርን የምታመልኩ አሕዛብ
ሁሉ። አትሰልቹኝና በመጀመሪያ ለንግግሬ
መነሻ ይሆን ዘንድ ፣ ወደ ኋላ ተመልሼ የታ
ሪክ ማስረጃ እንዳቀርብ ፍቀዱልኝ።
17 «የእሥራኤል አምላክ የሆነው እግዚ
አብሔር፣አባቶቻችንን መረጣቸው። ገና በግ
ብፅ አገር እያሉ ከፍ ከፍ አደረጋቸው።
በታላቅ ኃይሉም ከባርነት አገዛዝ ነፃ አው
ጥቶ፣ 18 ለአርባ ዓመታት በበረሃ መራቸው።
19-20 ከዚያም በከነዓን የነበሩትን ሰባት መን
ግሥታት አጥፍቶ ምድራቸውን ርስት አድ
ርጎ ሰጣቸው። ለአራት መቶ ሃምሳ ዓመ
ትም በዚህ በተሰጣቸው ርስት ተቀመጡ።
እስከ ነቢዩ ሳሙኤልም ድረስ በመሳፍንት
ሲገዙ ኖሩ።
21 «በኋላ ግን ፣ በንጉሥ መገዛትን ስለ
ፈለጉ እግዚአብሔር ከብንያም ወገን የቂስን
ልጅ ሳኦልን አስነሥቶ፣ለአርባ ዓመታት በላ
ያቸው ላይ አነገሠው። 22 ከሳኦልም ቀጥሎ
ዳዊትን አነገሠላቸው። እግዚአብሔር ስለ
ዳዊት፣ 'እንደ ልቤ የሆነና ትእዛዜን የሚፈ
ጽም የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ' ሲል
መስክሮለታል። 23 እግዚአብሔር በገባው
የተስፋ ቃል መሠረትም፣ከዳዊት ዘር የእሥ
ራኤል አዳኝ የሆነው ኢየሱስ ተወለደ።
24 «ኢየሱስ አገልግሎቱን በይፋ ጀምሮ
ለሰዎች ከመታየቱ በፊት፣መጥምቁ ዮሐንስ
የእሥራኤል ሕዝብ ሁሉ ከኃጢአታቸው
ተመልሰው ንስሐ እንዲገቡና እንዲጠመቁ
አስተማረ። 25 ዮሐንስ እንዲያከናውን የተመ
ደበለትን ተግባር እንደጨረሰም ፣ 'ነቢያት
ይመጣል' ብለው 'ትንቢት የተናገሩለት
መሲሕ እኔ እንዳልመስላችሁ ፤ እኔ ጎንበስ
ብዬ የጫማውን ማሠሪያ መፍታት እንኳን
የማይገባኝ፣እርሱ መሲሑ ከእኔ በኋላ ይመ
ጣል' አላቸው።
26 «እናንተ ወንድሞቼ የአብርሃም
ልጆች ፣ እንዲሁም እናንተ እግዚአብሔርን
የምትፈሩ አሕዛብ። ይህ ደኅንነት የመጣው
ለእከሌ ፣ ለእከሌ ሳይባል ለእኛ ለሁላችንም
ነው። 27 በኢየሩሳሌም የሚኖሩ አይሁድና
መሪዎቻቸው ኢየሱስን በመግደላቸው ፣
ከብዙ ዘመን በፊት ነቢያት ስለ እርሱ አሟ
ሚት አስቀድመው የተናገሩት ቃል ሳያው
ቁት እንዲፈጸም አድርገዋል። እርግጥ
ነው ፣ ነቢያት አስቀድመው የተናገሩትን
ቃል በየሳምንቱ በሰንበት ዕለት ፣ በየምኵ
ራቡ ሲነበብ ይሰሙታል። ግን የሰሙት
ቃል ስለ ኢየሱስ የተነገረ መሆኑን አላስተ
ዋሉም። ባለማስተዋላቸውም ይኸው ሰቀ
ሉት። 28 ለሞት የሚያደርሰው ምንም
ጥፋት ፣ ምንም በደል ሳይኖርበትም ፣ ኢየሱ
ስን ይገድለው ዘንድ ፣ ጲላጦስን አስቸገሩት።
29 ስለ እርሱ ነቢያት አስቀድመው እንደተ
ናገሩት ሁሉ ነገር ከተፈጸመ በኋላ ከመስ
ቀል አውርደው ቀበሩት።
30 «ነገር ግን እግዚአብሔር ኢየሱስን
ከሞት አስነሣው። 31 ከሞት ከተነሣም
በኋላ ከገሊላ ጀምሮ እስከ ኢየሩሳሌም ላል
ተለዩት ተከታዮቹ ብዙ ቀን ተገለጠላ
ቸው። እነዚህም ሰዎች ክርስቶስ ከሞት
መነሣቱን በሕዝብ ፊት በይፋ ከመመስከር
ወደ ኋላ አላሉም።
32-33 «ዛሬ እዚህ በመካከላችሁ የተገኘ
ነው እኔና በርናባስ፣እግዚአብሔር ለአባቶቻ
ችን የሰጠውን የተስፋ ቃል ፣ ክርስቶስን
ከሙታን በማስነሣት በእኛ በልጆቻቸው
ዘመን ስለፈጸመው 'የምሥራች ደስ ይበላ
ችሁ ፤ ደስ ብሎናል' እንላችኋለን። በዚህም
በዳዊት መዝሙር ውስጥ፣ 'አንተ ልጄ ነህ፤
እኔ ዛሬ ወለድኩህ' ተብሎ የተነገረለት ትን
ቢት ተፈጽሟል።
34 «እግዚአብሔር ከሞት እንደሚያስነ
ሣው አካሉም በመቃብር ፈርሶና በስብሶ

እንደማይቀር አስቀድሞ ተነግሮለታል።
'የተቀደሰውንና የታመነውን ለዳዊት ቃል
የገባሁለትን በረከት እሰጣችኋለሁ' ተብ
ሏል። 35 እንደዚሁም በሌላ ቦታ፥ 'ቅዱስ
ልጅህን በመቃብር ውስጥ ፈርሶና በስብሶ
እንዲቀር አታደርገውም' ተብሎለታል።
36 ይህ ቃል የተነገረው ስለ ዳዊት አልነበ
ረም። ለዳዊት የተነገረ አለመሆኑም የሚታ
ወቀው፥ ዳዊት በፊንታው የተመደበለትን
የእግዚአብሔርን ሥራ አከናውኖ ዘመኑን
ከፈጸመ በኋላ ስለሞተ ነው። ከአባቶቹም
ጋር ተቀብሮ አካሉ እንደ ማንኛውም ሰው
ፈርሷል፤ በስብሷልም። 37 እግዚአብሔር
ከሞት ያስነሣው ይህ ኢየሱስ ግን፥በመቃ
ብር ውስጥ በስብሶ አልቀረም።

38 «ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ፥አድምጡ!
በኢየሱስ አማካይነት ለኃጢአታችሁ ይቅ
ርታ ማግኘት እንድትችሉ፥ይኸው በሩ ተከ
ፍቶላችኋል። 39 በእርሱ የሚያምን፥የሙሴ
ሕግ ሊያስገኘው የማይችለውን ከኃጢአት
ባርነት ነፃ መውጣትን ያገኛል። 40 ስለዚህ
በነቢያት፥ 41 'እናንተ በእውነት ላይ የምታ
ፌዙ፥ እዩ፥ ተደነቁ፥ ጥፉም፤ ምክንያቱም
ማንም እንኳ ቢነግራችሁ የማታምኑትን
ሥራ በዘመናችሁ አደርጋለሁ' ተብሎ የተነ
ገረው ቃል በእናንተ እንዳይደርስ ተጠን
ቀቁ።»

42 ጳውሎስና በርናባስም ይህን ብለው
ከምኵራብ ሲወጡ፥በሚቀጥለውም ሳምንት
ተመልሰው መጥተው ስለዚሁ ነገር በበለጠ
እንዲያስተምሯቸው በሕዝቡ ተጠየቁ።
43 ስብሰባው ከተበተነ በኋላም፥ብዙ አይሁ
ድና ወደ አይሁድ ሃይማኖት የገቡ አሕዛብ
ተከተሉአቸው። ጳውሎስና በርናባስም የተ
ከተሏቸውን ሰዎች፥በእግዚአብሔር ጸጋ ጸን
ተው እንዲኖሩ አበረታቷቸው። 44 በሳምን
ቱም የከተማው ሕዝብ ተገልብጦ በመው
ጣት፥ጳውሎስና በርናባስ የሚያስተምሩትን
ለመስማት በምኵራቡ ውስጥ ተሰበሰበ።

45 አይሁድ ግን የሕዝቡን ብዛት ሲያዩ
ቅንዓት አደሮባቸው፥ ይሳደቡና ጳውሎስ
የሚያስተምረውንም ትምህርት ይቃወሙ
ጀመር።

46 ጳውሎስና በርናባስ ግን እንዲህ ሲሉ
ያለ ፍርሃት መለሱላቸው። «የምሥራቹ
ቃል አስቀድሞ ለእናንተ መነገር ስላለበት
ነግረናችኋል። እናንተ ግን አንሰማም፤አንቀ
በልም ብላችሁ ከዘላለም ሕይወት መንገድ
ወደ ጥፋት ጐዳና የምትሄዱ ከሆነ፥ከእንግ
ዲህ ወዲህ እኛ ወደ አሕዛብ ሄደን እናስተ
ምራለን። 47 ምክንያቱም ጌታ፥ 'ለዓለም
ሕዝብ ሁሉ መዳንን ታበሥር ዘንድ ለአሕ
ዛብ ብርሃን አድርጌሃለሁ' ብሎ አዞናልና
ነው።»

48 አሕዛብም ይህን ሲሰሙ፥ «ለካ ለእ
ኛም ትንቢት ተነግሮልናል!» ብለው ደስ
አላቸው። ስለ ሰሙትም የጌታ ቃል ልባዊ
ምስጋናቸውን አቀረቡ። ለዘላለም ሕይወት
የተዘጋጁትም ሁሉ አመኑ። 49 የእግዚአብ
ሔርም ቃል በዚያ አገር እየተስፋፋ ሄደ።

50 አይሁድ ግን፥ወደ አይሁድ ሃይማኖት
የገቡትን ሀብታም ሴቶችና የከተማውን ታላ
ላቅ ሰዎች በማስተባበር፥በጳውሎስና በበርና
ባስ ላይ ስደት አስነሥተው ከከተማ አስወ
ጧቸው። 51 ሐዋርያቱም ባሳደዷቸው
ሰዎች ላይ ምስክር እንዲሆን፥የእግራቸውን
አቧራ አራግፈው ወደ ኢቆንዮን ሄዱ።
52 ደቀመዛሙርቱም፥ በደስታና በመንፈስ
ቅዱስ ተሞሉ።

## ምዕራፍ 14

1 በኢቆንዮንም ጳውሎስና በርናባስ እንደ
ልማዳቸው ወደ ምኵራብ ገብተው፥ኃይል
የተሞላበት ስብከት ሰበኩ። ከዚህም የተነሣ
ከአይሁድና ከአሕዛብ ወገን ብዙ ሰዎች
በጌታ አመኑ።

2 በጌታ ማመን ያልፈለጉት አይሁዶች
ግን፥ በጳውሎስና በበርናባስ ላይ የማይገባ
መጥፎ ነገር እያስወሩ፥በአሕዛብ ዘንድ እን
ዲጠሉ የተቻላቸውን ሁሉ አደረጉ። 3 ጳው
ሎስና በርናባስ ግን የጌታን ቃል ያለ ፍር
ሃት እየሰበኩ፥በኢቆንዮን ብዙ ጊዜ ቆዩ።
ጌታም የጳውሎስና የበርናባስ ትምህርት
በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው፥ተአ
ምራትንና ድንቅ ሥራዎችን ለማድረግ የሚ
ያስችል ኃይል ሰጣቸው። 4 የከተማው
ሕዝብ ግን ከሁለት ተከፍሎ፥ግማሹ ክፍል
አይሁድን ሲደግፍ፥ግማሹ ደግሞ የጌታን
ቃል አምኖ በመቀበል የሐዋርያት ደጋፊ
ሆነ።

5-6 ከዚህ በኋላ አሕዛብና አይሁድ ከመሪ
ዎቻቸው ጋር ሆነው በድንጋይ ሊወግሯ
ቸው መዶለታቸውን ሲሰሙ፥ጳውሎስና በር
ናባስ ከኢቆንዮን ሸሽተው ልስጥራንና ደር
ቤን ወደሚባሉት፥የሊቃኦንያ ከተማዎችና
ወደ አካባቢው ሄዱ። 7 እዚያም የምሥራ
ቹን ቃል አስተማሩ።

8 በልስጥራንም እግሩ ሽባ የሆነ አንድ
ሰው ነበረ። ይህም ሰው ከተወለደ ጀምሮ
በእግሩ ቆሞ ሄዶ አያውቅም ነበር።

9-10 ጳውሎስ በሚያስተምርበት ጊዜ ጸጥ
ብሎ ያዳምጥ ነበር። ጳውሎስም ሽባውን
ሲመለከተው፥ ለመፈወስ የሚያበቃ እምነት
እንዳለው ስለተረዳ፥ «አንተ ሰው ተነሥና
በእግርህ ቁም» አለው። ሽባውም ወዲያ
ውኑ ተነሥቶ ቀጥ ብሎ በእግሩ ቆመ።
ወዲያውም እንደ ልቡም መራመድ ቻለ።
11 በዚያ የነበሩ ሰዎችም ጳውሎስ ያደረ
ገውን ተአምር ባዩ ጊዜ፥ ነገሩ ደንቋቸው፥
«ዛሬስ አማልክት በሰው ተመስለው ወደ
እኛ መጡ!» እያሉ በቋንቋቸው ጮኹ።
12 በጣዖቶቻቸውም ስም በርናባስን «ድያ»
አሉት። ዋናው ተናጋሪ ጳውሎስ ስለነበር፥
እርሱን ደግሞ «ሄርሜን» አሉት። 13 ከከተ
ማው ወጣ ብሎ የተሠራው የድያ ቤተ
መቅደስ ካህንም ኮርማዎችና የአበባ ጉን
ጉን አምጥቶ፥ ከተማው በር ላይ በሕዝቡ
ስም ለጳውሎስና ለበርናባስ መሥዋዕት ሊያ
ቀርብላቸው ተዘጋጀ።
14 ጳውሎስና በርናባስ ግን በሁኔታው
በጣም በማዘን፥ ልብሳቸውን ቀደው እየሮጡ
ከሕዝቡ ጋር ተደባለቁ። ቃላቸውንም ከፍ
አድርገው፥ 15 «እናንተ ሰዎች፥ ምነው እን
ዲህ ታደርጋላችሁ! እኛ እኮ እንደ እናን
ተው ሰዎች እንጂ፥ አማልክት አይደለንም።
ወደዚህ የመጣነውም በከንቱ የምታመልኳ
ቸውን እነዚህን ሰው ሰራሽ አማልክት ትታ
ችሁ ሰማይና ምድርን፥ ባሕርንና በውስጣቸ
ውም ያሉትን ፍጥረታት የፈጠረውን
ሕያው አምላክ እግዚአብበሔርን ብቻ፥ እን
ድታመልኩ ልናስተምራችሁ ነው። 16 ባለ
ፉት ዘመናት እግዚአብሔር፥ ሰዎች ሁሉ
ይበጀናል ብለው የመረጡትን መንገድ እን
ዲከተሉ ትቷቸው ነበር። 17 ይህንን ቢያደር
ግም እንኳን፥ አምላክነቱን የሚያስመሰክር
መልካም ሥራ ማድረጉን አላቋረጠም።
ዝናብ ከሰማይ ያዘንብላችኋል፤ እህል የምታ
መርቱበትንና የምትበሉበትን ጊዜ ለይቶ
ሰጥቶአችኋል። በዚህም ሁሉ ነገር ልባችሁ
በደስታ እንዲሞላ አድርጓል።»
18 ጳውሎስና በርናባስም፥ አማልክት አለ
መሆናቸውን አበክረው ቢያስተምሩአቸ
ውም፥ ሰዎቹ መሥዋዕት ሊያቀርቡላቸው
ቆርጠው በመነሣታቸው፥ ይህንን እንዳያደ
ርጉ ያስጣሏቸው ከብዙ ድካምና ትግል
በኋላ ነበር።
19 ከዚህ በኋላ አንዳንድ አይሁድ ከአንጾ
ኪያና ከኢቆንዮን መጥተው፥ የከተማውን
ሕዝብ አነሣስተው ጳውሎስን በድንጋይ አስ
ወገሩት። የሞተ ስለመሰላቸውም መሬት
ለመሬት ጎትተው ከከተማ ውጭ አውጥ
ተው ጣሉት። 20 ደቀመዛሙርቱ ግን ጳው
ሎስን ዙርያ ከበው ትንፋሹን ያዳምጡ
ነበር። ጥቂት እንደ ቆየም ደህና ሆኖ ተነ
ሥቶ ወደ ከተማ ገባ። በማግስቱም ከበርና
ባስ ጋር ወደ ደርቤን ሄዱ። 21 በዚያም አስ
ተምረው ብዙ ሰዎች በጌታ እንዲያምኑ
አደረጉ። ከዚህ በኋላ ወደ ልስጥራን ወደ
ኢቆንዮንና ወደ አንጾኪያ ተመለሱ። 22 በእ
ነዚህም ቦታዎች ሁሉ ክርስቲያኖች በእምነ
ታቸው ጸንተው እንዲኖሩ፥ «ወደ እግዚአ
ብሔር መንግሥት የምንገባው በብዙ
መከራ ከተፈተንን በኋላ ነው» እያሉ ያበረ
ታቷቸው ነበር። 23 በየቤተ ክርስቲያኑም
ሽማግሌዎችን ከሾሙላቸው በኋላ፥ የሚታ
መኑበት ጌታ እንዲጠብቃቸው በጾምና በጸ
ሎት ለእግዚአብሔር አደራ ሰጧቸው።
24 በኋላ በጲስድያ በኩል አድርገው
ወደ ጵንፍልያ መጡ። 25 በጴርጌንም የእግ
ዚአብሔርን ቃል አስተምረው ወደ አጣልያ
አመሩ።
26 በመጨረሻም መነሻቸው ወደነበረ
ችው ወደ አንጾኪያ በመርከብ ተመልሰው
ሄዱ። አንጾኪያ ጳውሎስና በርናባስ ለፈጸ
ሙት ሥራ ሁሉ፥ ለእግዚአብሔር ጸጋ
አደራ የተሰጡባት ሥፍራ ነበረች።
27 ወደ አንጾኪያ እንደ ደረሱ ምዕመና
ንን ሁሉ ሰብስበው፥ እግዚአብሔር በእነርሱ
አማካይነት ያደረገውን ነገር አሕዛብም
በጌታ እንዴት እንዳመኑ፥ ዘርዝረው ነገሩአ
ቸው። 28 በአንጾኪያም ከምዕመናን ጋር
ብዙ ጊዜ ቆዩ።

## ምዕራፍ 15

1 ጥቂት ሰዎች ከይሁዳ ወደ አንጾኪያ
መጥተው፥ «በሙሴ ሕግ መሠረት የግዝረ
ትን ሥርዓት ካልፈጸማችሁ ልትድኑ አትች
ሉም» እያሉ ክርስቲያኖችን ያውኩዋቸው
ጀመር። 2 ጳውሎስና በርናባስም እንደዚህ
እያሉ የሚያስተምሩትን ሰዎች አጥብቀው
ተከራከሩአቸው። በኋላም ጳውሎስና በርና
ባስ በአንጾኪያ ካሉት ክርስቲያኖች ሰው
ጨምረው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄዱና፥
ጉዳዩን ለሐዋርያትና ለቤተ ክርስቲያን
ሽማግሌዎች እንዲያቀርቡ ተወሰነ። 3 ከዚ
ያም ጳውሎስና በርናባስ ወደ ኢየሩሳሌም
ጉዞ ጀመሩ። እግረ መንገዳቸውንም በፊን
ቄና በሰማርያ በኩል ሲያልፉ እዚያ ለሚገ
ኙት ክርስቲያኖች፥ አሕዛብ በጌታ አምነው
እንደ ዳኑ ተናገሩ። የሰሙትም ቃል

ክርስቲያኖችን አስደሰታቸው።
4 ጳውሎስና በርናባስ ኢየሩሳሌም እንደ
ደረሱ፥ ሐዋርያትና የቤተ ክርስቲያን ሽማግ
ሌዎች፥እንዲሁም ምዕመናን ጭምር ተቀበ
ሉአቸው። እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ሆኖ
ያደረገውንም ነገር ሁሉ ኢየሩሳሌም ላሉት
ክርስቲያኖች ነገሯቸው። 5 ከፈሪሳውያን
ወገን የሆኑ አንዳንድ ክርስቲያኖች ተነሥ
ተው፥ «አሕዛብ በሙሴ ሕግ መሠረት መገ
ረዝና ሌሎችንም ሥርዓቶች መጠበቅ እንዳ
ለባቸው ሊነገራቸው ይገባል» አሉ። 6 ሐዋ
ርያትና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችም
ስለዚሁ ጉዳይ ተነጋግረው ለመወሰን ስብ
ሰባ አደረጉ።
7 በነገሩ ብዙ ከተወያዩና ከተከራከሩበት
በኋላ ጴጥሮስ ተነሥቶ የሚከተለውን ተና
ገረ።
«ወንድሞች ሆይ፥አሕዛብ በእኔ አማካይ
ነት የጌታን ቃል እንዲሰሙና እንዲያምኑ
እግዚአብሔር እኔን በመጀመሪያ እንደመረ
ጠኝ ታውቃላችሁ። 8 የሰዎችን ልብ መር
ምሮ የሚያውቅ እግዚአብሔር፥ለእኛ የሰጠ
ንን መንፈስ ቅዱስ ለአሕዛብም በመስጠት፥
እነርሱንም የተቀበላቸው መሆኑን መስክሮ
ላቸዋል። 9 ልባቸውንም እንደ እኛ በእም
ነት ስላነጻ በእነርሱና በእኛ መካከል
ምንም ልዩነት አላደረገም። 10 ታዲያ አባቶ
ቻችንም ሆኑ እኛ ልንሸከመው ያልቻልነ
ውን ቀንበር አሕዛብ ጫንቃ ላይ መጫን
እግዚአብሔርን መፈታተን አይሆንም?
11 ነገር ግን፥እኛም ሆንን አሕዛብ የምንድ
ነው ፥ ከክርስቶስ በሚገኘው ጸጋ ብቻ
ነው።»
12 ጴጥሮስ ተናግሮ እንዳበቃ በዚያ የተሰ
በሰበው ሰው ሁሉ ጸጥ አለ። በርናባስና
ጳውሎስም፥እግዚአብሔር በእነርሱ አማካይ
ነት በአሕዛብ መካከል ያደረጋቸውን ተአም
ራትና ብዙ ድንቅ ሥራዎች እንሥተው
ተናገሩ።
13 እነርሱም ንግግራቸውን ሲጨርሱ ያዕ
ቆብ በተራው ተነሥቶ የሚከተለውን ተና
ገረ። «ወንድሞቼ ሆይ፥ 14 እግዚአብሔር
ስሙን ለማስከበር ለራሱ የሚሆኑትን ሰዎች
ከአሕዛብ መካከል እንዴት እንደ መረጠ
ስምዖን ቀደም አድርጎ ነግሮናል። 15 ይህ
አባባሉም ከነቢያት ቃል ጋር የሠመረ
ነው። እስቲ ነቢዩ የሚናገረውን ቃል አድ
ምጡ፥
16 «ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
'ከዚህ በኋላ እመለሳለሁ፤የፈረሰውንም የዳ
ዊትን ቤት እሠራለሁ። ፍርስራሹንም
ጠግኜ እንደገና አቆመዋለሁ። 17 ይህንንም
የማደርገው ከቤተ እሥራኤል ውጪ ያሉ
ሰዎችና በስሜ የተጠሩ አሕዛብ ሁሉ እግዚ
አብሔርን እንዲፈልጉት ነው። 18 ከመጀመ
ሪያው ጀምሮ በነ ፈቃዱን ያስታወቀው
እግዚአብሔር ራሱ ይህንን ተናገረ።'
19 «ነገሩ እንዲህ ከሆነ፥ወደ እግዚአብ
ሔር የሚመለሱትን አሕዛብ ለአይሁድ ሃይ
ማኖት ሥርዓት መታዘዝ አለባችሁ በማለት
ሸክም መጫን የለብንም። 20 ሆኖም በእኛ
በኩል ለጣዖት የተሠዋ እንስሳ ሥጋ እንዳይ
በሉ፥ከዝሙት እንዲርቁ፥ታንቆ የሞተ እን
ስሳ ሥጋ፥እንዲሁም የእንስሳ ደም እንዳይ
በሉ እንጻፍላቸው። 21 እነዚህን ነገሮች
የሚከለክለው የሙሴ ሕግ እንደሆነ ከጥንት
ጀምሮ በየሰንበቱ በምኵራቦች ሁሉ ሲነበ
ብና ሲነገር ኖሮአል።»
22 ከዚህ በኋላ ሐዋርያት፥የቤተክርስቲ
ያን ሽማግሌዎችና ምዕመናን በሙሉ፥ከጳ
ውሎስና ከበርናባስ ጋር ተጨማሪ መልእክ
ተኞች ወደ አንጾኪያ ለመላክ ባንድ ድምፅ
ተስማሙ። ስለዚህም ከወንድሞች መካከል
የተመሰከረላቸውን በርስያን የተባለውን
ይሁዳንና ሲላስን መረጡ። 23 የመልእክቱም
ቃል የሚከተለው ነበር፥
«በኢየሩሳሌም ከምንገኝ ሐዋርያት ፥
የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና ምዕመናን።
በአንጾኪያ፥ በሶርያና በኪልቂያ ለምትገኙ
ከአሕዛብ ወገን ለሆናችሁ ወንድሞቻችን።
ሰላምታችን ይድረሳችሁ።
24 «ከመካከላችን አንዳንድ ሰዎች ወደ
እናንተ መጥተው፥ 'ካልተገረዛችሁና የሙ
ሴን ሕግና ሥርዓት ካልጠበቃችሁ በቀር
አትድኑም' በማለት እንዳወኩአችሁ ሰምተ
ናል። እነዚህ ሰዎች ይህን እንዲነግሩዋችሁ
ከእኛ የተቀበሉት ትእዛዝ አልነበረም።
25 ጉዳዩ በጣም አሳሳቢ ሆኖ ስላገኘነው፥
ሁላችንም በአንድነት ተሰብስበን ከተነጋገር
ንበት በኋላ፥ይህን ወስነናል። ውሳኔውንም
እንዲያስረዱችሁ ይሁዳንና ሲላስን፥ከውድ
ወንድሞቻችን ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር
ወደ እናንተ ልከናቸዋል። 26 በርናባስና
ጳውሎስ ለሕይወታቸው ሳይሳሱ ጌታ ኢየ
ሱስ ክርስቶስን ለማገልገል ቆርጠው የተ
ነሡ ወንድሞቻችን ናቸው። ይሁዳና ሲላ
ስም፥ስለጠየቃችሁት ጉዳይ የተስማማንበት
ንና በጽሑፍ የላክንላችሁን ውሳኔ በቃል
ያስረዱችኋል።
27-29 «ከሚከተሉት ነገሮች እንድትርቁ

ከማሳሰብ በስተቀር፥ሌላ ሸክም አንጭንባች
ሁም። ይህም የእኛ ብቻ ሳይሆን የመንፈስ
ቅዱስም ፈቃድ ነው። ለጣዖት የተሠዋ እን
ስሳ ሥጋ፥ታንቆ የሞተ እንስሳ ሥጋ፥እንዲ
ሁም የእንስሳ ደም አትብሉ፤ ከዝሙት
ራቁ። እነዚህን ነገሮች ከማድረግ ከተጠበቃ
ችሁ ይኸው በቂ ነው። በሉ ደህና ሁኑ።»
30 አራቱም መልእክተኞች ሳይውሉ ሳያ
ድሩ ወደ አንጾኪያ ሄዱ። እንደ ደረሱም
ክርስቲያኖችን ሁሉ ሰብስበው፥ይዘው የመ
ጡትን ደብዳቤ አስረከቡዋቸው። 31 ክርስቲ
ያኖች የደብዳቤውን ቃል ሰምተው በውሳ
ኔው በጣም ተደሰቱ።
32 ይሁዳና ሲላስም ትንቢት የመናገር
ስጦታ የተሰጣቸው ስለነበሩ፥የምዕመናንን
እምነት የሚያጠነክር ብዙ የማጽናኛ ቃል
ነገሩአቸው፤
33 ይሁዳና ሲላስ ለብዙ ቀናት በአንጾ
ኪያ ሰነበቱ። ከዚያም፥ይሁዳ ወንድሞችን
ተሰናብቶ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለስ፥ሲላስ
ግን በዚያው ለመቅረት ወሰነ። 34-35 ጳውሎ
ስና በርናባስ ደግሞ፥የእግዚአብሔርን ቃል
የሚሰብኩትንና የሚያስተምሩትን የጌታ
አገልጋዮች ለመርዳት፥በዚያው በአንጾኪያ
ቆዩ።
36 ከብዙ ቀኖች በኋላም፥ጳውሎስ በርና
ባስን፥ «ከዚህ በፊት የጌታን ቃል ወደ አስ
ተማርንባቸው ከተሞች ሄደን፥የክርስቲያኖ
ችን ሁኔታ እንይ» አለው። 37 በዚህ ጊዜ
ግን አንድ አስቸጋሪ ነገር ተፈጠረ። በርና
ባስ ማርቆስ አብሮአቸው እንዲሄድ ፍላ
ጐት ነበረው። 38 ጳውሎስ ግን ይህን አልተ
ቀበለም። ምክንያቱም ማርቆስ ከዚህ በፊት
ጳውሎስንና በርናባስን በጵንፍልያ ትቶአ
ቸው ስለሄደ፥ ቅሬታ ነበረውና ነው።
39 ጳውሎስና በርናባስም በዚህ ጉዳይ ሊግ
ባቡ ባለመቻላቸው፥በርናባስ ከጳውሎስ ተለ
ይቶ ማርቆስን ይዞ በመርከብ ወደ ቆጵሮስ
ሄደ። 40-41 ጳውሎስም ሲላስን ይዞ ለመሄድ
ወሰነ። በአንጾኪያ ያሉት ምዕመናንም፥
ሥራቸውን እንዲባርክላቸው ከጸለዩላቸውና
ለእግዚአብሔር አደራ ከሰጡአቸው በኋላ፥
ጳውሎስና ሲላስ በሶርያና በኪልቅያ የሚገ
ኙትን አብያተ ክርስቲያን ለማበረታታት
ጉዞአቸውን ቀጠሉ።

## ምዕራፍ 16

1 ጳውሎስና ሲላስ መጀመሪያ ወደ ደር
ቤን ቀጥሎ ወደ ልስጥራን ሄዱ። በልስጥራ
ንም ጢሞቴዎስን አገኙ። የጢሞቴዎስ
እናት በትውልድ አይሁዳዊት ስትሆን፥በእ
ምነትዋ ክርስቲያን ነበረች። አባቱ ግን የግ
ሪክ ተወላጅ ነበር። 2 ጢሞቴዎስ በልስጥራ
ንና በኢቆንዮን ባሉት ምዕመናን ዘንድ የተ
ወደደ ነበረ። 3 ስለዚህም ጳውሎስ ጢሞቴ
ዎስን ይዞ ለመሄድ ፈለገ። ነገር ግን፥በዚያ
የሚኖሩ አይሁድ የጢሞቴዎስ አባት ከአሕ
ዛብ ወገን መሆኑን ስለሚያውቁ፥ጢሞቴዎ
ስን ይዞት ከመሄዱ በፊት የግዝረትን ሥር
ዓት እንዲፈጽም አደረገው። 4 ከዚህ በኋላ
ጳውሎስና የሥራ ጓደኞቹ በየቤተ ክርስቲ
ያኑ እየተገኙ፥ በኢየሩሳሌም ስብሰባ ስለ
አሕዛብ በሐዋርያት የተወሰነውን ለምዕመ
ናን በማስረዳት፥ውሳኔው በተግባር ላይ እን
ዲውል አጥብቀው ያሳስቡ ነበር። 5 ከዚህም
የተነሣ ቤተ ክርስቲያን በእምነት እየጠነከ
ረች፥የክርስቲያኖች ቁጥር ዕለት በዕለት እየ
ጨመረ ይሄድ ነበር።
6 ጳውሎስና የሥራ ጓደኞቹ በእስያ የጌ
ታን ቃል እንዳይናገሩ መንፈስ ቅዱስ ስለ
ከለከላቸው፥በፍርግያና በገላትያ በኩል አድ
ርገው ሽቅብ አለፉ። 7 ከሚሲያ ድንበር
ሲደርሱም በስተሰሜን በኩል አድርገው
ወደ ቢታንያ ለመሄድ አሰበው ነበር። የጌታ
መንፈስ ግን ወደዚያ እንዲሄዱ አልፈቀደላ
ቸውም። 8 ስለዚህ በሚሲያ በኩል አድር
ገው ወደ ጢሮአዳ አለፉ።
9 ጢሮአዳም ሳሉ አንድ ሌሊት ጳውሎስ
ራእይ አየ። በራእዩም አንድ የመቄዶንያ
ሰው፥ «እዚህ ናና እርዳን» ሲለው ሰማ።
10 ጳውሎስ ይህን ራእይ ካየ በኋላ፥ ወደ
መቄዶንያ ሄደን ቃሉን እንድናስተምር
የጌታ ፈቃድ መሆኑን ሁላችንም ተረዳን።
11 ከጢሮአዳ በመርከብ ተሳፍረን በቀ
ጥታ ወደ ሳሞትራቄ ሄድን። በማግስቱም
በመርከብ ወደ ናጴሌ ተጓዝን። 12 ከናጴሌ
ተነሥተንም ከመቄዶንያ ከተሞች አንዷና
ትልቋ ወደ ሆነችው ወደ ፊልጵስዩስ ደረ
ስን። በዚያን ዘመን ፊልጵስዩስ የሮማውያን
ቅኝ ግዛት ነበረች። በዚችም ከተማ ብዙ
ቀናት ቆየን።
13 በሰንበት ቀን የጸሎት ቦታ ወደሆነ፥
ከከተማ ወጣ ብሎ ወደሚገኝ ወደ አንድ
የወንዝ ዳር ሄድን። በዚያም ለተገኙት
ሴቶች የእግዚአብሔርን ቃል ሰበክንላቸው።
14 ከሴቶቹም መካከል፥እግዚአብሔርን በቅን
ልብ የምታመልክ ልድያ የተባለች ከትያጥ
ሮን የመጣች አንዲት የሐር ጨርቅ ነጋዴ
ነበረች። ጌታም ልቧን ስለከፈተላት፥ ጳው
ሎስ በሚያስተምርበት ጊዜ የሚናገረውን

ሁሉ በጥሞና አዳምጣ ለመቀበል በቃች።
15 ልድያ ከነቤተ ሰቧ ከተጠመቀች በኋላ፣
«ክርስቲያን መሆኔን በእርግጥ ከተረዳችሁ
ልኝ ቤቴን እንደ ቤታችሁ ልትቆጥሩት ይገ
ባችኋል» ብላ ወደ ቤቷ እንድንገባላት ለመ
ነችን።
16 አንድ ቀን ወንዙ አጠገብ ወደሚገ
ኘው የጸሎት ቦታ ስንሄድ፣ ርኩስ መንፈስ
የነበረባት አንዲት የቤት አገልጋይ በመን
ገድ ላይ አገኘችን። ይህች ሴት ጠንቋይ ስለ
ነበረች፣እየጠነቆለች ለአሳዳሪዎቿ ብዙ ገን
ዘብ ታስገባላቸው ነበር። 17 ሴትዮዋም ከኋ
ላችን እየተከተለች፣ «እነዚህ ሰዎች በእው
ነት የኃያሉ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ስለ
ሆኑ፣ ኃጢአታችሁ የሚሰረይበትን መንገድ
ይነግሯችኋል» እያለች ድምፅዋን ከፍ አድ
ርጋ ለአላፊ አግዳሚው ትናገር ነበር።
18 በዚያ መንገድ ባለፍን ቁጥር ይህንኑ
ቃል እየደገመች እየደጋገመች ትናገር ስለነ
በር፣ አንድ ቀን ጳውሎስ ቢቸግረው ቆም
ብሎ፣ «አንተ ርኩስ መንፈስ ይችን ልጅ
ለቀህ እንድትወጣ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ
ስም አዝሃለሁ» ብሎ ገሠጸው። ርኩስ መን
ፈሱም ወዲያውኑ ልጅቱን ለቋት ወጣ።
19-21 አሳዳሪዎቿም በእርሷ ምክንያት
ገንዘብ ለማካበት የነበራቸው ዕድል መጨና
ገፉን ሲመለከቱ፣ ጳውሎስና ሲላስን ይዘው
እየጎተቱ ወደ አደባባይ አውጥተው፣ ከዳ
ኞች ፊት ካቀረቧቸው በኋላ፣ «እነዚህ
ሰዎች አይሁዳውያን ናቸው። በከተማችንም
ውስጥ ሁከት እንዲነሣ ሲያደርጉ አግኝተና
ቸዋል። በተጨማሪም ሕዝቡ በሮም ሕግ
የተከለከለውን ነገር እንዲያደርግ ያስተም
ራሉ» ሲሉ ወነጀሉዋቸው።
22 ሕዝቡም ጳውሎስንና ሲላስን ተቃ
ውሞ ተነሣ። ዳኞቹም ጳውሎስና ሲላስ
ራቁታቸውን በሽመል እንዲደበደቡ አዘዙ።
23 ከተደበደቡም በኋላ እሥር ቤት አስገብ
ተው፣ በጥብቅ እንዲጠበቁ አደረጉ። 24 የእ
ሥር ቤቱ ዘበኛም ጳውሎስና ሲላስን ወደ
ውስጠኛው ክፍል አስገብቶ፣እጆቻቸውንና
እግሮቻቸውን በግንድና በግንድ መካከል
ጠርንቆ አሠራቸው።
25 በእኩለ ሌሊትም ጳውሎስና ሲላስ
ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እግዚአብሔርን
በጸሎትና በዝማሬ ያመሰግኑት ነበር።
ሌሎች እሥረኞችም ያደምጡአቸው ነበር።
26 በድንገትም የእሥር ቤቱ መሠረት እስኪ
ናጋ ድረስ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ።
የእሥር ቤቱ በሮች ተከፈቱ፤እሥረኞች የታ
ሠሩባቸውም ሰንሰለቶች እየወለቁ ወደቁ።
27 የእሥር ቤቱ ዘበኛም ከእንቅልፉ ሲነቃ፣
የእሥር ቤቱ በሮች ተከፍተው ስላየ፣እሥረ
ኞቹ ያመለጡ መስሎት ራሱን ለመግደል
ሰይፉን መዘዘ።
28 ጳውሎስም፣ «ኧረ እባክህ በራስህ ላይ
ክፉ ነገር እንዳታደርስ! ሁላችንም ከዚህ
አልተነቃነቅንም» ሲል ጮኸበት።
29 ዘበኛውም መብራት አስበርቶ ወደ
ውስጥ ገባና በፍርሃት እየተንቀጠቀጠ፣ በጳ
ውሎስና በሲላስ እግር ላይ በግንባሩ
ተደፋ። 30 ከታሠሩበትም ክፍል አወጣቸ
ውና፣ «ጌቶቼ፣እንድድን ምን ማድረግ ይገ
ባኛል?» ሲል ጠየቃቸው።
31 እነርሱም፣ «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ
እመን፤አንተም ቤተ ሰብህም ሁሉ ትድናላ
ችሁ» አሉት።
32 ከዚህ በኋላ ለእርሱና ለቤተ ሰቡ
በሙሉ የእግዚአብሔርን ቃል ሰበኩላቸው።
33 የእሥር ቤቱ ዘበኛም የጳውሎስንና የሲላ
ስን ቁስል አጠበላቸው። ወዲያውም ከቤተ
ሰቡ ጋር ተጠመቀ። 34 ወደ ቤቱም ወስዶ
ምግብ አቀረበላቸው። በእግዚአብሔር በማ
መናቸውም እርሱና ቤተ ሰቡ በሙሉ
በጣም ደስ አላቸው። 35 በማግስቱም ዳኞቹ
መልእክተኞች ወደ እሥር ቤቱ ዘበኛ
ልከው፣ «እነዚያን ሰዎች ልቀቃቸው»
አሉት። 36 የእሥር ቤቱ ዘበኛም ጳውሎ
ስን፣ «ዳኞቹ አንተና ሲላስ በነፃ እንድትለ
ቀቁ አዘዋልና በሰላም ሂዱ» አለው።
37 ጳውሎስ ግን ለመልእክተኞቹ፣ «ነገሩ
መቼ እንዲህ ይሆንና? እኛ የሮም ዜጎች
ስንሆን፣ ያለ ምንም ጥፋት በአደባባይ ደብ
ድበውና አንገላተው አሥረውናል። ታዲያ
በአደባባይ ገርፈው አንገላተውና አሥረው
አሳድረው፣ እንደገና አሁን በድብቅ ‘ተለቃ
ችኋልና ሂዱ!’ ቢሉን፣እኛ መች እሺ የም
ንል ሰዎች ነን? ራሳቸው መጥተው ካልፈ
ቱን በስተቀር አንሄድም!» አለ።
38 ዳኞቹም ጳውሎስና ሲላስ የሮም
ዜጎች መሆናቸውን ከላኳቸው መልእክተ
ኞች ሲሰሙ፣ ክፉ ነገር ይደርስብናል
ብለው ፈሩ። 39 ከዚያም ወደ እሥር ቤቱ
ሄደው ጳውሎስና ሲላስን ይቅርታ ከጠየቋ
ቸው በኋላ፣ ከተማውን ለቀው እንዲሄዱላ
ቸው ለመኑአቸው። 40 ጳውሎስና ሲላስ ከእ
ሥር ቤቱ እንደወጡ በቀጥታ ወደ ልድያ
ቤት አመሩ። እዚያም ከክርስቲያን ወንድ
ሞች ጋር ተገናኝተው ካጽናኗቸው በኋላ
ከተማይቱን ለቀው ወጡ።

## ምዕራፍ 17

1 ጳውሎስና ሲላስ በአንፊጶልና በአጶሎ
ንያ ከተሞች በኩል አልፈው ወደ ተሰሎ
ንቄ ደረሱ። በተሰሎንቄም አንድ የአይሁድ
ምኩራብ ነበር። 2 ጳውሎስም እንደ ልማዱ
ወደ ምኩራቡ ገብቶ፥ሦስት ሰንበት በማከታ
ተል በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተነገሩ
ትን ትንቢቶች በመተንተን፥ስለ 3 ክርስቶስ
መከራ መቀበልና ከሞት መነሣት ካስተማረ
በኋላ፥ክርስቶስ ትንቢት የተነገረለት መሲሕ
መሆኑን አረጋገጠላቸው። 4 የጳውሎስን
ትምህርት ከሰሙት አይሁድ አንዳንዶቹ
በጌታ አመኑ። እንዲሁም ወደ አይሁድ ሃይ
ማኖት ገብተው ከነበሩት አሕዛብ መካከል፥
ብዙ ግሪኮችና የታወቁ ወይዛዝርትም በጌታ
ኢየሱስ አመኑ።

5 በጳውሎስና በሲላስ ትምህርት ቅናት
ያደረባቸው አይሁድ፥ያካባቢውን ቦዘኔ አሰ
ባስበውና አስተባብረው በከተማይቱ ውስጥ
ግርግር እንዲፈጠር አደረጉ። ጸጥታው ሲደ
ፈርስ ጳውሎስንና ሲላስን ይዘው ሕዝብ
ፊት ለማቅረብ እንዲመቻቸው የኢያሶንን
ቤት ከበቡ።

6 እንዳሰቡት ጳውሎስንና ሲላስን አላገኟ
ቸውም። ሆኖም ኢያሶንንና በዚያ ያገኟቸ
ውን ምዕመናን እየጎተቱ አውጥተው ከባለ
ሥልጣኖች ፊት አቀረቡአቸው። ወንጀላቸ
ውንም እያስረዱ፥ «ጳውሎስና ሲላስ የተ
ባሉ ዓለምን የበጠበጡ ሰዎች ወደ ከተማ
ችን ገብተዋል። 7 እነሱንም ኢያሶን በቤቱ
ተቀብሎ አስተናግዷቸዋል። እነዚህ ሰዎች
ንጉሣችን ኢየሱስ ነው እንጂ፥እኛ ቄሣር
የሚባል ንጉሥ አናውቅም፥ እያሉ በሕግ
ጸንቶ የቆመውን መንግሥት ለማናጋት የተነ
ሣሱ አመፀኞች ናቸው» አሉ።

8-9 ሕዝቡና የከተማይቱ ባለ ሥልጣኖች
ይህን ሲሰሙ ነገሩን እንደዋዛ ሊመለከቱት
አልቻሉም። ስለዚህም ኢያሶንንና የቀሩትን
ዋስ አስጠርተው ለቀቋቸው።

10 በተሰሎንቄ ያሉት ክርስቲያኖችም፥
ጳውሎስንና ሲላስን ከተማይቱን በቶሎ
ለቀው በሌሊት ወደ ቤርያ እንዲሄዱ ሸኟ
ቸው። ቤርያ እንደ ደረሱም እንደ ተለመ
ደው ወደ ምኩራብ ገቡ። 11 የቤርያ ነዋሪ
ዎች ከተሰሎንቄ ሰዎች ይልቅ አርቀው አሳ
ቢዎች ስለነበሩ፥የጳውሎስን ትምህርት በጥ
ሞና ያደምጡ ነበር። ጳውሎስ የሚያስተም
ረው ትምህርት እውነት መሆኑን ለማረጋገ
ጥም፥በየቀኑ ቅዱሳት መጻሕፍትን እያገላ
በጡ ይመረምሩ ነበር። 12 ከዚህም የተነሣ
ከመካከላቸው ብዙ አይሁዶች፥እንዲሁም
ብዙ የታወቁ የግሪክ ሴቶችና አያሌ የግሪክ
ወንዶችም በጌታ አመኑ።

13 ነገር ግን በተሰሎንቄ ያሉት አይ
ሁድ፥ጳውሎስ ቤርያ ገብቶ የሚያስተምር
መሆኑን ሲሰሙ፥እዚያው ድረስ ሄደው
አሁንም ሕዝቡን አሳድመው ሁከት አስነ
ሡባቸው። 14 በዚህ ጊዜ ምዕመናን፥ጳው
ሎስ ወዲያውኑ ተነሥቶ ወደ ባሕሩ
ዳርቻ እንዲሄድ አደረጉ። ሲላስና ጢሞ
ቴዎስ ግን እዚያው ቤርያ ቀሩ።
15-16 ጳውሎስን የሸኙት ምዕመናንም
አቴና አድርሰውት ወደ ቤርያ ተመለሱ።
ጳውሎስ፥ሲላስና ጢሞቴዎስ በቶሎ እንዲ
መጡለት መልእክት ልኮባቸው፥እስከዚ
ያው በአቴና ቆየ። ከተማይቱንም እየተዘ
ዋወረ ሲጐበኝ፥በብዙ ጣዖታት ተሞልታ
በማየቱ እጅግ አድርጎ አዘነ። 17 ስለዚህ
ወደ ምኩራብ እየገባ ከአይሁድና ወደ አይ
ሁድ ሃይማኖት ከተመለሱ ግሪኮች ጋር ተወ
ያየ። እንዲሁም ዕለት በዕለት በየደባባዩ
እየተገኘ፥ላገኘው ሁሉ የጣዖታቱን ከንቱ
ነት ያስረዳ ነበር።

18 የኤፊቆሮስና የኢስጦኢኰ ወገን ከሆኑ
ፈላስፎችም ጋር አጥብቆ ይከራከር ነበር።
ከእነርሱም አንዳንዶቹ ጳውሎስ ስለ ኢየሱ
ስና ስለትንሣኤው የሚናገረውን ሲሰሙ፥
«ይህ ለፍላፊ ምን ማለቱ ነው? የማንን የባ
ዕድ ሃይማኖት ነው ተቀበሉ የሚለን?»
እያሉ ይሳሳቁበት ነበር።

19-20 ከዚያም አርዮስፋጎስ ከተባለው
ሥፍራ ወዳለው የውይይት መድረክ ጋብ
ዘው፥ «ከዚህ በፊት የማናውቃቸውን አንዳ
ንድ ነገሮች ስትናገር ሰምተንሃል። ስለዚህ
የምታስተምረው ይህ አዲስ ሃይማኖት ምን
እንደሆነ በበለጠ ለማወቅ ስለምንፈልግ፥
እስቲ አብራርተህ አስረዳን?» አሉት።
21 ይህን ያሉትም የአቴና ነዋሪዎችና በአ
ቴና ያሉ የውጭ አገር ዜጎች፥ጊዜያቸውን
የሚያሳልፉት አዳዲስ አሳቦች በማቅረብና
በመከራከር ስለሆነ ነበር።

22 ጳውሎስም በአርዮስፋጎስ የውይይት
መድረክ ላይ ወጥቶ የሚከተለውን ንግግር
አደረገ፥ «እናንተ የአቴና ሰዎች፥ሃይማኖተ
ኞች መሆናችሁን በብዙ መንገድ ለመረዳት
ችያለሁ። 23 ይህንንም ለማለት የበቃሁት
ከተማችሁን ለማየት ስዘዋወር፥ በየቦታው
ብዙ መሠዊያዎችን ስለተመለከትኩ ነው።
ከነዚህም መሠዊያዎች በአንዱ ላይ፥ 'ለማ

ይታወቅ አምላክ' የሚል ተጽፎበት አይቻ
ለሁ። እንግዲህ አሁን የምነግራችሁም ስለ
ዚሁ ሳታውቁ ስለምታመልኩት አምላክ
ነው።

24 «ይህም አምላክ ዓለምንና በውስጧ
ያሉትን ነገሮች ሁሉ የፈጠረ ጌታ ነው።
እርሱ በሰዎች እጅ በተሠራ ቤተ መቅደስ
ውስጥ አይኖርም። 25 የሕይወትና የእስትን
ፋስ፥ የሌሎችም ነገሮች ሁሉ ሰጪ እርሱ
በመሆኑ፥ የሚጐድለው አንዳችም ነገር
የለም። ስለዚህም የሰው እርዳታ አያስፈልገ
ውም። 26 ሕዝቦችን ሁሉ ከአንዱ ከአዳም
ፈጥሮ በመላው ምድር ላይ እንዲኖሩ አደረ
ጋቸው። ለእያንዳንዱም ሕዝብ የታሪክ
ወቅት ወስኖ፥ ዳርና ድንበር ከልሎ ሰጣ
ቸው።

27 «ይህንንም ሁሉ ያደረገው ያለ ምክን
ያት አልነበረም። ምንም እንኳን እርሱ ከሰ
ዎች የራቀ ባይሆንም፥ሰዎች ራሳቸው እን
ዲፈልጉትና በመንፈሳቸው ተነሣሥተው
እንዲያገኙት በማለት ነው። 28 ሕይወት
የምናገኘውና የምንንቀሳቀሰው፥ የምንኖረ
ውም በእርሱ ነውና። ይህንንም በማሰብ ከባ
ለቅኔዎቻችሁ አንዳንዶቹ፥ 'እኛ የአምላክ
ልጆች ነን' ብለውታል። 29 ታዲያ፥ 'እኛ
የአምላክ ልጆች ነን' የምንል ከሆነ፥ ከወ
ርቅ፥ከብር ወይም ከማናቸውም ነገር የተቀ
ረጸውን ምስል አምላክ ነው ማለት ይገባ
ናል? እስቲ ይታያችሁ! 30 ከዚህ በፊት ባለ
ማወቅ የተደረገውን ስሕተት እግዚአብሔር
በይቅርታ አልፎታል። ከእንግዲህ ወዲህ
ግን ሰዎች ሁሉ ንስሐ በመግባት ከጣዖት
አምልኮና ከክህደት ሥራ ሁሉ ተመልሰው
እሱን ብቻ በማመን እንዲጸኑ አዟል።
31 ይህንንም ተግባር እንዲያከናውን በመረ
ጠው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት በዓ
ለም ላይ በእውነት የሚፈርድበትን ቀን አስ
ቀድሞ ወስኗል። እርሱን ከሞት በማስነሣ
ቱም የዚህን ነገር ትክክለኛነት አረጋግጦል
ናል።»

32 ጳውሎስ ስለ ሙታን ትንሣኤ የተናገ
ረው ነገር አንዳንዶቹን ሲያስቃቸው፥
ሌሎች ግን፥ «ስለዚህ ጉዳይ በሌላ ጊዜ በሰ
ፊው እንድትነግረን እንፈልጋለን» አሉት።
33 ጳውሎስ ከዚያ ተነሥቶ ወጣ። 34 ንግግሩ
ንም ካዳመጡት መካከል አንዳንዶቹ በጌታ
አምነው ተከተሉት። ካመኑትም መካከል
ዲዮናስዮስ የተባለው የአርዮስፋጎስ ሸንጎ
አባል፥ደማሪስ የተባለች አንዲት ሴት ወይዘ
ሮና ሌሎችም ነበሩ።

## ምዕራፍ 18

1 ከዚህ በኋላ ጳውሎስ ከአቴና ወደ ቆሮ
ንቶስ ሄደ። 2-3 በቆሮንቶስም በጳንጦስ ተወ
ልዶ ያደገ አቂላ የሚባል አንድ አይሁዳዊ
አገኘ። አቂላ ከሚስቱ ከጵርስቅላ ጋር ከኢ
ጣልያ ወደ ቆሮንቶስ ገና መምጣቱ ነበር።
ከኢጣልያ የመጣበትም ምክንያት አይሁድ
ሮምን ለቀው እንዲወጡ፥ ከንጉሠ ነገሥቱ
ከቀላውዴዎስ ትእዛዝ ወጥቶ ስለነበር ነው።
ጳውሎስም እንደ አቂላና ጵርስቅላ ድንኳን
መስፋት ይችል ስለነበር፥ማረፊያውን ከእነ
ርሱ ዘንድ አደረገ።

4 በየሰንበቱ ወደ ምኵራብ እየሄደ፥ለአይ
ሁድና ለግሪክ ሰዎች ስለ ክርስቶስ ያስተ
ምር፥ያስረዳም ነበር። 5 ሲላስና ጢሞቴዎስ
ከመቄዶንያ ከመጡ በኋላ ግን፥ኢየሱስ ትን
ቢት ተነግሮለት ሲጠበቅ የነበረው መሲሕ
መሆኑን ለአይሁድ ማስተማሩንና ማስረዳ
ቱን ከበፊቱ የበለጠ ሥራዬ ብሎ ያዘው።
6 ነገር ግን አይሁድ ተቃውሞና ስድብ ስላ
በዙበት፥ «ከእንግዲህ ጥፋታችሁ በራሳችሁ
ላይ ይመጣባችኋል እንጂ፥ እኔ ከደሙ
ንጹሕ ነኝ። ከዛሬ ጀምሮ አሕዛብን አስተ
ምራለሁ» በማለት የልብሱን አቧራ አራ
ገፈ።

7 ከዚህ በኋላ ቲቶስ ኢዮስጦስ ወደተባለ
እግዚአብሔርን ወደሚያመልክ ሰው ቤት
ሄዶ መኖር ጀመረ። የቲቶስ ቤትም ምኵ
ራቡ አጠገብ ነበር። 8 ቀርስጶስ የተባለው
የምኵራብ አለቃና ቤተ ሰቡ የጳውሎስን
ትምህርት ተቀብለው በጌታ አመኑ። እንዲ
ሁም ብዙ የቆሮንቶስ ሰዎች የጳውሎስን
ትምህርት ሰምተው በኢየሱስ ስላመኑ ተጠ
መቁ።

9 ጌታም አንድ ሌሊት በራእይ ለጳው
ሎስ ተገልጦ እንዲህ አለው። «አትፍራ፥
ተስፋ አትቁረጥ፤ ዝምም አትበል። 10 እኔ
ከአንተ ጋር ስለ ሆንኩ ማንም ሊጐዳህ አይ
ችልም። በዚች ከተማ ብዙ ሰዎች ስላሉኝ
ወንጌልን አስተምር።» 11 ጳውሎስም የእግ
ዚአብሔርን ቃል እያስተማረ አንድ ዓመት
ተኩል በዚያው ቆየ።

12 ጋልዮስ የአካይያ አስተዳዳሪ ሆኖ ከተ
ሾመ በኋላ፥አይሁድ ተባብረውና ተነባብ
ረው በጳውሎስ ላይ ተነሡበት። ይዘውም
ከጋልዮስ ፊት አቅርበው፥ 13 «ይህ ሰው
የሮም ቄሣርን ሕግ በሚጻረር መንገድ፥
ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ያስተ
ምራል» ሲሉ ከሰሱት። 14 ጳውሎስም ለክሱ

መልስ ለመስጠት ሲዘጋጅ፣ ጋልዮስ፣ «ሰማ
ችሁ እናንተ አይሁዶች! በደል ወይንም
ወንጀል ተፈጽሞባችሁ ቢሆን ኖሮ ክሳች
ሁን በተቀበልኩት ነበር። 15-16 እናንተ የም
ትነታረኩት ስለ ቃላት አገባብና ፍቺ፣ ስለ
አንዳንድ ስያሜዎች ስለ ሕግና ሥርዓታ
ችሁ ከሆነ ግን፣ የራሳችሁ ጉዳይ ስለሆነ
እናንተው እወቁበት። እኔን አያገባኝም»
ብሎ መለሳቸው።
17 ከዚያም አይሁድ የምኵራባቸውን
አስተዳዳሪ ሶስቴንስን ይዘው ደበደቡት።
ጋልዮስ ግን ድርጊቱን ከጉዳይም አልጣ
ፈው።
18 ጳውሎስም በቆሮንቶስ ለአያሌ ቀናት
ከሰነባበተ በኋላ፣ ምዕመናንን ተሰናብቶ አቂ
ላና ጵርስቅላን ይዞ ወደ ሶርያ ሄደ። ክንክ
ራኦስ እንደ ደረሱም ስለት ስለ ነበረበት
ጠጉሩን ተላጨ። 19 ወደ ኤፌሶን ሲደርሱ
ጵርስቅላንና አቂላን ትቷቸው ብቻውን ወደ
ምኵራብ ገብቶ አስተማረ። 20 በምኵራቡ
የነበሩትም ሰዎች አብሮአቸው እንዲሰነብት
ለመኑት። እርሱ ግን እዚያ መሰንበቱን ስላ
ልፈለገ፣
21 «እግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነ ተመ
ልሼ እመጣለሁ» ብሏቸው ከኤፌሶን በመር
ከብ ተሳፍሮ ጉዞውን ቀጠለ።
22 ቂሣርያ ሲደርስ ከመርከቡ ወርዶ
ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ። በዚያ የሚገኙትን
የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና ምዕመናን
ከጐበኘና ሰላምታ ከተለዋወጠ በኋላ ወደ
አንጾኪያ ተመለሰ። 23 በአንጾኪያ ጥቂት
ጊዜ እንደ ቆየም፣ ወደ ገላትያና ወደ ፍር
ግያ ሄዶ ከቦታ ቦታ በመዘዋወር፣ ክርስቲያ
ኖች በጌታ እምነት እንዲጸኑ አበረታታ
ቸው።
24 በዚህ ጊዜ፣ አጵሎስ የሚባል በግብፅ
አገር በእስክንድርያ ተወልዶ ያደገ አይሁ
ዳዊ ወደ ኤፌሶን መጣ። እርሱም በቅዱሳት
መጻሕፍት እውቀቱ እጅግ የተመሰገነ
መምህር ነበር። 25-26 አጵሎስም ከቅዱሳት
መጻሕፍት ስለ ጌታ መንገድ በሚገባ የተማ
ረና በጋለ መንፈሳዊ ቅንዓትም የሚሰብክ
ነበር። ስለ ክርስቶስ የነበረውም እውቀት
ስሕተት የሌለበት ነበር። ሆኖም ከዮሐንስ
ጥምቀት በቀር ሌላ ጥምቀት መኖሩን አያ
ውቅም ነበር። ያለ ፍርሃት በየምኵራቡ
ሲመሰክርና ሲያስተምር አቂላና ጵርስቅላ
ሰምተው፣ አጵሎስን ወደ ቤታቸው በመው
ሰድ፣ ስለክርስትና እምነት ፊት ከነበ
ረው እውቀት ይልቅ በተብራራ ሁኔታ
ገለጹለት።
27 አጵሎስ ወደ አካይያ አገር ለመሄድ
ማሰቡን ሲነግራቸው ምዕመናን አሳቡን
ደገፉ። በአካይያ የሚገኙ ክርስቲያኖችም፣
ለአጵሎስ መልካም አቀባበል እንዲያደርጉ
ለት የአደራ ደብዳቤ ጻፉለት። እዚያ እንደ
ደረሰም ምዕመናን በጌታ ጸጋ እንዲበረቱ
ስለ ረዳቸው፣ ለቤተ ክርስቲያን ትልቅ መጽ
ናናት ሆነ። 28 አጵሎስ፣ የኢየሱስን መሲሕ
ነት ከሚያስተባብሉ አይሁድ ጋር በይፋ
ክርክር እየገጠመና፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት
ማስረጃዎችን እየጠቀሰ አፋቸውን ያስይዛ
ቸው ነበር።

## ምዕራፍ 19

1 አጵሎስ ቆሮንቶስ ሳለ፣ ጳውሎስ በየብስ
ተጉዞ ኤፌሶን ደረሰ። በዚያም ጥቂት ምዕ
መናንን አግኝቶ፣ 2 «ባመናችሁ ጊዜ መን
ፈስ ቅዱስ ተቀበላችሁ?» ሲል ጠየቃቸው።
እነርሱም፣ «አልተቀበልንም። እንዲያ
ውም መንፈስ ቅዱስ የሚባል መኖሩንም
ገና ዛሬ ካንተ መስማታችን ነው» ብለው
መለሱለት።
3 እርሱም፣ «ለመሆኑ ምን ዓይነት ጥም
ቀት ነው የተጠመቃችሁት?» አላቸው።
እነርሱም፣ «የዮሐንስን ጥምቀት ነው»
አሉት።
4 ጳውሎስም፣ «የዮሐንስ ጥምቀትማ
ሰዎች ንስሐ ገብተው ወደ እግዚአብሔር
መመለሳቸውን የሚያመለክት ነበረ። ለዚ
ህም ማስረጃው ዮሐንስ ሕዝቡን በሚያስተ
ምርበት ጊዜ፣ 'ከእኔ በኋላ በሚመጣው
በኢየሱስ ክርስቶስ እንድታምኑ ይገባል'
ሲል ተናግሯል» አላቸው።
5 ይህንን ከሰሙ በኋላ በጌታ በኢየሱስ
ስም ተጠመቁ። 6 ከተጠመቁ በኋላ ጳውሎስ
እጁን ሲጭንባቸው፣ መንፈስ ቅዱስ ወረደባ
ቸው። ቀድሞ ተናግረው በማያውቁት
አዲስ ቋንቋ ተናገሩ፤ ትንቢትም ተነበዩ።
7 የተጠመቁትና መንፈስ ቅዱስን የተቀበ
ሉት ሰዎች ቁጥር አሥራ ሁለት ነበር።
8 ከዚያም ጳውሎስ በየሳምንቱ በየሰንበቱ
በማከታተል፣ በምኵራብ ሦስት ወር ስለ እግ
ዚአብሔር መንግሥት ያለፍርሃት አስተ
ማረ። 9 አንዳንዶች ሰዎች ግን ለማመን ስላ
ልፈለጉ፣ ትምህርቱን ይነቅፉና በይፋ ይሰ
ድቡ ነበር። ስለዚህም ጳውሎስ ከእነርሱ
ለይቶ ምዕመናንን ጢራኖስ በሚባለው የስብ
ሰባ አዳራሽ በየዕለቱ ያስተምር ጀመር።
10 በእስያ የሚኖሩ አይሁዶችና ግሪኮች፣ የእ

ግዚአብሔር ቃል እስኪደርሳቸው ድረስ
እያስተማረ ለሁለት ዓመት በዚህ ዓይነት
ቀጠለ። [11]ጌታም በጳውሎስ እጅ ለትንግ
ርት የሚታዩ ድንቅ ሥራዎችንና ተአምራ
ትን ያደርግ ነበር። [12]ሰዎችም ጳውሎስ
የዳሰሳቸውን መሀረቦቻቸውንና ልብሶቻቸ
ውን እየወሰዱ በበሽተኞች ላይ ያስቀምጡ
ነበር። በዚህን ጊዜ በሽተኞችም ይፈወሱ፥
በርኩሳን መናፍስትም የተያዙ ነፃ ይወጡ
ነበር።
[13]አጋንንትን ከሰዎች እናስወጣለን
እያሉ ከቦታ ቦታ ይዞሩ የነበሩ አንዳንድ
አይሁድም፥ «ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየ
ሱስ ስም ውጣ» በማለት አጋንንትን ለማስ
ወጣት ሞክረው ነበር። [14]የካህናቱ አለቃ
የአስቄዋ ሰባት ልጆች፥በዚህ ዓይነት መን
ገድ አጋንንትን ከሰዎች ለማስወጣት ሞክ
ረው አልሆነላቸውም። [15]እንዲያውም ሊያ
ስወጡት የሞከሩት ጋኔን፥ «ኢየሱስን አው
ቃለሁ፤ ጳውሎስንም አውቃለሁ። እናንተ
ደግሞ እነማን የምትባሉ ናችሁ?» አላ
ቸው። [16]ቀጥሎም ጋኔን ያደረበት ይኸው
ሰው ዘሎ አንቆ ደበደባቸው። እነርሱም
ልብሳቸው ሁሉ ተቀዳዶና ቆስለው ራቁታ
ቸውን እየሸሹ አመለጡ።
[17]ይህም ነገር ኤፌሶን በሚኖሩ አይሁ
ድና ግሪኮች ዘንድ ተሰማ። ስለዚህም በአካ
ባቢው ታላቅ ፍርሃት ተፈጠረ። የጌታን
የኢየሱስን ስም ሰዎች ያከብሩት ጀመር።
[18-19]በዚሁ ጊዜ በጌታ ካመኑት ሰዎች
መካከል ብዙዎቹ ቀድሞ ያደርጓቸው የነበ
ሩትን ክፉ ልማዶች ተናዘዙ። ብዙዎችም
የአስማትና የመተት መጽሐፎቻቸውን አም
ጥተው ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት አደባባይ
አቃጠሉት። የተቃጠሉት የጥንቆላ መጻሕ
ፍት ዋጋ ሃምሳ ሺህ ብር ይገመት ነበር።
[20]በዚህም ዓይነት፥የጌታ ቃል በዚያ አካ
ባቢ እየተስፋፋና እያየለ ሄደ።
[21]ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ፥ጳውሎስ በመቄ
ዶንያና በአካይያ አድርጎ ወደ ኢየሩሳሌም
ለመመለስ ወሰነ። ይህን ያቀደውም ከዚያ
ተነሥቶ ወደ ሮም ለመሄድ እንዲያመቸው
አስቦ ነበር። [22]ጢሞቴዎስንና ኤርስጦንን
«ወደ መቄዶንያ አልፋችሁ ቆዩኝ» ብሎ
አስቀድሞ ልኳቸው፥እርሱ በታናሽቱ እስያ
ለጥቂት ጊዜ ቆየ።
[23]በዚያን ጊዜ በኤፌሶን ከተማ የክርስት
ናን እምነት በሚመለከት ጉዳይ ከፍ ያለ
ሁከት ተፈጠረ። [24]የዚህም ሁከት ጠንሳሽ
ድሜጥሮስ የሚባል ሰው ነበር። ይህ ሰው
አንጥረኞች ቀጥሮ የአርጤምስን ምስል ብር
እያስቀለጠ በማሠራት፥ለራሱ ብዙ ገቢ ነበ
ረው። [25]ስለዚህ የራሱን ሠራተኞችና በተ
መሳሳይ ሙያ የተሰማሩትን ሌሎችንም
ሁሉ ሰብስቦ፥የሚከተለውን ንግግር አደረገ።
«ጉበዝ! መቼም ይህ ሥራ ለእኛ የማያ
ቋርጥ ገቢ የሚያስገኝልን መሆኑን አትስቱ
ትም። [26]ነገር ግን እንዳያችሁትና እንደ
ሰማችሁት፥ይህ ጳውሎስ የሚባል ሰው በኤ
ፌሶንና በመላው እስያ፥ 'እነዚህ ዓይን እያ
ላቸው የማያዩ፥ጆሮ እያላቸው የማይሰሙ፥
እግር እያላቸው የማይራመዱ ሰው ሠራሽ
ጣዖታትን ማምለክ አይገባም' እያለ በማስተ
ማር ብዙ ሰዎች አስቷል። [27]እንግዲህ
በዚህ ምክንያት ገቢያችን እያሽቆለቆለ
ሙያችንም እየተዋረደ መሄዱ ነው። ደግ
ሞስ በመላው ዓለም ዝናዋ ገኖ የምትመለ
ከው የታላቂቱ አምላክ የአርጤምስ ቤተ
መቅደስ እንዴት ማላገጫ ሆኖ ይቅር? ክብ
ሯና ገናንነቷስ እንዴት እንደዚህ ይዋ
ረድ?»
[28]ሠራተኞቹም የድሜጥሮስን ንግግር
ካዳመጡ በኋላ በቁጣ ተሞልተው፥ «የኤፌ
ሶኗ አርጤምስ ታላቅ ናት! የኤፌሶኗ አር
ጤምስ ገናና ናት!» እያሉ ይጮኹ
ጀመር።
[29]ጩኸታቸውም በአካባቢው ስለ ተሰማ
ብዙ ሕዝብ እንደ ጉድ ወጣ። ከተማይቱም
በሁከትና በጩኸት ተሞላች። ሕዝቡም የጳ
ውሎስ የሥራ ጓደኞች የሆኑትን፥ ጋይዮስ
ንና አርስጥሮኮስን ይዘው እየጎተቱ ወደጨ
ዋታ ሜዳ ወሰዷቸው። [30]ጳውሎስም
ሕዝቡ ወደ ተሰበሰበበት ሜዳ ሊገባ ቆርጦ
ተነሥቶ ነበር። ምዕመናን ግን ከለከሉት።
[31]ከእስያም አንዳንድ ወዳጆቹ የሆኑ ሮማ
ውያን መኰንኖች፥ ጳውሎስ ዘንድ ሰው
ልከው ሕዝቡ ወደ ተሰበሰበበት አደባባይ
እንዳይገባ አጥብቀው አስጠነቀቁት።
[32]በዚያ ከተሰበሰቡትም ሰዎች መካከል
አንዱ አንድ ሲያወራ፥ሌላው ደግሞ ሌላ
ነገር እያለ መጯጯህ እንጂ፥የሚደማመጥ
አልነበረም። ሁከቱ ድብልቅልቅ ያለ ስለነ
በር፥ ከተሰበሰቡት ሰዎች መካከል ለምን
ወደዚያ ቦታ እንደ መጣ እንኳን በትክክል
የሚያውቅ ብዙ አልነበረም።
[33]ከሕዝቡ መካከል ጥቂት ሰዎች እስክ
ንድሮስን እንዲናገር ገፍተው ወደ ፊት አቀ
ረቡት። እርሱም ጸጥታ እንዲሰፍን በእጁ
ምልክት አሳይቶ ሊናገር ሲል፥ [34]አይሁ
ዳዊ መሆኑን በማወቃቸው፥ «የኤፌሶኗ አር

ጤምስ ታላቅ ናት! የኤፌሶኗ አርጤምስ
ገናና ናት!» እያሉ ሁለት ሰዓት ሙሉ
ጮኹ፤
35 በመጨረሻ ግን የከተማይቱ ከንቲባ
ሕዝቡን ጸጥ ካደረገ በኋላ ፥ «የኤፌሶን
ከተማ ነዋሪዎች ሆይ ፥ የኤፌሶን ከተማ ፥
ምስሏ ከሰማይ የወረደው ፥ የታላቂቱ አርጤ
ምስ አምልኮ ማዕከል መሆንዋ በመላው
ዓለም የታወቀ ነው። 36 ማንም የፈለገውን
ቢያወራ ይህን የሚክድ ሰው ስለሌለ ፥ እስቲ
ላንዳፍታ ረጋ በሉ፤ በችኮላም ምንም ነገር
አታድርጉ። 37 እነዚህ ያመጣችኋቸው
ሰዎች ከመቅደስ የሰረቁት ዕቃ የለም። የም
ናመልካትን አርጤምስንም አልሰደቡም።
38 ድሜጥሮስና መሰሎቹ አንጥረኞች እነዚ
ህን ሰዎች የሚከሱበት ነገር ካላቸው ፥
ዳኞች በችሎት ላይ ስላሉ ፥ ጉዳዩን ሊያቀር
ቡላቸው ይችላሉ። 39 እናንተም የምታሰሙ
ባቸው ሌላ ጥፋት ካለ ደግሞ ፥ በከተማው
መማክርት ጉባዔ ፊት ቀርቦ ሊታይ ይች
ላል 40 ዛሬ በደረሰው ምክንያት የለሽ፤ ግርግ
ርና ሁከት ፥ ከሮማውያን ባለሥልጣኖች
ዘንድ ጥያቄ ቢቀርብ የምሰጠውን መልስ
አላውቅም!» ብሎ ንግግሩን ደመደመ።
41 ንግግሩንም ከፈጸመ በኋላ ሕዝቡ እን
ዲበተን አደረገ።

## ምዕራፍ 20

1 ሁከቱ እንደ በረደም ጳውሎስ ደቀመዛ
ሙርቱን ሰብስቦ እንዲጽናኑና እንዲበረቱ
ከመከራቸው በኋላ ተሰናብቷቸው ወደ
መቄዶንያ ሄደ። 2 እግረ መንገዱን በሚያል
ፍባቸው ከተሞች የሚገኙትን ክርስቲያኖ
ችም እያጽናናና እያበረታታ ወደ ግሪክ
አገር መጣ። 3 በዚያም ሦስት ወር ቆይቶ
ወደ ሶርያ በመርከብ ለመጓዝ አሰበ። ነገር
ግን በዚያ የሚገኙ አይሁድ እርሱን ለማጥ
ፋት እንደ መከሩበት ስለ ሰማ ፥ አሳቡን
ለውጦ በመቄዶንያ በኩል አድርጎ ለመሄድ
ወሰነ።
4 የቤርያ ተወላጅ የሆነው ሱሲጳጥሮስ ፥
ከተሰሎንቄ የመጡት አርስጥሮኮስና ሲኮን
ዱስ ፥ የደርቤኑ ጋይዮስና ጢሞቴዎስ ፥ ከእስያ
ሰዎች ቲኪቆስና ጥሮፊሞስ አብረውት
ነበሩ። 5 እነርሱም ቀድመው ሄደው በጢሮ
አዳ ቆዩን። 6 እኛ ግን እርሾ ያልገባበት
ቂጣ የሚበላበት በዓል ካለፈ በኋላ ፥ ከፊልጵ
ስዩስ በመርከብ ተሳፍረን አምስት ቀን ተጉ
ዘን ፥ እነርሱ ወዳሉበት ወደ ጢሮአዳ ደረ
ስን። በጢሮአዳም አንድ ሳምንት ቆየን።

7 የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን በሆነው
እሑድ ማታ ፥ እንጀራ አብረን ለመቊረስ
ተሰበሰብን። ጳውሎስ በማግስቱ መሄዱ ስለ
ነበር ፥ ለተሰበሰበው ሕዝብ እስከ እኩለ
ሌሊት ድረስ ንግግር አደረገ። 8 እኛ በተሰበ
ሰብንበት ፎቅ ብዙ መብራት ይበራ ነበር።
9 መስኮት ላይ ተቀምጦ የጳውሎስን ረጅም
ንግግር ያዳምጥ የነበረ አውጤኪስ የሚሉት
ወጣት እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ስለ ወሰ
ደው ፥ ከሦስተኛው ፎቅ ተምዘግዝጎ ወደቀ።
ሰዎች ተሯሩጠው ከወደቀበት ቢያነሡት
ሞቶ አገኙት። 10-12 ጳውሎስም ወርዶ ጎን
በስ ብሎ አቀፈውና ፥ «አይዟችሁ ሕይወቱ
አላለፈችምና አትደንግጡ» ብሎ አጽናና
ቸው። ወዲያውም ወጣቱ ደኅና ሆኖ ዓይ
ኑን ያቁለጨልጭ ጀመር። ሕዝቡም በደ
ስታ ተሞላ፤ ጳውሎስም ከሕዝቡ ጋር ወደ
ፎቅ ተመልሶ የጌታን መታሰቢያ ራት በሕ
ብረት ተካፈሉ። ከዚያም እዚያ ለነበሩት
ሰዎች ሌላ ረጅም ንግግር ሲያደርግ አድሮ
ሊነጋጋ ሲል ተሰናብቶአቸው ሄደ።
13 ጳውሎስን ለመቀበል ስላሰብን እኛ
ቀድመን በመርከብ ወደ አሶን አመራን።
ጳውሎስ በእግሩ ለመሄድ ወስኖ ስለነበር ፥
እኛ በመርከብ ቀድመን ሄድን። 14 አሶን
ላይ ከጳውሎስ ጋር ከተገናኘን በኋላ ፥ አብ
ረን ወደ ሚጢሊኒ በመርከብ ጉዞአችንን
ቀጠልን። 15 በማግስቱም ኪዩ ከተባለው
ቦታ ደረስን። በሁለተኛው ቀን በሳሞን
በኩል አድርገን በሦስተኛው ቀን ላይ ሚሊ
ጢን ደረስን።
16 ጳውሎስ በእስያ ብዙ ጊዜ መቆየት
ስላልፈለገ ፥ በኤፌሶን በኩል ማለፍ አልወደ
ደም። ምክንያቱም ለጰንጠቆስጤ በዓል ኢየ
ሩሳሌም ለመዋል ስለ ፈለገ ተቻኩሎ
ነበር። 17 ስለዚህ ጳውሎስ ከሚሊጢን ወደ
ኤፌሶን ሰው ልኮ ፥ የቤተ ክርስቲያን ሽማግ
ሌዎችን አስጠራቸው።
18 ከመጡም በኋላ እንዲህ አላቸው።
«የታናሽቱን እስያ ምድር ከረገጥኩበት
ዕለት አንሥቶ ፥ ከእናንተ ጋር እንዴት እንደ
ኖርሁ ጥሩ አድርጋችሁ ታውቃላችሁ።
19 አይሁድ እኔን ለመግደል ብዙ ጊዜ እየዶ
ለቱ በመከራ ላይ መከራ ቢያመጡብኝም ፥
ለነፍሴ ሳልሳሳ በፍጹም ትሕትናና እንባዬን
በማፍሰስ ፥ ጌታን አገለግያለሁ። 20 በየቤታች
ሁም ሆነ ፥ በየስብሰባው ቦታ ሳስተምራችሁ
የሚጠቅማችሁን ሁሉ ነግሬአችኋለሁ። ያስ
ቀረሁባችሁ ምንም ነገር የለም። 21 አይሁ
ድም ሆኑ አሕዛብ ንስሐ እንዲገቡና በጌታ

ኢየሱስ እንዲያምኑ አስተምሬአለሁ።
22 «አሁን ወደ ኢየሩሳሌም እንድሄድ
መንፈስ ቅዱስ ስለ አዘዘኝ ይኸው ለመሄድ
ተነሥቻለሁ። በኢየሩሳሌም ምን እንደሚጠ
ብቀኝ ግን በትክክል አላውቅም። 23 ይሁን
እንጂ በየደረስኩባቸው ከተሞች ሁሉ፣ መን
ፈስ ቅዱስ በኢየሩሳሌም እሥራትና መከራ
እንደሚያገኘኝ አስታውቆኛል። 24 ቢሆንም
ከጌታ የተቀበልኳትን መልእክት ለማዳረስ
እጥራለሁ እንጂ፣ የሚጠብቀኝን እሥራትና
መከራ ከምንም አልቆጥረውም። የተሰጠች
ኝም መልእክት የክርስቶስን የፍቅሩን ጽና
ትና የርኅራኄውን ብዛት ላልሰሙት ማሰ
ማት ነው።
25 «እስከ አሁን ድረስ በመካከላችሁ እየ
ተገኘሁ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሳስ
ተምራችሁ ነበር። ካሁን ጀምሮ ግን እንለያ
ያለን። እስከ ወዲያኛውም አንገናኝም።
26-27 ከእግዚአብሔር ቃል ያስቀረሁባችሁ
አንድም ነገር የለም። ሁሉንም አስተምሬአ
ችኋለሁ። ስለዚህ ከመካከላችሁ በጌታ
አምኖ ያልዳነ ቢኖር፣ የራሱ ጥፋት ነው።
እኔ ግን ከደሙ ንጹሕ ነኝ።
28 «ክርስቶስ በደሙ የዋጃትን ቤተ ክር
ስቲያኑን እንድትጠብቁ መንፈስ ቅዱስ እና
ንተን መሪዎች አድርጎ ስለ ሾማችሁ፣ ምዕ
መናንን በሚገባ የመጠበቅና የመንከባከብ
ኃላፊነት አለባችሁ። 29 እኔ ከሄድኩ በኋላ
እንደ ቀበሮ አድብተው ምዕመናንን የሚተ
ናኰሉ ሐሰተኞች መምህራን፣ በመካከላችሁ
እንደሚገቡ ጥሩ አድርጌ አውቃለሁ።
30 ከእናንተው መካከልም ተከታይ ለማግ
ኘት ሲሉ፣ እውነተኛውን ትምህርት እያጣ
መሙ የሚያስተምሩ ሰዎች ይነሣሉ።
31 ከእናንተ ጋር በኖርኩባቸው ሦስት ዓመ
ታት ውስጥ፣ ቀንና ሌሊት እንባዬን እያፈሰ
ስኩ፣ የቱን ያህል እንደመከርኩአችሁና እን
ደገሠፅኩአችሁ እያስታወሳችሁ በጥንቃቄ
ኑሩ።
32 «አሁንም ለእግዚአብሔር፣ እንዲሁም
በእምነት ሊያንጻችሁና በቅዱሳን መካከል
ርስት ሊሰጣችሁ ለሚችል ጸጋ ለሞላበት
ቃሉ፣ እናንተን አደራ ሰጥቻችኋለሁ።
33 «ማንም ሰው ብርና ወርቅ ወይም
ልብስ እንዲሰጠኝ እጅ እጁን እንዳላየሁ
ራሳችሁ ታውቃላችሁ። 34 እንደዚሁም በእ
ጆቼ ሠርቼ ራሴንም ሆነ አብረውኝ የነበሩ
ትን እረዳ ነበር እንጂ፣ ማንንም እንዳላስቸገ
ርኩ ከእናንተ የተሰወረ አይደለም። 35 'ከመ
ቀበል ይልቅ መስጠት ብዙ በረከት አለበት'
ሲል ጌታ የተናገረውን ቃል በማስታወስ፣
ሠርታችሁ በምታገኙት ገቢ ደካሞችን መር
ዳት እንዴት እንደሚገባ፣ ራሴ ምሳሌ ሆኜ
በየጊዜው ያሳየኋችሁ ስለሆነ፣ ይህንኑ ከመፈ
ጸም ቸል አትበሉ።»
36 ጳውሎስ ንግግሩን ሲጨርስ አብሮአ
ቸው ተንበርክኮ ጸለየ። 37 እነርሱም አቅ
ፈው እየሳሙ ሲሰናበቱት፣ ስቅስቅ ብለው
ያለቅሱ ነበር። 38 ይልቁንም፣ «እስከ ወዲያ
ኛው አንገናኝም» ብሎ ስለ ተናገረ እጅግ
አዘኑ። ከዚያም በኋላ እስከ መርከቡ መግ
ቢያ ድረስ ሸኝተውት ተመለሱ።

## ምዕራፍ 21

1 የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌ
ዎች ተሰነባብተን ከተለያየን በኋላ፣ በቀጥታ
ወደ ቆስ ሄድን። በማግስቱም ሩድ፣ ከዚያም
ወደ ጳጥራ ደረስን። 2 ከጳጥራ ወደ ፊንቄ
የሚሄድ መርከብ ስላገኘን፣ በዚሁ መርከብ
ተሳፍረን ጉዞ ቀጠልን። 3 የቆጵሮስን ደሴት
በስተግራችን እየተውን፣ የሶርያ ወደብ ወደ
ሆነችው ወደ ጢሮስ አመራን። የምንጓዝ
በት መርከብም ጭነቱን ጢሮስ አራገፈ።
4 በጢሮስ የሚኖሩትን ምዕመናን ፈልገን
ካገኘን በኋላ ፣ ከእነርሱ ጋር ሰባት ቀን
ቆየን። እነርሱም በመንፈስ ሆነው፣ ጳውሎስ
ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ አስጠነቀቁት።
5 ጉዞአችንን የምንቀጥልበትም ዕለት ሲደ
ርስ፣ ሴቶችና ሕፃናት እንኳ ሳይቀሩ ምዕመ
ናኑ ሁሉ፣ እስከ ባሕሩ ዳርቻ ድረስ ሸኙን።
ከባሕሩ ዳር አብረን ተንበርክከን ጸለይንና
ተሰነባብተን ተለያየን። 6 ከዚያም እኛ በመ
ርከብ ተሳፍረን ጉዞአችንን ስንቀጥል ፣ እነ
ርሱ ወደ የቤታቸው ተመለሱ።
7 ከጢሮስ ተጉዘን ወደ ጰጢሌማይስ
እንደ ደረስን፣ በዚያ የሚኖሩትን ምዕመናን
ፈልገን አገኘናቸው። አንድ ቀን ብቻ አብረ
ናቸው ውለን ካደርን በኋላ ፣ 8 በማግስቱ
ወደ ቂሣርያ ሄድን። ከሰባቱ ዲያቆናት
አንዱ የሆነው ፣ ወንጌላዊው ፊልጶስ እዚያ
ይኖር ስለነበረ ፣ ወደ እርሱ ቤት ገባን።
9 ፊልጶስ ትንቢት የመናገር ስጦታ ያላቸው
አራት ያላገቡ ሴት ልጆች ነበሩት።
10 በፊልጶስ ቤት ብዙ ቀኖች ቆየን።
እዚያ በቆየንባቸውም ዕለታት፣ ትንቢት የመ
ናገር ስጦታ ያለው አንድ አጋቦስ የተባለ
ሰው ከይሁዳ መጣ። 11 እርሱም ወደ ነበርን
በት ቤት ገብቶ የጳውሎስን መታጠቂያ ስቅ
ወስዶ የራሱን እጅና እግር በማሠር፣ «መን
ፈስ ቅዱስ የዚህን መታጠቂያ ባለቤት፣ አይ

ሁድ በኢየሩሳሌም እንደዚህ አድርገው
አሥረው ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታል
ይላል» በማለት ትንቢት ተናገረ።
12 ይህንንም ስንሰማ እኛና እዚያ የነበ
ሩት ምዕመናን ሁሉ፣ጳውሎስን ወደ ኢየሩ
ሳሌም እንዳይሄድ አጥብቀን ለመንነው።
13 ጳውሎስ ግን፣ «እንዲህ እያለቀሳችሁ
ለምን ልቤን በኀዘን ታስጨንቁታላችሁ።
እኔ እንደሆንኩ በኢየሩሳሌም ለመታሠር
ብቻ ሳይሆን፣ስለ ጌታ ኢየሱስ ስም ለመሞ
ትም ጭምር ተዘጋጅቻለሁ። እባካችሁ አታ
ስቸግሩኝ» ሲል መለሰ። 14 ጳውሎስ ወደ
ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ፣ብንለው ብናረገው
ፈቃደኛ አልሆነም። ከዚያም፣ «የእግዚአብ
ሔር ፈቃድ ይሁን» ብለን ነገሩን ተው
ነው።
15 ከዚህ በኋላ ዕቃችንን አዘጋጅተን
ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ ቀጠልን። 16 ከቂሣር
ያም ጥቂት ምዕመናን ተከተሉን። እነር
ሱም ወደ ምናሶን ቤት ወሰዱን። ምናሶን
ቀደም ብሎ በጌታ ኢየሱስ ያመነ የቆጵሮስ
ተወላጅ ነበር። 17 ኢየሩሳሌም ስንደርስ ክር
ስቲያን ወንድሞቻችን፣ «እንኳን ደኅና
መጣችሁ» እያሉ የጋለ አቀባበል አደረጉ
ልን።
18 በማግስቱም ጳውሎስ፣ያዕቆብንና የኢ
የሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን
ለመገናኘት ይዞን ሄደ። 19 ከሰላምታ በኋ
ላም፣እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል በእ
ርሱ አማካይነት ስለ አደረገው ነገር በሰ
ፊው አወጋቸው።
20 እነርሱም ጳውሎስ ስለ ነገራቸው
ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ። በኋላ
ግን እንዲህ አሉት። «ወንድማችን ሆይ፣ከአ
ይሁድ መካከል በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች
በጌታ በኢየሱስ እንዳመኑ ታውቃለህ። ነገር
ግን እነርሱ፣ 'የአይሁድ ሕግና ሥርዓት እን
ዳለ መጠበቅ አለበት' ብለው ለሙሴ ሕግ
በጣም የሚቀኑ ናቸው። 21 አንተ ደግሞ
ከዚህ በፊት በአሕዛብ መካከል የሚኖሩትን
በጌታ ያመኑትን አይሁድ፣ 'ልጆቻችሁን
ብትገርዙዋቸው አይጠቀሙም፤ ባትገርዙዋ
ቸውም አይጎዱም' እያልክ በማስተማር
የሙሴን ሕግ ሥርዓት እንዲሽሩ ታደርጋለህ
ተብሎ እዚህ ተወርቶብሃል። 22 መቼም
አሁን እዚህ መምጣትህን መስማታቸው
የማይቀር ነገር ነው። ታዲያ ምን ማድረግ
ይሻል ይመስልሃል?
23 «ስለዚህ አንድ ነገር ብታደርግስ?
እንደ አይሁድ ሥርዓት ስለት ያለባቸው
አራት ሰዎች እዚህ እኛ ዘንድ አሉ።
24 የሙሴን ሕግ ሥርዓት የማትቃወም መሆ
ንህ እንዲታወቅ፣ወደ ቤተ መቅደስ ሂድና
በሙሴ ሕግ መሠረት አብረሃቸው ጠጉርህን
ተላጭ። ጠጉራቸውንም ለመላጨት የሚጠ
የቀውን ገንዘብ አንተው ክፈልላቸው። ይህ
ንንም ያየ ሁሉ ባንተ ላይ የተወራብህ ሁሉ
ውሸት መሆኑን ይረዳል። አንተ ራስህ የሙ
ሴን ሕግ ሥርዓት ስትፈጽም ሲያዩ፣ከእነ
ርሱ ያልተለየህ መሆንህን ያምናሉ። በዚ
ህም ነገሩን ማብረድ ይቻላል። 25 «ከአሕ
ዛብ ወገን በክርስቶስ ያመኑትን ግን፣ 'የአይ
ሁድን ሥርዓት መጠበቅ አለባችሁ' ብለን
አናስገድዳቸውም። ከዚህ በፊት ለጣዖት
የተሠዋ እንስሳ ሥጋ፣ታንቆ የሞተ እንስሳ
ሥጋ፣እንዲሁም የእንስሳ ደም እንዳይበሉና
ከዝሙት እንዲርቁ ያስተላለፍነውን ውሳኔ
መጠበቃቸው በቂ ነው።»
26-27 ጳውሎስም በማግስቱ አራቱን
ሰዎች ይዞ መንጻት ጀመረ። ከዚያም የመን
ጻቱን ሥርዓት የሚፈጽሙበትንና ለያንዳንዳ
ቸው መሥዋዕቱን የሚያቀርቡበትን ቀን
ለማስታወቅ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ። ሰባቱን
ቀን ለመጨረስ ጥቂት ሲቀራቸው ግን፣ከእ
ስያ የመጡ አይሁድ ጳውሎስን በቤተ መቅ
ደስ ውስጥ በማየታቸው ሕዝቡን ሁሉ በማ
ነሣሣት፣ከበው ያዙት። 28 «እናንተ የእሥ
ራኤል ሰዎች፣ወጥታችሁ እርዱን! በየአገሩ
እየዞረ የአይሁድን ሕዝብ፣ የአይሁድን
ሕግና ቤተመቅደስ እየተቃወመና እያራከሰ
የሚያስተምረው ሰው እዚህ ገብቶላችኋል!
ይባስ ብሎ ደግሞ ይኸው አሕዛብን እስከ
ቤተ መቅደስ በማስገባት የተቀደሰውን
ሥፍራ አርክሶታል» አሉ። 29 እንዲህ ያሉበ
ትም ምክንያት ቀደም ሲል ጳውሎስን የኤ
ፌሶን ተወላጅ ከሆነው ከጥሮፊሞስ ጋር
ከተማ ውስጥ አይተውት ነበርና፣እርሱን
ይዞ ወደ ቤተ መቅደስ የገባ መስሏቸው ስለ
ነበር ነው።
30-31 ከዚህ የተነሣም ከተማይቱ በሙሉ
ታወከች፤ ተሸበረች። ሕዝቡም እንዳለ
ወጥቶ ጳውሎስን ከቤተ መቅደስ ጎትቶ አወ
ጣው። የቤተ መቅደሱን አጥር በር ዘግተው
ደብድበው ሊገድሉት ሲሉ፣ የሮማውያን
ጸጥታ አስከባሪ ኃይል አዛዥ በከተማው
ውስጥ የተነሣውን ግርግርና ውካታ እንደ
ሰማ፣ 32 ወታደሮቹን አስከትሎ በፍጥነት
ደረሰ። ሰዎቹም የጸጥታ አስከባሪውን ኃይል
አዛዥ ባዩ ጊዜ፣ጳውሎስን መደብደባቸውን
አቆሙ። 33 የጸጥታ ጥበቃ ኃይል አዛዡም

ጳውሎስ በሁለት ሰንሰለት እንዲታሠር
አዘዘ። ከዚህ በኋላም ማን መሆኑንና ምን
እንዳደረገ ሕዝቡን ጠየቀ። 34 ግን አንዱ
አንድ ነገር ሲናገር፥ሌላው ደግሞ ሌላ ነገር
እየተናገረ መደማመጥ አልተቻለም። አዛ
ዡም በዚህ ጫጫታና ድብልቅልቅ መካ
ከል እርግጠኛውን ነገር ማወቅ ስለተሳነው፥
ጳውሎስ ወደ ወታደሮች ጦር ሠፈር እንዲ
ወሰድ ትእዛዝ ሰጠ። 35 ጳውሎስም ከቤተ
መቅደሱ ግቢ መውጫ ደረጃዎች አጠገብ
ሲደርስ ሰዎቹ ሊገድሉት አሰፍስፈው ስለ
ተነሡ፥ወታደሮቹ በትከሻቸው ላይ ተሸክ
መው አወጡት። 36 ያም ሆኖ ሰዎቹ በቀ
ላሉ የሚመለሱ አልነበሩም። ከኋላ ኋላ እየ
ተከተሉ፥ «መገደል አለበት! መገደል አለ
በት!» እያሉ ይጮኹ ነበር።

37-38 ወደ ወታደሮቹ ሠፈር ለመግባት
ጥቂት ሲቀራቸው፥ጳውሎስ የጸጥታ ጥበቃ
ኃይል አዛዡን፥ «አንድ ቃል ብቻ እንዳናግ
ርህ ብትፈቅድልኝ?» ሲል በግሪክ ቋንቋ
ጠየቀው።

የጸጥታ ጥበቃ ኃይል አዛዡም፥ «የግሪክ
ቋንቋ መናገር ትችላለህ እንዴ? አሁን በቀ
ርቡ አራት ሺህ ነፍሰ ገዳዮችን ይዞ በረሃ
የገባው ግብፃዊ አንተ አይደለህም?» ሲል
ጠየቀው።

39 ጳውሎስም፥ «እኔ አይደለሁም። እኔ
በኪልቅያ አውራጃ በምትገኘው በጠርሴስ
ተወልጄ ያደግሁ አይሁዳዊ ነኝ። ለሕዝቡ
ንግግር እንዳደርግ እባክህ ፍቀድልኝ?»
አለው።

40 ንግግር እንዲያደርግ ከተፈቀደለት
በኋላ፥ደረጃው ላይ ቆሞ ሕዝቡ መንጫጫ
ቱን እንዲያቆም በእጁ ምልክት አሳየ።
ሕዝቡም ጸጥ እንዳለ፥ጳውሎስ በዕብራይስጥ
ቋንቋ የሚከተለውን ንግግር አደረገ።

## ምዕራፍ 22

1 «ወንድሞቼና አባቶቼ፥ለቀረበብኝ ክስ
የምሰጠውን የመከላከያ መልስ አድምጡ።»
2 ጳውሎስ በዕብራይስጥ ቋንቋ በመናገሩ
ሕዝቡ ከበፊቱ ይልቅ ጸጥ ብሎ ያዳምጠው
ጀመር። እርሱም እንዲህ ሲል ንግግሩን
ቀጠለ። 3 «እኔ በኪልቅያ ግዛት በምትገ
ኘው በጠርሴስ ከተማ የተወለድሁ አይሁ
ዳዊ ነኝ። ጠርሴስ ብወለድም ያደግሁት
በዚችው በኢየሩሳሌም ከተማ ነው። ከታወ
ቀው መምህር ከገማልያል እግር ሥር ተቀ
ምጬ፥የአይሁድን ሕግና ሥርዓት ጠንቅቄ
ተምሬአለሁ። ዛሬ እናንተ ስለ እግዚአብ
ሔር እንደምትቀኑ፥እኔም ያን ጊዜ ስለ
እርሱ እቀና ነበር። ለሃይማኖታችንም ከፍ
ያለ ቅንዓት ነበረኝ። 4 እግዚአብሔርንም
ያስደሰትኩ መስሎኝ ክርስቲያኖችን ወንድ
ሴት ሳልል እስከ ሞት ድረስ አሳድጃአቸዋ
ለሁ፤ብዙዎቹንም ወህኒ ቤት እንዲገቡ አድ
ርጌአለሁ። 5 ይህ ደግሞ እውነት መሆኑን፥
ሊቀ ካህናቱና የአይሁድ ሸንጎ አባላት
በሙሉ የሚያውቁት ነው። ምክንያቱም፥
እነርሱ ራሳቸው ክርስቲያኖችን አሣስሬ
ወደ ኢየሩሳሌም እንዳመጣ ወደ ደማስቆ
ስሄድ፥በዚያ የሚገኙት የምኩራብ ኃላፊ
ዎች እንዲተባበሩኝ የአደራ ደብዳቤ ጽፈ
ውልኝ ነበርና ነው።

6 «ለዚሁ ዓላማ ወደ ደማስቆ ስሄድ፥
ከቀኑ ስድስት ሰዓት ገደማ፥ድንገት ታላቅ
ብርሃን ከሰማይ በራብኝ። 7 መሬት ላይ በግ
ንባሬ ተደፍቼ ሳለሁ፥ 'ሳውል፥ሳውል!
ለምን ታሳድደኛለህ?' የሚል ድምፅ
ሰማሁ።

8 «እኔም፥ ጌታ ሆይ፥ 'ለመሆኑ አንተ
ማን ነህ?' አልኩ። እርሱም፥ 'አንተ የምታ
ሳድደኝ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነኝ' አለኝ።
9 አብረውኝ ወደ ደማስቆ ይሄዱ የነበሩት
ሰዎች፥በዙሪያችን የፈሰሰውን ብርሃን ከማ
የት በስተቀር ድምፁን አልሰሙም።

10 «እኔም፥ 'ጌታ ሆይ፥ታዲያ ምን ላድ
ርግ?' አልሁት። ጌታም፥ 'ተነሣና ወደ
ደማስቆ ሂድ። ምን ማድረግ እንደሚገባህም
እዚያው ይነገርሃል' አለኝ። 11 ከአየሁት
ታላቅ ብርሃን የተነሣ ዓይኖቼ ስለታወሩ፥
አብረውኝ የነበሩት ሰዎች እየመሩ እስከ
ደማስቆ አደረሱኝ።

12 «ደማስቆ እንደ ደረስኩም፥ ሐናንያ
የሚባል ሰው ሊፈልገኝ መጣ። ሐናንያ
ደማስቆ ውስጥ የሚኖሩ አይሁድ የሚያከብ
ሩት መንፈሳዊ ሰው ነበር። 13 እርሱም አጠ
ገቤ ቆሞ፥ 'ወንድሜ ሳውል ሆይ፥ዓይኖችህ
ይብሩልህ!' አለኝ። ወዲያውኑም በሩልኝ።
ሐናንያንም አጠገቤ ቆሞ አየሁት።

14 «ሐናንያም፥ 'የአባቶቻችን አምላክ
ፈቃዱን እንድታውቅ፥ጻድቁን ጌታ እንድታ
ይና ድምፁን እንድትሰማ መርጦሃል።
15 ስለዚህ ያየኸውንና የሰማኸውን ሁሉ ለሌ
ሎች ታስታውቃለህ። 16 በል አሁንም ቶሎ
ተነሣና የጌታ የኢየሱስን ስም በመጥራት
ተጠመቅ፤ከኃጢአትህም ንጻ' አለኝ።

17-18 «ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሼ ከመ
ጣሁ በኋላም ቤተ መቅደስ ገብቼ ስጸልይ፥

ጌታ በራእይ ተገልጦ፣ 'እነዚህ ሰዎች ስለ
እኔ የምትሰጠውን ምስክርነት ስለማይቀበሉ
ትተሃቸው ፈጥነህ ከኢየሩሳሌም ውጣ'
ብሎ አዘዘኝ።
19 «እኔም፣ 'ጌታ ሆይ፣ በስምህ ያመኑ
ትን ክርስቲያኖች ከምኵራብ እያወጣሁ
እንደ ደበደብኩና እንዳሣሠርኩ እነርሱ
ራሳቸው ያውቃሉ። 20 የአንተ ምስክር የነበ
ረው እስጢፋኖስ በተገደለ ጊዜም እኔ የወን
ጀሉ ተባባሪ ሆኜ፣ የገዳዮቹን ልብስ ቆሜ
ጠብቄአለሁ። በደለኛ እኮ ነኝ' አልኩት።
21 «ጌታም መልሶ፣ 'በሩቅ ወዳሉ አሕ
ዛብ እልክሃለሁና ከኢየሩሳሌም ውጣ'
አለኝ።»
22 ጸጥ ብለው ያዳምጡ የነበሩት ሰዎች
'አሕዛብ' የሚለውን ቃል እንደሰሙ፣ «እን
ደዚህ ያለው አመፀኛ በሕይወት መኖር
አይገባውም፤ ወዲያ ግደሉት!» እያሉ ተን
ጫጩ። 23 በንዴት ልብሳቸውን እያወለቁ
ያውለበልቡ፣ አቧራም ወደ ሰማይ ይበትኑ
ጀመር።
24 ስለዚህ የጸጥታ ጥበቃ ኃይል አዛዡ፣
በጳውሎስ ላይ አደጋ እንዳያደርሱበት ስለ
ሠጋ፣ «ወደ ሠፈር ውሰዱት» ብሎ አዘዘ።
ይሁን እንጂ ሕዝቡ እንደዚያ የሚንጫጫበ
ትን ምክንያት ማወቅ ስለፈለገ ጳውሎስ እየ
ተገረፈ እንዲመረመር ተጨማሪ ትእዛዝ
ሰጠ።
25 ጳውሎስም ሊገርፉት ሲያሥሩት፣ አጠ
ገቡ ቆሞ የነበረውን መኰንን፣ «እንዴት
ነው ጕበዝ! እንዲያው ለመሆኑ አንድ
የሮማ ዜጋ ወንጀል መፈጸም አለመፈጸሙ
ሳይረጋገጥ፣ ያለ ፍርድ እንድትገርፉት ሥል
ጣን ተሰጥቷችኋል?» ሲል ጠየቀው።
26 መኰንኑም ወዲያውኑ ወደ አዛዡ
ሄደ። «ኧረ ጉድ ፈላ! ይህ ሰው 'የሮም
ዜጋ ነኝ' ይላል!» አለው።
27 አዛዡም ወደ ጳውሎስ ቀርቦ፣
«ሮማዊ ነህ እንዴ?» ብሎ ጠየቀው።
ጳውሎስም፣ «አዎን ነኝ» ሲል መለሰ
ለት።
28 አዛዡም፣ «እኔ የሮምን ዜግነት ያገኘ
ሁት እንዲህ በቀላሉ አይደለም። ብዙ ገን
ዘብ ከስክሼ ነው» አለ።
ጳውሎስም፣ «እኔ ግን ምንም ገንዘብ
አላወጣሁበትም፤ ጠርሴስ ተወልጄ በማደጌ
ብቻ ያገኘሁት ዜግነት ነው» አለው።
29 ጳውሎስን እየገረፉ ለመመርመር አሰ
ፍስፈው የነበሩት ወታደሮችም፣ ሮማዊ
መሆኑን ሲሰሙ ከአጠገቡ ገለል አሉ። የጸ
ጥታ ጥበቃ ኃይል አዛዡም፣ የሮም ዜግነት
ያለውን ሰው ነገር ሳያጣራ፣ እጁን በሰንሰ
ለት በማሠሩ ፈራ።
30 በማግስቱም አዛዡ ጳውሎስ የታሠረበ
ትን ሰንሰለት አስወለቀለት። አይሁድ ለምን
እንደሚከሱት ማወቅ ስለ ፈለገ፣ ሊቀ ካህና
ቱንና የከፍተኛውን የአይሁድ ሸንጎ አባላት
ለስብሰባ ጠራ። ስብሰባውም እንደተጀመረ፣
ጳውሎስን አምጥቶ በፊታቸው አቁሞ ሁኔ
ታው እንዲጣራ አደረገ።

## ምዕራፍ 23

1 ጳውሎስ የአይሁድን ከፍተኛ ሸንጎ
አባላት ትኩር ብሎ እየተመለከተ፣ «ወንድ
ሞቼ ሆይ፣ እስከዚች ቀን እግዚአብሔር እን
ዳደርግ ያዘዘኝን ሁሉ ፈጽሜአለሁ፤ ሕሊና
ዬም አይወቅሰኝም» ብሎ ንግግሩን ሲጀ
ምር፣ 2 ሊቀ ካህናቱ ሐናንያ በጳውሎስ
አጠገብ የቆሙትን ሰዎች፣ «ዝም ትሉታላ
ችሁ? በጥፊ አትሉትም?» ሲል እንዲመ
ቱት አዘዘ። 3 በዚህ ጊዜ ጳውሎስ ሊቀ ካህ
ናቱን፣ «አንተ በኖራ የተለሰነ ግድግዳ የም
ትመስል ግብዝ! በሕጉ መሠረት ለመፍረድ
ተቀምጠህ፣ እንዴት ያለ ሕግ እንዲመቱኝ
ታዛለህ? እኔን እንዳስመታኸኝ፣ አንተንም
ደግሞ እግዚአብሔር ይመታሃል» አለው።
4 በጳውሎስ አጠገብ የነበሩትም ሰዎች፣
«እንዴት እንዲህ ብትደፍር ነው፣ እግዚአብ
ሔር የሾመውን ሊቀ ካህናት እንዲህ አድር
ገህ የምትሳደበው?» አሉት።
5 ጳውሎስም፣ «ይቅርታ አድርጉልኝ፤
ሊቀ ካህናት መሆኑን አላወቅሁም ነበር።
'በሕዝብህ አለቃ ላይ ክፉ አትናገር'
ተብሎ በመጽሐፍ ተጽፎአልና ለወደፊቱ
አይለምደኝም» ሲል መለሰ።
6 በዚያ የነበሩትም ግማሾቹ፣ ፈሪሳውያን
ግማሾቹ ደግሞ ሰዱቃውያን ነበሩ። ጳውሎ
ስም በመካከላቸው ልዩነት መኖሩን ስለሚ
ያውቅ፣ «ወንድሞቼ ሆይ፣ እኔ የፈሪሳዊ
ልጅ ፈሪሳዊ ነኝ። አሁን እዚህ ለፍርድ የቀ
ረብኩት፣ በሃይማኖታችን ትምህርት መሠ
ረት የሙታን ትንሣኤ መኖሩን በማመኔ
ነው» አለ።
7 ጳውሎስ የተናገረው ይህ ነገር፣ የሸንጎ
ውን አባላት እርስ በርሳቸው አጋጭቶ ለሁ
ለት ከፈላቸው። ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያ
ንም እርስ በርስ ይከራከሩ ጀመር። 8 ምክን
ያቱም ሰዱቃውያን፣ «የሙታን ትንሣኤ
የለም፤ መላእክትና መንፈስ የሚባል ነገርም
የለም» ሲሉ፣ ፈሪሳውያን ግን እነዚህ ነገ

ሮች ሁሉ መኖራቸውን ያምኑ ነበር።
9 ስለዚህ፥ «ጳውሎስ የተናገረው ትክክል
ነው፤ትክክል አይደለም» በማለት ሲከራከሩ
ውካታው ሌላ ነገር ሆነ። ከፈሪሳውያን
ወገን የነበሩ ጥቂት የአይሁድ ሃይማኖት
መምህራን ተነሥተው፥ «ይህ ሰው ምንም
ጥፋት የለበትም። በደማስቆ መንገድ ያናገ
ረው መልአክ ወይም መንፈስ ሊሆን ይች
ላል። ስለዚህ የምናውቀው ምንም ነገር
የለም» ሲሉ ነገሩን አቃለሉት።
10 እርስ በእርሳቸው ሲነታረኩ ክርክሩ
ወደ ከረረ ጠብ እየተለወጠ ሄዶ፥ከአስጊ
ደረጃ ላይ ስለ ደረሰ አዛዡ፥ ጳውሎስን
ይዘው እንዳይዘነጣጥሉት ፈራ። ስለዚህም፥
«ይህን ሰው ከመካከላቸው አውጥታችሁ
ወደ ሠፈር ውሰዱት» ብሎ ወታደሮቹን
አዘዘ።
11 በዚያንም ሌሊት ጌታ ጳውሎስ አጠ
ገብ ቆሞ፥ «አገልጋዬ ጳውሎስ፥አይዞህ አት
ፍራ! በኢየሩሳሌም እንዲሁ እንደ መሰከርክ
ልኝ ሁሉ፥እንደዚሁም በሮም ትመሰክርል
ኛለህ» አለው።
12-13 ሲነጋም ቁጥራቸው ከአርባ በላይ
የሆነ የአይሁድ ተወላጆች ተሰብስበው
«ጳውሎስን ካልገደልን በቀር፥እህልና ውኃ
አንቀምስም» ተባብለው ተማማሉ።
14-15 እነርሱም ወደ ሊቀ ካህናቱና ወደ
አገር ሽማግሌዎች ቀርበው፥ «ጳውሎስን
ሳንገድል እህልና ውኃ ላንቀምስ ተማምለና
ልና ጳውሎስን ለምርመራ ወደ እናንተ እን
ዲልከው አዛዡን ጠይቁት። እኛም እናንተ
ዘንድ ከመድረሱ በፊት መንገድ ላይ አድፍ
ጠን እንገድለዋለን» አሉአቸው።
16 አይሁድ በዚህ ዓይነት መንገድ ጳው
ሎስን ለመግደል ቆርጠው መነሣታቸውን
የጳውሎስ የእኅቱ ልጅ እንደሰማ፥ወደ ወታ
ደሮች ሠፈር ሄዶ ጉዳዩን በዝርዝር ለጳው
ሎስ ነገረው።
17 ጳውሎስም ከመኰንኖቹ አንዱን
ጠርቶ፥ «ይህ ልጅ ለአዛዡ የሚነግረው
ብርቱ ጉዳይ ስላለው፥ ወደ እርሱ አድር
ሰው» ሲል ለመነው። 18 መኰንኑም ልጁን
አዛዡ ፊት አቅርቦ፥ «ይህ ወጣት የሚያነጋ
ግርህ ጉዳይ ስላለው ወዳንተ እንዳስገባው
ጳውሎስ ጠየቀኝ» አለው።
19 አዛዡም የልጁን እጅ በመያዝ ከሰው
ገለል አድርጎ «በል እስቲ የምትነግረኝ
ምንድን ነው?» ሲል ለብቻው ጠየቀው።
20 ልጁም፥ «ነገ አይሁዶች ‘ጳውሎስን
ለጥያቄ ስለምንፈልገው ከፊታችን እንዲቀ
ርብ ላከው’ ብለው ሊጠይቁህ ይመጣሉ።
21 አንተ ግን፥ እሺ ብለህ እንዳትልከው።
ምክንያቱም ከመካከላቸው ከአርባ በላይ
የሆኑ ሰዎች ‘ጳውሎስን ካልገደልን እህል
አንበላም፥ውኃም አንጠጣም’ ብለው ተማ
ምለዋል። ስለዚህ ወደ እነርሱ የምትልከው
ከሆነ መንገድ ላይ አድፍጠው ይገድሉ
ታል» ሲል ነገረው።
22 አዛዡም ልጁን፥ «ይህን ነገር ለእኔ
መንገርህን ሌላ ሰው አይስማው» ብሎ አሰ
ጠንቀቀው። 23 ከዚህ በኋላ ከመኰንኖቹ
ሁለቱን ጠርቶ፥ «ዛሬ ከምሽቱ በሦስት
ሰዓት፥ወደ ቂሣርያ የሚሄዱ ሁለት መቶ
መሣሪያ የታጠቁ፥ሁለት መቶ ጦር የያዙ፥
ሰባ ፈረሰኞች አዘጋጁ። 24 ለጳውሎስም
ፈረስ ይጫንለት። ከዚያም ወደ አስተዳዳ
ሪው ወደ ፊልክስ ዘንድ ያድርሱት» ሲል
አዘዛቸው። 25 የሚከተለውንም ደብዳቤ
ጻፈ።
26 «ከቀላውዴዎስ ሉስዮስ ለክቡር ፊል
ክስ፥
«ሰላም ለአንተ ይሁን።
27 «ይህን ሰው አይሁድ ይዘው ሊገድ
ሉት ሲሉ ወታደሮች ልኬ አዳንኩት።
ይህን ያደረግሁት የሮማ ዜጋ መሆኑን ስለ
ደረስኩበት ነው። 28 ጥፋቱንም ለማወቅ
ፈልጌ ወደ አይሁድ ሸንጎ አቅርቤው
ነበር። 29 ክሳቸው ግን ‘የሃይማኖት ሕጋች
ንን ይቃወማል’ የሚል እንጂ፥ ለሞት
ወይም ለእሥራት የሚያበቃው አይደለም።
30 በመንገድ ላይ አድብተው ሊገድሉት
መክረው መጨረሳቸውን ስለደረስኩበትም፥
ይኸው ወደ አንተ ልኬዋለሁ። ከሳሾቹ በክ
ርክሩ እንገፋበታለን የሚሉ ከሆነ ግን፥
አንተ ፊት እንዲቀርቡ ነግሬያቸዋለሁ።»
31 ወታደሮቹም በታዘዙት መሠረት ጳው
ሎስን በጠፍ ጨረቃ እስከ አንቲጳጥሪስ
ድረስ ሸኙት። 32 ሲነጋም ፈረሰኞቹ ጳውሎ
ስን ቂሣሪያ እንዲያደርሱት አድርገው፥እግ
ረኞቹ ወታደሮች ወደ ሠፈራቸው ተመ
ለሱ።
33 ፈረሰኞቹ ቂሣርያ እንደደረሱ ጳውሎ
ስን ወደ ዋና አስተዳዳሪው አቅርበው፥ከቀላ
ውዴዎስ ሉስዮስ ከተላከው ደብዳቤ ጋር
አስረከቡት። 34 እሱም ደብዳቤውን ካነበበ
በኋላ ጳውሎስን፥ «የየት አገር ሰው ነህ?»
ሲል ጠየቀው። ጳውሎስም የኪልቅያ ተወ
ላጅ መሆኑን ነገረው። 35 ከዚያም፥ «መል
ካም ነው፤ጉዳይህ ከሳሾችህ ሲመጡ እነሱ
ባሉበት ይታያል» ብሎ በሄሮድስ ቤተ መን

ግሥት ውስጥ በሚገኘው እሥር ቤት እንዲ
ቆይ አዘዘ።

## ምዕራፍ 24

1 ከአምስት ቀን በኋላ ሊቀ ካህናቱ ሐና
ንያ፥ ከአገር ሽማግሌዎች ጥቂቶቹን አስከ
ትሎ ጠርጠሉስ የተባለውን ጠበቃ ይዞ፥
ጳውሎስን ለመክሰስ ወደ ቂሣርያ ወረደ።
2 ጠርጠሉስም ጳውሎስን በአስተዳዳሪው
ፊት እንዲህ ሲል ከሰሰው።
«ክቡር ፊልክስ፥ አንተ አስተዳዳሪያችን
ሆነህ ከተሾምክበት ጊዜ ጀምሮ ፍጹም
የሆነ ሰላም አግኝተናል። ለሕዝባችንም ኑሮ
ጠቃሚ የሆኑ ብዙ ተግባሮች ተፈጽመ
ዋል። 3 ስለነዚህ ነገሮች ሁሉ ከፍ ያለ ምስ
ጋና አቀርባለሁ። 4 ከዚህ ቀጥዬም በዚህ
ሰው ላይ ያለንን ክስ አሳጥሬ ስለማቀርብ፥
ሳትሰለች በትዕግሥት እንድታዳምጠኝ እለ
ምንሃለሁ። 5 ይህ ሰው በየአገሩ እየዞረ በአይ
ሁድ መካከል ከፍተኛ ሁከትና ብጥብጥ
ሲፈጥር ቆይቷል። በዚህም ላይ የሮም መን
ግሥት ተቀናቃኝ የሆኑት፥የናዝራዊው ኢየ
ሱስ ተከታዮች ዋና መሪ ነው። 6 ቤተ መቅ
ደሳችንን ለማርከስ ሲሞክር እጅ ከፍንጅ
ያዝነው። 7 ሆኖም የጸጥታ ጥበቃ ኃይል
አዛዡ ሉስዮስ፥ መጥቶ ከእጃችን በኃይል
ነጥቆ ወደዚህ ላከው። 8 እኛም በነገሩ የም
ንገፋበት ከሆነ፥ከፊትህ ቀርበን በሮማውያን
ሕግ መሠረት ክስ አቅርበን፥ ክርክራችንን
እንድንቀጥል ስላዘዘን ይኸው መጥተናል።
ይህ ያቀረብነው ክስ ትክክል መሆኑንም
አንተው ራስህ አሁን ስትጠይቀው ልትደር
ስበት ትችላለህ።»
9 በዚያ የነበሩ አይሁድም፥ «ቃሉ ቃላ
ችን ነው» ብለው ክሱን በአንድ ድምፅ
ደገፉ።
10 አስተዳዳሪውም ጳውሎስ ለቀረበበት
ክስ መልስ እንዲሰጥ በእጁ ምልክት አሳ
የው። ጳውሎስም የሚከተለውን የመከላከያ
መልስ አቀረበ።
«ክቡር አስተዳዳሪያችን ሆይ፥ ይህን
ሕዝብ ለብዙ ዓመታት ማስተዳደርህን ስለ
ማውቅ በፊትህ ቆሜ የመከላከያ መልሴን
ሳቀርበ ደስ ይለኛል። 11 በቤተ መቅደስ
ውስጥ የአምልኮት ሥርዓት ለመፈጸም ወደ
ኢየሩሳሌም ከመጣሁ አሥራ ሁለት ቀን
እንደማይበልጥ፥ አንተው ራስህ ማረጋገጥ
ትችላለህ። 12 በየትኛውም ከተማ ወይም
የአይሁድ ምኵራብ ውስጥ፥ ሁከት ሳስነሣ
ወይም ሕዝብን ወደ አመፅ ስገፋፋ፥ያገኘኝ
ሰው የለም። 13 አሁን ይህንንም ያንንም
ሲያደርግ አግኝተነዋል፥ ብለው ላቀረቡብኝ
ክስ ሁሉ አንዳችም ማስረጃ ለማቅረብ የሚ
ችሉ አይደሉም።
14-15 «እነርሱ እንደሚያምኑት፥ እኔም
በሙሴና በነቢያት መጻሕፍት አምናለሁ።
እነርሱ እንደሚያምኑት፥እኔም የጻድቃንና
የኃጥአን ትንሣኤ መኖሩን አምናለሁ። ነገር
ግን እኔ 'የደኅንነት መንገድ ነው' ብዬ የማ
ምነውን እነሱ 'የስሕተት ትምህርት ነው'
ስለሚሉ፥ በዚህ አሳብ እንለያያለን። 16 በበ
ኩሌ ግን በእግዚአብሔርና በሰዎች ፊት
ንጹሕ ሕሊና እንዲኖረኝ የሚቻለኝን ሁሉ
አደርጋለሁ።
17 «ከኢየሩሳሌም ውጭ ብዙ ጊዜ ከቆ
የሁ በኋላ ለወገኖቼ እርዳታ የሚሆን ገንዘ
ብና፥ለእግዚአብሔር የማቀርበውን መሥዋ
ዕት ይዤ ተመልሼ መጣሁ። 18 እነዚህ
ሰዎች ያገኙኝ፥ሕጉ በሚያዘው መሠረት፥
ጠጉሬን ተላጭቼ ስለት ሳደርስ እንጂ፥ሰዎ
ችን ሰብስቤ ሁከትና አመፅ ሳስነሣ አይደ
ለም። 19 እኔ ቤተ መቅደስ ውስጥ ሆኜ
ሥርዓተ አምልኮ በምፈጽምበት ጊዜ፥ከታና
ሽቱ እስያ የመጡ ጥቂት አይሁድ በዚያ
ነበሩ። በተንኰል ተነሣስተው የከሰሱኝ እነ
ዚያ ሰዎች፥ በእርግጥ ክሳቸው እውነት
ከሆነ ራሳቸው እዚህ ተገኝተው ማስረዳት
ይገባቸው ነበር። 20 በዚህም የሚገኙት እነ
ዚህ ከሳሾቼ ራሳቸው ተሰብስበው ስለመረ
መሩኝ፥ በእርግጥ ጥፋት አግኝተውብኝ
ከሆነ እስቲ ያስረዱ? 21 ያን ጊዜ የተናገር
ኩት ነገር ቢኖር፥ 'እዚህ የቀረብኩት
ሙታን እንደሚነሡ በማመኔ ተከስሼ ነው'
የሚል ቃል ነበር።»
22 ፊልክስም ክርስቲያኖችን ደህና አድ
ርጎ ያውቅ ስለነበር፥ «የጸጥታ ጥበቃ ኃይል
አዛዡ ሉስዮስ ሲመጣ፥ለጉዳዩ ውሳኔ እሰጥ
በታለሁ» ብሎ አይሁድን አሰናበታቸው።
23 ጳውሎስም ተመልሶ ወደ እሥር ቤት
ሄደ። ይሁን እንጂ ፊልክስ፥ጳውሎስን ለሚ
ጠብቀው ኃላፊ መኰንን፥ «በጥንቃቄ ጠብ
ቀው፤እሥራቱን ግን አታጥብቅበት፤ጠያቂዎ
ቹንም አትከልክል» የሚል ትእዛዝ
ሰጠው።
24 ከጥቂት ቀኖች በኋላ ፊልክስ፥አይሁዳ
ዊት ከሆነችው ሚስቱ ከድሩሲላ ጋር ሆኖ፥
ጳውሎስን አስጠራው። ጳውሎስም የዘላለም
ሕይወትን ለመውረስ በኢየሱስ ክርስቶስ
ማመን እንደሚያስፈልግ ለባልና ሚስቱ ነገ
ራቸው። 25 እንዲሁም ስለ ጽድቅ፥ ራስን

ስለ መግዛትና ስለሚመጣው ፍርድ አስተማ
ራቸው። ፊልክስ የሰማው ቃል ስላስፈራው
ጳውሎስን ፥ «ለዛሬ ይኸው ይበቃናል ፤
ሲመች በሌላ ጊዜ ደግሞ ትነግረናለህ»
አለው።
26 ፊልክስ ፥ ጳውሎስ ጉቦ እንዲሰጠው
ስለሚፈልግ ብዙ ጊዜ እያስጠራው ያነጋግ
ረው ነበር። 27 ከሁለት ዓመት በኋላ ፥ ፊል
ክስ ከቦታው ተነሥቶ በምትኩ ጶርቅዮስ
ፊስጦስ የተባለ ሰው ተሾመ። ፊልክስም
አይሁድን ደስ ለማሰኘት ሲል ፥ ጳውሎስን
ከእሥር ቤት ሳይፈታው ትቶት ሄደ።

## ምዕራፍ 25

1 ፊስጦስ አዲሱን ሥራውን ለመጀመር
ቂሣርያ በመጣ በሦስተኛው ቀን ፥ ወደ ኢየ
ሩሳሌም ወረደ። 2 እዚያ በቆየበትም ጊዜ
የካህናት አለቆችና የአይሁድ መሪዎች ወደ
እርሱ ቀርበው ከጳውሎስ ጋር ያላቸውን
ክስ በማንሣት ፥ 3 «ወደ ኢየሩሳሌም እንዲ
መጣ አድርግልን» ብለው ለመኑት። ይህን
ያሉትም በመንገድ አድፍጠው ጳውሎስን
ለመግደል አቅደው ስለነበር ነው። 4 ፊስጦስ
ግን ፥ «ጳውሎስ አሁን ቂሣርያ በእሥር ላይ
ይገኛል። እኔም በቅርቡ ተመልሼ ወደዚ
ያው ሂያጅ ነኝ። 5 እንፋረደዋለን የምትሉ
ከሆነ ግን ፥ ሰው መርጣችሁ ልትልኩ ትችላ
ላችሁ እንጂ ፥ ወደዚህስ መልሼ አልከውም»
አላቸው።
6 ፊስጦስ አንድ አሥር ቀን ያህል በኢየ
ሩሳሌም ከሰነበተ በኋላ ፥ ወደ ቂሣርያ ተመ
ለሰ። ቂሣርያ በገባ በማግስቱም ችሎት ተቀ
ምጦ የጳውሎስን ጉዳይ ማየት ጀመረ።
7 ጳውሎስ ከእሥር ቤት ተጠርቶ እንደ
ቀረበ ፥ ከኢየሩሳሌም የመጡት አይሁድ ከበ
ውት ቆሙ። ወንጀሉን አክብደውም በማስ
ረጃ ያልተደገፈ ክስ አቀረቡበት። 8 ጳውሎስ
ለቀረበበትም ክስ ፥ የአይሁድን ሕግ አለመቃ
ወሙን ፥ ቤተ መቅደስን አለማርከሱን ፥ በሮም
መንግሥት ላይም አለማመፁን ፥ ሳይደናገጥ
አንድ በአንድ መልሱን ሰጥቶ ፥ «ጥፋተኛ
አይደለሁም» አለ።
9 ፊስጦስ ግን አይሁዶችን ለማስደሰት
ሲል ፥ «ወደ ኢየሩሳሌም ሄደህ ክሱ በእኔው
ዳኝነት ቢታይ ምን ይመስልሃል?» ሲል
ጳውሎስን ጠየቀው።
10-11 ጳውሎስም ፥ «እኔ በዚህ ነገር
ፈጽሞ አልስማማም! አሁን የቆምኩት ልፋ
ረድበት በሚገባኝ በቄሣር ሹም ችሎት
ነው። ደግሞም አይሁድን ምንም እንዳልበ
ደልኳቸው ልቦናህ አሳምሮ ያውቃል።
በሞት የሚያስቀጣ በደል ፈጽሜ ከተገኘሁ
'መገደል አይገባኝም' የምል ሰው አይደለ
ሁም። ነገር ግን ወንጀለኛ አለመሆኔ እየታ
ወቀ ፥ አንተም ሆንክ ሌላ ባለሥልጣን እንዲ
ገድሉኝ ለባላጋሮቼ አሳልፎ ሊሰጠኝ አይገ
ባም። ስለዚህ ቄሣር ፊት እንድቀርብ ይግ
ባኝ ይሰጠኝ» አለ።
12 ፊስጦስም ከአማካሪዎቹ ጋር በቆይታ
ከተነጋገረ በኋላ ፥ «ለቄሣር ይግባኝ ካልክ ፥
ቄሣር ፊት ትቀርባለህ» አለው።
13 ከጥቂት ቀኖች በኋላ ንጉሡ አግሪጳና
በርኒቄ ፥ ፊስጦስን 'ሹመት ያዳብር' ለማለት
ወደ ቂሣርያ መጡ። 14 በቂሣርያም ብዙ
ቀኖች ቆዩ። በእነዚያም ጊዜያት ፊስጦስ
የጳውሎስን ጉዳይ ለንጉሥ አግሪጳ እንዲህ
ሲል አቀረበለት። «ፊልክስ ሳይፈታው
ትቶት የሄደ ጳውሎስ የሚባል አንድ እሥ
ረኛ እዚህ አለ። 15 በቅርቡ ኢየሩሳሌም በነ
በርኩበት ጊዜ የካህናት አለቆችና የአገር
ሽማግሌዎች በጳውሎስ ላይ ያቀረቡትን ክስ
አንሥተው እንድፈርድበት ጠየቁኝ። 16 እኔ
ግን ፥ በሮማውያን ሕግ መሠረት ከሳሽና ተከ
ሳሽ ቀርበው ጉዳዩ በአግባቡ ሳይጣራ ፥ በማ
ንም ሰው ላይ መፍረድ የማይቻል መሆኑን
ገለጽኩላቸው።
17 «በነገሩ ሊገፉበት ወደዚህ እንደ
መጡ ፥ ክሱ ወዲያውኑ እንዲሰማ አደረግሁ።
ከሳሽ ተከሳሽንም አቅርቤ ጉዳዩን በሚገባ
መርምሬአለሁ። 18 ይሁን እንጂ የቀረበው
ክስ እንደ ጠበቅሁትና እንደ ገመትኩት
አልነበረም። 19 ፍሬ ነገሩ ስለ ሃይማኖታቸ
ውና ሞቶ ስለነበረው ፥ ጳውሎስ ግን 'ሕያው
ነው' ስለሚለው ስለ ኢየሱስ ነበረ።
20 እኔም በዚህ ክርክር ላይ ፍርድ መስጠቱ
ስለከበደኝ ጳውሎስን ፥ 'ወደ ኢየሩሳሌም
ሄደህ ዳኝነቱን እኔው ራሴ ባየው ምን ይመ
ስልሃል?' ብዬ ጠየቅሁት። 21 ወደ ኢየሩሳ
ሌም መሄዱን ስላልፈለገ ፥ ቄሣር ፊት ልቅ
ረብ ብሎ ይግባኝ ጠየቀ። እኔም ምንም
ማድረግ ባለመቻሌ ወደ እሥር ቤት እንዲ
መለስ አድርጌ ፥ ይኸው አሁን ወደ ቄሣር
ልልከው እየተዘጋጀሁ ነው።»
22 አግሪጳም ፥ «የዚህን ሰው ጉዳይ እኔም
ለመስማት እፈልግ ነበር» አለው።
ፊስጦስም ፥ «እንግዲያውስ ነገ አቀርበዋ
ለሁ» ብሎ መለሰለት።
23 በማግስቱም አግሪጳና በርኒቄ የክብር
ልብሳቸውን ለብሰው ፥ በጦር መኰንኖችና

በከተማው ታላላቅ ሰዎች ታጅበው ፥ ወደ
ችሎት ገቡ። ፊስጦስም ጳውሎስን ከታሠረ
በት አስመጣው።
24 ከዚህ በኋላ ፊስጦስ የሚከተለውን ንግ
ግር አደረገ። «ንጉሥ ሆይ፥እንዲሁም የተከ
በራችሁ የጦር መኰንኖችና የከተማው ነዋ
ሪዎች ፤ ይህ እፊታችሁ የቀረበው እሥረኛ
በኢየሩሳሌምና በዚህ በቂሣሪያ የሚኖሩ
አይሁድ በሞት እንዲቀጣ ክስ ያቀረቡበት
ሰው ነው። 25 እኔ ግን ለሞት የሚያበቃ
ምንም ጥፋት አላገኘሁበትም። እሱ ራሱ
ለቄሣር ይግባኝ ባይል ኖሮ፥እለቀው ነበር።
ይግባኝ በማለቱ ብቻ ሌላ አማራጭ መን
ገድ ባለመኖሩ ፥ ወደሮም እንዲሄድ ወሰኛ
ለሁ። 26 ይህ ሰው ይከሰስ እንጂ ወንጀሉ
በሕግ የሚያስቀጣው ባለመሆኑ ፥ ለቄሣር
ምን ብዬ እንደምጽፍ ግራ ገብቶኛል።
27 የተከሰሰበትን ወንጀል ገልጠው ሳይጽፉ፥
አንድን እሥረኛ ዝም ብሎ ወደ ቄሣር
መላክ ትክክለኛ ነገር አይደለም። ስለዚህ
እዚህ ያላችሁት ፥ ሁሉ በተለይም ንጉሥ
አግሪጳ፥ ጉዳዩን መርምራችሁ አስተያየታች
ሁን እንድትሰጡኝ አሳስባለሁ።»

## ምዕራፍ 26

1 አግሪጳም ጳውሎስን ፥ «እስቲ አንተ
ደግሞ የበኩልህን አስረዳን» አለው።
ጳወሎስም እጁን አንሥቶ እንዲህ አለ፥
2 «ንጉሥ አግሪጳ ሆይ ፥ የተከሰስኩበትን
ነገር በዝርዝር ለአንተ ለማስረዳት ዕድል
በማግኘቴ ደስ ይለኛል። 3 ምክንያቱም
አንተ ስለ አይሁድ ሕግና ሥርዓት የማታው
ቀው ነገር የለምና። ስለዚህ በትዕግሥት እን
ድትሰማኝ አስቀድሜ እለምንሃለሁ።
4 «ከሕፃንነቴ ጀምሮ በጠርሴስ ከተማና
በኢየሩሳሌም ፥ በአይሁድ ሕግና ሥርዓት
ተኰትኩቼ ማደጌን አይሁድ ሁሉ ያው
ቃሉ። 5 እውነቱን መናገር አይፈልጉም
እንጂ ፥ በሃይማኖታችን የታዘዙትን ወግና
ሥርዓት አጥብቀው በመያዝ ከታወቁት ፈሪ
ሳውያን አንዱ መሆኔን ፥ ሊመሰክሩ ይችሉ
ነበር። 6 አሁን ተከስሼ ከዚህ የቀረብኩበት
ዋና ምክንያት ፥ እግዚአብሔር ለአባቶቻችን
ቃል የገባላቸውን ተስፋ ተቀብዬ በማመኔ
ነው። 7 ይህንን የተስፋ ቃል ለማግኘት ፥
አሥራ ሁለቱም የእሥራኤል ነገዶች ከጥ
ንት ጀምሮ ፥ ቀንም ሌትም ሲጠባበቁ ኖረ
ዋል። አሁን ግን አይሁድ እኔን የከሰሱኝ
በዚህ ተስፋ ምክንያት ነው እንጂ ፥ ሌላ
በደል ተገኝቶብኝ አይደለም። 8 ታዲያ ትን
ሣኤ ሙታንን በማመኔ መከሰስ ይገባኝ
ነበር? ለመሆኑ እናንተ ሙታንን ማስነሣት
እግዚአብሔርን የሚሳነው ነገር እንደሆነ
አድርጋችሁ ለምን ትገምታላችሁ?
9 «እኔ ራሴ የናዝሬቱ ኢየሱስን ስም
መቃወም አለብኝ ብዬ አስብ ነበር። 10 በኢ.
የሩሳሌም ያደረግሁትም ይህንኑ ነው። በተ
ለይም ከሊቀ ካህናቱ ሥልጣን ተቀብዬ ፥
ብዙ ክርስቲያኖችን እያሳደድኩ አሣስሬአ
ለሁ። እንዲገደሉ በተወሰነባቸው ጊዜም
በምክሩ ነበርኩበት። 11 ከእነርሱ ብዙዎቹን
በየምኵራቡ እንዲቀጡ እያደረግሁ፥ሃይማኖ
ታቸውን ለማስካድ ሞክሬአለሁ። በእነርሱ
ላይ እንደ እሬት የመረረ ጥላቻ ስለ ነበረኝ፥
ከኢየሩሳሌም አልፎ በባዕድ አገር ከተሞች
ውስጥ እንኳን የሚኖሩትን ለማሳደድ
ፈቃድ እስከ ማውጣት ደርሻለሁ። በእው
ነቱ ምን ያላደረግሁባቸው በደል አለ?
12 «አንድ ቀን ፥ ይህንኑ ክርስቲያኖችን
የማሳደድ ተግባሬን ለመቀጠል ፥ ከሊቀ ካህ
ናቱ ሥልጣን ተቀብዬ ወደ ደማስቆ ጉዞ
ጀመርኩ። 13 በመንገድ ላይ ሳለሁም በጠ
ራራ ፀሐይ በእኔና አብረውኝ በሚሄዱት
ሰዎች ዙሪያ ፥ እጅግ በጣም የሚያንጸባርቅ
ብርሃን ከላይ በራ። 14 በዚህ ጊዜ ሁላችንም
ወደ ምድር ወደቅን። ወዲያውም በዕብራይ
ስጥ ቋንቋ እንዲህ የሚል ድምፅ ሰማሁ።
'ሳውል፥ሳውል! ለምን ታሳድደኛለህ? እኔን
ተቃውምኩ ስትል የምትጐዳው መልሰህ
ራስህን ነው።'
15 «እኔም ፥ 'ጌታ ሆይ ፥ ለመሆኑ አንተ
ማን ነህ?' አልኩት። እርሱም፥ 'እኔ፥አንተ
የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ። 16 አሁንም ተነ
ሥና ቁም ፤ የተገለጥኩልህ ምስክሬ ሆነህ
እንድታገለግለኝ ልሾምህ ነው። ዛሬ ያየኸ
ውንና ወደፊትም የማሳይህን ሁሉ ለሰዎች
ትናገራለህ። 17 ከወገኖችህ ከአይሁድና ከአ
ሕዛብም እጅ አድንሃለሁ። 18 ያሉበትን
ሁኔታ መረዳት እንዲችሉ ዓይናቸውን እን
ድትከፍት፥ከጨለማ ወደ ብርሃን እንድታወ
ጣቸውና ፥ ከሰይጣን የጨለማ አገዛዝ ወደ
እግዚአብሔር መንግሥት በንስሐ እንዲመ
ለሱ እንድታደርጋቸው ፥ እልክሃለሁ። በእኔ
በማመናቸውም ኃጢአታቸውን ይቅር እላ
ለሁ። ከተመረጡትም ጋር ርስትን ይወር
ሳሉ' አለኝ።
19 «ንጉሥ ሆይ ፥ ስለዚህ ከላይ በራእይ
ለተገለጠልኝ ጌታ ከመታዘዝ ወደ ኋላ
ማለት አልፈለግሁም። 20 በመጀመሪያ በደ
ማስቆ ፥ ቀጥሎም በኢየሩሳሌምና በይሁዳ

የሚኖሩትን አይሁድንና አሕዛብን ፣ ንስሐ
እንዲገቡና ንስሐ መግባታቸውንም በመል
ካም ሥራቸው እንዲገልጡ አስተምሬአ
ለሁ። 21 እንግዲህ አይሁድ ከቤተ መቅደስ
ውስጥ የያዙኝና ሊገድሉኝም የፈለጉት ይህ
ንን ስላስተማርኩ ነበር። 22 እግዚአብሔርም
ስለ ረዳኝ ይኸው ለትንሹም ለትልቁም
ቃሉን እየመሰከርኩ እስካሁን በሕይወት
አለሁ። ነቢያትና ሙሴ ይሆናል ፣ ይፈጸማል
ብለው ከአስተማሩት ውጭ የተናገርኩት
አንድም ነገር የለም። 23 ነቢያትና ሙሴ
አስቀድመው ክርስቶስ መከራ እንደሚቀበ
ልና እንደሚሞት ፣ ከሙታንም የመጀመሪ
ያው ሆኖ እንደሚነሣና የደኅንነትን ብርሃን
ለአይሁድም ለአሕዛብም እንደሚያበራላ
ቸው ተናግረዋል። እኔም ያስተማርኩት ይህ
ንኑ ነው።»

24 ጳውሎስ ይህንን ሲናገር ፊስጦስ አቋረ
ጠውና ፣ «ጳውሎስ አበድክ መሰለኝ፤ መጽ
ሐፍ መመራመር ሲበዛ አእምሮን ያስታል
ማለት ነው?» አለው።

25 ጳውሎስም ፣ «የተከበርክ ፊስጦስ
ሆይ ፣ ጤናማ የሆነ ሰው የሚናገረውን ትክክ
ለኛ ነገር ተናገርኩ እንጂ ፣ ንግግሬ አእምሮ
ውን የሳተ ሰው ንግግር የሚመስለው ከምኑ
ላይ ነው? እንደ እውነቱ ከሆነ ፣ እኔ እብድ
አይደለሁም። 26 ከዚህ በላይ ስለተናገርኳ
ቸው ነገሮች ንጉሥ አግሪጳ አሳምሮ ያው
ቃል። ስለሆነም ፣ በፊቱ ስናገር ነፃነት ይሰማ
ኛል። እነዚህ ነገሮች ሁሉ በድብቅ የተፈ
ጸሙ ድርጊቶች አለመሆናቸውንም ፣ ንጉሡ
አይስተውም ብዬ አምናለሁ። 27 ንጉሥ
ሆይ ፣ የነቢያትን ትንቢት ታምን የለ?
አምን ፣ እንደምታምን አውቃለሁ።»

28 አግሪጳም ፣ «በቀላሉ አግባብተህ እኮ
ክርስቲያን ልታደርገኝ ምንም አልቀረ
ህም!» አለው።

29 ጳውሎስም ፣ «ንጉሥ ሆይ ፣ ምንም
ይሁን! አንተ ብቻ ሳትሆን ዛሬ እዚህ የሚገኙ
ሰዎች ሁሉ ፣ በዚህ በታሠርኩበት ሰንሰለት
መታሠር አይድረስባቸው እንጂ ፣ እንደ
እኔው አምነው ክርስቲያን እንዲሆኑ ወደ
እግዚአብሔር እጸልያለሁ» አለ።

30 ከዚህ በኋላ ንጉሡ አግሪጳ ፣ አገር አስ
ተዳዳሪው ፊስጦስና በርኒቄ ፣ አብረዋቸው
በዚያ የነበሩትም ሁሉ ከተቀመጡበት
ተነሡ። 31 ከአዳራሹም ወጥተው ሲሄዱ ፣
«ይህ ሰው እንኳን ለሞት ለእሥራትም የሚ
ያበቃ ጥፋት አላደረገም» ተባባሉ።

32 አግሪጳ ፊስጦስን ፣ «ይህ ሰው እኮ ለቄ
ሣር ይግባኝ ባይል ኖሮ መፈታት ይችል
ነበር» አለው።

## ምዕራፍ 27

1 በመጨረሻም በመርከብ ወደ ሮም እን
ድንሄድ ስለተወሰነ ፣ ጳውሎስንና ሌሎችን
እሥረኞች በአውግስጦስ ጦር ውስጥ ባልደ
ረባ ለሆነ ፣ ዩልዮስ ለሚሉት መኰንን አስረ
ከቡአቸው። 2 በሜዲቴራንያን ባሕር ጠረፍ
የሚገኙ የታናሹ እስያ ወደቦችን አዳርሳ ፣
ወደ ሮም በምትጓዝ መርከብ ተሳፍረን ለመ
ሄድ ተነሣን። የተሰሎንቄ ከተማ ነዋሪ የሆ
ነው መቄዶንያዊው አርስጥሮኮስም ከእኛ
ጋር ነበር።

3 በማግስቱ ሲዶና ገባን። የጦር መኰንኑ
ዩልዮስ ጳውሎስን በደህና ዓይን ያየው ስለነ
በረ ፣ ከመርከቢ ወርዶ ወዳጆቹን እንዲጠይ
ቅና የሚያስፈልገውን እርዳታ እንዲያገኝ
ፈቀደለት። 4 ከዚያም ስንነሣ ነፋሱ ፊት
ለፊት መንፈስ ስለጀመረ ፣ የቆጵሮስን ደሴት
ተገን አድርገን አለፍን። 5 በኪልቅያና በጵን
ፍልያ አጠገብ አልፈን በሉቅያ ከሚገኘው
ሙራ ከተባለ ወደብ ደረስን። 6 በዚያም
ወደ ኢጣሊያ የሚሄድ የእስክንድርያ መር
ከብ ስላገኘን ፣ የነበርንበትን መርከብ ትተን
በዚህኛው መርከብ ጉዞአችንን ቀጠልን።

7-8 የባሕር ሞገድ ስላጋጠመን ቀስ እያ
ልን ተጉዘን ቀኒዶስ አጠገብ ደረስን። በዚ
ህም ላይ ነፋሱ እንደ ልብ አላንቀሳቅስ ስላ
ለን ፣ ቀርጤስን ተገን አድርገን ጥግ ጥጉን
አልፈን ፣ ሰልሙና አጠገብ ደረስን። ከዚያም
ለላሲያ ከተማ ቅርብ ወደሆነችው ‘ውብ
ከለላ’ ወደምትባለው ትንሽ ወደብ ደረስን።
9 በ‘ውብ ከለላ’ ብዙ ቀኖች መቆየት ግድ
ሆነብን። የአይሁድ ‘የማስተሰሪያ ቀን’
በዓል አልፎ ክረምት ቀርቦ ስለነበር ፣ የአየሩ
ጠባይ ለመርከብ ጉዞ አደገኛ መሆኑን ጳው
ሎስ በመረዳቱ ፣ የመርከቧን አዛዥ መኰን
ኖች እንዲህ ሲል አስጠነቀቃቸው።

10 «ጌቶቼ ፣ የወደፊት ጉዞአችን አደጋ
እንዳለበት ይታየኛል። አደጋውም መርከቢ
ቱንና ጭነቱን ብቻ የሚጐዳ ሳይሆን ፣ በሰው
ሕይወትም ላይ ጉዳት ሊያመጣ የሚችል
ነው።» 11 የእሥረኞቹ ኃላፊ መኰንን ግን
ጳውሎስ ከሚናገረው ይልቅ ፣ የመርከቡ አዛ
ዥና የመርከቡ ባለቤት የሚሉትን ይሰማ
ነበር። 12 ‘ውብ ከለላ’ ለክረምቱ ማሳለፊያ
ምቹ ባለመሆኗ አብዛኞቹ መንገደኞች
ፍንቄ ወደተባለው የቀርጤስ ወደብ
ሄደው ፣ ክረምቱ እስኪያልፍ በዚያ ለመቆ

የት አሣብ አቀረቡ።
13 ከዚህ በኋላ ቀላል የደቡብ ነፋስ መን
ፈስ ጀመረ። የመርከቧ ሠራተኞችም ከፊት
ለፊት ኃይለኛ ነፋስ መንፈሱን ያቆመ መስ
ሏቸው ፥ መርከቧን አንቀሳቅሰው የባሕሩን
ዳር ዳር ይዘን መጓዝ ጀመርን።
14-15 ነገር ግን ምንም ያህል ሳንጓዝ ፥
ወዲያውኑ ከፊት ለፊታችን «አውራቂስ»
የሚባል ኃይለኛ ነፋስ መንፈስ ጀመረ።
ከዚህም የተነሣ መርከቢቱ በተፈለገው አቅ
ጣጫ መሄድ ባለመቻልዋ በነፋሱ ኃይል
እየተንገላታች፥
16 ቄዳ ከምትባለው ደሴት አጠገብ ደረ
ስን። ከዚያ ስንደርስ ደሴቲቱን ተገን አድር
ገን በመጓዝ፥የመርከቢቱን ሕይወት ማዳኛ
ጀልባ እጃችን ለማስገባት ቻልን። 17 ከዚ
ያም ጥንካሬ እንድታገኝ በማሰብ የመርከቧ
ዙሪያ በገመድ ጥፍር ተደርጎ ታሠረ። መር
ከበኞቹ፥ነፋሱ መርከቧን ገፍቶ ስርቲስ ከተ
ባለ አሸዋማ ሥፍራ ወስዶ እንዳይሰነቅራት
ፈርተው፥የመርከቧን ሸራ አውርደው እን
ዲሁ እንድትነዳ አደረጉ።
18 ነፋሱ በማግስቱም እያየለ ሄደ። መር
ከበኞቹም የተጫኑትን ዕቃዎች ወደ ባሕር
መጣል ጀመሩ። 19 በሦስተኛውም ቀን
ነፋሱ እየባሰበት ስለሄደ ፥ በመርከቧ ላይ
የሚገኙትን ገመዶችና መዘውሮች ሁሉ እያ
ነሡ ወደ ባሕሩ ጣሉ። 20 በዚህ ዓይነት
ችግር ውስጥ ረጅም ጊዜ በመቆየታችን ፥
እተርፋለሁ ብሎ ያሰበ ማንም ሰው አልነበ
ረም።
21 የመርከቧ ተሳፋሪዎችም ምግብ የሚ
ባል ነገር ሳይቀምሱ ብዙ ጊዜ ሆኖ ነበር።
ስለዚህ ጳውሎስ መካከላቸው ቆሞ እንዲህ
አለ ፥ «እናንተ ሰዎች ፥ መጀመሪያውኑ እኔ
ያልኳችሁን ሰምታችሁ ቢሆን ኖሮ ፥ ይህ
ሁሉ ጉዳትና ጥፋት ባልደረሰብንም ነበር።
22 አሁንም አይዞአችሁ! መርከቧ ትጐዳለች
እንጂ ፥ እኛ ምንም ክፉ ነገር ሳይደርስብን
በደህና እንገባለን። 23 ይህንንም ነገር የማመ
ልከው እግዚአብሔር ዛሬ ሌሊት መልአ
ኩን ልኮ ፥ 24 'ጳውሎስ ፥ አይዞህ አትፍራ!
ከቄሣር ፊት መቅረብ ስላለብህ ምንም አይ
ነካህም። እንዲሁም ከአንተ ጋር በጉዞ ላይ
ያሉትን ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር ከሞት
ያድናቸዋል' ብሎ ገልጾልኛል። 25 ስለዚህ
ጌታ የተናገረውን እንደሚፈጽም ስለማ
ምን ፥ ምንም አንሆንም። 26 ሆኖም ወደ አን
ዲት ደሴት ዳርቻ መድረስ ይኖርብናል»
አላቸው።

27 በአሥራ አራተኛው ሌሊት በአድርያ
ባሕር በኩል ነፋሱ እያንገላታን ስንጓዝ ፥
መርከበኞቹ ወደ ምድር የቀረቡ መሰላ
ቸው። 28 ስለዚህ የባሕር ጥልቀት መለኪያ
መሣሪያ ሲጥሉ ፥ የባሕሩ ጥልቀት አርባ
ሜትር ያህል ሆነ። ጥቂት ቆይተው መለኪ
ያውን እንደገና ቢጥሉ ደግሞ ጥልቀቱ
ሠላሳ ሜትር ያህል ሆነ። 29 በዚህ ጊዜ
መርከቧ ከባሕር ጠረፍ አለት ጋር ተላትማ
እንዳትሠበር ስለፈሩ ፥ ከመርከቧ በስተኋላ
አራት መልሕቆች ወደ ባሕሩ ጣሉ። ሌሊ
ቱም በደህና እንዲነጋላቸው ጸለዩ።
30 መርከበኞቹ ሁኔታው ስላላማራቸው ፥
እኛን ትተው መርከቡ ላይ ባለችው ጀልባ
ሾልከው ለመጥፋት ተማከሩ። መልሕቅ
የሚጥሉ መስለው ጀልባዋን ወደ ባሕሩ
ለማውረድ ጉድ ጉድ ሲሉ ጳውሎስ አወቀባ
ቸው። 31 ለጦር መኰንኑና ለወታደሮቹም ፥
«እነዚህ መርከበኞች ጥለውን ከሄዱ ልት
ድኑ አትችሉምና በነገሩ እወቁበት!» ብሎ
ነገራቸው። 32 ወታደሮቹም ጀልባዋ ከመር
ከቡ ጋር የተያያዘችበትን ገመድ ቆርጠው
ብቻዋን እንድትንሳፈፍ ለቀቋት።
33 ሲነጋም ጳውሎስ ፥ «እህል ከቀመሳ
ችሁ ይኸው ዛሬ ሁለት ሳምንት ሆናችሁ።
34 ጉዳት ሊደርስባችሁ ይቅርና ከጠጉራ
ችሁ አንዲቷ እንኳ ስለማትጠፋ ፥ እባካች
ሁን እህል ቅመሱ» ብሎ ለመናቸው።
35 ይህን ካለ በኋላ ከመርከበኞቹ ስንቅ
ላይ አንሥቶ እግዚአብሔርን አመሰገነና
ሁሉም እያዩት በላ። 36 ይህንንም ሲያዩ
ፍርሃቱ ቀለላቸውና ሁሉም እህል ቀመሱ።
37 በመርከቧ ውስጥ በጠቅላላው ሁለት
መቶ ሰባ ስድስት ሰዎች ነበርን። 38 ከበ
ሉም በኋላ የተጫነውን ስንዴ ወደ ባሕር
እየጣሉ ፥ የመርከቧን ጭነት ማቃለል
ጀመሩ።
39 ሲነጋ የባሕሩ ጠረፍ የየትኛው አገር
እንደሆነ ማወቅ አልቻሉም። አሸዋ ያለበ
ትን የባሕር ሰርጥ እንዳዩ ፥ መርከቧን ወደ
ዚያ ለማስጠጋት አሰቡ። 40 መልሕቆቹንም
ስበው ባሕር ውስጥ ጣሉ። የመቅዘፊያው
ንም ገመድ ፈትተው ፥ አነስ ያለውን ሸራ
ወጥረው በነፋሱ ኃይል ብቻ እየተገፋ ወደ
የብስ ለመድረስ ጉዞ ጀመሩ። 41 ይሁን
እንጂ መርከቧ ከአሸዋ ቁልል ጋር በመጋ
ጨቷ በፍንጫዋ ተተክላ ቀረች። የመርከቧ
የኋላ ክፍልም ከማዕበሉ ብርታት የተነሣ ፥
መሰባበር ጀመረ።
42 በዚህ ጊዜ ወታደሮቹ የጦር መኰንን

ኑን፤ «እሥረኞቹ ዋኝተው እንዳያመልጡ
እንግደላቸው» አሉት። 43 እርሱ ግን ጳው
ሎስን ለማዳን ስለፈለገ፣አሳባቸውን አልተቀ
በለም። ከዚህ በኋላ ዋና የሚችሉት ቀድ
መው በዋና ወደ ጠረፉ እንዲሄዱ አዘዘ።
44 የቀሩት ደግሞ በመርከቢ ስብርባሪ ላይ
እየተንሳፈፉ ወደ ዳር እንዲደርሱ ነገሩ
ቸው። በዚህ ዓይነት፣ሁሉም ጉዳት ሳይደር
ስባቸው በደህና ወደ ምድር ደረሱ።

## ምዕራፍ 28

1 ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣የረገጥናት ምድር
መላጥያ የምትባለዋ ደሴት መሆንዋን ተረ
ዳን። 2 የደሴቲቱ ነዋሪዎች ደግነት የተሞላ
በት አቀባበል አደረጉልን። ዝናብ በመጣ
ሉም በርዶን ስለነበር፣የምንሞቀው እሳት
ግር አድርገው አነደዱልን።
3 ጳውሎስም ጭራሮ ሰባስቦ እሳቱ ላይ
ሲጨማምር፣ከጭራሮው ውስጥ የነበረ ተና
ዳፊ እባብ ሙቀት ስለተሰማው፣ወጥቶ እጁ
ላይ ተጠመጠመ። 4 የደሴቲቱ ነዋሪዎችም
እባቡ እጁ ላይ ተንጠልጥሎ ሲያዩ፣ «ይህ
ሰው ነፍሰ ገዳይ መሆን አለበት። አያችሁ፣
ከባሕር አምልጦ በደህና ቢወጣ እንኳ፣የአ
ምላክ ፍርድ አልለቀቀውም፤ይከታተለዋል»
ተባባሉ።
5 ጳወሎስ ግን ምንም ጉዳት ሳያደርስ
በት እባቡን ከእጁ ላይ አራግፎ፣ እሳቱ
ውስጥ ጨመረው። 6 ሰዎቹም፣ ከአሁን
አሁን ሰውነቱ ያብጣል፤ ወይም መርዙ
አዙሮ ይጥለዋል ብለው ይጠባበቁ ጀመር።
ግን ብዙ ጊዜ ተጠባብቀውት ምንም እንዳ
ልሆን ሲያዩ፣አሳባቸውን ለውጠው፣ «ይህስ
ሰው ሳይሆን፣አምላክ መሆን አለበት» ተባ
ባሉ።
7 ባረፍንበትም ሥፍራ አጠገብ የደሴ
ቲቱ አስተዳዳሪ የፑፕልዮስ ርስት ነበር።
አስተዳዳሪውም በቤቱ ተቀብሎ፣ሦስት ቀን
ሙሉ ደህና አድርጎ አስተናገደን። 8 የፑፕ
ልዮስ አባትም በተቅማጥ በሽታና በትኩሳት
ታሞ ተኝቶ ነበር። ጳውሎስ በሽተኛው
ወደተኛበት ክፍል ገብቶ ጸልዮ እጁን
ሲጭንበት ተፈወሰ። 9 ከዚህም የተነሣ በደ
ሴቲቱ የሚኖሩ በሽተኞች ሁሉ መጥተው
ከበሽታቸው ተፈወሱ። 10 ብዙ ስጦታዎ
ችም አቀረቡልን። ለመሄድ ስንነሣም፣ለመ
ንገድ የሚያስፈልገንን ስንቅ አምጥተው
በመርከቢ ላይ ጫኑልን።
11 መርከባችን ጉዳት ከደረሰባት ከሦስት
ወር በኋላ፣ከእስክንድርያ መጥታ መላውን
ክረምት በደሴቲቱ ወደብ ቆማ በከረመች
ሌላ መርከብ ተሳፍረን ጉዞ ጀመርን። የመ
ርከቢ አርማ፣ ‘መንታ አማልክት’ የሚል
ነበር። 12 ሰራኩስ ከደረስን በኋላም ሦስት
ቀን ውለን አደርን። 13 ከሰራኩስም ተጉዘን
ሬጊዩም ደረስን፣ በዚያ አንድ ቀን እንደ
ቆየን ከደቡብ የሚነሣው ነፋስ መንፈስ ስለ
ጀመረ ጉዞአችን ተቃንቶ በማግስቱ ፑቲዮ
ሉስ ደረስን። 14 በፑቲዮሉስ ያገኘናቸው
ክርስቲያኖችም አብረናቸው ለሰባት ቀናት
እንድንቆይ ለመኑን። ከዚያም ጉዞአችንን
ወደ ሮም ቀጠልን።
15 በሮም የሚኖሩት ክርስቲያኖች መም
ጣታችንን ሰምተው፣ ከሮም ስድሳ ኪሎ
ሜትር ርቆ ወደሚገኘው «የአፍዮስ አደባ
ባይ» መጥተው ተቀበሉን። ሌሎቹ ደግሞ
ከሮም ሃያ አምስት ኪሎ ሜትር ርቆ ከሚገ
ኘው «ሦስቱ ማረፊያዎች» ከሚባለው ቦታ
ድረስ መጥተው ተቀበሉን። ጳውሎስ ምዕ
መናንን ሲያይ እግዚአብሔርን አመሰገነ፤
መንፈሱም ተበራታ።
16 ሮም እንደገባንም ጳውሎስ አንድ
የሚጠብቀው ወታደር ተሰጥቶት ለብቻው
እንዲኖር ተፈቀደለት። 17 ከሦስት ቀን በኋ
ላም ሮም ከተማ የሚኖሩትን የአይሁድ
ታላላቅ ሰዎች ሁሉ አስጠራ። በተሰበሰቡም
ጊዜ፣እንዲህ አላቸው፣
«ወንድሞቼ ሆይ፣ምንም ሳላጠፋ፣የአባ
ቶቻችንንም ሥርዓት ሳላፈርስ በኢየሩሳሌም
ያሉ አይሁድ ይዘው አሥረው ለሮማውያን
አሳልፈው ሰጡኝ። 18 ሮማውያንም ከመረ
መሩኝ በኋላ፣ እንኳን ለሞት ለእሥራት
የሚያበቃ ጥፋት ስላላገኙብኝ ሊፈቱኝ አስ
በው ነበረ። 19 ነገር ግን አይሁድ እኔ ሞቼ
ካላዩ እንቅልፍ የማይወስዳቸው መሆኑን
ስለተረዳሁ፣ለቄሣር ይግባኝ አልኩ። እንግ
ዲህ ወደዚህ የመጣሁበት ፍሬ ነገር ባጭሩ
ይኸው ነው እንጂ፣ወገኖቼ አይሁድ በድለ
ውኛል ብዬ ለመክሰስ አይደለም። 20 ዛሬ
ወደዚህ እንድትመጡ የጠራኋችሁ ይህንኑ
ሁኔታ እንድትረዱት ልነግራችሁ ሲሆን፣
ሌላው ደግሞ እንድንተዋወቅ ስለ ፈለግሁ
ነው። እንደምታዩት በዚህ ሰንሰለት ለመታ
ሠር የበቃሁት ስለ መሲሑ መምጣት፣ለአባ
ቶቻችን የተሰጠው ተስፋ መፈጸሙን በማ
መኔ ብቻ ነው።»
21 እነርሱም፣ «እኛ ስለ አንተ የሰማነው
ነገር፣ ወይም ከይሁዳ የተጻፈልን ደብዳቤ
የለም። ከኢየሩሳሌም የመጡትም ሰዎች

ስለአንተ የነገሩን ምንም ክፉ ነገር የለም።
22 ነገር ግን እነዚህ፣ ‘ክርስቲያኖች’ የሚባ
ሉት ሰዎች በየአገሩ ተቃውሞ የተነሣባ
ቸው መሆኑን እናውቃለን። አንተ የምታም
ንበት የተለየ ነገር ካለ ብትነግረን ለመስ
ማት ዝግጁ ነን» አሉት።

23 በጉዳዩ ላይ ለመነጋገርም ቀጠሮ
ያዙ። በቀጠሮውም ዕለት አይሁድ ብዙ
ሆነው ጳውሎስ ወዳረፈበት ሥፍራ መጡ።
እርሱም ከሙሴ ሕግና ከነቢያት መጻሕፍት
ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረውን ቃል እየ
ጠቀሰ፣ ከጥዋት ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ
አስተማራቸው።

24 ከእነርሱ መካከል ግማሾቹ የተናገረ
ውን ሲያምኑ፣ ግማሾቹ ግን አልተቀበሉ
ትም። 25 በመካከላቸው አለመስማማት መፈ
ጠሩን ጳውሎስ በመገንዘቡ ወደየቤታቸው
ከመሄዳቸው በፊት እንዲህ አላቸው። «መን
ፈስ ቅዱስ በኢሳይያስ አድሮ፣ ‘ወደ አይ
ሁድ ሄደህ እንዲህ በላቸው፤ 26 መስማት
ትሰማላችሁ፣ ግን አታስተውሉም፤ ማየትም
ታያላችሁ፣ ግን አጥርታችሁ አትመለከቱም፤
27 ምክንያቱም ልባችሁ ደንድኖአል፤ ጆሮአ
ችሁም ደንቁሮአል፤ ዓይኖቻችሁም እውቀ
ትን እንዳያስተውሉ ታውረዋል። ይህን
ሁሉ የምታደርጉት ለማየት፣ ለመስማት፣
ለማስተዋልና ወደ እኔም ተመልሳችሁ ለመ
ዳን ስላልፈለጋችሁ ነው’ ብሎ የተናገረው
ትክክለኛ ነገር ነው። 28-29 ስለዚህ አንድ
ነገር ልትገነዘቡ ይገባል። እናንተ ይህን ከእ
ግዚአብሔር የተላከውን ደኅንነት አንቀበ
ልም ካላችሁ፣ መልእክቱ ለአሕዛብም
ጭምር የተላከ በመሆኑ እነርሱ ይሰሙ
ታል፤ ይቀበሉታልም።»

30 ጳውሎስም በተከራየው ቤት ሁለት
ዓመት ሙሉ ተቀመጠ። ሊጠይቁት የሚመ
ጡትን እየተቀበለ፣ 31 ስለ እግዚአብሔር
መንግሥትና ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ
ፍርሃት ያስተምራቸው ነበረ። እንዳያስተ
ምር የከለከለው ማንም አልነበረም።



# ለመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች የተጻፉ መልእክቶች

ደቀመዛሙርቱ ከማያምኑ ከአይሁድና ከአሕዛብ ተቃዋሚዎቻቸው የሚደርስባቸውን ማናቸውንም ዓይነት መከራና ሥቃይ ሳይፈሩ፥የክርስቶስን ወንጌል በየአገሩ እንደሰበኩ ተመልክተናል። ሕይወታቸውን በደስታ ለሞት አሳልፈው እስከ መስጠት በመድረሳቸውም፥ በቃል ያስተማሩት ትምህርት የቱን ያህል እውነት መሆኑን በተግባር ለማስመስከር ችለዋል። ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ስመ ጥር የሆነው ጳውሎስ ነው። ጳውሎስ በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ላይ የመረረ ጥላቻ በነበረው ወቅት፥ክርስቲያኖች ናቸው የተባሉትን ሁሉ እያሳደደ በማሳሠር «ሰላም ነሺዎች፥ፀጥታ አደፍራሾች» ናቸው በማለት ለሮማውያን ገዢዎች አሳልፎ ይሰጣቸው ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን እነዚሁኑ ክርስቲያኖች ለማደን ወደ ደማስቆ ከተማ ሲገሠግሥ፥ከሞት የተነሣው ኢየሱስ ተገለጠለት። ጌታ ፍቅሩንና ክብሩን ስለገለጠለትም በክርስቲያኖች ላይ የነበረው ጥላቻ ተወግዶ አስተሳሰቡ ተለወጠ። ኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅና የዓለም መድኃኒት መሆኑንም ለማመን በቃ።

በሚቀጥሉት ገጾች ውስጥ የምታገኙዋቸው የመጀመሪያዎቹ 13 መልእክቶች ይህ ታላቅ ሐዋርያ ለመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች የጻፋቸው ናቸው። ከዚያም ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው የዕብራውያን፥የያዕቆብ፥የጴጥሮስ፥የዮሐንስና የይሁዳ መልእክቶች ይገኛሉ። እነዚህ መልእክቶች በልዩ ልዩ ምክንያት፥ለልዩ ልዩ ማሕበረ ምዕመናንና ግለ ሰቦች የተጻፉ ናቸው። ሁሉም የሚያንፀባርቁት አንድ እውነት አለ። ይህም፥ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአተኞችን ለማዳን ወደዚህ ዓለም መምጣቱንና የሚያምኑበትን ሁሉ ከአባቱ ጋር የሚያስታርቃቸው መሆኑን ነው።

# ሐዋርያው ጳውሎስ
# ለሮም ሰዎች የጻፈው መልእክት

## መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ሲሆን፣ የተጻፈበትም ዘመን በ58 ዓ.ም. ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን መልእክት ለመጻፍ የተነሣሣበት ምክንያት የክርስቶስን ወንጌል በሰፊው ለማስረዳት ሲል ነው። በዚህ መልእክቱም አንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር ፊት ከበደሉ እንዴት እንደሚነጻና ደኅንነትን እንዴት እንደሚያገኝ ለሚቀርብ ጥያቄ፣ ቁልጭ ያለ መልስ ሰጥቶአል። ከዚህም በላይ ከክርስቶስ ጋር አንድ ስለ መሆናችንና ከእርሱ ጋር አንድ በመሆናችንም ስለምናገኘው በረከት ገልጿል። በተጨማሪም ሐዋርያው፣ ክርስቲያኖች እንዴት ባለ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር እንዳለብን በዚሁ መልእክቱ በሚገባ ዘርዝሮ ጽፎአል።

---

## ምዕራፍ 1

1 የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማስተማር
ተለይቶ ከተጠራው ሐዋርያ፣ ከኢየሱስ ክርስ
ቶስ አገልጋይ ከጳውሎስ የተላከ። 2 ይህ ወን
ጌል እንደሚሰበክ በብሉይ ዘመን በነበሩ
ነቢያት አማካይነት እግዚአብሔር ተስፋ
መግባቱ በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፏል።
3 ወንጌሉም ስለ እግዚአብሔር ልጅ ስለ
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያበሥር የም
ሥራች ቃል ነው። እርሱም በሥጋ ከዳዊት
ዘር የተወለደ ሲሆን፣ 4 በቅድስናው መን
ፈስ፣ ከሙታን በተነሣበትም መለኮታዊ የእ
ግዚአብሔር ልጅ መሆኑ ተረጋግጧል።
5 ስለስሙ ክብር፣ በክርስቶስ በኩል እግዚ
አብሔር ጸጋውንና የሐዋርያትን ጥሪ አድሎ
ናል። ይህም በዓለም አካባቢ እየተዘዋወርን
ሰዎች ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም እንዲያም
ኑና ለእግዚአብሔር እንዲታዘዙ እንድናስተ
ምራቸው ነው።
6-7 እናንተም በሮም የምትገኙ ወገኖቻ
ችን የእግዚአብሔር ወዳጆችና ቅዱሳን እን
ድትሆኑ ተጠርታችኋል። በዚህ ጥሪውም
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝብ ሆናች
ኋል። የአባታችን የእግዚአብሔር፣ የጌታች
ንም የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ይብዛላ
ችሁ።
8 በክርስቶስ ማመናችሁን ዓለም በሙሉ
አውቆታል። በደረስኩበት ቦታ ሁሉ ሰዎች
ስለ እናንተ ሲያወሩ እሰማለሁ። እኔም
ይህን በመስማቴ ስለ እናንተ እግዚአብሔ
ርን አመሰግነዋለሁ፤ 9 ስለ እናንተም ባለማ
ቋረጥ ዘወትር እጸልያለሁ። ይህ እውነት
ለመሆኑም፣ የልጁን የኢየሱስ ክርስቶስን
የምሥራች ቃል በማብሠር ከልቤ የማገለግ
ለው እግዚአብሔር ምስክር ነው።
10 አሁንም ቢሆን መጥቼ እያችሁ ዘንድ
እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መንገዴ እንዲ
ቃናልኝ እጸልያለሁ። 11 ወደ እናንተ ለመ
ምጣት የምናፍቀውም በእምነት ጸንታችሁ
ለመገኘት የሚያበቃችሁን መንፈሳዊ ስጦታ
እንዳካፍላችሁ ነው። 12 የእግዚአብሔር
ፈቃዱ ሆኖ ከመጣሁም እርስ በርሳችን እን
ጽናናለን። ከዚህም በላይ ደግሞ አብሬአ
ችሁ በምሆንበት ጊዜ የጋራ እምነታችን
ጽናትና ጥንካሬን ይሰጠናል ብዬ ይበልጡን
ተስፋ አደርጋለሁ።
13 የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፣ ብዙ
ጊዜ ወደ እናንተ ለመምጣት እያሰብኩ ሳይ
ሳካልኝ ቀርቷል። በሌሎቹ የአሕዛብ ወገ
ኖች መካከል ተገኝቼ ሳስተምር ያገኘሁትን
ፍሬ፣ በእናንተም መካከል ተገኝቼ በማስተ
ማር እንዳገኝ ተመኝቼ ነበር። 14 ምክንያ
ቱም ለሰለጠኑና ላልሰለጠኑ፣ በእውቀት ለበ
ሰሉና ገና ማይማን ለሆኑ የወንጌሉን ቃል
የማስተማር ግዴታ አለብኝ። 15 ስለዚህ ወደ
ሮም መጥቼ እናንተንም ለማስተማር ትልቅ
ምኞት አለኝ።
16 የክርስቶስን ወንጌል ለማስተማር አላ
ፍርም። ምክንያቱም የወንጌሉ ቃል ያመኑ
በትን ሁሉ አድኖ ወደ ሰማያዊት አገር
የሚያደርስ የእግዚአብሔር ኃይል ነው።
ይህም የወንጌል ቃል የተሰበከው አስቀድሞ
ለአይሁድ ከዚያም ለግሪኮች ነበር። 17 እግ

ዚአብሔር በቸርነቱ በነፃ እንዳጸደቀንና
ለመንግሥቱ ብቁ አድርጎ እንዳዘጋጀን የወ
ንጌሉ ቃል ያውጅልናል። ይህም የሚሆ
ነው ክርስቶስ እንደሚያድነን አምነን ስንቀ
በለው ነው። ምክንያቱም በቅዱሳት መጻሕ
ፍት ፣ «ጻድቅ በእምነት ሕያው ሆኖ ይኖ
ራል» ተብሎ ተጽፏልና።
18እውነት እንዳትታወቅ በክፋት መጋ
ረጃ በሚሸፍኗት ኃጢአተኞች ላይ የእግዚ
አብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣል። 19እግዚ
አብሔር ሰዎች ስለ እርሱ ማወቅ የሚገባቸ
ውን ነገር በግልጽ እንዲያውቁት ስላደረገ፣
ከእነርሱ የተሰወረ አይደለም። 20ዓለም ከተ
ፈጠረ ጀምሮ በዓይን ሥጋ የማይታየው የእ
ግዚአብሔር ባሕርይ ፣ ዘላለማዊ ኃይሉና
አምላክነቱ በፍጥረት አማካይነት ግልጽ
ሆኖ ታይቶአል። ስለዚህ እንደነዚህ ያሉ
የአዋቂ አጥፊዎች የእግዚአብሔርን ሕል
ውና ለመካድ ምክንያት የላቸውም።
21ምንም እንኳን እግዚአብሔርን ቢያው
ቁትም ፣ ለአምላክነቱ የሚገባውን ክብርና
ምስጋና አልሰጡትም። በዚህ ፈንታ ስለ
እግዚአብሔር የተሳሳተ አሳብ ማሰብ
ጀመሩ። ማስተዋል የተሳነው አእምሮአቸ
ውም በጨለማ ተዋጠ። 22በእነርሱ ቤት
'አዋቂዎች ነን' ብለው አሰቡ፤ግን አላዋቂ
ዎች ሆነው ተገኙ። 23ከዚህ የተነሣም ዘላ
ለማዊ የሆነውን የአምላክ ክብር ፣ በሰው ፣
በወፎች ፣ በእንስሳትና በደረታቸው በሚሳቡ
ፍጥረታት መልክ ለወጡ። እንጨት ጠር
በው ድንጋይ አለዝበው ፣ ለሠሯቸው የጣዖ
ታት ምስልም ሰገዱ።
24ስለዚህም እግዚአብሔር ለተፈጥሮ
ባሕርያቸው በማይስማማ መንገድ እርስ በር
ሳቸው አስነዋሪና ወራዳ ለሆነ የዝሙት
ሥራ ተገዢዎች እንዲሆኑ ተዋቸው።
25እስከዚህ የደረሱትም እግዚአብሔርን
አውቀውት ሳለ ፣ እርሱን በማምለክ ፈንታ
ሆን ብለው ዓይነ ልቦናቸውን ጨፍነው
የሐሰትን መንገድ በመከተላቸው ፣ ፈጣሪ
አምላክን ትተው እርሱ የፈጠራቸውን ነገ
ሮች በማምለካቸውና በማገልገላቸው ነው።
እግዚአብሔር ግን ለዘላለም የተመሰገነ
ነው። አሜን!
26እግዚአብሔርም ይህን ለመሰለው
ወራዳና አሳፋሪ ምኞት አሳልፎ የሰጣቸው
በዚህ የተነሣ ነው። ሴቶቻቸው ከወንዶች
ጋር የተለመደውን የግብረ ሥጋ ግንኙነት
መፈጸም ትተው ፣ ባልተለመደ መንገድ
እርስ በርሳቸው የግብረ ሥጋ ግንኙነትን
እስከ መፈጸም ደረሱ። 27ወንዶችም ከሴ
ቶች ጋር መፈጸም የሚገባቸውን የግብረ
ሥጋ ግንኙነት ትተው እርስ በርሳቸው የግ
ብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም ሰውነታቸ
ውን አዋረዱት። ለዚሁም አሳፋሪ ለሆነ
አድራጎታቸው ተገቢ የሆነውን ቅጣት ተቀ
በሉ።
28እግዚአብሔርን ለማወቅ ስላልፈለ
ጉም ፣ እግዚአብሔር መደረግ የሌለበትን
ወራዳ ተግባር እንዲፈጽሙ ፣ ብልሹ ለሆነ
አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው። 29ሕይወታ
ቸው በተለያየ ኃጢአትና ክፋት የተሞላ
ነው፤በስስት ፣ በጥላቻ ፣ በቅናት ፣ በነፍስ መግ
ደል ፣ በጥል ፣ በሐሰት ፣ በምሬት ፣ በወሬኛነት ፣
30በሐሜት ፣ እግዚአብሔርን በመጥላት ፣
ሰውን በማዋረድ ፣ በትዕቢትና በትምክሕት
ተሞልቷል። ክፋትን የሚመኙ ፣ ለወላጆቻ
ቸው የማይታዘዙ ፣ 31የማያስተውሉ ፣ ውል
የሚያፈርሱና ጨካኞች ሆነዋል። 32ይህን
የሚያደርጉ ሁሉ በሞት መቀጣት እንደሚ
ገባቸው በሕገ እግዚአብሔር መታዘዙን እነ
ዚህ አመፀኞች ያውቃሉ። ይሁን እንጂ ፣
ራሳቸው እያወቁ ከማጥፋታቸውም በላይ ፣
ሌሎች ሰዎችም እነዚሁኑ ነገሮች እንዲያደ
ርጉ ይገፋፏቸዋል።

## ምዕራፍ 2

1እናንተ ፣ 'ለምን እንዲህ ታደርጋላ
ችሁ' ብላችሁ በሌሎች ሰዎች ላይ የፈረዳ
ችሁበትን ያንኑ ነገር መልሳችሁ ካደረጋች
ሁት ጥፋታችሁን የምታመካኙበት አይኖ
ርም። በሌሎች ላይ ስትፈርዱ በራሳችሁም
ላይ ትፈርዳላችሁ። 2እግዚአብሔር እንደ
ዚህ የሚያደርጉትን ሰዎች ይፈርድባቸዋል
እንጂ አይተዋቸውም። 3እናንተ በሌሎች
ላይ የምትፈርዱ ሰዎች ፣ እናንተው መልሳ
ችሁ ያንኑ የምታደርጉት ከሆነ ከእግዚአብ
ሔር ፍርድ እንዴት ታመልጣላችሁ?
4ወይስ ቸርነቱንና ትዕግሥቱን ትንቃላ
ችሁ? በቸርነቱ ብዛት የቻላችሁና የታገሣ
ችሁ ንስሐ እንድትገቡ ጊዜ ሊሰጣችሁ
ፈልጎ አይደለምን?
5ነገር ግን እናንተ ልበ ደንዳኖች በመሆ
ናችሁ ፣ ንስሐ ለመግባት አልፈለጋችሁም።
ስለዚህ በእልከኝነት ጸንታችሁ በመገኘታ
ችሁ ፣ እግዚአብሔር ቁጣውን በሚገልጥበ
ትና ትክክለኛ ፍርዱን በሚሰጥበት ቀን አስ
ቃቂ ቅጣት ይጠብቃችኋል። 6እግዚአብሔ
ርም በእያንዳንዱ ሰው ላይ እንደ ሥራው
ይፈርድበታል። 7ከእግዚአብሔር የሚገኘ

ውን ምስጋና ፥ ክብርና የዘላለም ሕይወት
ፈልገው፥ፈቃዱን እየፈጸሙ ለሚኖሩ እግዚ
አብሔር የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል።
8 ነገር ግን እግዚአብሔርን በሚክዱ እውነ
ትን በሐሰት በሚለውጡና አመፅን በሚ
ወዱ ሰዎች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይወር
ድባቸዋል። 9 ከአይሁድም ሆኑ ከአሕዛብ ፥
ሥራቸው ክፉ የሆነ ሰዎች ሁሉ ፥ የሚጠብ
ቃቸው መከራና ሥቃይ ነው። 10 ነገር ግን
የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለሚፈጽሙ ፥ ከአይ
ሁድም ሆኑ ከአሕዛብ ፥ ክብር ምስጋናና
ሰላም ይጠብቃቸዋል። 11 እግዚአብሔር በሰ
ዎች መካከል የሚያዳላ አምላክ አይደለ
ምና።
12 የሙሴ ሕግ ለአሕዛብ አልተሰጣቸ
ውም። ይሁን እንጂ ኀጢአት የሚሠሩ ሕግ
ባይሰጣቸውም በኀጢአታቸው ይቀጡበ
ታል። ለአይሁድ ግን የኦሪት ሕግ ተሰጥቷ
ቸዋል። ሕጉን የሚያፈርሱትም በሕጉ
መሠረት ይቀጡበታል። 13 ምክንያቱም
ማንም ሰው በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ
ሊባል የሚችለው የኦሪትን ሕግ በመስማቱ
ብቻ ሳይሆን ሕጉ የሚያዘውን በመፈጸሙ
ነውና። 14 አሕዛብ ሕግ የላቸውም፤ባይኖራ
ቸውም ክፉውንና በጎውን በተፈጥሮ ባሕር
ያቸው ለይተው ስለሚያውቁ ሕጉ የሚያዘ
ውን ነገር ይፈጽማሉ። የተጻፈ ሕግ ባይኖራ
ቸውም ክፉ ሥራ ሲሠሩ የሕሊና ወቀሳ ፥
በጎ ሥራ ሲሠሩ የመንፈስ ሰላም ያገኛሉ።
15 ሕጉ የሚያዘው ነገር ሁሉ በልባቸው
መጻፉን ሕሊናቸው ያስገነዝባቸዋልና።
ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ በሠሩት ሥራ
የገዛ ሕሊናቸው ይወቅሳቸዋል፤በሌላ ጊዜ
ደግሞ ይመሰክርላቸዋል። 16 እግዚአብሔር
በኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጆች የልባቸ
ውን ምሥጢር ገልጾ የሚፈርድበት ቀን
ይመጣል። እኔም የምሰብከው የወንጌል
ቃል ይህንኑ ያረጋግጣል።
17 አንተ አይሁዳዊ ፥ በአይሁዳዊነትህ
ትመካለህ፤በኦሪት ሕግ ትተማመናለህ፤ ‘እግ
ዚአብሔርንም የማውቅ እኔ ብቻ ነኝ’ ትላ
ለህ። 18 የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቃለሁ
ባይ ነህ፤መልካም ማድረግንም ከሕጉ መጽ
ሐፍ ተምረሃል። 19 የእግዚአብሔርን መን
ገድ አውቃለሁ ከማለትህ የተነሣም ፥ «ዕው
ሮችን ለመምራት በጨለማ ላሉትም ብርሃን
ለመስጠት እችላለሁ» ትላለህ። 20 ሕጉ
እውቀትና እውነት የሞላበት በመሆኑ ፥
«ያልተማሩትንና ሕፃናት የሆኑትን ማስተ
ማር እችላለሁ» ትላለህ።
21 ታዲያ ሌሎችን የምታስተምር ከሆ
ንክ ፥ ራስህን ለምን አታስተምርም? «አትስ
ረቁ» ብለህ ታስተምራለህ፤ ታዲያ አንተስ
ትሰርቃለህ? 22 «አታመንዝሩ» ትላለህ ፤
ታዲያ አንተስ ታመነዝራለህ? ለጣዖት የሚ
ደረገውን አምልኮ ትጸየፋለህ፤ ታዲያ አን
ተስ የቤተ መቅደስን ንብረት ትዘርፋለህ?
23 የእግዚአብሔርን ሕግ በማወቅህ ትመ
ካለህ፤ታዲያ አንተ ለምን ሕግን በመተላለፍ
እግዚአብሔርን ታቃልለዋለህ? 24 «በእና
ንተ ምክንያት የእግዚአብሔር ስም በአሕ
ዛብ መካከል ይሰደባል» ተብሎ ተጽፏል።
ይህም እናንተን የሚመለከት ነው።
25 የሙሴን ሕግ የምትጠብቁ ከሆነ መገ
ረዛችሁ ጠቃሚ በሆነ ነበር። ግን ሕጉን
ካልጠበቃችሁት በመገረዛችሁ ምን ጥቅም
ታገኙበታላችሁ? 26 ስለዚህ ፥ ያልተገረዘው
አሕዛብ የሕግን ትእዛዝ የሚፈጽም ከሆነ ፥
እግዚአብሔር ይህን ሰው እንደተገረዘ ሊቆ
ጥረው ይችላል። 27 አንተ ፥ በተጻፈው ሕግ
መሠረት የተገረዝህ ብትሆንም ፥ ሕጉ የሚያ
ዘውን ፈጽመህ ካልተገኘህ ፥ ያልተገረዘ ነገር
ግን የሕግን ትእዛዝ የሚፈጽም አሕዛብ ያሳ
ጣሃል።
28 ከአይሁድ ቤተ ሰብ መወለዳችሁ
ብቻ ወይም ሥርዓተ ግዝረትን መፈጸማ
ችሁ ብቻ አይሁድ ሊያሰኛችሁ አይች
ልም። 29 እውነተኛ አይሁዳዊ አፍአዊ ሥር
ዓተ ግዝረትን የፈጸመ ሳይሆን ፥ በመንፈስ
ቅዱስ አማካይነት የልቡን ጠማማነት ያቀና
ሰው ነው። እግዚአብሔር የሚፈልጋቸውም
አፍአዊ ሥርዓተ ግዝረት ለይስሙላ የፈጸ
ሙትን ሳይሆን ፥ ልቦናቸውና መንፈሳቸው
የተለወጠውን ነው። እንዲህ ያለ ሰው ምስ
ጋናን ከሰው ሳይሆን ከራሱ ከእግዚአብሔር
ይቀበላል።

## ምዕራፍ 3

1 ታዲያ ነገሩ እንዲህ ከሆነ ፥ አይሁዳዊ
በመሆን የሚገኘው ጥቅም ምንድን ነው?
የመገረዝስ ጥቅሙ እምኑ ላይ ነው? 2 በእር
ግጥም አይሁዳዊ መሆን በብዙ ረገድ
ጥቅም አለው። ምክንያቱም እግዚአብሔር
በመጀመሪያ ቃሉን እንዲጠብቁ አደራ የሰ
ጣቸው ለእነርሱ ነበር። 3 ከእነርሱ መካከል
አንዳንዶቹ የተሰጣቸውን ሕግ በታማኝነት
ጠብቀው አልተገኙም። ታዲያ እነርሱ የተ
ሰጣቸውን ሕግ ሳይጠብቁ በመቅረታቸው
እግዚአብሔር የሰጣቸውን ተስፋ ሳይፈጽም
ላቸው ቢቀር ቃለ አባይ ሊያደርገው ይች

ላል? ፈጽሞ አይችልም! 4 በመጽሐፍ፣
«የተናገርከው እውነት ሆኖ ይገኛል፤ባላጋ
ራህንም በፍርድ ትረታዋለህ» ተብሎ እንደ
ተጻፈ፣ሰዎች ሁሉ ሐሰተኞች ቢሆኑም እግ
ዚአብሔር እውነተኛ ነው።

5 ነገር ግን የእኛ ኃጢአተኛነት የእግዚ
አብሔርን ጽድቅ በሰዎች ዘንድ በግልጽ
እንዲታይ ካደረገ ምን እንላለን? ወይስ እን
ደሰዎች አስተሳሰብ የእኛ ኃጢአተኛነት
የእርሱን ጻድቅ መሆን ስለሚያሳይ፣እግዚአ
ብሔር ሊቀጣን አይገባም ለማለት እንችላ
ለን? 6 እንዲህ ያለውን ነገር ልንናገረው
ቀርቶ ልናስበውም አይገባንም። እንዲህ ከሆ
ነማ እግዚአብሔር በዓለም ላይ መፍረድ
አይችልም ማለት ነዋ! 7 ‘የእኔ መዋሸትና
ኃጢአተኛነት የእርሱን እውነተኛነት
አልቆ ካሳየና ክብሩንም ከፍ ከፍ ካደረገ፤
እንዴት በኃጢአቴ ሊፈርድብኝ ይችላል?’
እንል ይሆናል። 8 ይህን ዓይነት አስተሳሰብ
የሚኖረን ከሆነ፣ ‘መልካም ነገር እንድና
ገኝ፣ክፉ ነገር እናድርግ’ ወደሚለው አስተ
ሳሰብ ያደርሰናል። የዚህ ዓይነቱ አሳብ ያላ
ቸውን ሰዎች እግዚአብሔር እንደሚፈርድ
ባቸው ማወቅ አለብን። እኔም እንዲህ ያለ
ውን ትምህርት እንደማስተምር አድርገው
አንዳንድ ሰዎች መገመታቸው የሚገርም
ነው።

9 ታዲያ እኛ አይሁዶች ከአሕዛብ እንሻ
ላለን? አንሻልም። ምክንያቱም አይሁድም
ሆኑ አሕዛብ፣በጠቅላላው ሰዎች ሁሉ የኃ
ጢአት ተገዢ መሆናቸውን ከዚህ በፊት
በግልጽ ተነጋግረንበታል። 10 ስለዚህም
ጉዳይ በቅዱሳት መጻሕፍት፣ «ጻድቅ
የለም። ከሰዎች መካከል ጻድቅ የሆነ አንድ
ሰው እንኳ አይገኝም» ተብሎ ተጽፏል።

11 «አስተዋይ የሆነ፣ እግዚአብሔርን
የሚፈልግ ማንም የለም። 12 ሰዎች ሁሉ
ተሳስተዋል። ከእግዚአብሔርም መንገድ
ርቀዋል። መልካም የሚያደርግ አንድ ሰው
እንኳ የለም። 13 ንግግራቸው በመቃብር
ውስጥ ከበሰበሰ ሬሣ እንደሚወጣ ግማት
ነው። በምላሳቸው ያታልላሉ። ምላሳቸው
የእባብ መርዝ ይተፋል። 14 አፋቸው እርግ
ማንና መራርነት ሞልቶበታል። 15 እግሮቻ
ቸው የሰውን ደም ለማፍሰስ ፈጣኖች
ናቸው። 16 በየደረሱበት ሁሉ ሥቃይንና
መከራን ይፈጥራሉ። 17 የሰላምን መንገድ
አያውቁትም። 18 እግዚአብሔርንም አይፈሩ
ትም።»

19 በኦሪት ሕግ የተጻፈው ትእዛዝ ሁሉ
የሚመለከተው፣ ሕግ የተሰጣቸውን አይሁ
ድን ነው። ስለዚህ ራሱን ነፃ ለማውጣት
በእግዚአብሔር ፊት መልስ መስጠት የሚ
ችል ማንም የለም። የዓለምም ሕዝብ ሁሉ
ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች መሆኑን እና
ውቃለንና።

20 ምክንያቱም የሕጉን ትእዛዝ በመጠ
በቅ በእግዚአብሔር ፊት የጸደቀ ማንም
የለም። ሕግ የሚያገለግለው አንድ ሰው
ኃጢአት መሥራቱን እንዲያውቅ ለማድረግ
ብቻ ነው።

21 አሁን ግን በሙሴ የሕግ መጻሕፍትና
በነቢያት ትንቢት፣ይመጣል ተብሎ ይነገር
የነበረው፣ የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገል
ጧል። ይህም ጽድቅ በኦሪት ሕግ ላይ የተ
መሠረተ ስላይደለ፣ 22 በአይሁድና በአሕዛብ
መካከል ልዩነት ሳይኖር፣ኢየሱስ ክርስቶስን
ለሚያምኑ ሁሉ ይሰጣቸዋል። 23 ሰዎች
ሁሉ ኃጢአትን ስለ ሠሩ፣ የእግዚአብሔር
ክብር ርቋቸዋል። 24 ይሁን እንጂ ኢየሱስ
ክርስቶስን በማመን ምንም ዓይነት ዋጋ ሳን
ከፍል በምንቀበለው የእግዚአብሔር ጸጋ
ብቻ መጽደቅ እንችላለን።

25 በደሙ ያስገኘውን የኃጢአትን ሥር
የት በእምነት እንድንቀበል እግዚአብሔር
ኢየሱስ ክርስቶስን ወደዚህ ዓለም መሥዋ
ዕት አድርጎ ላከው። እግዚአብሔርም ይህ
ንን በማድረጉ የእርሱን የፍርድ መንገድ
ቅንነት ገልጿል። ለምን ቢባል ባለፉት ዘመ
ናት የተደረገውን ኃጢአት ሁሉ በትዕግ
ሥቱ ሸፍኖ እንዳለፈው ሁሉ፣ 26 በአሁኑ
ዘመን ደግሞ ይህን ያደረገው፣ራሱ ጻድቅ
እንደሆነና በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምነው
ንም እንደሚያጸድቅ ለማሳየት ነው።

27 ታዲያ ደኅንነታችንን ያገኘነው ‘በዚ
ህና በዚያ ነው’ ብለን መመካት እንችላ
ለን? ልንመካ የምንችልበት ምንም ነገር
የለም። እኛ ጽድቅን ያገኘነው፣ «መልካም
አድርጉ» የሚለውን የኦሪት ሕግ ትእዛዝ
በመጠበቅ ሳይሆን፣ ቤዛ የሆነልንን ክርስቶ
ስን በማመናችን ብቻ ነውና። 28 አንድ ሰው
በእግዚአብሔር ፊት የሚጸድቀው የሕጉን
ትእዛዝ በመጠበቅና በሚፈጽማቸው በጎ
ሥራዎች ሳይሆን በእምነቱ ነው።

29 እግዚአብሔር በዚህ መንገድ የሚያድ
ናቸው አይሁድን ብቻ ነውን? አይደለም!
አሕዛብም በዚሁ መንገድ የመዳን እድል
ተሰጥቷቸዋል። 30 እግዚአብሔር በሰዎች
መካከል አያዳላም። እርሱ የተገረዙትን አይ
ሁድም ሆነ፣ያልተገረዙትን አሕዛብ የሚያ

ጸድቀው በእምነታቸው ነው። [31] ታዲያ
የምንድነው በእምነት ከሆነ፥ሕግን እንሽራ
ለን? እንዴት ተደርጎ! እንደ እውነቱ ከሆነ
ለሕግ ተገቢውን ቦታ የምንሰጠው በኢየሱስ
ክርስቶስ ስናምን ብቻ ነው።

## ምዕራፍ 4

[1-2] እስቲ የአይሁድ ነገድ አባት ስለሆ
ነው ስለአባታችን ስለ አብርሃም እንነጋገር።
አብርሃም የጸደቀው በበጎ ሥራው ነውን?
ይህ ቢሆንማ ኖሮ የሚመካበት ነገር ይኖ
ረው ነበር። ነገር ግን አብርሃም፥ ‘ይህን በጎ
ሥራ ሠርቻለሁ’ ብሎ በእግዚአብሔር ፊት
የሚመካበት አንዳችም ነገር የለም። [3] ምክ
ንያቱም ስለ እርሱ በመጽሐፍ፥ «አብርሃም
በእግዚአብሔር አመነ፤ በማመኑም እንደ
ጽድቅ ተቆጠረለት» ተብሎ ተጽፏል።
[4] አንድ ሰው ሠርቶ የሚከፈለው ደመ
ወዝ የላቡ ዋጋ እንጂ እንደ ችሮታ የሚቆ
ጠርለት አይደለም። [5] እንዲሁም ደኅንነት
የሚገኘው በበጎ ሥራ ከሆነ፥ በእግዚአብ
ሔር ጸጋ የተገኘ ሊሆን አይችልም። ነገር
ግን አንድ ሰው በጎ ሥራ ባይኖረውም፥
ኃጢአተኞችን በቸርነቱ በሚያጸድቅ ጌታ
ካመነ፥እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል።
[6] ዳዊት ያለ ምንም በጎ ሥራ እግዚአብ
ሔር ያጸደቀው ሰው ስለሚቀበለው በረከት
እንዲህ ሲል ይናገራል፤ [7] «ኃጢአታቸው
ይቅር የተባለላቸውና የተደመሰሰላቸው
ሰዎች የተባረኩ ናቸው። [8] እግዚአብሔር
ኃጢአቱን የማይቆጥርበት ሰው የተባረከ
ነው።»
[9] ታዲያ ዳዊት የተናገረው ይህ የበረከት
ቃል ለተገረዙት ብቻ ነው? ወይስ ላልተገ
ረዙትም ጭምር? ላልተገረዙትም ጭምር
እንጂ ለተገረዙት ብቻ ነው አንልም። ምክ
ንያቱም ቀደም ሲል፥ «አብርሃም እግዚአብ
ሔርን አመነ፤በማመኑም ጸደቀ» ብለን ተና
ግረናልና ነው።
[10] አብርሃም በእምነት የጸደቀው መቼ
ነው? ከመገረዙ በፊት ነው? ወይስ ከተገ
ረዘ በኋላ? አብርሃም በእምነት የጸደቀው
ሳይገረዝ በፊት እንጂ ከተገረዘ በኋላ አይደ
ለም።
[11] አብርሃም የተገረዘው ጽድቅን ከእግዚ
አብሔር ከተቀበለ በኋላ ነው። ታዲያ የተገ
ረዘው ጽድቅን ከተቀበለ በኋላ ከሆነ መገ
ረዙ በእምነት መጽደቁን የሚያሳይ ምል
ክት ነው። ስለዚህ አብርሃም ሳይገረዙ በእ
ምነት ብቻ ለሚጸድቁ ሁሉ አባታቸው
ነው። [12] እንዲሁም አብርሃም ለተገረዙትም
አባት ነው። አባታቸው ሊሆን የቻለው በመ
ገረዛቸው ብቻ ሳይሆን እርሱ ከመገረዙ
በፊት የነበረውን እምነት ተቀብለው የእር
ሱን አርአያ በመከተላቸው ነው።
[13] እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ «አንተና
ዘርህ ዓለምን ትወርሳላችሁ» ብሎ ተስፋ
ሰጥቶት ነበር። አብርሃም ይህንን ተስፋ ከእ
ግዚአብሔር ሊቀበል የቻለው የሕጉን ትእ
ዛዝ በመፈጸሙ ሳይሆን፥ እግዚአብሔርን
በማመኑ ነው። [14] እግዚአብሔር የሰጠውን
ተስፋ፥ ሕግን በመጠበቅ ማግኘት ቢቻል
ኖሮ እምነት ከንቱ ነገር በሆነ ነበረ። እግዚ
አብሔርም ለሚያምኑት የሰጠው ተስፋ
ዋጋቢስ ሆኖ ይቀር ነበር። [15] ሕግ የእግዚአ
ብሔርን ፍርድ ያመጣል። ሕግ ከሌለ ግን
ሕግን መተላለፍ የሚባል ነገር ስለማይኖር
አይፈረድብንም ማለት ነው።
[16] አብርሃም እግዚአብሔር የሰጠውን
ተስፋ በእምነት ተቀበለ። ይህም ተስፋ
በጸጋ ላይ የተመሠረተ ነበር። አብርሃም
እግዚአብሔርን በማመኑ የሁላችንም አባት
ስለሆነ፥የሙሴ ሕግ የተሰጣቸውም ሆኑ የአ
ብርሃም እምነት ያላቸው ትውልዶች
ሁሉ፥ እንደ እርሱ በጸጋ የእግዚአብሔርን
ተስፋ ይወርሳሉ። [17] በመጽሐፍ ስለ አብር
ሃም፥ «የብዙ ሕዝብ አባት አደርግሃለሁ»
ተብሎ ተነግሮለታል። ስለዚህ አብርሃም
ለሙታን ሕይወት በሚሰጠው፥ያልነበረውን
ወደ መኖር በሚያመጣው ባመነበት በእግ
ዚአብሔር ፊት፥የሁላችንም አባት ነው።
[18] አብርሃም፥ በሥጋ ተስፋ የሚደረግ
አንዳች ነገር ሳይኖር የእግዚአብሔርን የተ
ስፋ ቃል ብቻ ይዞ አመነ። ስለዚህም
«ዘርህ ይበዛልሃል» ተብሎ በተነገረው መሠ
ረት የብዙ ሕዝብ አባት ሆነ። [19] ይህ ተስፋ
በተነገረው ጊዜ አብርሃም የመቶ ዓመት
ሽማግሌ ነበር። ሣራም አርጅታ አፍጅታ
ነበር። ይሁን እንጂ አብርሃም እምነተ ጽኑ
ስለነበረ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ
ተቀብሎ ልጅ እንደሚወልድ አመነ።
[20] አብርሃም እግዚአብሔር የሰጠውን
ተስፋ እንደሚፈጽምለትም አልተጠራጠ
ረም። እምነተ ጽኑ ስለ ነበረም፥ተስፋው
ከመፈጸሙ በፊት አስቀድሞ ለእግዚአብ
ሔር ምስጋና አቀረበ። [21] እግዚአብሔር የሰ
ጠውን የተስፋ ቃል ለመፈጸም እንደሚ
ችል እርግጠኛ ነበረና። [22] ስለዚህ እግዚአብ
ሔር አብርሃምን ስለ እምነቱ አጸደቀው።

23 ይህ፥ «ስላመነ ጸደቀ» የሚለው ቃል
የተጻፈው ስለ አብርሃም ብቻ አይደለም።
24 ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን
ከሞት ባስነሣው አምላክ ለምናምን ለእ
ኛም ጭምር ነው። እግዚአብሔር እኛንም
እንደ አብርሃም በእምነታችን ያጸድቀናል።
25 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታ
ችን ሞተ። በእግዚአብሔርም ፊት ሊያጸድ
ቀን ከሞት ተነሣ።

## ምዕራፍ 5

1 ስለዚህ በእምነት ከጸደቅን፥ በጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር እው
ነተኛ ሰላምን አግኝተናል። 2 በማመናችንም
የእግዚአብሔርን ጸጋ ተሳታፊዎች ወደሆን
በት፥ አሁን ወደምንገኝበት መንፈሳዊ ሕይ
ወት አድርሶናል። የእግዚአብሔር ክብር
ተካፋዮች እንድንሆን በተሰጠንም ተስፋ
እንመካለን።
3 እንዲሁም ትዕግሥትን እንደምንማር
በማወቅ መከራና ችግር ሲደርስብን እንደሰ
ታለን። 4 ትዕግሥት እምነታችን እንዲጸና
ተስፋችንም እየበረታ እንዲሄድ ስለሚያደ
ርግ መንፈሳዊ ብርታትን ይሰጠናል። 5 በተ
ሰጠን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የእግዚአ
ብሔር ፍቅር በልባችን ፈሶአልና የተቀበል
ነው ተስፋ አያሳፍረንም።
6 የሚረዳን አጥተን፥ ግራ ተጋብተን ሳለ
እግዚአብሔር በወሰነው ትክክለኛ ጊዜ ክር
ስቶስ ለእኛ ለኃጢአተኞች ሲል ሞተልን።
7 ለጻድቅ ሰው ሲል ሕይወቱን አሳልፎ የሚ
ሰጥ ሰው ማግኘት በጣም ያስቸግራል።
በደግ ሰው ምትክ ግን ለመሞት ፈቃደኛ
የሚሆን ምናልባት ሊገኝ ይችል ይሆናል።
8 ነገር ግን እግዚአብሔር የቱን ያህል የወደ
ደን መሆኑን እስቲ አስቡ። ኃጢአተኞች
ሆነን ሳለ ክርስቶስ ስለ እኛ ሞተልን።
9 ደሙን አፍስሶ ከኃጢአታችን በማንጻት
ካጸደቀንም፥ ከሚመጣው ከእግዚአብሔር
ቁጣ ደግሞ እንደሚያድነን አንጠራጠርም።
10 እግዚአብሔር ገና ጠላቶቹ ሳለን በልጁ
ሞት ከታረቀን፥ ዕርቅን ካገኘን በኋላማ
በልጁ ሕይወት እንደሚያድነን ምን ጥያቄ
አለው!
11 ይህም ብቻ አይደለም። በልጁ በኢየ
ሱስ ክርስቶስ አስታራቂነት ይቅርታውን ባገ
ኘንበት በእግዚአብሔር ደስ ይለናል፤ ሐሴ
ትም እናደርጋለን።
12 በአንዱ አዳም ምክንያት ኃጢአት
ወደ ዓለም ገባ። በኃጢአትም ምክንያት
ሞት ወደ ሰው ልጆች ሁሉ ተላለፈ። ሰዎ
ችም ሁሉ ኃጢአተኞች ስለሆኑ በሞት ጥላ
ሥር ወደቁ። 13 የሙሴ ሕግ ከመምጣቱ
አስቀድሞ ኃጢአት በዓለም ላይ ነበር።
ነገር ግን በዚያን ጊዜ ኃጢአትን የሚከለ
ክል ሕግ ስላልነበረ፥ ሕጉን መተላለፍ እንደ
ኃጢአት አይቆጠርም ነበር። 14 ይሁን
እንጂ ከአዳም እስከ ሙሴ ድረስ በሰው
ሁሉ ላይ ሞት ነገሠ። ሌላው ቀርቶ ኃጢአ
ታቸው እንደ አዳም የእግዚአብሔርን ትእ
ዛዝ መተላለፍ ባልሆነው ሁሉ ላይ ሠፈነ።
አዳምም ሊመጣ ወዳለው ወደ ክርስቶስ
ያመለክታል። እዚህ ላይ በአዳምና ከእርሱ
በኋላ ወደ ዓለም በመጣው በክርስቶስ መካ
ከል፥ 15 እንዲሁም በእግዚአብሔር ይቅር
ታና በሰው በደል መካከል ያለውን ታላቅ
ልዩነት እንመልከት። የአንዱ የአዳም ኃጢ
አት በብዙ ሰዎች ላይ ሞትን አመጣ። ነገር
ግን በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚ
አብሔር ስጦታና ምሕረት ለብዙ ሰዎች
ደረሰ። 16 የስጦታው ውጤት፥ ከአንዱ ሰው
ማለትም ከአዳም ኃጢአት ውጤት፥ እንደ
ሚበልጥም በተጨማሪ ልብ እንበል። የእግ
ዚአብሔር ፍርድ በአንድ ኃጢአት ምክን
ያት በሰው ሁሉ ላይ ኩነኔን አመጣ። ስጦ
ታው ግን በብዙ ኃጢአት ላይ ይቅርታን
በማስገኘት ጽድቅን አመጣ።
17 በአንድ ሰው ውድቀት ምክንያት
ሞት በዚሁ በአንድ ሰው በኩል በሁሉ ላይ
የሠለጠነ ከሆነ፥የተትረፈረፈውን የእግዚአብ
ሔርን ጸጋ በነፃ የተቀበሉና የጸደቁ ሁሉ
በአንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በበ
ለጠ በሕይወት ይኖራሉ። 18 የአዳም አንድ
በደል በሰዎች ሁሉ ላይ ቅጣትን ሲያመጣ፥
የክርስቶስ አንድ የጽድቅ ሥራ ግን፥ሰዎች
ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁና በሕይ
ወት እንዲኖሩ አድርጎአቸዋል። 19 አዳም
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመተላለፉ ብዙ
ዎችን ኃጢአተኞች አድርጓቸዋል። ክርስ
ቶስ ግን ለአባቱ በመታዘዙ ብዙዎችን አጽ
ድቋቸዋል።
20 ሕግ በመኖሩ ሕግን የሚተላለፉ ሁሉ
ኃጢአት ምን መሆኑን ያውቃሉ። ነገር ግን
ኃጢአተኛነታችንን በይበልጥ እየተረዳን
በሄድን ቁጥር ተትረፍርፎ የተሰጠን የእግዚ
አብሔር የይቅርታ ጸጋ ምን ያህል ታላቅ
እንደሆነ እንገነዘባለን። 21 ሞት ባለበት ቦታ
ኃጢአት እንደነገሠ ሁሉ፥ በጌታችን በኢየ
ሱስ ክርስቶስ የዘላለምን ሕይወት የሚያስገ
ኘው ጸጋ ጽድቅ ባለበት ሁሉ ይነግሣል።

## ምዕራፍ 6

1 ታዲያ እግዚአብሔር ጸጋውን ያበዛል
ናል በማለት ኃጢአት መሥራታችንን መቀ
ጠል አለብን ማለት ነውን?
2-3 እግዚአብሔርም አይበለው! ከእርሱ
ጋር ሕብረት እንዲኖረን በጌታችን በኢየሱስ
ስም በተጠመቅንበት ጊዜ፣ ኃጢአት መሥ
ራት የሚቀናው አሮጌው ባሕርያችን ከእ
ርሱ ጋር የሞተ መሆኑን እንዴት ዘነጋች
ሁት? 4 ለኃጢአት ሲገዛ የኖረው አሮጌው
ባሕርያችን በክርስቶስ ሞት አብሮት የተቀ
በረ ሲሆን፣ በአዲስ ሕይወት እንድንኖርም
እግዚአብሔር አብ በኃይሉ ግርማ ክርስቶ
ስን ከሞት እንዳስነሣው እኛንም አስነሥቶ
ናል።
5 በሞቱ እርሱን ከመሰልነው በትንሣኤ
ውም እንመስለዋለን። 6 ከእንግዲህ ወዲህ
ለኃጢአት እንዳንገዛ አሮጌው ባሕርያችን
ከክርስቶስ ጋር በመስቀል ላይ ተሰቅሎአል።
7 አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ከኃጢአት ባር
ነት ነፃ ይሆናልና። 8 ከክርስቶስ ጋር ከሞ
ትን በኋላ በአዲስ ሕይወት ከእርሱ ጋር እን
ደምንኖር እናምናለን። 9 ክርስቶስ ከሞት
እንደተነሣ፣ ዳግመኛም እንደማይሞትና ከእ
ንግዲህ ወዲህ ሞት በእርሱ ላይ ሥልጣን
እንደሌለው እናውቃለን። 10 ክርስቶስ በኃ
ጢአት ምክንያት አንድ ጊዜ ሞቷል። ከአ
ሁን ወዲያ ግን ለዘላለም ለእግዚአብሔር
ይኖራል። 11 እናንተም ከኃጢአት ሥልጣን
ነፃ ለመሆን እንደሞታችሁና በኢየሱስ ክር
ስቶስ ሕያው ሆናችሁ ለእግዚአብሔር እን
ደምትኖሩ አድርጋችሁ ራሳችሁን ቁጠ
ሩት።
12 ስለዚህ ኃጢአት በሚች ሥጋችሁ ላይ
እንዳይሠለጥንበት ለሥጋችሁ ፈቃድ አት
ገዙ። 13 ማንኛውንም የሰውነታችሁን
ክፍል ለክፋትና ለኃጢአት መሣሪያ አድር
ጋችሁ አታቅርቡ። ነገር ግን ከሞት የተነሣ
ችሁ እንደመሆናችሁ መጠን፣ ለበጎ ተግባር
መገልገያ እንዲሆን የሰውነታችሁን ክፍ
ሎች በሙሉ የጽድቅ መሣሪያ አድርጋችሁ
ለእግዚአብሔር አቅርቡለት። 14 ከዚህ
በኋላ፣ የምትኖሩት ለኦሪት ሕግ በመታዘዝ
ሳይሆን ለእግዚአብሔር ጸጋ በመገዛት በመ
ሆኑ፣ ኃጢአት በሕይወታችሁ ላይ ሊነግሥ
አይችልም።
15 ታዲያ፣ የእግዚአብሔር ጸጋ ከኃጢ
አት ነፃ አውጥቶናል ብለን እንዳሻን ኃጢ
አት እንሥራ ማለት ነውን? በፍጹም
አይደለም።
16 ለአንድ ሰው አገልጋይ ሆናችሁ ስታ
ድሩለት ያ ሰው በሚያዛችሁ ጊዜ ሁሉ
ፈቃዱን መፈጸም እንዳለባችሁ የታወቀ
ነው። ሞትን ለሚያስከትልባችሁ ኃጢአት፣
ወይም ጽድቅን ለሚሰጣችሁ እግዚአብ
ሔር፣ ከሁለት ለአንዱ መታዘዝም እንደዚሁ
ነው። 17 ምንም እንኳ ከዚህ በፊት ለኃጢ
አት ተገዢዎች ሆናችሁ ብትኖሩም፣ ለእግ
ዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና፣ የተማ
ራችሁትን የእውነት ቃል በመቀበል 18 ከኃ
ጢአት ቀንበር ነፃ ወጥታችሁ የጽድቅ ተገ
ዢዎች ሆናችኋል።
19 ፍሬ ነገሩን በቀላሉ ለመረዳት እንድ
ትችሉ ከፍ ብዬ በጠቀስኩት ምሳሌ መሠ
ረት፣ ከዚህ በፊት ራሳችሁን ለርኩሰትና
ለልዩ ልዩ ኃጢአት ተገዢ አድርጋችሁት
ነበር። ከእንግዲህ ወዲህ ግን፣ ለጽድቅና ለቅ
ድስና አገልጋዮች እንድትሆኑ መላ ሰውነታ
ችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡለት።
20 የኃጢአት ተገዢዎች በነበራችሁበት
ጊዜ ጽድቅን ለማድረግ ምንም ፍላጎት አል
ነበራችሁም። 21 ያን ጊዜ በደስታ ትፈጽ
ሙት ከነበረው፣ ዛሬ ግን ከምታፍሩበት
መጥፎ ተግባር ያገኛችሁት አንዳችም
ጥቅም የለም። እነዚህን ነገሮች በማድረጋ
ችሁ ያተረፋችሁት ነገር ቢኖር ሞት ብቻ
ነበር። 22 ዛሬ ግን ከኃጢአት ባርነት ነፃ
ወጥታችሁ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሆና
ችኋል። ከእርሱ የሚገኘውንም ቅድስናና
የዘላለም ሕይወት ተቀብላችኋል።
23 የኃጢአት ዋጋ ሞት ነው። በጌታችን
በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር
የምንቀበለው ስጦታ ግን የዘላለም ሕይወት
ነው።

## ምዕራፍ 7

1 ወንድሞቼ ሆይ፣ ሕግን ጠንቅቃችሁ
የምታውቁ ናችሁና መቼም ሕግ በሰው ላይ
ሥልጣን ያለው ሰውየው በሕይወተ ሥጋ
እስካለ ድረስ ብቻ መሆኑን ትገነዘባላችሁ።
2 አንዲት ባለትዳር ሴት ባልዋ በሕይ
ወተ ሥጋ እስካለ ድረስ በጋብቻ ውል የታ
ሠረች ናት። ባልዋ ከሞተ በኋላ ግን፣ የጋብ
ቻው ውል እንደቀረ ስለሚቆጠር ከታሠረች
በት የጋብቻ ሕግ ነፃ ትሆናለች። 3 ባልዋ
በሕይወተ ሥጋ እያለ ግን ሌላ ወንድ ብታ
ገባ በሕግ ፊት እንዳመነዘረች ትቆጠራለች።
ባልዋ ከሞተ በኋላ ግን ከታሠረችበት የጋ
ብቻ ሕግ ነፃ ስለምትሆን፣ ሌላ ወንድ ማግ

ባት ትችላለች። አመንዝራ ተብላም አትቆ
ጠርም።
4 እንዲሁም ወንድሞቼ ሆይ፣በክርስቶስ
ሞት አማካይነት፣ ለኦሪት ሕግ እናንተም
ሞታችኋል። አሁን ግን፣ለእግዚአብሔር አገ
ልግሎት የተለያችሁ እንድትሆኑ ከሞት
የተነሣው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ገንዘ
ቦች ሆናችኋል። 5 ለሥጋችን ፈቃድ ተገዝ
ተን በነበርንበት ዘመን ሕጉ ያሳወቀን ክፉ
ምኞቶች በልቦናችን እየተጠነሰሱ የእግዚአ
ብሔርን ትእዛዝ ስናፈርስ፣ኃጢአት በመሥ
ራታችንም የሞትን ፍሬ ስናጭድ ኖረናል።
6 አሁን ግን ከክርስቶስ ጋር አብረን በመሞ
ታችን፣አሥሮ ይገዛን ከነበረው ከሕግ ባር
ነት ነፃ ወጥተናል። ከእንግዲህ ወዲህ የምና
ገለግለው ከመንፈስ ቅዱስ ባገኘነው አዲስ
ሕይወት እንጂ በኦሪት ሕግ መሠረት አይደ
ለም።

7 ነገሩ እንዲህ ከሆነ፣ሕግ ራሱ ኃጢአት
ነበር ማለት እንችላለን? ፈጽሞ አንችልም!
ምክንያቱም ኃጢአት ምን መሆኑን ለማ
ወቅ የቻልነው ሕግ በመኖሩ ነው። ሕጉ፣
«ክፉ ነገር አትመኝ» ባይል ኖሮ፣ክፉ ነገር
መመኘት ኃጢአት መሆኑ በምን ይታወቅ
ነበር? 8 ኃጢአት ሕግን መሣሪያ በማድረግ
ልዩ ልዩ ክፉ ምኞት በውስጤ እንዲፈጠር
አደረገ። ሕግ ከሌለ ኃጢአትም እንደሌለና
እንደሞተ ይቆጠራል።
9 ሕግ ከመደንገጉ በፊት ሕያው ነበ
ርኩ። ሕጉ ተደንግጎ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ
ግን፣ ኃጢአት ሕይወት ዘራ፤በእኔ ላይም
ሞትን አስከተለ። 10 ሕይወት እንዳገኝበት
የተሰጠኝም ያ ሕግ አጥፊዬ ሆኖ ተገኘ።
11 ስለዚህ ኃጢአት ሕግን መሣሪያ በማድ
ረግ አታለለኝ። የሕጉን ትእዛዝ በመተላለ
ፌም ገደለኝ። 12 ስለዚህ ልብ ብለን ካስተዋ
ልነው ሕጉ ቅዱስ ነው። ትእዛዛቱም የተቀ
ደሱ፣መልካምና ትክክለኛ ናቸው።
13 ታዲያ ሞትን ያመጣብኝ—ያ መል
ካሙ ነገር—ሕግ፣ነውን? ሊሆን አይችልም።
ሞትን ያመጣው ሕግ ሳይሆን ኃጢአት
ነው። ኃጢአት ሕግን መሣሪያ አድርጎ
ሞትን ሊያስከትልብኝ ችሏልና። በዚህም
በሕግ ትእዛዝ አማካይነት፣የኃጢአት ትክክ
ለኛ መልኩ ሊገለጥ ችሏል። 14 ሕግ መንፈ
ሳዊ መሆኑን እናውቃለን። ችግሩ ከሕግ
አይደለም። ነገር ግን ለኃጢአት ባሪያ ሆኜ
የተሸጥኩ እኔ መንፈሳዊነት የሌለኝ ሰው
ነኝ።
15 እኔ የማደርገውን ለይቼ አላውቅም።
ከዚህ የተነሣም የምወደውን ነገር በማድ
ረግ ፈንታ የማልወደውን ነገር ሳደርግ እገ
ኛለሁ። 16 የማልወደውን የማደርግ ከሆ
ነም፣ሕጉ ትክክለኛ መሆኑን ሕሊናዬ ተረ
ድቶታል ማለት ነው። 17 እንደ እውነቱ
ከሆነ እነዚህን የማልወዳቸውን ነገሮች የማ
ደርገው፣ ወድጄ ሳይሆን በውስጤ ያለው
ኃጢአት እየገፋፋኝ ነው።
18 ከእኔ ኃጢአተኛ ባሕርይ ምንም ዓይ
ነት በጎ ነገር እንደማይገኝ አውቃለሁ። በጎ
ነገር ለማድረግ ፍላጎት ቢኖረኝም እንኳ፣
ይህንኑ በሥራ ላይ ማዋል አይሆንልኝም።
19 የምፈልገውን መልካም ነገር ላድርግህ
ስለው አይሳካልኝም። የማልወደውን መጥፎ
ነገር ግን ላደርገው ባልፈልግም፣ሳደርገው
እገኛለሁ። 20 እንግዲህ ማድረግ የማልፈልገ
ውን ነገር ሳደርግ የምገኘው፣ወድጄ ሳይ
ሆን በውስጤ ያለው ኃጢአት እየገፋፋኝ
ነው።
21 ስለዚህ ይህን የመሰለ ሕግ በሥራ ላይ
ሆኖ አየዋለሁ። በጎ ነገር ለማድረግ በምነሣ
በት ጊዜ ከዚህ መጣ ሳልለው፣ክፉው ነገር
ተሽቀዳድሞ ከተፍ ይላል። 22-24 ውስጣዊ
ሕይወቴ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ቢፈጽም
ደስ ይለዋል። ሥጋዊ ባሕርዬ ውስጥ ግን
ሌላ የኃጢአት ሕግ ይገኛል። ይህም የኃጢ
አት ሕግ በልቦናዬ ውስጥ ካለው የእግዚአ
ብሔር ሕግ ጋር ጦርነት ገጥሞ ይዋጋዋል።
ያ በሥጋዊ ባሕርዬ ውስጥ ያለው የኃጢ
አት ሕግ፣ድል ነሥቶ ባርያው ያደረገኝም
ስለዚህ ነው። እንግዲህ እንዲህ ካለው አስቸ
ጋሪ ጣጣ ውስጥ ነው የገባሁት። ለመሆኑ
ምን ዓይነት ጐስቋላ ሰው ነኝ? ከዚህ
ለሞት ከተሰጠ ሰውነትስ ማን ይገላግለ
ኛል? 25 በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግ
ዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው። በውስጣዊ
ልቦናዬ የእግዚአብሔር ሕግ ተገዢ ስሆን፣
በሥጋዊ ባሕርዬ ግን የኃጢአት ሕግ አገል
ጋይ ነኝ።

## ምዕራፍ 8

1 ከእንግዲህ ወዲህ የኢየሱስ ክርስቶስ
ወገኖች የሆኑ ኵነኔ የለባቸውም። 2 ምክንያ
ቱም በክርስቶስ ኢየሱስ ያገኘሁት ሕይወ
ትን የሚሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል፣
ከታሠርኩበት ከኃጢአትና ከሞት ሕግ ነፃ
አውጥቶኛልና። 3 ከሥጋዊ ባሕርያችን የተ
ነሣ ሕግ ሊፈጽመው ያቃተውን፣እግዚአብ
ሔር አንድ ልጁን ኃጢአተኛ በሆነ በሰው
ሥጋ አምሳል ወደዚች ዓለም ልኮ፣ኃጢአ

ትን እንዲያስወግድ አድርጎታል። 4 ይህን
ንም ያደረገው ለሥጋ ፈቃዳችን ሳንገዛ መን
ፈስ ቅዱስን በመታዘዝ ለምንኖር ፤ በሕግ
በኩል የሚፈለግብን ትእዛዝ እንዲፈጸም
ነው።

5 ደካማ ለሆነው የሥጋ ፈቃዳቸው የሚ
ገዙ ሥጋዊ ፍላጎታቸውን ለመፈጸም የሚያ
ስችላቸውን ነገር ብቻ ይመኛሉ። ለመንፈስ
ቅዱስ ፈቃድ የሚገዙ ግን እግዚአብሔርን
ደስ የሚያሰኝ ሥራ ለመሥራት ያስባሉ።
6 ስለ መንፈሳዊ ነገሮች ማሰብ ሕይወትን
ያስገኛል ፤ ሰላምንም ይሰጣል። ስለ ሥጋዊ
ነገሮች ማሰብ ግን ሞትን ያስከትላል።
7 ምን ጊዜም ቢሆን ሥጋዊ ተፈጥሮ ለእግዚ
አብሔር ሕግ ስለማይታዘዝ፥ መታዘዝም ስለ
ማይችል የእግዚአብሔር ጠላት ነው።
8 ለሥጋዊ ፈቃድ የሚገዙ እግዚአብሔርን
ደስ ማሰኘት አይችሉም።

9 እናንተ ግን እንደዚህ አይደላችሁም።
የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረባችሁ ስለሆነ
ለሥጋዊ ፈቃድ አትገዙም። የክርስቶስ መን
ፈስ የማያድርበት ሰው የክርስቶስ ወገን
ሊሆን አይችልም። 10 ሥጋችሁ በኃጢአት
ምክንያት የሞተ ቢሆንም፥ ክርስቶስ በውስ
ጣችሁ ካደረ መንፈሳችሁ ከጽድቅ የተነሣ
ሕያው ይሆናል። 11 ኢየሱስን ከሞት ያስነ
ሣው የእግዚአብሔር መንፈስ ካደረባችሁ፥
ይኸው መንፈሱ የሚሞተው ሥጋችሁን
ሕይወት ያለው ያደርገዋል።

12 ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ ፥ ለሥጋዊ
ፈቃድ ተሸንፋችሁ ልትገዙለት አይገባም።
13 ለሥጋ ፈቃዳችሁ ተገዢዎች ከሆናችሁ
ትሞታላችሁ። የሥጋ ፈቃዳችሁን በመንፈስ
ቅዱስ ኃይል ድል ከነሳችሁት ግን በሕይ
ወት ትኖራላችሁ። 14 በእግዚአብሔር መን
ፈስ የሚመሩ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች
ናቸው።

15 ስለዚህ የተሰጠን መንፈስ በአባቱ
እቅፍ እንዳለ ልጅ፥ 'አባ፥ አባባ!' ብለን
በድፍረት እግዚአብሔርን የምንጠራበት
የልጅነት መንፈስ እንጂ፥የሚያስፈራና የሚ
ያሸማቅቅ የተገዢነት መንፈስ አይደለም።
16 በእርግጥም የእግዚአብሔር ልጆች መሆ
ናችንን፥ራሱ መንፈስ ቅዱስም ሆነ የራሳች
ንም መንፈስ ያረጋግጥልናል። 17 የእግዚአብ
ሔር ልጆች ከሆንን፥ወራሾች ነን። ከልጁ
ከኢየሱስ ክርስቶስም ጋር አብረን የርስቱ
ተካፋዮች እንሆናለን። ከእርሱ ጋር አብረን
መከበር የምንችለውም ፥ የክርስቶስ የመከ
ራው ተካፋዮች ሆነን ስንገኝ ነው።

18 ይህ አሁን የምንቀበለው መከራ ወደ
ፊት ከሚጠብቀን ክብር ታላቅነት ጋር
ሊመዛዘን አይችልም። 19 የእግዚአብሔር
ልጆች የሚገለጡበትን ያችን ዕለት ፍጥረት
ሁሉ በትዕግሥትና በተስፋ ይጠባበቃል።
20-21 በራሱ ፈቃድ ሳይሆን በእግዚአብሔር
ፍርድ ኃጢአትና ሞት የሰፈነበት ፍጥረታ
ዊው ዓለም፥እነዚህ ሁሉ ነገሮች ተወግደው
ለት፥ የእግዚአብሔር ልጆች የሚቀዳጁትን
የክብር ነፃነት ተካፋይ ለመሆን በተስፋ
ይጠባበቃል።

22 እስካሁን ድረስም ፍጥረት ሁሉ
በምጥ ጣር ተይዞ እንደሚቃትት እናውቃ
ለን። 23 የሚቃትተውም ፍጥረት ብቻ አይ
ደለም። ወደ ፊት ተዘጋጅቶ ለሚጠብቀን
ክብር መነሻና መሠረት የሆነውን የመንፈስ
ቅዱስን ስጦታ የተቀበልን ሁላችን፥ 'ያች
ዕለት ከመቼ መቼ ደርሳ እግዚአብሔር በስ
ጠን ተስፋ መሠረት፥ሕመምና ሞት የማይነ
ካውን አዲስ አካል ለብሰን፥የልጅነት ማዕር
ጋችንን እንቀበል ይሆን?' ብለን እንቃትታ
ለን፤እንናፍቃለንም።

24 በዚህ ተስፋ ድነናል። በዓይነ ሥጋ
የምናየውንና በእጃችን የገባውን ነገር ገና
ወደፊት እንደምናገኘው አድርገን በተስፋ
አንጠብቀውም። 25 እግዚአብሔር ይሰጠናል
ብለን በተስፋና በትዕግሥት የምንጠብቀው
ገና በእጃችን ያልገባውን ነገር ነው።

26 እንደዚሁም በየዕለቱ በሚገጥመን
ችግርና በምንጸልይበትም ጊዜ ፥ የመንፈስ
ቅዱስ እርዳታ አይለየንም። ለምንና እን
ዴት መጸለይ እንደሚገባን በውል ለይተን
ስለማናውቅ ፥ መንፈስ ቅዱስ ራሱ ቃላት
በትክክል ሊገልጡት በማይቻል ሁናቴ ይጸ
ልይልናል። 27 መንፈስ ቅዱስ ስለ እኛ በሚ
ጸልይበት ጊዜ ስለ ምን እንደሚጸልይልን
የሰዎችን ሁሉ ልብ ገልጦ የሚመረምረው
እግዚአብሔር ያውቀዋል። ምክንያቱም
መንፈስ ቅዱስ ለቅዱሳን የሚጸልየው እንደ
እግዚአብሔር ፈቃድ ነውና። 28 እግዚአብ
ሔርን የምንወደው ከሆነና እንደ ፈቃዱም
የተጠራን ከሆነ ፥ የሚደርስብን ነገር ሁሉ
ለእኛው ጥቅም እንደሚሆን እናውቃለን።

29 ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ በብዙ ወንድ
ሞች መካከል በኩር እንዲሆን ፥ እግዚአብ
ሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን ሁሉ ልጁን
እንዲመስሉ ወሰነ። 30 ስለዚህ እግዚአብ
ሔር ቀደም ብሎ የወሰናቸውን ጠራቸው።
የጠራቸውንም አጽድቆ የክብሩ ተካፋዮች
አደረጋቸው።

31 ታዲያ ከዚህ በኋላ ምን የሚጨመር
ነገር ይኖራል? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር
ከሆነ ማንስ ሊቃወመን ይችላል? 32 እግዚ
አብሔር ለገዛ ልጁ እንኳ ሳይራራ ስለ እኛ
እንዲሞት አሳልፎ ከሰጠው፥ ከእርሱ ጋር
አብሮ ሁሉንም ነገር እንዴት አትረፍርፎ
አይሰጠንም?

33 እግዚአብሔር የመረጣቸውን ሰዎች
ማን ሊከሳቸው ይችላል? የሚያጸድቅ እግ
ዚአብሔር ነው።

34 የሚፈርድባቸውስ ማነው? ኢየሱስ
ክርስቶስ ይፈርድባቸዋልን? እንዴት ተደ
ርጎ! ስለ እኛ የሞተውና ከሞት ተነሥቶም
በእግዚአብሔር አብ ቀኝ የተቀመጠው ጌታ
ችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይማልድልናል።

35 ይህ ከሆነ ከክርስቶስ ፍቅር ማን ሊለ
የን ይችላል? መከራ፥ ጭንቀት፥ ረሃብ፥
ስደት፥ መገረፍ፥ ፍርሃት፥ የተመዘዘ ሰይፍ፥
የትኛውም ዓይነት ችግር፥ ሞትም ቢሆን
ከክርስቶስ ፍቅር ሊለየን አይችልም።

36 «ስለ አንተ ፍቅር በየቀኑ እንገደላ
ለን። እንደሚታረዱ በጎችም ተቆጠረናል»
ተብሎ በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈ ስለሆነ
እነዚህ ነገሮች ሁሉ እንደሚደርሱብን አው
ቀን እንጠብቃለን።

37 እነዚህ ሁሉ ነገሮች በሕይወት ዘመና
ችን ቢያጋጥሙንም፥ በወደደን በጌታችን
በኢየሱስ ክርስቶስ ከድል አድራጊዎች
በላይ ነን። 38 ከዚህም የተነሣ፥ ሞትም ሆነ
ሕይወት፥ መላእክትም ሆኑ መናፍስት፥
አሁን ያለውም ሆነ ወደፊት የሚመጣው፥
39 ማንኛውም፥ 'አለሁ' የሚል ኃይል፥ ከፍ
ታም ሆነ፥ ዝቅታ፥ ወይም ማናቸውም ፍጥ
ረት ቢሆን፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ
ካገኘነው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እን
ደማይችል ተረድቻለሁ።

## ምዕራፍ 9

1 በክርስቶስ ውስጥ ሆኜ እውነትን እናገ
ራለሁ። እንደማልዋሽም መንፈስ ቅዱስ
ለሕሊናዬ ያረጋግጥልኛል። የሥጋ ዘመዶቼ
ስለሆኑት ስለወንድሞቼ ስለእሥራኤላውያን
ሳስብ 2-3 ልቦናዬ ከባድ ኀዘን ሳይሰማው፥
መንፈሴም ክፉኛ ሳይጨነቅ ውሎ ያደረበት
ቀን የለም። እነርሱ ይዳኑልኝ እንጂ ከክርስ
ቶስ ተለይቼ ኲነኔ እንኳ ቢደርስብኝ ቅር
አይለኝም። 4 እነርሱ እግዚአብሔር ከዓለም
ሕዝብ ለይቶ የመረጣቸው፥ ልጆቹ ያደረጋ
ቸው፥ ክብሩን የገለጠላቸው፥ ቃል ኪዳን የገ
ባላቸው፥ ሕጉን የሰጣቸው፥ የአምልኮን ሥር
ዓት ያስተማራቸው የተስፋውንም ቃል የሰ
ጣቸውና 5 የአሥራ ሁለቱ ነገደ እሥራኤል
አባቶች ዝርያ ናቸው። ከሁሉ በላይ የሆነ
ውና ለዘላለም የተባረከው አምላክ ጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ የተወለደው ከእ
ነርሱው ወገን ነው። እርሱም ለዘላለም የተ
መሰገነ ነው፤አሜን!

6 ይህ ከሆነ፥ ታዲያ እግዚአብሔር ለአይ
ሁድ ሕዝብ የሰጠውን ተስፋ ሽሮታል
ማለት ነው? ይህን ማለት አይቻልም። ምክ
ንያቱም ከእሥራኤል ዘር የተወለዱ ሁሉ
እሥራኤላውያን ናቸው ማለት አይደለም።
7 በልደተ ሥጋ ከአብርሃም ዘር ስለተገኙ
ብቻ የአብርሃም ልጆች ናቸው ማለት አይ
ቻልም። አብርሃም ሌሎች ልጆች እንዳሉት
ቢታወቅም፥ ተስፋ የተነገረለት ለልጁ ለይስ
ሐቅና ከእርሱም ለሚገኘው ልጅ ለያዕቆብ
ዘር መሆኑ በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፏል።
8 ይህም ማለት በሥጋ ከአብርሃም ተወለዱና
ሁሉም የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው
ማለት አይደለም። የእግዚአብሔር ልጆች
ተብለው የሚቆጠሩት፥ እግዚአብሔር ለአብ
ርሃም በገባለት የተስፋ ቃል መሠረት የተወ
ለዱለት ብቻ ናቸው።

9 እግዚአብሔር፥ «የዛሬ ዓመት መጥቼ
እጐበኛችኋለሁ። ሚስትህ ሣራም ወንድ
ልጅ ትወልድልሃለች» የሚል የተስፋ ቃል
ለአብርሃም ሰጥቶት ነበር። 10 ይህም ብቻ
አይደለም። ርብቃ ከአባታችን ከይስሐቅ
መንታ ልጆች በፀነሰች ጊዜ፥ 11 ልጆቹ ተወ
ልደው አድገው ክፉ ወይም ደግ ከመሥራ
ታቸው በፊት ገና በእናታቸው ማሕፀን ሳሉ
እግዚአብሔር ለርብቃ፥ 12 «ታላቁ ለታናሹ
ይገዛል» ብሏታል። ይህም 13 «ያዕቆብን
ወደድኩ፤ዔሳውን ግን ጠላሁ» ተብሎ በቅ
ዱሳት መጻሕፍት የተጻፈው ቃል እግዚአብ
ሔር የሰውን ድርጊት ተከትሎ ሳይሆን፥ማን
ኛውንም ነገር በራሱ የምርጫ እቅድ የሚ
ሠራ መሆኑን ያስገነዝበናል።

14 እንግዲህ ይህ ምንን ያመለክታል?
እግዚአብሔር ያዳላል ማለት ነው? ይህን
ማለት አንችልም። 15 ምክንያቱም እግዚአ
ብሔር ለሙሴ፥ «ልምረው የምፈልገውን
እምረዋለሁ፤ልራራለት ለምፈልገውም እራ
ራለታለሁ» ብሎታል። 16 ስለዚህ የእግዚአ
ብሔርን በረከት ማግኘት የሚቻለው በሰው
ፈቃድ ወይም ጥረት ሳይሆን በእግዚአብ
ሔር ምሕረትና ቸርነት ብቻ ነው።

17 በቅዱሳት መጻሕፍት፥ «ፈርዖን ሆይ፥
ኃይሌን ለማሳየትና ስሜንም በሰዎች ሁሉ

ዘንድ ለማሳወቅ አነሣሣሁህ» ተብሎ የተነገ
ረውን እዚህ ላይ ልንጠቅሰው እንችላለን።
18 ስለዚህ እግዚአብሔር ሊምረው የፈለገ
ውን ሲምረው ሌላውን ደግሞ እልኸኛ ያደ
ርገዋል። 19 ምናልባት ከእናንተ አንዳንዶቻ
ችሁ፥ «የእግዚአብሔርን ፈቃድ መቃወም
ካልተቻለ፥ ታዲያ እግዚአብሔር ሰዎችን
ለምን በክፉ ሥራቸው ተጠያቂ ያደርጋቸ
ዋል?» ትሉ ይሆናል።
20 ለዚህ ጥያቄ እኔ ያለኝ መልስ፥ «እን
ዲህ ያለውን ቃል ለእግዚአብሔር መመለስ
የምትችል ለመሆኑ አንተ ማን ነህ? የሸክላ
ዕቃ፥ሠሪውን ባለሙያ ‘ለምን በዚህ ዓይነት
ቅርጽ ሠራኸኝ’ ሊለው ይችላልን?
21 ወይስ የሸክላ ሥራ ባለሙያው ከአንዱ
የሸክላ አፈር ላይ እንሥቶ፥አንዱን ሽልሞ
ሸላልሞ በክብር የሚቀመጥ ዕቃ፥ሌላውን
ግን በክብር ሊይዙት ለማይገባ አገልግሎት
የሚውል ተራ ዕቃ አድርጎ ለመሥራት
መብት የለውምን? 22 ጌታ እግዚአብሔርስ
እስከ አሁን ድረስ የታገሣቸውን፥ለጥፋት
የተመደቡትን ሰዎች ቁጣውንና ኃይሉን
ሊገልጽባቸው ሙሉ ሥልጣን የለውምን?
23-24 እነርሱን የታገሣቸው፥ ከአይሁድም
ሆነ ከአሕዛብ ወገን መርጦ ለክብሩ ላዘጋ
ጀን ለእኛ፥ምሕረቱንና የክብሩን ባለጠግነት
ሊያሳይ ስለፈለገ ነው።»
25 ነቢዩ ሆሴዕ፥ «ሕዝቤ ያልነበረውን
‘ሕዝቤ’ ብዬ እጠራዋለሁ። ያልተወደደው
ንም ሕዝብ፥ ‘የተወደደ’ እለዋለሁ።
26 ‘ሕዝቤ አይደላችሁም’ በተባሉበት
ሥፍራ፥ ‘የሕያው እግዚአብሔር ልጆች’
ተብለው ይጠራሉ» ብሏል።
27 ነቢዩ ኢሳይያስም፥ «የእሥራኤል
ሕዝብ ብዛት እንደ ባሕር አሸዋ ቢሆን
እንኳ የሚድኑት ጥቂቶች ብቻ ናቸው።
28 ጌታ በፍጥነት በዓለም ላይ ፍርዱን ይሰ
ጣል» ሲል ተናግሯል።
29 በሌላም በታ ይኸው ነቢይ፥ «ጌታ
እግዚአብሔር ለትውልዳችን ዘር አስቀርቶ
ምሕረቱን ባያሳይ ኖሮ፥እኛም አይሁዶች
እንደ ሰዶምና ገሞራ ሰዎች በጠፋን ነበር»
ብሏል።
30 እንግዲህ ስለዚህ ጉዳይ ምን ማለት
ይቻላል? የእግዚአብሔርን ጽድቅ ለማግ
ኘት ምንም ጥረት ያላደረጉት አሕዛብ በእ
ምነታቸው ምክንያት ለመጽደቅ ሲችሉ፥
31 የተመረጡት የእግዚአብሔር ወገን የተባ
ሉት እሥራኤላውያን ግን፥ እንጸድቃለን
ብለው ሕግን ቢጠብቁም ሊጸድቁ አልቻ
ሉም። 32 ‘ታዲያ ለምን ይሆን ለመጽደቅ
ያልቻሉት?’ ቢባል፥ በእምነት ሳይሆን
ሕጉን በመጠበቅና በበጎ ሥራቸው ለመጽ
ደቅ ስለፈለጉ ነው። 33 ስለዚህም «ተመል
ከቱ በጽዮን የሚያደናቅፍና የሚያሰናክል
ድንጋይ አኖራለሁ፤ ይህ ድንጋይ ሰዎችን
ያደናቅፋቸዋል፤ ነገር ግን በእርሱ የሚያ
ምኑ ሁሉ አያፍሩበትም» ተብሎ እንደተጻ
ፈው የእንቅፋት ድንጋይ አደናቀፋቸው።

## ምዕራፍ 10

1 ወንድሞቼ ሆይ፥እሥራኤላውያን እንዲ
ድኑ ያለኝ ምኞትና ጉጉት ይህ ነው አይባ
ልም። ጌታ እንዲያድናቸውም የዘወትር
ጸሎቴ ነው። 2 እነርሱም ስለ እግዚአብሔር
ከፍ ያለ ቅንዓት እንዳላቸው አውቃለሁ።
ነገር ግን ይህ ቅንዓታቸው በትክክለኛ እው
ቀት ላይ የተመሠረተ አይደለም። 3 ከእግዚ
አብሔር የሚሰጠውን ጽድቅ ንቀው፥ሕግን
በመጠበቅና በበጎ ሥራ ላይ የተመሠረተ
ውን የራሳቸውን የጽድቅ መንገድ በመከ
ተል እውነተኛውን ጽድቅ እምቢ አሉ።
4 በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ እንዲጸድቁ ክርስ
ቶስ ሕግን ፈጽሞላቸዋል። ስለዚህ ሕግን
በመጠበቅ ለመጽደቅ አይቻልም።
5 ሕግን በመጠበቅ ስለ መጽደቅ ሙሴ፥
«አንድ ሰው ሕግ የሚያዘውን ሁሉ መጠ
በቅ ከቻለ፥ሕግ ራሱ ሕይወት ይሰጠዋል»
ሲል ጽፎአል። 6 በእምነት የሚገኘው
ጽድቅ ግን፥ «ክርስቶስን ወደ ምድር ለማ
ውረድ ወደ ሰማይ መውጣት አያስፈልግ
ህም። 7 ወይም ወደ ሲኦል ወርደህ ክርስቶ
ስን ከሙታን መካከል ማስነሣት የለብህም»
ይላል።
8 ነገር ግን መጽደቅ ስለሚቻልበት መን
ገድ እንዲህ ይላል። «የእግዚአብሔር ቃል
በአጠገብህ ይገኛል፤ በአፍህና በልብህም
ውስጥ ነው።» ይህም የእግዚአብሔር ቃል
እኛ የምናስተምራችሁ የእምነት ቃል
ነው። 9 ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፋችሁ
ብትመሰክሩ፥እግዚአብሔርም ከሞት እንዳስ
ነሣው በልባችሁ ብታምኑ ትድናላችሁ።
10 ምክንያቱም ሰው በልቡ አምኖ ይጸድ
ቃል። ስለ እምነቱም በመመስከሩ ይድ
ናል። 11 ይህ እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ
እንዲህ የሚል ቃል በመጽሐፍ ተጽፎ ይገ
ኛል፤ «በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍ
ርም።» 12 ይህ ቃል የተጻፈው በአይሁድና
በአሕዛብ መካከል ምንም ልዩነት ሳይደረግ
ለሁሉ ነው። የሁሉም ጌታ የሆነው ኢየ

ሱስ ፥ ለሚለምኑት ሁሉ በረከቱን የሚሰጥ
ባለጸጋ አምላክ ነው። 13 በቅዱሳት መጻሕ
ፍት ፥ «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድ
ናል» ተብሏል።
14 ነገር ግን የማያምኑበት አድነን ብለው
እንዴት ሊጠይቁት ይችላሉ? ስለ እርሱ
ካልተነገራቸውስ እንዴት አድርገው ያምኑ
ታል? የወንጌልን ቃል የሚነግራቸው ሰው
ከሌለስ ስለ እርሱ እንዴት ሊሰሙ ይች
ላሉ? 15 መልእክተኞችስ ካልተላኩ ወንጌ
ልን እንዴት ማስተማር ይችላሉ? ስለዚህ
ነገር መጽሐፍ ፥ «መልካሙን የምሥራች
ቃል ለማብሠር የሚሮጡ እግሮች እንዴት
ያማሩ ናቸው!» ይላል።
16 ነገር ግን የወንጌሉን ቃል የሰሙ
እሥራኤላውያን ሁሉ አልተቀበሉትም።
ኢሳይያስም ፥ «ጌታ ሆይ ፥ የተናገርነውን
ቃል ማን አምኖ ተቀበለ?» ሲል ተናግ
ሯል። 17 ስለዚህ እምነት የሚገኘው ስለ
ክርስቶስ የሚናገረውን የወንጌል ቃል ከመ
ስማት ነው።
18 እሥራኤላውያን የእግዚአብሔርን
ቃል ሰምተዋልን? አዎን ፥ ሰምተዋል። ምክ
ንያቱም ቃሉ «ድምጻቸው ወደምድር ሁሉ
ወጥቷል ፤ ቃላቸውም እስከዓለም ዳርቻዎች
ደርሷል» ይላልና መስማታቸው የተረጋገጠ
ነው። 19 ወይስ ደግሞ እሥራኤላውያን እነ
ርሱ አናምንም ቢሉ እግዚአብሔር ሌሎቹን
እንደሚያድናቸው ምናልባት አላስተዋሉ
ይሆንን? ሙሴ ፥ «አሕዛብን ስለማድናቸው
እናንተም በዚህ ቀንታችሁ እንድትቆጩ
አደርጋችኋለሁ» ሲል ተናግሯል። 20 በኋላ
ደግሞ ኢሳይያስ በድፍረት ፥ «ላልፈለጉኝ
ሰዎች ተገኘሁ ፤ ላልጠየቁኝም ሰዎች ተገለ
ጥሁ» ብሏል። 21 ስለ እሥራኤላውያን ግን ፥
«ወደማይታዘዝና ወደ እኔ ወደማይመጣ
ሕዝብ ቀኑን ሙሉ እጆቼን ዘረጋሁ»
ይላል።

## ምዕራፍ 11

1 እንግዲያውስ እግዚአብሔር ሕዝቡን
እሥራኤላውያንን ትቷቸዋል ማለት ነው?
የለም አልተዋቸውም። ምክንያቱም እኔም
ራሴ ከአብርሃም ዘር ፥ ከብንያም ወገን የተወ
ለድሁ እሥራኤላዊ ነኝ።
2 እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን
እሥራኤላውያንን አልተዋቸውም። ስለዚህ
በመጽሐፍ የተጻፈውን አታስታውሱም?
ኤልያስ በእግዚአብሔር ፊት እሥራኤልን
እንዲህ ሲል ከሷቸው ነበር። 3 «ጌታ ሆይ ፥
ነቢያትህን ገደሉ። ለአንተ መሥዋዕት የሚ
ቀርብበትን መሠዊያም አፈራረሱ። ከነቢ
ያት መካከል ከሞት የተረፍሁ እኔ ብቻ
ነኝ። እኔንም ሊገድሉኝ ይፈልጋሉ።»
4 እግዚአብሔር ለኤልያስ የሰጠው
መልስ ታዲያ ምን ይመስላችኋል? «ኤል
ያስ ሆይ ፥ ከሞት የተረፍከው አንተ ብቻ
አይደለህም። በኣል ለተባለው ጣዖት ያልሰ
ገዱ ሌሎች ሰባት ሺህ ሰዎች አሉኝ» ብሎ
ታል።
5 እንዲሁም ደግሞ በአሁኑ ጊዜ ከእሥ
ራኤላውያን መካከል እግዚአብሔር በጸጋው
የመረጣቸው ጥቂት ሰዎች ይገኛሉ። 6 እነ
ዚህም የዳኑት በፈጸሙት በጎ ሥራ ሳይሆን
በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው። በበጎ ሥራ
ቸው ቢድኑማ ኖሮ የእግዚአብሔር ጸጋ
ዋጋቢስ በሆነ ነበር።
7 ከዚህ ሁሉ የተነሣ ፥ የእሥራኤል
ሕዝብ የፈለጉትን አላገኙም። እግዚአብ
ሔር የመረጣቸው ጥቂቶች ብቻ ሲያገኙት ፥
የቀሩት ግን ደንዝዘው ቀርተዋል። 8 በመጽ
ሐፍ ፥ «ዓይናቸው እንዳያይ ፥ ጆሮአቸውም
እንዳይሰማ ፥ እግዚአብሔር አደንዝዟቸዋል።
ስለዚህ እስከ ዛሬ ድረስ ለመስማትም ለማየ
ትም አይችሉም» ተብሎ ተጽፏል።
9 ዳዊትም ፥ «ምግባቸው ተሰናክለው
የሚወድቁበት ወጥመድና እርግማን ይሁንባ
ቸው። 10 እንዳያዩ ዓይናቸው ይታወር ፤ ወገ
ባቸውም ለዘላለም በችግር ይጉበጥ»
ብሏል።
11 ታዲያ እሥራኤላውያን ተሰናክለው
ለዘላለም ጠፍተዋል? የለም አልጠፉም!
እሥራኤላውያን ኃጢአት በመሥራታቸው
እንዲቆጩና እንዲቀኑ ለማድረግ ደኅንነት
ለአሕዛብ ተሰጠ። 12 እሥራኤላውያን እግዚ
አብሔር በክርስቶስ የሚገኘውን ደኅንነት
ሲሰጣቸው ለመቀበል ፈቃደኛ ሆነው ባለ
መገኘታቸው ፥ ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆኑ
ትን በረከት ፥ የቀረው የዓለም ሕዝብ ለማግ
ኘት በቅቷል። እነርሱ የእግዚአብሔርን በረ
ከት አንቀበልም በማለታቸው የእነርሱ እም
ቢታ እንዲህ ያለውን በረከት ለአሕዛብ ያስገ
ኘላቸው ከሆነ ፥ እሥራኤላውያን በሙሉ በክ
ርስቶስ በሚያምኑበት ጊዜ የሚገኘው በረ
ከት የቱን ያህል ይሆን?
13 እንደምታውቁት እግዚአብሔር ለእና
ንተ ለአሕዛብ ሐዋርያ አድርጎ ሾሞኛል።
14 ምናልባት በዚህ መንገድ ከወገኖቼ ከእ
ሥራኤላውያን መካከል ፥ እናንተ ያገኛችሁ
ትን ደኅንነት በማየት ቀንተውና ተቆጭ

ተው በጌታ አምነው እንዲድኑ ፥ ለአንዳን
ዶቹ ምክንያት እሆናቸዋለሁ ብዬ እስባ
ለሁ። 15 እነርሱ ካለማመናቸው የተነሣ በረ
ከቱን ሲያጡ የዓለም ሕዝብ ከእግዚአብ
ሔር ጋር መታረቅ ከቻለ፥እነርሱ ወደ እግ
ዚአብሔር የሚመለሱበት ጊዜ ምንኛ ድንቅ
ይሆን! ልክ ሞቶ እንደ መነሣት ያህል
ነው። 16 ምጣዱን የሚያሟሸው የመጀመሪ
ያው ጥቢኛ ከተቀደሰ ቡሆው በሙሉ የተቀ
ደሰ ይሆናል። እንዲሁም የአንድ ዛፍ
ሥሮች ከተቀደሱ፥ቅርንጫፎቹም የተቀደሱ
ይሆናሉ።

17 ነገር ግን የአብርሃም ዘር ከሆኑት ቅር
ንጫፎች አንዳንዶቹ በመሰበራቸው፥ባለቤት
እንደሌለው እንደ ዱር ወይራ የሆናችሁት
እናንተ አሕዛብ ፥ በእነርሱ እግር ተተካ
ችሁ። የወይራ ቅርንጫፎች ከሥሩ ከሚወ
ጣው ግንድ ጋር የተያያዙ እንደ መሆና
ቸው መጠን፥እናንተም እግዚአብሔር ለአ
ብርሃምና ለልጆቹ ከሰጠው በረከት ተካፋ
ዮች ለመሆን በቅታችኋል።

18 በተሰበሩት ቅርንጫፎች ምትክ በመግ
ባታችሁ ደግሞ አትመኩበት። እናንተ የዛፉ
ቅርንጫፎች እንጂ ሥሩ እንዳይደላችሁ
መርሳት የለባችሁም። ስለዚህ ሥሩ እናን
ተን ይሸከማችኋል እንጂ ሥሩን የምትሸከ
ሙት እናንተ አይደላችሁም። 19 ምናልባት
እናንተ፥ «ቅርንጫፎቹ የተሰበሩት እኛ በእ
ነርሱ ምትክ ቦታ እንድንይዝ ነው» ትሉ
ይሆናል።

20 አዎን! ልክ ናችሁ። ነገር ግን፥ቅርን
ጫፎች የነበሩት የተሰበሩት ስላላመኑበት
ሲሆን፥እናንተም በእነርሱ ቦታ ለመተካት
የበቃችሁት ስላመናችሁበት ነው። ይህም
በመሆኑ ትሑቶችና አመስጋኞች እንጂ
ትምክሕተኞች መሆን እንደማይገባችሁ ላስ
ጠነቅቃችሁ እወዳለሁ። 21 ምክንያቱም እን
ዳያችሁት እግዚአብሔር ከሥር ከመሠረቱ
ቅርንጫፎች ለነበሩት እሥራኤላውያን ያል
ራራላቸው ከሆነ፥እናንተስ እንዴት ይራራ
ልናል ብላችሁ ታስባላችሁ?

22 የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጥብቅ
መሆን ልብ ብላችሁ አስተውሉ። እግዚአብ
ሔር የማይታዘዙትን አምርሮ ይቀጣቸዋል።
ለሚወዱትና ለሚታዘዙት ግን ቸርነቱን
ያሳያቸዋል። ይሁን እንጂ እርሱን በማመ
ንና ለቃሉ በመታዘዝ ጸንታችሁ የማትኖሩ
ከሆናችሁ እናንተም ተቆርጣችሁ ትጣላላ
ችሁ። 23 እሥራኤላውያንም አምነው ቢመ
ለሱ ተቆርጠው ከተጣሉበት ዛፍ እግዚአብ
ሔር ራሱ መልሶ ሊያስገባቸው ይችላል።

24 የዱር ወይራ ቅርንጫፎች የነበራች
ሁት አሕዛብ ፥ በእግዚአብሔር የተተከለ
ወይራ ዛፍ ቅርንጫፎች መሆን ከቻላችሁ፥
ከዛፉ ተቆርጠው የተጣሉት የመጀመሪያ
ዎቹ ቅርንጫፎች እሥራኤላውያንማ ወደ
ቀድሞ ቦታቸው መመለስ እንዴት አይች
ሉም?

25 ወንድሞቼ ሆይ፥በዚህ ትምክህት እን
ዳያድርባችሁ ይህንን ምሥጢር እንድታው
ቁት እወዳለሁ። ያላመኑት እሥራኤላውያን
እምቢተኛነት ዘለቄታ የለውም። እንዲያ
ውም እንዲህ ባለው ሁኔታ የሚቆዩት አሕ
ዛብ በሙሉ በክርስቶስ አምነው እስኪድኑ
ድረስ ብቻ ነው። 26 ከዚያ በኋላ እሥራኤላ
ውያን በሙሉ ይድናሉ። ነቢያት ስለዚህ
ጉዳይ እንዲህ ብለው ተናግረዋል ፤ «ነፃነ
ትን የሚያስገኝ አዳኝ ከጽዮን ይወጣል።
የያዕቆብ ዘር ከሆኑት እሥራኤላውያን አለ
ማመንን ያርቅላቸዋል። 27 ይህም ኃጢአታ
ቸውን በማስወገድላቸው ጊዜ የምገባላቸው
ቃል ኪዳን ነው።»

28 በአሁኑ ጊዜ ከእሥራኤላውያን መካ
ከል ብዙዎቹ የወንጌልን ቃል ባለመቀበላ
ቸው የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆነዋል።
ይህም ሁናቴ እናንተን ጠቅሞአችኋል። እግ
ዚአብሔር በረከቱን አሕዛብ ለሆናችሁት
ለእናንተ ሰጥቶአችኋልና። ነገር ግን ለአብር
ሃም ፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ በሰጠው ተስፋ
ምክንያት አሁንም ቢሆን እሥራኤላውያን
በእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝብ ናቸው።
29 እግዚአብሔር በሚያደርገው ምርጫና
በሚሰጠው ስጦታ፥ «ይህን እንዴት፥ወይም
ለምን አደረግሁት?» ብሎ የሚጸጸት አይደ
ለምና። 30 እናንተ ድሮ ለእግዚአብሔር
የምትታዘዙ አልነበራችሁም። አሁን ግን
በእሥራኤላውያን እምቢተኝነት ምክንያት
የእግዚአብሔርን ምሕረት አግኝታችኋል።
31 እናንተ እምቢተኞች በነበራችሁበት ጊዜ
የእግዚአብሔርን ምሕረት እንዳገኛችሁ
ሁሉ ፥ እነርሱም የእግዚአብሔርን ምሕረት
እንዲያገኙ ለጊዜው የማይታዘዙ ሆነዋል።
32 እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ ምሕረት
ሊሰጥ ስለፈለገ እምቢተኝነታቸው እንዲገዛ
ቸው አድርጓቸዋል።

33 የእግዚአብሔር ጸጋ ምንኛ ታላቅ
ነው? ጥበቡና እውቀቱስ የቱን ያህል
ጥልቅ ነው? ፍርዱንስ ማን ሊመረምረው
ይችላል? መንገዱንስ ማን ያውቀዋል?
34 መጽሐፍ እንደሚለው ፥ «የእግዚአብሔ

ርን አሳብ የሚያውቅ ማን ነው? ምክር
ሊሰጠው የሚችል ከቶ ማን አለ? 35 ማን
አበደረው? ለማንስ የተበደረውን ከፈለ?»
36 ማናቸውም ነገር የተፈጠረው በእግዚአብ
ሔር ሲሆን፥የሚኖረውም በእርሱ አማካይ
ነት ነው። ስለዚህ ለእርሱ ከዘላለም እስከ
ዘላለም ድረስ ክብር ምስጋና ይግባው።
አሜን!

## ምዕራፍ 12

1 ወንድሞች ሆይ፥ ደስ የሚያሰኝ ሕያ
ውና የተቀደሰ መሥዋዕት አድርጋችሁ ሰው
ነታችሁን ለእግዚአብሔር እንድታቀርቡለት
እለምናችኋለሁ። እግዚአብሔር ያደረገላች
ሁን ሁሉ ብታስቡት ለእርሱ አገልግሎት
ሰውነታችሁን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ
የሚገባችሁ መሆኑን ትገነዘባላችሁ። 2 የዚ
ህን ዓለም ሰዎች ጠባይ እንዳትከተሉ ተጠ
ንቀቁ። በአሳባችሁም በአድራጎታችሁም
ሁሉ ፍጹም የተለወጣችሁ ሁኑ እንጂ እነ
ርሱን አትምሰሉዋቸው። ይህን ብታደርጉ
እግዚአብሔር የሚደሰትበት ፍጹምና በጎ
ፈቃዱ ምን እንደሆነ ማወቅ ትችላላችሁ።
3 ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ጸጋም እመ
ክራችኋለሁ። ራሳችሁን ያለ መጠን ከፍ
አድርጋችሁ በማየት በትዕቢት አትወጠሩ፥
እግዚአብሔር በሰጣችሁ እምነት መጠን
ትሑታን ሁኑ። 4 አንድ አካል የተለያየ አገ
ልግሎት የሚሰጡ የተለያዩ የሰውነት ክፍ
ሎች አሉት። 5 እኛም እንደዚሁ ብዙዎች
ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ሆነናል።
ስለዚህ እያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ከዋናው
አካል ላይ እንደተያያዘና የተለየም ተግባር
እንዳለው፥እኛም በክርስቶስ ሕብረት አለን።
6 መንፈስ ቅዱስ ለያንዳንዳችን ልዩ ልዩ
ስጦታዎችን አድሎናል። ስለዚህ እግዚአብ
ሔር በጸጋው የሰጠንን ልዩ ልዩ ስጦታ በተ
ግባር ላይ ልናውለው ይገባል። ትንቢት
የመናገር ጸጋ የተሰጠው እንደ እምነቱ
መጠን ትንቢት ይናገር። 7 የማስተዳደር
ስጦታ የተሰጠህ አገልግሎትህን በትጋት
መቀጠል አለብህ። የማስተማር ጸጋ የተሰጠ
ህም በሚገባ አስተምር። 8 ምክር የመለገሥ
ጸጋ የተሰጠው ይህንኑ ከማከናወን ወደ ኋላ
አይበል። እግዚአብሔር ያደለውም ሌሎችን
ለመርዳት እጁን በሰፊው ይዘርጋላቸው።
መቼም ስጦታ አያልቅ ነገር ነውና ሌሎችን
የመምራት ጸጋ የተሰጠው ይህንኑ በትጋት
ያከናውን። ያዘኑትን የማረጋጋትና የተቸገሩ
ትን የመርዳት ጸጋ የተሰጣቸውም ይህንኑ
ተግባር በደስታ ይፈጽሙ።
9 ፍቅራችሁ ግብዝነት የሌለበት ይሁን።
ክፉውን ነገር ጥሉ፤ በጎውንም ነገር
ውደዱ። 10 ከልብ በሆነ እውነተኛ ፍቅር
እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፤ያለ ሽንገላም ተባ
በሩ። 11 በሥራችሁ ስንፍና ሳታሳዩ ጌታን
በፍጹም ልባችሁ አገልግሉት።
12 እግዚአብሔር በሰጣችሁ ተስፋ ደስ
ይበላችሁ። መከራ ሲደርስባችሁ፥ ታገሡ፤
በጸሎትም ተጠመዱ። 13 በችግር ላይ የሚ
ገኙ ክርስቲያን ወንድሞቻችሁን በሚያስፈ
ልጋቸው ሁሉ እርዱዋቸው፤እንግዶችንም
በቤታችሁ ተቀብላችሁ አስተናግዱዋቸው።
14 የሚያሳድዱዋችሁን መርቁዋቸው
እንጂ አትርገሙዋቸው። 15 ደስ ከሚላቸው
ጋር ደስ ይበላችሁ፤ከሚያዝኑትም ጋር የኀ
ዘናቸው ተካፋይ ሁኑ። 16 እርስ በርሳችሁ
የምትግባቡ ሁኑ፤ትዕቢተኞችና ኩራተኞች
አትሁኑ፤ነገር ግን ድሆችን ለመርዳት ፈቃ
ደኞችና ትሑቶች ሁኑ። «ያለ እኔ ማን
አዋቂ አለ» በሚል አጉል መንፈስ አትወ
ጠሩ።
17 ክፉ ላደረገባችሁ ክፉ አትመልሱ
ለት፤ በተግባራችሁም ሐቀኝነታችሁን
አሳዩ። 18 ከሰዎች ጋር አትጣሉ፤በተቻለ
መጠን ከሁሉም ጋር ተግባብታችሁ በሰላም
ኑሩ።
19 ወዳጆቼ ሆይ፥የተፈጸመባችሁን በደል
ለእግዚአብሔር ሰጥታችሁ ተዉት እንጂ
ራሳችሁ አትበቀሉ። በቅዱሳት መጻሕፍት፥
«የምበቀል እኔ ነኝ ይላል እግዚአብሔር»
ተብሎ ተጽፏል። 20 ይልቅስ አንድ ነገር
ልንገራችሁ። ጠላታችሁ ተርቦ ብታዩት
አብሉት፤ቢጠማም አጠጡት። ይህን ብታደ
ርጉ የሐፍረትና የጸጸት ፍም በራሱ ላይ
ትከምራላችሁ። 21 ስለዚህ ክፉን ተግባር
በበጎ ተግባር አሸንፉት እንጂ ለክፉ ነገር
አትሸነፉ።

## ምዕራፍ 13

1 ማንኛውም ሥልጣን የሚገኘው በእግ
ዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነና ያለ እግዚአብ
ሔርም ፈቃድ በሥልጣን ላይ የተቀመጠ
መንግሥት ስለሌለ፥ ለመንግሥት ባለሥል
ጣን መታዘዝ ይገባናል። 2 ስለዚህም፥በሕግ
የተቋቋመ መንግሥት ላወጣው ሕግ አንታዘ
ዝም ማለት፥እግዚአብሔር ለደነገገው ሥር
ዓት እንዳለመታዘዝ ይቆጠራል። ይህ አለመ
ታዘዝም ቅጣትን ያስከትላል። 3 ምን ጊዜም
ባለሥልጣኖችን የሚፈሩ ወንጀለኞች ብቻ

ናቸው። ስላማዊና ወንጀለኛ ያልሆኑ ሰዎች
አይፈሩዋቸውም። እናንተም ባለሥልጣኖች
እንዳያስፈሩአችሁ ከፈለጋችሁ የወጣውን
ሕግ አክብሩ። ይህን ካደረጋችሁ የሚያስፈ
ራችሁ ነገር አይኖርም ፤ እንዲያውም ከባለ
ሥልጣኖቹ ምስጋና ታገኛላችሁ። 4 ባለሥል
ጣኖች የአንድ አገር ዜጎችን መብት ለማስ
ጠበቅ ግዴታቸውንም ለማስፈጸም ፥ ከእግዚ
አብሔር አደራ የተሰጣቸው የሕዝብ አገል
ጋዮች ናቸው። ሕግ የምታፈርሱና የማትታ
ዘዙ ከሆናችሁ ተገቢውን ቅጣት ለመስጠት
ስለሚገደዱ ልትፈሩዋቸው ይገባል። 5 ስለ
ዚህ ቅጣትን በመፍራት ብቻ ሳይሆን የሕ
ሊናችሁን ዳኝነት በመከተል ለባለሥልጣን
መታዘዝ ይገባችኋል።

6 ለመንግሥት ግብር የምትከፍሉትም
ከላይ በጠቀስኳቸው ምክንያቶች ነው። ባለ
ሥልጣኖች ግዴታቸውን ሲፈጽሙ የሚያገ
ለግሉት እግዚአብሔርን ነው። 7 ስለዚህ
ለመንግሥት መከፈል የሚገባችሁን ክፍያ
በወቅቱ ክፈሉ። ግብር ለሚሰበስብ የመንግ
ሥት ባለሥልጣን ግብራችሁን አጠናቁ።
ቀረጥ ለሚሰበስበውም ቀረጥ ክፈሉ። መፈ
ራት የሚገባውን ፍሩ ፥ መከበር የሚገባው
ንም አክብሩ። 8 ከሰው የተበደራችሁትን
ዕዳ ሁሉ መልሳችሁ ክፈሉ። እርስ በርሳ
ችሁ ተዋደዱ፤ሌላ ዕዳ ቢኖርባችሁ ያ እርስ
በርሳችሁ የምትዋደዱት ፍቅር ብቻ መሆን
አለበት። ሌላውን ሰው የሚወድ የእግዚአብ
ሔርን ሕግ ፈጽሟልና። 9 ምክንያቱም ፥
«አታመንዝር ፥ አትግደል ፥ አትስረቅ ፥ አት
መኝ» የሚሉት ሌሎችም ትእዛዛት በሙሉ
በዚህ፥ «ባልንጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ
ውደድ» በሚለው ትእዛዝ ይጠቃለላሉ።
ባልንጀራችንን እንደ ራሳችን አድርገን ከወ
ደድነውም ከላይ የተዘረዘሩትን ሕጎች ሁሉ
ልንጥሳቸው አንችልም። 10 ፍቅር በማንም
ሰው ላይ ክፉ ሥራ አያሠራንም። ስለዚህም
ሰዎችን ስናፈቅራቸው ሕግጋትን በሙሉ
ፈጸምን ማለት ነው።

11 ያለንበትን ጊዜ በማወቅ እነዚህን የዘረ
ዘርናቸውን ነገሮች ሁሉ መፈጸም አለብን።
ከእንቅልፍ እንድንነቃ የሚያስፈልግበት
ጊዜው አሁን ነው። በመጀመሪያ ካመንበት
ጊዜ ይልቅ ደኅንነታችን ወደ ግቡ የሚደር
ስበት የጌታ መምጫ ቀን እየቀረበ ነው።
12 ሌሊቱ አልፏል ፤ ጌታ የሚመለስበትም
ጊዜ በጣም ሩቅ አይደለም። ስለዚህ የጨለ
ማን ክፉ ሥራዎች ሁሉ እናስወግድ። በብ
ርሃን ውስጥ የምንኖር እንደ መሆናችን የመ
ልካሙን ሥራ ልብስ እንልበስ። 13 አግባ
ብና ሥርዓት ባለው መንገድ እንኑር። ዘፈ
ንን፥ስካርን፥ዝሙትን፥መዳራትን፥ክርክርንና
ቅናትን ከእኛ እናርቅ። 14 እንደሚገባችሁ
ለመኖር የሚያስችላችሁን ብርታት እንዲሰ
ጣችሁ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት።
ሥጋዊ ፍላጎታችሁንና ምኞታችሁን ለመፈ
ጸም አትጣጣሩ።

## ምዕራፍ 14

1 በእምነት ደካማ የሆነውን ሰው ፥በእም
ነቱ ደካማነት ሳትነቅፉት በልበ ሰፊነት
ተቀበሉት። 2 አንድ ሰው ማንኛውንም ዓይ
ነት ምግብ ሳይመርጥ ለመብላት እንደተፈ
ቀደለት ያምናል። ሌላው ግን በእምነት
ደካማ የሆነው ፥እንደዚህ ያለ እምነት ስለሌ
ለው አትክልት መብላትን ይመርጣል።
3 ስለዚህ ሁሉን ነገር ለመብላት እንደተፈቀ
ደላቸው የሚያምኑ ፥ የማይበሉትን መንቀፍ
የለባቸውም። አትክልት ብቻ የሚበሉትም፥
ያገኙትን የሚበሉትን መንቀፍ አይገባቸ
ውም። ምክንያቱም ያገኙትን የሚበሉት
ንም ሆነ የማይበሉትን፥ሁለቱንም እግዚአብ
ሔር ተቀብሎአቸዋልና። 4 ሁሉም የእግዚአ
ብሔር አገልጋዮች ናቸው። ስለዚህ ተጠያ
ቂነታቸው በእግዚአብሔር እስከሆነ ድረስ፥
ያጠፉት ጥፋት ካለ ሊፈርድባቸው የሚ
ችል እግዚአብሔር እንጂ እናንተ አይደላች
ሁም። እናንተ በእግዚአብሔር አገልጋዮች
ላይ ለመፍረድ ምን ሥልጣን አላችሁ?
ቢቆም ወይንም ቢወድቅ ለገዛ ጌታው
ነው። የሁሉ ጌታ የሆነው እግዚአብሔር
እያንዳንዱን አገልጋይ ተገቢውን ነገር እን
ዲፈጽም አቅፎና ደግፎ ሊያቆመው ይች
ላል።

5 አንዳንድ ሰዎች አንዱን ቀን ከሌሎቹ
ቀናት የበለጠ አድርገው ያከብሩታል።
ሌሎች ሰዎች ደግሞ ቀናት ሁሉ እኩል
መሆናቸውንና አንዱ ቀን ከሌላው ይበልጥ
መከበር እንደሌለበት ያምናሉ። ይህን በመ
ሳሰሉ ጉዳዮች ላይ እያንዳንዱ ሰው የራሱ
የሆነ አስተሳሰብ ሊኖረው ይገባል። 6 አንድ
ሰው አንዱን ቀን ከሌሎች ቀኖች የተለየ
አድርጎ የሚያከብረው ያንን ቀን በማክበሩ
ጌታ ደስ የሚለው መስሎ ስለሚታየው
ነው። ያገኘውን የሚበላውም እግዚአብሔ
ርን እያመሰገነና እያከበረ ይመገባል። የተገ
ኘውን ሁሉ የማይበላውም ቢሆን የማይበላ
በት ምክንያት ፥ እግዚአብሔርን ለማስደሰ
ትና ለማክበር ሲል ነው። 7 ሕይወታችን

ሆነ ሞታችን፥የእኛ የግል ጉዳይ ብቻ አይ
ደለም። 8 ብንኖር ለጌታ እንኖራለን፥ብንሞ
ትም ለጌታ እንሞታለን። ስለዚህ በሕይወት
ብንኖርም ብንሞትም ያው የእርሱ ነን።
9 ክርስቶስ የሞተውና ከሞት የተነሣው፥በሕ
ይወት ሥጋ እያለንም ሆነ ከሞትን በኋላ
የእኛ ጌታ ለመሆን ነው።
10 ታዲያ እናንተ ወንድሞቻችሁን የም
ትንቁዋቸውና የምትነቅፏቸው ለምንድን
ነው? እያንዳንዳችን ፍርዳችንን ለመቀበል
በክርስቶስ የፍርድ ዙፋን ፊት እንደምን
ቆም አታውቁምን? 11 በቅዱሳት መጻሕ
ፍት፥ «እኔ ሕያው ነኝና ጉልበት ሁሉ
በእኔ ፊት ይንበረከካል። ምላስም ሁሉ እኔ
እግዚአብሔር እንደሆንኩ ይናገራል»
ተብሎ ተጽፏል። 12 እያንዳንዳችንም ስለ
ራሳችን ሥራ በእግዚአብሔር ፊት ቀርበን
መልስ እንሰጣለን። 13 ስለዚህ ከእንግዲህ
ወዲህ እርስ በእርሳችን መነቃቀፍን እን
ተው። ይልቁን ወንድሞቻችን እንዳይደናቀ
ፉና ወደ ኃጢአት እንዳይወድቁ በየበኩላ
ችን እንርዳቸው።
14 እኔ በበኩሌ፥ክርስቲያን እንደመሆኔ
መጠን፥ ርኩስ ነው ተብሎ የሚነቀፍ
ምንም ምግብ እንደሌለ አውቃለሁ። ነገር
ግን አንድ ሰው፥ «ይህ ምግብ ርኩስ ነው»
ብሎ የሚያምን ከሆነ ያ ምግብ ለእርሱ
ርኩስ ነው። ስለዚህ ባይበላው ይሻለዋል።
15 በምትመገቡት ምግብ ምክንያት ወንድ
ሞቻችሁን የምታሳዝኑ ከሆነ፥ይህ አድራጎ
ታችሁ ለወንድሞቻችሁ ፍቅር እንደሌላ
ችሁ ያሳያል። ክርስቶስ እነርሱን ለማዳን
ሲል የሞተላቸውን ወንድሞቻችሁን፥እና
ንተ በምትመገቡት ምግብ ምክንያት አሳዝ
ናችሁ የክርስትና ሕይወታቸው እንዲጐዳ
አታድርጉ። 16 ስለዚህ እናንተ መልካም
ነው ያላችሁት ነገር እንደ መጥፎ ነገር እን
ዳይቆጠርባችሁ ተጠንቀቁ። 17 ምክንያቱም
ክርስትና፥ጽድቅና ሰላም ከመንፈስ ቅዱስም
የሚገኝ ደስታ እንጂ፥የመብልና የመጠጥ
ጉዳይ አይደለም። 18 በዚህ ዓይነት መንገድ
ክርስቶስን ብናገለግል እግዚአብሔር ደስ
ይለዋል። ከሰዎችም ምስጋና እናገኛለን።
19 ስለዚህ ከላይ እንደጠቀስኩት፥እርስ በእር
ሳችን በሰላም የምንኖርበትን፥መንፈሳዊ
ሕይወታችን የሚዳብርበትንና የምንረዳዳበ
ትን ነገሮች እናድርግ።
20 በምግብ ምክንያት የእግዚአብሔርን
ሥራ ማፍረስ አይገባንም። ማናቸውም
ምግብ ንጹሕ ነው። ነገር ግን ያን ምግብ
በመብላታችን ወንድሞቻችን እንደሚሰና
ከሉ እያወቅን በእነርሱ ፊት መመገብ
ትልቅ ስሕተት መሆኑን አትዘንጉ። 21 ወን
ድሞቻችንን የሚያሰናክል ሆኖ ከተገኘ፥
ሥጋ መብላቱንና የወይን ጠጅ መጠጣቱን
መተውና ወንድሞቻችንን የሚጐዳ ማናቸ
ውንም ነገር አለማድረጉም ይመረጣል።
22 ስለነዚህ ነገሮች ያላችሁ ምንም ዓይነት
እምነት በእናንተና በእግዚአብሔር መካከል
ብቻ ይቅር። ትክክል ነው ብሎ አምኖ
በሚያደርገው ነገር የማይጸጸት ሰው የተባ
ረከ ነው። 23 ሊያደርግ ያሰበው ነገር ስሕ
ተት መሆኑን የሚያውቅም እንዲህ ያለውን
ነገር ከማድረግ ይቆጠብ። ሕሊናው እየወቀ
ሰው ካደረገው ግን ኃጢአት ሥራ ማለት
ነው። አንድ ነገር ትክክል መሆኑንና አለመ
ሆኑን ለይተው ሳያውቁ በመጠራጠር የሚደ
ረግ ማናቸውም ነገር ኃጢአት ነውና።

## ምዕራፍ 15

1 እኛ በእምነት ጠንካራ የሆንነው በእ
ምነታቸው ደካማ የሆኑትን ሰዎች ሕሊና
እንዳናሳዝን መጠንቀቅ ይኖርብናል። የራሳ
ችንን ጥቅምና ፍላጎት ብቻ በመመልከት
እነርሱ የሚጠራጠሩበትንና እንደ ስሕተት
አድርገው የሚቆጥሩትን ማናቸውንም ነገር
ከማድረግ፥ራሳችንን መግታት አለብን። ከራ
ሳችን ጥቅም ይልቅ የወንድሞቻችንን
ጥቅም እናስቀድም። 2 እያንዳንዳችን ወንድ
ማችን የሚጠቀምበትንና የሚታነጽበትን
ነገር እናድርግለት እንጂ የራሳችንን ጥቅም
ብቻ አንመልከት። 3 በዳዊት መዝሙር፥
«የተቃዋሚዎችህ ዘለፋ በእኔ ላይ ወረደ
ብኝ» ተብሎ እንደተጻፈው፥ክርስቶስ ራሱን
ደስ ለማሰኘት ያደረገው አንዳችም ነገር
የለም። 4 በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉት
ቃላት፥እንድንጽናናባቸው፥ተስፋ እንድናገ
ኝባቸውና ትምህርት እንዲሆኑን ስለ እኛ
ጥቅም ተጽፈዋል።
5 ትዕግሥትን የሚያድለንና መጽናናትን
የሚሰጠን እግዚአብሔር የክርስቶስን ምሳሌ
ነት ተከትላችሁ እርስ በርሳችሁ በፍጹም
መግባባት ለመኖር ያብቃችሁ። 6 በዚህም
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት የሆነ
ውን አምላክ ሁላችንም በአንድ ልብና በአ
ንድ አፍ እናመሰግነዋለን።
7 ክርስቶስ እናንተን በጋለ ፍቅር እንደተ
ቀበላችሁ፥ወደ እናንተም የሚመጡትን
ሁሉ በጋለ ፍቅር ተቀበሏቸው። በዚህም
የእግዚአብሔር ስም ይመሰገንበታልና።

[8]እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ለይስሐቅና ለያ
ዕቆብ የሰጠውን ተስፋ የሚፈጽም ታማኝ
አምላክ መሆኑን ለማረጋገጥ፥ክርስቶስ የአይ
ሁድ ሕዝብ አገልጋይ ሆኖ ወደዚህ ዓለም
መምጣቱን እንድታስታውሱ። [9]እንዲሁም
አሕዛብ ደኅንነትን እንዲያገኙና እግዚአብ
ሔርን እንዲያመሰግኑት ለማድረግ የመጣ
መሆኑንም መዘንጋት የለባችሁም። ስለዚ
ህም ጉዳይ በዳዊት መዝሙር፥ «በአሕዛብ
መካከል አመሰግንሃለሁ፤ለስምህም እዘምራ
ለሁ» ተብሎ አስቀድሞ ተጽፏል።
[10]እንዲሁም፥ «እናንተ አሕዛብ፥ከተመ
ረጠው የእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ደስ ይበ
ላችሁ» ተብሎ ተነግሮላቸዋል።
[11]ደግሞ በሌላ ቦታ፥ «አሕዛብ ሆይ፥
እግዚአብሔርን አመስግኑት፤ ሕዝቦችም
አመስግኑት» የሚልም ቃል ተጽፎ ይገ
ኛል።
[12]ነቢዩ ኢሳይያስም፥ «እርሱ ከእሴይ
ዘር ይወለዳል፤በአሕዛብም ላይ ይነግሣል።
እነርሱም ተስፋ ያደርጉታል» ሲል ትን
ቢት ተናግሮላቸዋል።
[13]ተስፋ የሰጣችሁና ያመናችሁበት እግ
ዚአብሔር አሁንም ሰላሙንና ደስታውን
ይስጣችሁ። በውስጣችሁ በሚኖረው በመን
ፈስ ቅዱስም ኃይል ተስፋችሁ እየበዛ እንዲ
ሄድ ይርዳችሁ።
[14]ወንድሞቼ ሆይ፥ በጎነትን የተሞላ
ችሁ፥ በእውቀት የበለጸጋችሁና አንዳችሁ
ሌላውን ለማስተማር የሚያበቃ መንፈሳዊ
እውቀት እንዳላችሁ በእርግጥ ተረድቻለሁ።
[15]ቢሆንም አንዳንድ ነገሮችን ማንሣቱ
ተገቢ መስሎ ስለታየኝ፥ በዚህ መልእክት
ላይ በድፍረት ጽፌላችኋለሁ። በድፍረት
ለመጻፍ የበቃሁትም እግዚአብሔር በሰጠኝ
ጸጋ ተነሣሥቼ እንጂ እንዲያው አይደለም።
[16]ይህም ጸጋ የተሰጠኝ የኢየሱስ ክርስቶስ
ሐዋርያ ሆኜ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእ
ናንተ ለአሕዛብ በማብሠር በመንፈስ ቅዱስ
አማካይነት ተቀድሳችሁ እግዚአብሔርን
ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት ሆናችሁ በፊቱ
እንድትቀርቡ ለማድረግ ነው። [17]ስለዚህ
ኢየሱስ ክርስቶስ በእኔ አድሮ ይህን እንድ
ሠራ ስላደረገኝ እመካበታለሁ። [18]‘ጌታ
ሌሎቹንም እንደ እኔ መሣሪያው አድርጎ
ተጠቅሞባቸዋል? አልተጠቀመባቸውም?’
የሚለውን ጉዳይ ማንሣት የሚገባኝ አይመ
ስለኝም። በእኔ አድሮ ግን አሕዛብ ወደ እግ
ዚአብሔር እንዲመለሱ ማድረጉን ስለማ
ውቅ በዚህ እመካለሁ። [19]አሕዛብ ወደ እግ
ዚአብሔር የተመለሱት፥ መንፈስ ቅዱስ
በእኔ አድሮ በሠራው የድንቅና የተአምራት
ኃይል ነው። ከኢየሩሳሌም አንሥቶ እስከ
እልዋሪቆን ድረስ እየዞርኩ የክርስቶስን ወን
ጌል በሙሉ ለማዳረስ የበቃሁት በዚህ
ሁኔታ ነበር።
[20]በዚህም ጊዜ ሁሉ በተቻለኝ መጠን
ከእኔ በፊት ማንም ሄዶ የወንጌልን ቃል
ባላስተማረበት ቦታ እየሄድኩ ስለ ክርስቶስ
አስተምሬአለሁ። ይህን ያደረግሁትም አንዱ
ቀድሞ መሠረት በጣለበት ላይ መሥራት
ስላልፈለግሁ ነው። [21]ይህም ነቢዩ ኢሳይ
ያስ፥ «ከዚህ በፊት ስለ እርሱ ያልተነገራ
ቸው ያያሉ፤ስለ እርሱ ሰምተው የማያው
ቁም ያስተውላሉ» ብሎ እንደተናገረው
ነው። [22]እንግዲህ እስካሁን ወደ እናንተ
ለመምጣት ያልቻልኩበትም ምክንያት
ይኸው ነው።
[23]አሁን ግን በዚህ አካባቢ ባሉት አገ
ሮች የነበረኝን ሥራ ስላጠናቀቅሁ፥ከብዙ
ጊዜ ጀምሮ ስመኘው የነበረውን እውን ለማ
ድረግ ወደ እናንተ መምጣቴ አልቀረም።
[24]ወደ እስፔን ለመሄድ ስለምፈልግ እግረ
መንገዴን ሮም መጥቼ ልጐበኛችሁ አቅጃ
ለሁ። ለጥቂት ጊዜም አብረን ከቆየን በኋላ
እንደምትሸኙኝ ተስፋ አደርጋለሁ።
[25]ባሁኑ ጊዜ ግን ለአይሁድ ክርስቲያ
ኖች የሚሰጥ የገንዘብ እርዳታ ይዤ ወደ
ኢየሩሳሌም እወርዳለሁ። [26]ይህም የእር
ዳታ ገንዘብ በመቄዶንያና በአካይያ የሚገኙ
ክርስቲያኖች፥ ከባድ ችግር ለተጫናቸው
በኢየሩሳሌም ላሉት ክርስቲያኖች እንዳደር
ስላቸው አዋጥተው የሰጡኝ ገንዘብ ነው።
[27]ይህን እርዳታ ለማድረግ የተነሣሡትም
ለአይሁድ ክርስቲያኖች እነርሱም በፈንታ
ቸው መክፈል የሚገባቸው ዕዳ መኖሩ ስለ
ተሰማቸው፥በበጎ ፈቃድ ተነሥተው ያደረ
ጉት ነው። ‘ዕዳው ምንድነው?’ ቢባል፥
አሕዛብ ለአይሁድ የመጣውን መንፈሳዊ
በረከት ተካፍለዋልና እንዲህ ባለው የችግር
ጊዜ፥ ሌላው ቢቀር በገንዘብ መርዳቱን
ተገቢ ሆኖ ስላገኙት ነው። [28]ስለዚህ ይህን
የተሰበሰበውን የገንዘብ እርዳታ ለኢየሩሳ
ሌም ምዕመናን ካደረስኩላቸው በኋላ ወደ
እስፔን ስሄድ እግረ መንገዴን ጐራ ብዬ
አያችኋለሁ። [29]ወደ እናንተ በምመጣበ
ትም ጊዜ ከክርስቶስ የሚገኘውን ታላቅ በረ
ከት በሙላት ይዤላችሁ እንደምመጣ እር
ግጠኛ ነኝ።
[30]ወንድሞቼ ሆይ፥ሥራዬ የተቃና እን

ዲሆንልኝም ሁልጊዜ እንድትጸልዩልኝ በጌ
ታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ
ፍቅር እለምናችኋለሁ። 31 ደግሞም በኢየሩ
ሳሌም ካሉ ከማያምኑ ሰዎች ተንኰልና
ክፋት እግዚአብሔር እንዲጠብቀኝ ጸልዩ
ልኝ። እንዲሁም በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲ
ያን የምሰጠው አገልግሎት ለክርስቲያኖች
በረከት እንዲሆንላቸው ጸልዩልኝ። 32 ይህ
ሁሉ በሚገባ ከተከናወነልኝም በእግዚአብ
ሔር ፈቃድ ወደ እናንተ የምመጣው በደ
ስታ ተሞልቼ ነው። ከእናንተ ጋር የምቆይ
በት ጊዜ መልካም እንደሚሆን ይሰማኛል።
33 የሰላም አምላክ ከሁላችሁ ጋር
ይሁን፤አሜን!

## ምዕራፍ 16

1 በክንክራኦስ ከተማ ባለችው ቤተ ክርስ
ቲያን የምታገለግለው እኅታችን ፌቤን ወደ
እናንተ ትመጣለች። 2 በምትመጣበትም
ጊዜ፣በጌታ ስም መልካም አቀባበል እንድ
ታደርጉላት አሳስባችኋለሁ። ፌቤን ለእኔም
ሆነ ለብዙ ክርስቲያኖች ትልቅ እርዳታ
ያደረገች ክርስቲያን እኅታችን ነች። ስለዚህ
በሚያስፈልጋት በማናቸውም ነገር ሁሉ
እርዳታችሁን እንድታደርጉላት አደራ እላ
ችኋለሁ። 3 የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ሥራ
አብረውኝ ለሚሠሩት ወዳጆቼ ለጵርስቅላና
ለአቂላ የከበረ ሰላምታ አቅርቡልኝ። 4 ጵር
ስቅላና አቂላ ለእኔ ሲሉ ሕይወታቸውን
ጭምር ለሞት አሳልፈው እስከመስጠት የደ
ረሱ ባለውለታዎቼ ናቸው። እነርሱ ያደረጉ
ልኝ በጎ ነገር ምን ጊዜም የሚረሳ አይደ
ለም። እኔ ብቻ ሳልሆን ከአሕዛብ ወገን
የሆኑ ክርስቲያኖችም በዚሁ አድራጎታቸው
ሁልጊዜም እንዳመሰገኑዋቸው ናቸው።
5 እንዲሁም በጵርስቅላና በአቂላ ቤት
ለጸሎትና ለአምልኮ ለሚሰበሰቡት ክርስቲያ
ኖች ሁሉ ሰላምታዬን አቅርቡልኝ። በታና
ሽቱ እስያ ከሚገኙት ክርስቲያኖች ሁሉ
ቀደም ብሎ በጌታ ላመነው ለወዳጄ ለአጤ
ኔጦን የከበረ ሰላምታዬን አቅርቡልኝ።
6 እናንተን በታማኝነት በማገልገል ብዙ የደ
ከመችውንም እኅታችንን ማርያን በጌታ
ስም ሰላም በሉልኝ። 7 ከእኔ ጋር ታሥረው
ለነበሩት አይሁዳውያን ወገኖቼ ለአንዲራኒ
ቆንና ለዩልያን ሰላምታዬን አቅርቡልኝ።
እነዚህ ሁለቱ ከእኔ በፊት ቀደም ብለው
በጌታ ያመኑና በሐዋርያትም ዘንድ የታወቁ
ወንድሞች ናቸው። 8 በጌታ የምወደውን
ጵልያጦንን ሰላም በሉልኝ። 9 በክርስቶስ
የሥራ ባልደረባችን ለሆነው ለኢሩባኖንና
ለወዳጄ ለስንጣክን ሰላምታዬን አቀርባለሁ።
10 ለክርስቶስ ታማኝ መሆኑ ተፈትኖ
ለተረጋገጠለት ለኤጤሌን እንዲሁም ለአርስ
ጣባሉ ቤተ ሰቦች ሰላምታዬን አቅርቡልኝ።
11 አይሁዳዊ ወገኔ ለሆነው ለሄሮድዮና እን
ዲሁም ከንርቀሱ ቤተ ሰቦች መካከል በጌታ
ላመኑት ሁሉ ሰላምታ አቅርቡልኝ።
12 ጌታን በታማኝነት ለሚያገለግሉት ለጥሮ
ፊሞናና ለጢሮፊሞሳ እንዲሁም ጌታን በማ
ገልገል ብዙ ለደከመችው ለተወደደችው
እኅታችን ለጠርሲዳ የከበረ ሰላምታ አቅርቡ
ልኝ። 13 በጌታ ለተመረጠውና በአገልግሎት
ሥራው ለታወቀው ለሩፎን፣ እንዲሁም
እንደ ልጅዋ ትንከባከበኝ ለነበረችው እናቱ
ጭምር፣ ጳውሎስ ሰላምታ አቅርቦላችኋል
በሉልኝ። 14 እንዲሁም ለአስቀሪጦን፣ለአፍለ
ሶንጳ፣ለሄሮሜን፣ለጳጥሮባ፣ለሄርማንና ከእነ
ርሱም ጋር ላሉት ወንድሞች ሁሉ ሰላምታ
ዬን አቅርቡልኝ። 15 ለፍሌጎን፣ለዩልያ፣ለኔ
ርያና ለእኅቱ፣ለአልንጦን፣ከእነርሱም ጋር
ላሉት ክርስቲያኖች ሁሉ የከበረ ሰላምታ
አቅርቡልኝ። 16 እርስ በርሳችሁም በተቀ
ደሰ መሳሳም ሰላም ተባባሉ። የክርስቶስ
አብያተ ክርስቲያን ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላ
ችኋል።

17 ወንድሞቼ ሆይ፣ የተማራችሁትን
ትምህርት ከሚቃወሙና የሰዎችን እምነት
በማናጋት መከፋፈል ከሚፈጥሩ ሰዎች እን
ድትጠነቀቁ እለምናችኋለሁ። እንደዚህ
ያሉትን ሰዎች ልትርቋቸው ይገባል።
18 ምክንያቱም እነዚህን የመሰሉትን ነገሮች
የሚፈጽሙ ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን
የሚያገለግሉት አይደሉም። ድካማቸውና
ጥረታቸው ሁሉ የራሳቸውን ጥቅም ለማዳ
በር ብቻ ነው። አፈ ጮሌዎች ስለሆኑና
በቃል መሸንገል ስለሚችሉ ብዙ የዋሆችን
ያታልላሉ። 19 መቼም የእናንተ ታዛዥነት
በማንም ዘንድ የታወቀ ሆኖአል። እኔም
በዚህ ምክንያት ታላቅ ደስታ ይሰማኛል።
ነገር ግን ለበጎ ነገር ጥበበኞች፣ለክፉ ደግሞ
የዋሆች እንድትሆኑ እመክራችኋለሁ።
20 የሰላም አምላክ እግዚአብሔርም ሰይጣ
ንን ከእግራችሁ ሥር ፈጥኖ ይቀጠቅጥላች
ኋል። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በረከት
ይደርባችሁ።

21 የሥራ ባልደረባዬ የሆነው ጢሞቴ
ዎስ ሰላምታ ያቀርብላችኋል። እንዲሁም
ዘመዶቼ ሉቂዮስ፣ኢያሶንና ሱሲጴጥሮስ ሰላ
ምታ ያቀርቡላችኋል። 22 ይህን መልእክት

በጽሑፍ ያሠፈርሁ እኔ ጤርጥዮስም በጌታ
ስም ሰላምታ አቀርብላችኋለሁ። 23 እዚህ
ያሉት ክርስቲያኖች በቤቱ እንዲሰበሰቡ
ያደረገውና እኔንም በእንግድነት የተቀበለኝ
ጋይዮስ ፥ ሰላምታውን ለእናንተ እንዳቀርብ
ለት ጠይቆኛል። የከተማይቱ ማዘጋጃ ቤት
ገንዘብ ያዥ ፥ ኤርስጦስና ወንድማችንም
ቊአስጥሮስ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።
24 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላ
ችሁ ጋር ይሁን፤አሜን!
25 ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባስተማ
ርኳችሁ ፥ ለብዙ ዘመናት ተሰውሮ አሁን
በተገለጠው የወንጌል ቃል መሠረት ፥ በእም
ነታችሁ ጸንታችሁ ለመኖር ለሚያበቃችሁ
ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። 26 ለብዙ
ዘመናት ተሰውሮ የቆየው ይህ እውነት ፥
አሁን በነቢያት መጻሕፍት አማካይነት ተገ
ልጧል። የተገለጠውም ዘላለማዊ በሆነው
በግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት ፥ ሰዎች ሁሉ
ይህን እውነት ተቀብለውና አምነው እርሱን
እንዲታዘዙት ነው። 27 እርሱ ብቻ ጥበበኛ
ለሆነው ለእግዚአብሔር ፥ በጌታችን በኢየሱስ
ክርስቶስ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ
ክብር ምስጋና ይሁን ፥ አሜን።

የናንተው
ጳውሎስ